አጋንት እግዚአብሔር

አሳታሚ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ማኅበረ ቅዱሳን

አዘጋጅ ፦ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ

ተርጓሚ ፦ ቀሲስ እሸቱ ታደሰ

2005 ዓ.ም

©ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻፫ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታይቶ ታርሞ ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ፡-

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- lemat@eotc-mkidusan.org
Website:- www.eotc-mkidusan.org

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. ይዘት ---- 1
2. መግቢያ ---- 3

ክፍል አንድ

3 ስለ እመርቱ ትእዛዛት ---- 4
4 ስለ ትእዛዛት አስፈላጊነት ---- 5
5 በቅጥር እመር ስለመሆናቸው ---- 7
6 ስለ ሁለቱ ጽላት ---- 9
7. ስለ አስታዋሽነታቸው ---- 11
ሀ. አትገደል ---- 11
ለ. አታመንዝር ---- 11
ሐ. አትስረቅ ---- 12
መ. መመኘት ---- 12
ሠ. ሰንበትን ማክበር ---- 13

ክፍል ሁለት

8 የመጀመሪያ ትእዛዛት ---- 17
ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ ---- 22
9 የተተረጐመ ምስል ከእንተ አታድርግ ---- 40

ክፍል ሦስት

10 ሁለተኛ ትእዛዝ
የእግዚአብሔር አምላክህን
ስም በከንቱ አትጥራ ---- 42

ክፍል አራት

11 ምስተኛ ትእዛዝ
«የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ» ---- 69

ከፍል አምስት

12 አራተኛ ትእዛዝ

«አባትና እናትህን አክብር» ——— 91

ከፍል ስድስት

13 አምስተኛ ትእዛዝ

«አትግደል» ——— 130

ከፍል ሰባት

14 ስድስተኛ ትእዛዝ

«አታመንዝር» ——— 148

ከፍል ስምንት

15 ሰባተኛ ትእዛዝ

«አትስረቅ» ——— 171

ከፍል ዘጠኝ

16 ስምንተኛ ትእዛዝ

«በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር» ——— 182

ከፍል አሥር

17 ዘጠነኛ ትእዛዝ

«የባልንጀራህ ቤት አትመኝ» ——— 190

ከፍል አሥራ አንድ

18 አሥረኛ ትእዝዝ

«ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» ——— 196

ከፍል አሥራ ሁለት

19 «ሕጋገተ ወንጌል» ——— 203

ከፍል አሥራ ሦስት

20 ማጠቃለያ ——— 210

መግቢያ

ሕግ የሚለውን ቃል የአለቃ ኪዳነወልድ ሰፍሊ መዝገበ ቃላት «በቀሙ የተወሰነ፣የተጻፈ ሥርዓት፣ልማድረግ የሚያዝዝ፣ከማድረግ የሚከለክል፣ አታድርጉ የሚል» በማለት ይፈታዋል። በዚህ ፍቺ መሠረት በእነዚህ በየፈርጁ የተለያየ አስገዳጅ ወይም ከልካይ ባሕርይ ባላቸው ሕግጋት መሠረትነት ላይ ተመርኩዞ የሚገዛ ወይም የሚያስተዳድር አንድ አካል መኖሩን ያስታውሳል። ይህ አስገዳጅ ወይም ከልካይ ባሕርይ ያለው ትእዛዝ ደግሞ በመናገር ወይም በጽሑፍ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን መዘንጋት አይገባም። ስለሆነም ሕግ ስንል የተጻፈውን ብቻ ሳይሆን ያልተጻፈን ፡- በቃልና በል ማድ የሚሠራበትን ጭምር የሚያጠቃልል መሆኑን ማስተዋል ይገባል። በዚህ ውስጥ በልማድ የሚሠራባቸው ያልናቸው ሰው በተፈጥሮ ባሕርዩ የተነሣ ማንም ሳያገዝደው የሚፈጽማቸውና የሚመራባቸው ሕግጋተ ልቡና ናቸው።

የሰው ልጆች ፈጣሪ የሆነው ዘለዓለማዊ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በሥርዓትና በሕግ እንዲመራ አድርጎታል። ለአፈጣጣሩ ሥርዓት አበጅቶ ሥራውን የጀመረው እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ከአማኖ ከሥርዓት ውጭ የሆነ አንድ እንኳ እንዲኖር አልፈቀደምና ለሁሉም እንደየወገኑ የሚመራበት፣ የሚኖርበት፣ የሚመገብበትና የሚያ ጥፉበት ሥርዓት ሠርቶለታል። ይህ ሕግና ሥርዓት በተለይ በሰው ልጅ ዘንድ በልቡና የተቀረጸ፣በቃል የተነገረ ወይም የተጻፈ ሊሆን ይችላል። በዚህ መልክ ሕጉንና ሥርዓቱን በሰው ልቡና ከመቅረጽ አንሥቶ በቃሉ በመናገርና በጽሑፍም በመከተብ የሕግ ባለቤትና ምንጭ የሆነው ልዑል አምላክ በየዘመኑ የተለያዩ ሕግጋትን ለሰው ልጆች ገልጧል። ከዚህ በመነሣት ሕግ የሚለውን ቃል «በልቡና የተቀረጸ፣በቃል የተነገረ፣በጽሑፍ የመፈረ ለማድረግ የማዘዝ ከማድረግ ከመከልከል ባሕርይ ያለው» በማለት ልንፈታው እንችላለን። የእግዚአብሔር ሕግ በንጉሥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የመነጨ በቃለ እግዚአብሔር የተነገረ፣በእግዚአብሔር የተሰጠ፣ በእርሱ የታዘዘ አምላካዊ ድንጋጌ ነው። ይህም ሳይታዘዙ እግዚአብሔር የሚወደውን እርሱ የሚደሰትበትን ሁሉ በአእምሮአቸው አንቅተው ከልባቸው አመንጭተው በመሥራት በቅድስና ከኖሩት ቀደምት አበው፣እግዚአብሔር በቃሉ ብቻ አየተናገራቸው ያዘዛቸውን በመፈጸም ለቅድስና የበቁትንና በጣቶቹ ጽፎ በጽላት ቀርጾ የሰጣቸውን ሕግ በሥራ ላይ በማዋል ለጽድቅ የታደሙትን ትጉሳን አባቶቻችንን ዜና መዋዕል በማጥናት የምናረጋግጠው እውነታ ነው።

በዚህ መሠረት የእግዚአብሔር ሕግ በሦስት ዘመናት ለነበሩት የሰው ልጆች የሕይወት መመሪያ እንዲሆን የተሰጠ እንደመሆኑ ሁሉ በሦስት መንገ ተከፍሏል። በሕገ ልቡና ዘመን በነበሩት አበው ዘንድ የነበረው ሕግ ሕገ ልቡና ነው። በዘመነ አሪት የነበሩትም የሚመሩት በሕገ አሪት ነበር። በዘመነ ወንጌል ያሉትም በሕገ ወንጌል የሚመሩ ሆነዋል። በዚህ ምክንያትም ሕገ እግዚአብሔርን በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

1. ሕገ ልቡና
2. ሕገ አሪት
3. ሕገ ወንጌል

ሕገ ልቡና ፡-

ሕገ ልቡና ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው በተንተ ተፈጥሮ የተሰጠው የመጀመሪያው ሕግ ነው። ይህም በሰው ኅሊና ተጽፎ በልቡናውም ተቀርጾ ከሰውነቱ ጋርም ተዋሕዶ የሚኖር፣ ሁሌጊዜም ደጉን፣ተስማሚውን ነገር እንዲሠራ ተክሶ የሆነውን ግን እንዲጠላና እንዲተው እንዲሸሸውም የሚያነሣሣ፣የእግዚአብሔርንም ቅዱስ ፈቃድ የሚገልጥና የሚያሳውቅ ነው። ይህ ሕግ የጽሕፈት መሣሪያዎችን የማይሻ ነው። ምክንያቱም በልብ ሰሌዳነት ላይ የተጻፈ በመሆኑ ነው። ጸሐፊውም እግዚአብሔር ነው። ሕገ ልቡና በቅዱሳን መላእክት ዘንድ የተጠና በለሆነ ከተፈጥሮአቸው ጀምሮ እስከ አሁን አልተ ለጠጠም ለዘለዓለምም አይለወጥም እንቶ ይኖራል እንጂ። ሰውም እንደ እዚህ ግኩሉ ን መላእክት የደማኖቱን ሠውቶና ጠብቆ ፈጣሪውን በመፍራትና በማምለክ እንዲኖር ነበር የተፈጠረው። ሄኖ.19÷22። እግዚህ ሕገ ልቡና ሰው በእእምሮ ጠባይዕ ወሎቶ እግዚአብሔርን በማምለክ የፈጣሪውንም ፈቃድ በመፈጸም የኖረበትና የሚኖርበት ሕግ ነው። ሮሜ.2÷12–15።

የሕግ መጻሕፍት ከተጻፉበት ከ1400 ዓ.ዓ. በፊት የነበሩት ተደምት አበው ሁሉ እግዚአብሔርን አገልግለው መንገዳቸውንም ከእርሱ ጋር በግድረግ ፍጹማንና ጻድቃን ለመባል የበቁት በሕገ ልቡና መሪነት በተገለጠላቸው ሥርዓተ አምልኮ እንተው በመገኘታቸው ነው። በዚያ ዘመን ስለ አምልኮተ እግዚአብሔርም ሆነ ስለ አፈጻጸሙ ሥርዓት በፊደላ የተጻፈ ወይም የተነገረ ሕግ አልነበረም። ይሁን እንጂ እነዚህ ቀደምት አበው ለእግዚአብሔር ባሕርይ በሚገባ ሥርዓተ አምልኮ ይኖሩና የተለያዩ መንፈሳውያን አገልግሎቶችን በእግዚአብሔር ፊት ይፈጽሙ ነበር። ለምሳሌ ሥርዓተ መሥዋዕት ሕግ ሆኖ የተሰጠው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1400 ዓ.ዓ. አካባቢ ጀምሮ ሲሆን ከዚህ ዘመን አራት ሺህ ዓመታት አስቀድሞ የአዳም ልጆች የሆኑት አቤልና ቃየል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደአቀረቡ መጽሐፍ ይነግረናል። ዘፍ.4÷3-5። ከእነርሱ በፊት አብሔት ይሆናቸው ዘንድ መሥዋዕት ሲሰዋ ያዩት ሰው አልነበረም። መሥዋዕት የሚቀርብበት የተሰጠ ሥርዓትም አልነበረም። አቤልና ቃየል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ መልካም መሆኑን ያስተማራቸው ግንም ሳይኖር ያመኩት በሕገ ልቡና ነው። ጻድቁ ኖኅም መሠዊያን እንደ አዘጋጀና ከእንስሳትና ከአዕዋፍ ከመገናኘው ንጹሕ የሆኑትን መርጦ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደአቀረበ ተጽፏል። ይህን ያደረገው ከሕገ ልቡና የተነሣ ነው እንጂ በዚያ ዘመን ስለዚህ የመሥዋዕት አቀራረብ የተሠራ ሕግ አልነበረም። ዘፍ.8÷20። ከዚህም ሴላ ጻድቁ አባታችን አብርሃምና ያዕቆብም ሳለእዚ አብሔር አሥራት ያወጡ እንደነበር ተጽፎ ይገኛል። ይህም ሕግ ባልተሰጠበት ዘመን በተግባር ተፈጽሞ መገኘቱ ከሕገ ልቡና የተነሣ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ዘፍ.14÷20። ዘፍ.28÷20-22። በዚህ ዓይነትም ሕገ ልቡና ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ዘመን በነበሩት አባቶቻችን ዘንድ ተሠርተዋልና። ዝሂ መሠረትም በሕገ ልቡና እየተመሩ ፈጣሪአቸውን ወቅተው በአምልኮት ጸንተው ፈቃሉን እየፈጸሙ ለመኖራቸው ከብር የበቁና ቅድስናን ገንዘብ አድርገው ዐጽድት ሥራ ለመኖሩ የምሉ አበው ብዙዎች ናቸው። በዚያው መጠን ደግሞ ስተፈጥሮ የተሰጣቸውንና በልቡናቸው የተቀረጸውን ሕግ ተጠቅመው ፈጣሪአቸውን ወደ ማወቅ በአምልኮትም ወደ መጠመድ መድረስ የተሳናቸውና ከተፈጠሩበት ዓላማ + እግዚአብሔርን በማምለክና በማመስገን ከመኖር- የመጡና የወደቁ ብዙ ናቸው። እነዚህ በሕገ ልቡና መኖር አትቶለቸው መከቲ እንደሌለው በግ በሞት መንገድ የሚቅበዘበዙትን ፍጥረታቱን ቢያያቸው ስለ አዘኑላቸው ሕባ ረዳት አድርጎ ሰጣቸው። ሰው በሕገ ልቡና እየተመራ ወደድነት ሊደ ርስ ባለመቻሉ በሕግ እየተመራ ወደ መዳን እንዲደርስ ጠቅቲና አጋዥ ይሆነው ዘንድ ሕግ አሪትን ሠራለት።

<u>ሕገ አሪት፡-</u>
ሕገ አሪት እግዚአብሔር በእጪ ሙሴ አማካኝነት ሕዝበ እሥራኤል እንዲመሩበት የተሰጠ ሕግ ነው። ሕገ አሪት በሚባልበት ጊዜ ከሕገ ልቡና በተጨማሪ ሰውን ወደ ድኅነት ለማድረስ የተሰጡ ሕግጋትን የሚያጠቃልል ነው። ይህም ማለት በዘመነ አሪት በቃል በመናገርና በጽሑፍ በመቅረጽ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ለሕዝቡ የሰጣቸውን ሁሉ የሚመለከት ነው። በተለይ ግን ስለ ሕገ አሪት በሚነገርበት ጊዜ በጽላተ ሕጉ ተቀርጸው ለእጪ ሙሴ የተሰጡትን አሥርቱን ትእዛዛት የሚያመለክት ነው። ዘጸ.20÷1-17። የዚህ መጽሐፍ ዓላማም ስለ እነዚህ ሕግጋተ አሪት በመተንተን ማቅረብ ስለሆነ ስለዚህ ክፍል በሰፊው መጻፍ አላስፈለገም።

<u>ሕገ ወንጌል፡-</u>
ሕገ ወንጌል በሐዲስ ኪዳን ዘመን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጡ ሕግጋትን የሚያመለክት ነው። እነዚህም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ያስተማራቸው ሕግጋት ናቸው። እነዚህም ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ ዝርዝራቸውንና ስለ እነርሱም ያለውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በዚህ መጽሐፍ የመጨ..ሻ ክፍል በአጭሩ እንመለከታለን።

ክፍል አንድ

ስለ አሠርቱ ትእዛዛት በጠቅላላው

ክፍል አንድ

ስለ አሠርቱ ትእዛዛት በጠቅላላው

ሀ. በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል የተደረጉ ኪዳናት ስለመሆናቸው፡

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት ለቀደምት አበው የተሰጡ ቢሆኑም ከእኛ በፊት የነበሩት እንኳ አደረጉት ሁሉ በዚህ ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖችም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀመዛሙርቱ ካስተማሩት የክርስትና ትምህርት ጋር በማጣመርና በማዋሐድ እንድንመራባቸውና እንድንጠቀምባቸው የተደነገጉ ናቸው። ከሁሉ አስቀድሞ ደግሞ አሠርቱ ትእዛዛት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉ ኪዳናት መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል። ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ይህንኑ ለሕዝቡ ሲናገር አሠርቱን ትእዛዛት በመጥቀስ «አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እግዚአብሔር ዛሬ በዚህ ባሕይወት ካለነው ከእኛ ከሁላችን ጋር እንጂ ከአባቶቻችን ጋር ብቻ ይህችን ቃል ኪዳን አላደረገም።» በማለት አስገንዝቧል። ዘዳ.5÷2–3። ይህም እነዚህ ኪዳናት በየዘመኑ የነበሩትንና አሁንም ያሉትን ሕዝበ እግዚአብሔር ሁሉ የሚመለከቱ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው። እነዚህ ኪዳናትም በጽላተ ሕጉ የተጻፉ ናቸው። ዘዳ.5÷22።

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት የተቀረጹባቸው ወይም የተጻፉባቸው ጽላትም «የቃል ኪዳኑ ጽላት» ይባላሉ። ዘዳ. 9÷11። እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት መጽሐፍም «የቃል ኪዳኑ መጽሐፍ» ተብሏል። ኢያ.1÷7። ይህም እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የገባው ቃል ኪዳን የተቀረጸባቸው ጽላት፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተጻፈበት መጽሐፍ ማለት ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔር ትእዛዛት በእኛና በእርሱ መካከል እኛ እግዚአብሔርን ባመንን /በመለከን/ ጊዜ የተመሠረቱ ቃል ኪዳኖች ናቸው።

አምላካችን እግዚአብሔር እነዚህን ቃል ኪዳናት ከእኛ ጋር ያደረገው የእርሱን አስፈሪነት በሚገልጡ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ነበር። እግዚአብሔር አሠርቱን ትእዛዛት በሰጠ ጊዜ ተራራው ይናወጥ ነበር፣ የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር፣ ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር። ዘጸ.19÷16–19። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ሙሴም፦ እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበረ፤» በማለት ሁኔታውን ገልጦታል። ዕብ. 12÷21። ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዛት ምን ያህል አስፈሪና ሰዎች ሁሉ ሊያከብሯቸውና ሊፈጽሟቸው የሚገቡ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው።

ለ. ስለ ትእዛዛቱ አስፈላጊነት

እነዚህ ትእዛዛት የተሰጡት በእግዚአብሔር ከመሆኑም በላይ በራሱ /በእግዚአብሔር/ አንደበት የተነገሩ ናቸው። ዘጸ.20÷1። ይህ በራሱ አስፈላጊና ጠቃሚ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ነገር አንድ ስንኳ የማይጠቅም የለም፤ እርሱ በባሕርዩ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ የሰው ልጆችም ወደ ቅድስናው መቅደስ እንድንገባ ስለሚሻ የሚሰጠን ሁሉ ሕግም ቢሆን ትእዛዝም ቢሆን ራሳችንን ወደእርሱ እንድናቀርብበት ነውና ጠቃሚ ነው። እርሱም ደግሞ አስቀድሞ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።» በማለት ለሙሴ ነግሮት ነበር። ዘሌ.19÷2። ስለዚህም ነው ሰውን ወደቅድስናው መቅደስ ለማድረስ የተሰጡ ናቸው የተባለው።

እነዚህ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ መሆናቸውና በጽላተ ሕጉ ላይ ተቀርጸው ለነቢዩ ሙሴ መሰጠታቸው አስፈላጊና ጠቃሚዎች መሆናቸውን የሚያመለክት ነው። ዘዳ.9+10። በመጽሐፍ እንደተገለጠው ነቢዩ ሙሴ ከተራራው የተነገረውን የእግዚአብሔርን ሕግ ተቀብሎ ከመ ረደ በኋላ ከተራራው በታች የሚቃጠል መሥዋዕት የደ ኅንነትም መሥዋዕት አቅርቦ ደሙን ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በመቀጠልም «በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገውን የቃል ኪዳኑን ደም እነሆ» በማ ለት መናገሩ የእነዚህን ትእዛዛት አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው። ዘጸ.24+4–10።

እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት አስፈላጊና ጠቃሚ ባይሆኑ ኖሮ በፈጣሪአችን በእግዚአብሔርና በወዳጁ በሙሴ እጅ ከአንድ ጊዜ በላይ በመደጋገም ባልተጻፉም ነበር። ለምሳሌ በዘጸአት 20÷1–17 እና በዘዳግም 5÷6–21 ተመ ዝግቦ የምናገኘው በቂ መረጃ ይሆናል። እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ጽፏቸዋል፣ የመጀመሪያው ነቢዩ ሙሴ በሰበራቸው ሁለት ጽላት ላይ ሲሆን ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ነቢዩ ሙሴ በመጀመሪያዎቹ ዓይነት በድጋሚ በቀረጻቸው ጽላት ላይ ነው። ዘዳ.10÷4–1። ዘጸ.34+1

የእነዚህ ትእዛዛት ለሰው መሰጠት የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድም ጭምር ነው። በሌላም በኩል እነዚህ ትእ ዛዛት ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጭ እንዳንሆንና ከኃጢአት እንድንድንባቸው፣ ከጠላት ሰይጣንም እንድንጠበቅባቸው የተ ሰጡ የእግዚአብሔር አምላካችን ስጦታዎች ናቸው። በቅዱስ መጽሐፍም የተጻፈው ሁሉ እኛ እንማርበትና እንታረምበት እንጠቀምበትም ዘንድ የተጻፈ ስለሆነ የእነዚህ ትእዛዛት ዓላ ማም ይኸው ነው።

ይህ ሁሉ እንግዲህ የእነዚህን ትእዛዛት አስፈላጊነት የሚያስገነዝብ በመሆኑ እኛም ጠቃሚነታቸውን እንዲሁም የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን በመረዳት ራሳችንን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብና የእግዚአብሔርን ጸጋ ገንዘብ ለማድረግ የሕይወት መመሪያዎቻችን አድርገን ልንከተ ላቸውና በተግባርም ልንፈጽማቸው ያስፈልጋል።

ሐ. በቁጥር አሥር ስለመሆናቸው

አሥር ቁጥር የምሉዕነት ምሳሌና መግለጫ ነው። እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛትም በአሥር ቁጥር መወሰናቸው ምሉዕ መሆናቸውን ማለትም ሁሉን የሚያጠቃልሉ ሕ ግጋትና ትእዛዛትን በውስጣቸው ያካተቱ መሆናቸውን የሚገልጥ ነው። ሕግጋትና ትእዛዛት ሁሉ በእነዚህ አሥር ትእዛዛት የሚጠቃለሉ ናቸው።

የቁጥራቸው በአሥር መወሰን ምሉዓን ትእዛዛት መሆናቸውን የሚያስረዳ ስለመሆኑ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመለከታለን።

<u>የአሥሩ ደናግል ምሳሌ</u>፦ ማቴ.25÷1። በዚህ ምሳሌ መ ሠረት «አሥር» በመላው ዓለም የሚኖሩ የሰው ልጆችን የሚያመለክት ነው። ይህም የጻድቃንና የኃጥአን ሁሉ ምሳሌ ነው። ጌታቸው እስኪመጣ ድረስ ነግደውና አትርፈው እንዲጠብቁት አሥር ምናን የተሰጣቸው ባሪያዎችም ቁጥራ ቸው ወይም ብዛታቸው አሥር ነበር። ሉቃ.19÷13። ንግድ የተባለው ምግባር ትሩፋት ሲሆን እነዚህ አሥር ባሪያዎች ደግሞ የሰው ልጆች ሁሉ ምሳሌ ናቸው። ጌታውም የእግዚ አብሔር ምሳሌ ነው። የሰው ሁሉ ሲባልም የጻድቃንና ኃጥ አን ሁሉ ማለት ነው። ከእነዚህም አሥር ባሪያዎች መካከል የፌተኛው ነግዶ ያተረፈው «ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ» ብሎ ለጌታው መለሰ። ሉቃ.19÷17። ይህ ሰው በተሰጠው ችሎታ በሚገባ በመሥራት የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃትና በአሸናፊነት የተወጣ ፍጹም ሆኖ እናገኘዋለን። የተሰጠውን ኃላፊነት በሚገባ በመወጣቱም ከጌታው የተቀበለው ዋጋ ፍጹም ነው። ጌታው «አንተ በጎ ባሪያ፥ በጥቂት የታመንህ ስለሆንህ በአሥር ከተማዎች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ» ሲል ፍጹም ዋጋ ሰጥቶታል።

የጠፋው ድሪም ምሳሌም አሥር ቁጥር የፍጹም ነገር መግለጫ መሆኑን የሚያመለክት ነው። በወንጌል የተጠ

እንድ ሕግ ሀዋቂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊፈ ትነው ሽቶ «መምህር ሆይ+ ከሕግ ማንኛይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? »ብሎ በጠየቀው ጊዜ ጌታም መልሶ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኀሳብህም ውደድ፤ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች+እርሷም+ ባልንጀራህን እንደራስህ/ እንደ ነፍስህ/ ውደድ የምትለው ናት። አሪትና ነቢያት በእነ ዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ነቢያትም ተሰቅለዋል» በማለት መልስ መስጠቱ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ማቴ.22+35–40። ይህም ደግሞ የትእዛዛት ሁሉ መጀመሪያ ፍቅረ እግዚአ ብሔር የሚቀጥለውም ፍቅረ ሰብእ መሆኑን ግልጥ አድርጎ የሚያስረዳ ነው። በጽላቱ ላይ መጀመሪያ የተጻፉት ፍቅረ እግዚአብሔርን የሚመለከቱት ትእዛዛት መሆናቸው ወደ ሌሎች የተቀደሱ ተግባራት ሁሉ የሚያደርሰው እነዚህን በፍቅረ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረቱ ትእዛዛት መፈጸም ነውና አስፈላጊነታቸውን የበለጠ ጉልህ ያደርገ ዋል። በሁለተኛ ደረጃ ፍቅረ ሰብእን የሚመለከቱት ትእዛዛት መጻፋቸው ፍቅረ ቢጽ ከፍቅረ እግዚአብሔር የሚገኝና ተከታዩ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ ባስተ ማረው ጸሎት /በአቡነ ዘበሰማያት/ ላይ ተመሳሳይ የሆነ ቅደም ተከተልን አስተምሮናል። «አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ..... ፈቃድህ...በምድር ትሁን....»ካለ በኋላ የሚቀጥለው በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የሚደረግ ጸሎት ነው እናገኘዋለን። ማቴ. 6+9–14።

እንግዲህ እነዚህ ሁለቱ ጽላተ ሕግ ሰለው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት መሠረታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ሕግጋተ እግዚአብሔርን፣ ፍቅረ እምላክንና ፍቅረ ሰብእን በየግጻቸው የያዙ መሆናቸውን በማሰብ የሚገባቸውን ክብር መስጠት ይጠበቅብናል+ የሕግ እግዚአብሔር ሠሌዳዎች ናቸውና።

ሠ. ስለ አስታዋሽነታቸው

እነዚህ ትእዛዛት ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉና በጽላቱ ላይ የተቀረጹ ቢሆኑም ከጥንት ጀምሮ ግለትም ክነቢዩ ሙሴና ከጽላቱም አስቀድሞ በተግባር የነበሩ ናቸው። ቀድሞ በነበሩባቸው ዘመናት በጽሑፍ ያልሰፈሩ በመሆናቸው የተነሣ በኋላ ዘመን በሚሰጡት የተጻፉ ትእዛዛት እንዳይለወጡና ፈጽመው እንዳይረሱ፣ ዘወትርም እየታወሱ እንዲኖሩ እግዚአብሔር ለነቢዩ ሙሴ የሰጣቸው የቀደሙት ትእዛዛት ማስታወሻዎች ናቸው እንጂ እንግዳ ትእዛዛት አይደሉም።

ለምሳሌም የሚከተሉትን እንመልከት፦

ሀ. አትግደል–

ይህ ትእዛዝ በጽላቱ ሁለተኛው ክፍል ፍቅረ ሰብእን በሚመለከት ከተጻፉት መካከል አንዱ ሆኖ ከተቀረጸ በኋላ የታወቀ አዲስና ቀድሞ ያልነበረ እንግዳ አይደለም። ለሙሴ ከተሰጠ በኋላ ብቻ የታወቀ ቢሆን ኖሮ ቃየል ወንድሙ አቤልን በግፍ በመግደሉ እግዚአብሔር አምላክ በከባድ እርግማን ባልቀጣውም ነበር። ዘፍ.4+13። ይህ ምንባብም ትእዛዙ በጽላተ ሕጉ ላይ ከመቀረጹና በጽሑፍ ከመሰጠቱ በፊት ከሕገ ልቡና ዘመን ጀምሮ በሰዎች አእምሮ የሚ ታወቅ እንደነበር የሚያስረዳ ነው። በመሆኑም በሕገ ልቡና ሊሠራበት የነበረ የአእምሮ ሕግ ሆኖ የኖረ እንጂ አዲስ አይደለም።

ለ. አታመንዝር፦

ሰዎች ዝሙት ኃጢአት መሆኑን ያወቁት ከሙሴ ዘመን በኋላ ብቻ ነውን? ፈጽሞ አይደለም። ከነቢየ እግዚ አብሔር ሙሴ በፊት በመቶ በሚቆጠሩ ዓመታት ይቀድም

የነበረው ጻድቁ ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት ለኃጢአት በጋ በዘችው ጊዜ «እንዴት ይህንን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን አሠራለሁ?» በማ ለት እምቢታውን መግለጡ ኃጢአት በተለይም ማመንዘርና ዝሙት በኃጢአትነቱ ከዘመነ ሙሴ በፊትም የሚታወቅ ለመሆኑ ግልጥ ማስረጃ ነው። ዘፍ.39÷9። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር አምላክ በጥፋት ውኃ ዓለምን የቀጣው የሰው ልጆች ለክፉ ሥራ የተገዙና ኃጢአተኞች በመሆናቸው ነው። ዘፍ.6÷5–8። ዘፍ.7÷19።

ሴኬም የያዕቆብን ሴት ልጅ ዲናን ባስነወራት ጊዜ የያዕቆብ ልጆች እጅግ አዘኑ፣ አምርረውም ተቆጡ «በእሥ ራኤል ላይ ስንፍናን አድርጓልና። የያዕቆብም ልጆች እኅታቸውን ያስነወራትንና ያረከሳትን የሴኬምን ቤት ሁሉ በዘበዙ፣ ወንዶችንም ሁሉ ገደሉ።» ዘፍ.34÷5–19። ስለዚህ ተጽፈው ለነቢዩ ሙሴ ከተሰጡት ትእዛዛት በመቶዎች በሚቆጠሩ ዓመታት ቀደም ብሎ ዝሙትና አመንዝራነት እንደ ክፉ ሥራና ርኩሰት ይቆጠር የነበረ በመሆኑ አዲስ ትእዛዝ አለመሆኑን በዚህ እናውቃለን።

ሐ. <u>አትስረቅ</u>፦ መስረቅ ክፉ ሥራ ወይም ኃጢአት እንደሆነ ቀደም ብሎ የሚታወቅ ለመሆኑ ያዕቆብ ከላባ ጋር ሲከራከርባቸው የነበሩት የተሰረቁ የላባ አማልክት ታሪክ በቂ ምስክር ነው። ዘፍ.31÷30–39።

መ. <u>መመኘት</u>፦ ይህም ኃጢአት መሆኑን ከሙሴ በፊት ቀደም ብሎ ከነበረው ከኢዮብ ቃላት ለመረዳት ይቻላል። እርሱ «ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፣ እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» ብሎ የተናገረው ቃል ይህንኑ የሚ ያስረዳ ነው። ኢዮ.31÷1።

ሠ. <u>ሰንበትን ማክበር</u>፦ ይህም ከአሥርቱ ትእዛዛት መስጠት በፊት የሚታወቅ ነው። እሥራኤል ከሰማይ የወረደላቸውን

መና እንዲለቅሙ በታዘዙ ጊዜ ሰንበትን እንዲያከብሩ ተነግሮአቸው ነበር። «እግዚአብሔርም የተናገረው ይህ ነው፤ ነገ እረፍት ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው።» ዘጸ.16÷23–29። ከዚህም ይበልጥ ቀደም ብሎ እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረቱን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ማረፉ ሰንበትን ማክበር ቀድሞውኑ እንዲታወቅ ሥርዓት ለመሥራ ት ነበር። ይህም ሰንበትን ማክበር ከቀድሞ ጀምሮ ማለትም ከሙሴ በፊትም የሚታወቅ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ዘፍ.2÷2–3።

እንግዲህ አሠርቱ ትእዛዛት ተጽፈውና በጽላት ተቀርጸው ከመሰጠታቸው በፊት በሰዎች አእምሮና በልቡናቸውም ተቀርጸው ይሠራባቸው የነበሩ መሆናቸውን ለማስረዳት ከላይ ያቀረብናቸው ምሳሌዎች በቂ ናቸው። ዋናው ነጥብ በእግዚአብሔር ጣቶች ተጽፈውና በጽላተ ሕጉ ላይ ተቀርጸው ለነቢዩ ሙሴ የተሰጡት እነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት ቀደም ብሎ የሚታወቁና በሕገ ልቡና አባቶቻችን እየፈጸሟቸው ኖረው ለጽድቅ የበቁባቸው መሆናቸውን ማወቅ ነው።

እነዚህ በእግዚአብሔር የተነገሩና በጣቶቹ የተጻፉት በጽላት ላይም ተቀርጸው ለነቢዩ ሙሴ የተሰጡት አሠርቱ ትእዛዛት በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል የተደ ረገው የቃል ኪዳን ምልክቶች በመሆናቸው፣ የተመራቸ ውና ያከበራቸው በሕይወት ዘመኑም በተግባር የፈጸማቸው በረከትን፣ የናቃቸውና የሻራቸው ያልተመራባቸውም ሰው ዳግሞ መርገምን የሚቀበልባቸው ናቸው። ስለዚህም አሠርቱ ትእዛዛት በአሥር ቁጥር የተወሰኑ ቢሆኑም በውስጣቸው የያዙት ምሥጢር እጅግ ሰፊ በመሆኑ እያንዳንዳቸውን በቅደም ተከተላቸው መሠረት መመርመርና መረዳት አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም በሚቀጥሉት ክፍሎች አሠርቱን ትእዛዛት በመተንተንና ከክርስትና መሠረተ እምነት አንፃር የያዙትን ጥልቅ መንፈሳዊ ምሥጢር በመመርመር እግዚአብሔር

አምላክ በእነርሱ አማካኝነት እንድንሠራ ያዘዘውንና እንጸን ሠራ የከለከለውን በሚገባ ዐውቀን እንጠቀም ዘንድ በሰፊው እንማራለን::

ስለእነዚህ አሥር ትእዛዛተ እግዚአብሔር ሲወሣ መዘንጋት የሌለበት አንድ ጠቃሚ ነጥብ አለ:: ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ ስለእነዚህ አሠርቱ ትእዛዛት ማንነት ያለው የአመለካከት ልዩነት ነው:: ይህ ልዩነትም የሚያተኩረው በትእዛዛቱ ማንነትና በቁጥራቸው ላይ እንጂ በእያንዳንዱ ትእዛዛት ትርጓሜ አንባር አለመሆኑን ግን ያስተውሏል::

በዚሁ መሠረት የትእዛዛቱን ማንነት በተመለከተ አንዳንድ ሊቃውንት «የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለውን /ዘጸ.20+5/ እንደ ሁለተኛ ትእዛዝ በመቁጠር እስከ «አትመኝ» ድረስ ያለውን ብቻ አሥር በ ማድረግ «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» /ዘሌ.19+18/ የሚለውን ከአሠርቱ ትእዛዛት ቁጥር ያስወጡታል:: እነዚህ ሊቃውንት በዘዳግም 5+22 «እግዚአብሔር በተራራው ላይ በእሳትና በደመናው በጨለማውም ውስጥ ሆኖ በታላቅ ድምፅ እነዚህን ቃሎች ለጉባኤችሁ ሁሉ ተናገረ፤ ምንም ምን አልጨመረም:: በሁለቱም የድንጋይ /ጽላት (ሠሌዳዎች) ላይ ጻፋቸው+» የሚለውን ምንባብ በመተቸስና በሃይማኖተ አበው ምዕራፍ 130 የቀረበውን መሠረት በማድረግ አሠርቱ ትእዛዛት በዘጸ.20+1–21 የተዘረዘሩት ብቻ ናቸው በማለት ሃሳባቸውን ያጠናክራሉ::

ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ «የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለው «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» በሚለው የመጀመሪያው ትእዛዝ ውስጥ የሚጠ ቃለልና አምልኮን የሚመለከት በመሆኑ እንደተለየ ትእዛዝ ብቻው ሊቆጠር አይገባውም:: ስለዚህ በዘሌዋውያን 19+18 የተጠቀሰው «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለው አሥረኛ ሆኖ መጨመር አለበት ይላሉ:: ለዚህ ሃሳባቸውም በወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥያስተምርበት ጊዜ

ስለተእዛዛት የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሃሳብህም ውደድ /ፈጽመህ አምልክ/ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት:: ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፣ እርሷም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትለው ናት» በማለት መናገሩ ፍቅረ ሰብእን እንደ አንድ ዋነኛ ትእዛዝ በመቁጠሩ ነው በማ ለት ይከራከራሉ:: ማቴ.22+35–40:: በሁለቱም ወገን ከመ ጽሐፍ የተጠቀሱ ማስረጃዎች ቢቀርቡም ሁለቱንም ለመ ንቀፍ ባይቻል እንኳ አንዱን በመቀበል ከአንደኛው ወገን የቀረበውን አቋም ለመደገፍ እንገደዳለን:: ትእዛዛቱ አሥር ናቸው:: አሥሩም ደግሞ የተለያየ ምሥጢር ያላቸውና እ ንዳንዳቸውም በተለያዩ አርእስተ ጉዳዮች ላይ የተመሠ ናቸው:: በዚህም ምክንያት በአንድ ተመሳሳይ በሆነ ጉ ላይ የሚያተኩሩና ስለአንድ ነገር የሚናገሩ ሃሳቦችን ብ ድነት አጠቃለሉ ከመቀበል ይልቅ በተናጠል መመልከትና ሁለት ማድረግ ቁጥር ከማብዛት ሌላ በቀደመው ከተ ተሰው የተለየ አዲስ ሃሳብን የሚጨምር ሊያደርገው አይችልም:: «ከእኔ በቀር ለሌች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ትእዛዝ «የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸው» ከሚለው የሚለይበት አንጻችም ሀሳብ ስለሌለና ሁለቱም ሐረጎች አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መኖሩንና እርሱም ብቻ ሊመለክ የሚ ገባ መሆኑን የሚያስረዱ በመሆናቸው ተጠቃለለው እንደ አንድ ትእዛዝ መወሰድ/መቆጠር/ የሚገባቸው መሆኑን የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ያምንበታል:: ስለሆነም ሁለተኛውን የሊቃውንት ሃሳብ በመደገፍ የትእዛዛቱ ቁጥር /አሥ ርንታቸው/ በዘሌዋውያን 19+18 የተጠቀሰውን የሚያካትት መሆን አለበት የሚል አቋም በመያዝ የትእዛዛቱ ዝርዝር እንደሚከተለው ተርቧል::

1. «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ:: ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ::...የማናቸውንም ነገር ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም፤»

ዘጸ.20+2–6::

2. «የእግዚአብሔር የአምላክን ስም በከንቱ አትጥራ፤» ዘጸ. 20+7

3. «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ:: /አክብረውም/» ዘጸ.20+18::

4. «አባትህንና እናትህን አክብር፤» ዘጸ.20+12::

5. «አትግደል::» ዘጸ.20+13::

6. «አታመንዝር::» ዘጸ.20+14::

7. «አትስረቅ::» ዘጸ.20+15::

8. «በሐሰት አትመስክር::» ዘጸ.20+16::

9. «አትመኝ» ዘጸ.20+17::

10. «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» ዘሌ.19+18::

አሥርቱ ትእዛዛት በመባል የሚታወቁትና በጽላተ ሕጉ ላይ በእግዚአብሔር ጣቶች የተቀረጹት /የተጻፉት/ የእግዚአብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው:: ከዚህ በሚቀጥሉት ክፍሎችም የእነዚህ ሕግጋትና ትእዛዛት ምሥጢራዊነት፣ ትርጓሜና ማብራሪያ በሰፊው የቀረበ ስለ ሆነ እንባቢያን በማስተዋል እንዲመለከቱአቸውና ራሳቸውን በመመርመር እንዲጠቀሙባቸው ተጋብዘዋል::

ክፍል ሁለት

የመጀመሪያው ትእዛዝ

«ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ:: ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ:: ከላይ በሰማይ ካለው+ በታች በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ+ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ:: አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም::»

ዘጸ.20+2–6

ይህን የመጀመሪያውን ትእዛዝ በሚከተሉት ንዑሳን አርእስት በመከፋፈል እንመለከተዋለን::

እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ

አምላካችንና ፈጣሪአችን አግዚአብሔር በፍጹም ቸር ነቱ የሚወደን መሆኑንና ማንነቱንም ጭምር «አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ::» በማለት ገልጠልናል:: ብዙ ጊዜም ራሱን በተለያየ መንገድ ለሰው ልጆች ገልጧል:: ለምሳሌም ለነቢዩ ሙሴ «እኔ የአባትህ አምላክ+ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ» ብሎታል:: ዘጸ.3+6:: በዚህም በሙሴ አማካኝነት አምላክነቱን ለሕዝቡ ሁሉ ገልጧል:: ያደገረላቸውንም ቸርነት አስታውሶ ያንን የቸርነት ሥራ የሠራላችሁ አምላካችሁ እኔ ነኝ በማለት በፍቅር ጽንፍ ማን መሆኑን ገለጠላቸው እንጂ «እኔ ሰማይንና

ምድርን በውስጧም ያለውን ሁሉ የፈጠርኩ እግዚአብሔር ነኝ» ወይም «እኔ ምንም ምን የሚሳነኝ የሌለ ልዑልና ኃያል አምላክ ነኝ» በማለት በሚያስፈራ ግርማው ራሱን የገለጠ አይደለም። ይልቅስ የሚረዳ፣ የሚያድን፣ ሰውን ወዳጅ፣ ሰውንም ከማፍቀሩ የተነሣ ከግብፅ ባርነት እሥራኤልን ያወጣ መሆኑን በመጥቀስ በቸርነቱ እንዲያውቁት ከፍቅሩም የተነሣ እንዲወዱት ራሱን በዚህ መልክ ገለጠ።

እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅርና መልካም ሃሳብ እንዳይዘነጉ ዘወትር ሰዎችን ያስታውሳቸዋል። የእርሱን ፍቅር ምሕረቱንና ቸርነቱን ባስታወሱ ጊዜ ደግሞ ይወዱታል። ስለፍጹም ፍቅሩም ያፈቅሩታልና ስለዚህ አስቀድሞ ያደረገላቸውን ቸርነት በማንገር ራሱን ለሰዎች ገልጧል። አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ከሚያስፈራና ከሚያስደንግጥ ቃል ይልቅ ዘወትር በጆሮአችን የሚነግረን «እኔ ይህንንና ይህን ከመሰለ ደዌ የፈወስኳችሁ፣ በዚህ ዓመት ያቀዳችሁትን እንድታከናውኑ የረዳኋችሁ፣ ከዚህ ወይም ደግሞ ከዚያ ችግር ያወጣኋችሁ፣ ከመከራም የከለልኳችሁ፣ መልካሙን ሁሉ ያደረግሁላችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እኔ ነኝ» በማለት ነው። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አስፈሪ ስለሆነ ሳይሆን ቸርና መሐሪ ስለመሆኑና ስለ አደረገልን የተቀደሰ ይቅርታው እንዳንረሳው ስለሚፈልግ፣ ስለምንፈራው ሳይሆን ስለምንወደው እንድናስታውሰው ስለሚሻ አምላክነቱን በአደረገልን ቸርነት ገልጦልናል።

እኛ ከልግድ የተነሣ ዝንጉዎች ስለሆንን እግዚአብሔር አምላካችን ለእኛ ያለውን ፍቅሩንና የሚያደርግልንን እንዲሁም ያደረገልንን ቸርነቱን ያሳስበናል፣ ያስታውሰናል። በአብዛኛውም እግዚአብሔርን የምናስታውሰው የምንሻውን ነገር በምንጠይቅበት ጊዜና የጠየቅነውን ከማግኘታችን አስቀድሞ ነው። የለመንነው ከተሰጠንና የምንሻው ከተደረገልን በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዘነጋዋለን። እርሱ ልዑል እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ደካማ ባሕሪያችንን ስለሚያውቅ ነው «እኔ ከባርነት ቤት ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ» በማለት ባደረገልን ቸርነት ራሱን የገለጠልን። በዚህም «የተዋረዳችሁበትን፣ በባርነት የተገዛችሁበትን፣ ምርኮኞች የነበራችሁበትን ዘመንና በዚያ ዘመን ያደረግሁላችሁን እያሰባችሁ አምልኩኝ» ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለእኛ ያለውን ፍቅሩንም እያሰብን ከፍቅር በመነጨ አምልኮ እንድናመልከው ጭምር እየነገረን ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ዘወትር የሚያደርግልንን በጎ ነገር ባለመዘንጋት የሚገባውን ሁሉ ልናቀርብለት ያስፈልጋል።

ከዚህ አንፃርም በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ «አቤቱ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ አንተ ይህን ሁሉ ቸርነት ያደረግህልኝ አምላኬ ነህ። እኔም በሕይወት እስትንፋሴ ሕያው ሆኜ በምኖርበት ዘመን ሁሉ ተናግሬው ስለማልፈጽመው ቸርነትህ ለአንተ እገዛልሃለሁ» ማለት ምንኛ ያማረ ነው። ስለዚህም ልቡናችንን ሰብስበን እግዚአብሔር ያደረገልን ቸርነቱን፣ ምሕረቱንና ፍቅሩን በማስታወስና በማሰብ ከፊቱ እንንበርከክ። እርሱንም «አቤቱ ያደረግህልኝን ቸርነት አልረሳም፣ ፍቅርህንና ምሕረትህን በዘነጋሁ ጊዜ በኃጢአት እወድቃለሁና የሚያስታውስ የሚያስተውልም ልቡናን ስጠኝ»እንበለው። ፈጣሪአችን ልዑል እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለእኛ ማስታወቁ ለመልካም ነው። እርሱ አምላካችን ከእኛ ጋር ሆኖ በእኛ የሚያደርገው ነገር ማስታወቁ ለመልካም ነው። እርሱ አምላካችን ከአኛ ጋር ሆኖ በእኛ የሚያደርገው ነገር ደግሞ ድንቅ ነው። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ከመስጠቱ በፊት ፍቅሩንና ቸርነቱን እንድናስብ ያደርገናል። ምክንያቱም ትእዛዛቱን ከቸር አባት እንደተሰጠ ትእዛዝ እንጂ ከክፉ ባለሥልጣን እንደ ተሰጠ መመሪያ እንዳንቆጥራቸውና ከፍቅሩም የተነሣ ያዘዘንን ለመፈጸም እንድንተጋ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ነቱን በፍቅር ዐውቀንና አምነን እንጂ ከፍርሃት የተነሣ እንድናመልከው የሚሻ አምላክ አይደለም።

ከዚህም ሌላ አምላካችን እግዚአብሔር እኛ ምንም እንኳ ኃጢአተኞች ብንሆን ሳይተወን የቸርነቱን ሥራ የሠራልንና እየሠራልንም ያለ መሆኑን እያሰብን እንድናመልከው ይሻል። ለዚህ ነው «ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» በማለት በትእዛዙ መግቢያ የተናገረው።

«እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግም የሚያመለክተው አምልኮን ነው፤ አምላካችን እግዚአብሔር ነው ማለትን ያስከትላልና። ነቢዩ ዳዊት «መኑ ውእቱ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር፤ ወመኑ እግዚአብሔር ዘእንበለ አምላክነ፡– ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማነው? ከአምላካችንስ በቀር እግዚአብሔር ማነው?» ሲል እንደተናገረው። መዝ.17÷31። ኢያሱም «እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።» እንዳለው ኢያ.24÷15። በወንጌልም «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» ተብሎ እንደተጻፈው።ማቴ.4÷10። አምልኮ ሲባልም ዘወትር በቤተ እግዚአብሔር እየተገኙ መጸለይን፣ መጸምን፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ መመርመርን ወዘተ የሚያጠቃልል ነው። እነዚህን የአምልኮ መገለጫ የሆኑ የተቀደሱ ምግባራት የማያደርግ ማንም ሰው «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» በሚለው ኃይለ ቃል ይወቀሳል። ምክንያቱም አምላኩ የሆነ እግዚአብሔር ሊቀጣጠረው ይገባልና ለእርሱ የሚገባውን አምልኮ ለባለቤቱ ለእግዚአብሔር መስጠት ይጠበቅበታልና። ይህን ባለመፈጸሙ እነዚህ ቃላት ይወቅሱታል።

ማንም ቢሆን ሥርዓተ አምልኮውን የሚፈጽመው ተገድዶ አይደለም፣ ስለራሱ ጥቅም ብሎ ነው እንጂ። ይህም በጥሩ ሁኔታ በቅዳሴ ጎርጎርዮስ ተገልጧል። «አቤቱ የእኔ አገልግሎት ለአንተ የሚያስፈልግ አይደለም የአንተ እም ላክነት ግን ለእኔ ያስፈልገኛል እንጂ።» «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግ የፍቅር መገለጫ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅር ያመለክታልና። እግዚአብሔር «ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም... ወዳጆች ግን ብያ ችኋለሁ።» እንዳለ ወዳጆች እንጂ ባሮች ብሎ አልጠራንም። ዮሐ.15÷15። ከዚህም የተነሣ በጸሎታችን «አባታችን ሆይ» እንለዋለን። እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛም እንወደዋለን። 1ዮሐ.4÷19። እግዚአብሔር እኛ ለእርሱ የሚኖረንን ፍቅር ከቀድሞ ጀምሮ ይሻው ነበረ። ይህንንም በነቢዩ ሙሴ «እሥራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤

አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።» ሲል በተናገረው ቃሉ ገልጦታል። ዘዳ.6÷4–6።

ልዑል እግዚአብሔር ዘልባዊ ፍቅር ላይ የተመሠረተውን እንጂ የታይታ አምልኮን አይሻም። እሥራኤላውያንን ስለኃጢአታቸው በወቀሳቸው ጊዜ «ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፥ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፥ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና» ብሎ ነበር። ኢሳ.29÷13። እንዲሁም ደግሞ በወንጌል «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።» ማለት የታይታ አምልኮን የማይወድ መሆኑን የሚገልጥ ነው። ማቴ. 15÷10። እንዲት ልናመልከው እንደሚገባ ሲናገርም «ልጄ ሆይ፥ ልብህን ስጠኝ፥ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ።» በማለት አምልኮ ፍጹም ልባዊ መሆን እንዳለበት አስገንዝቧል። ምሳ.23÷26።

በመሆኑም «እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ» የሚለው ሐረግ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙና ለእርሱም እንዲገዙ፤ በእርሱ እንዲያምኑና እንዲያመልኩትም የሚያደርግና የሚያበረታታ፤ ሕይወታቸውን ለእርሱ እንዲሰጡ የሚያስገነዝብ ነው። በዚህ ሁኔታ አምላክነቱን ለሰው ከገለጠ በኋላ ነው ትእዛዛቱን የሰጠው። በዚህ መሠረትም ከፍጹም ፍቅሩ የተነሣ ያደረገሁላችሁን ቸርነት እያሰባችሁ የምታመልኩኝ አምላካችሁ እኔ ነኝና «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» በማለት አዝዟል።

ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ

አንዳንድ ሰዎች ይህንን ትእዛዝ በሚያነቡበት ወይም በሚሰሙበት ጊዜ «ይህ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው?» ይህ ሊነገር የሚገባው ለከሐድያንና ለመናፍቃን ወይም ከሥጋዊ ዕውቀታቸው የተነሣ አለበለዚያም ከፍልስፍና

በመነጨ ሁኔታ ከሃይማኖት ያፈነገጡትን ነው። እኔ ግን በሳምንት ይሽን ያህል ቀን እጾማለሁ፣ አሥራት አወጣለሁ፣ በየሰዓቱ እጸልያለሁ፣ ከልብ ሆኜ እዘምራለሁ፣ የቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብሮችን ያለማቋረጥ እከታተላለሁ፣ ስለሆነም ይህ ትእዛዝ አይመለከተኝም» ይሉ ይሆናል።

ነገር ግን ይህ ትእዛዝ ማንንም ከማን ሳይለይ ሁሉንም የሚመለከት ነው። «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ተብሎ መነገሩ በሰው ልጅ እጅ የተጠረቡትንና የለዘቡትን ሰው ያቆማቸውንና በባሕር፣ ወይም በፀሐይ ወይም በእሳት ወዘተ የተመሰሉትንና በተለያዩ ስያሜዎች የሚታወቁትን ጣዖታትን ብቻ ማለት አይደለም። በዚህ አንጻር አንዳንድ ሰዎች ኃይላቸውን ያመልካሉ፣ ውበታቸውን፣ ዝናቸውን ወዘተ ያመልካሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች በየፊናቸው የየራሳቸው ጣዖታትና አማልክት አሏቸው ማለት ነው። እንደዚህም ሆነው እየኖሩ ደግሞ እነዚህ ሁሉ «በእውነት እግዚአብሔርን፣ እናመልካለን በእርሱም እናምናለን።» ሊሉ ይደመጣሉ። በእነርሱ ዘንድ ግን አውነትም ሃይማኖትም ፈጽሞ የለም።

በቀደምት ዘመናት የነበሩ ሰዎች ከፍርሃት ወይም ከመጠን በላይ ከሆነ ፍቅር የተነሣ አሊያም ለአንዳች ጥቅም ሲሉ እንግዳ አማልክትን ያመልኩ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል። በእነርሱ አመለካከት ጥሩና መጥፎ የሚሏቸው አማልክት ነበሯቸው።ጥሩ ከሚሏቸው ጥቅምን ፍለጋ፣ መጥፎ የሚሏቸውን ደግሞ በመፍራት ያመልኳቸው ነበር። ለምሳሌ ታላላቅ ነገሥታትን ለጥቅም ሲሉ፣ መናፍስትን፣ ታላላቅ ወንዞችን፣ ኤሷቴዎችን እላትንና የመሰሰሉትን ግዙፋን ፍጥረታት በመፍራት ያመልካሉ። መሳ.12+8–14። ከዚህ በመነሣት ዋና ዋና የተባሉትን የባዕድ አምልኮ ዓይነቶች እንደሚከተለው በዝርዝር እንመልከት፦–

ሀ/ ገንዘብን ማምለክ

ገንዘብ ብዙ ሰዎች የተንበረከኩለትና የተገዙለት በሰዎች ልቡና ውስጥም የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚተናቀን ጣዖት ነው። ስለዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ «ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፣ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፡...ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።» በማለት ነግሮናል። ማቴ.6+24።

ማንም ሰው እግዚአብሔርን አመልካለሁ እያለ ገንዘብን ከተገቢው መጠን በላይ የሚያፈቅር ከሆነ ራሱን ያሞኛል። ገንዘብን ከእግዚአብሔር አስበልጠ መውደድ ጣዖትን ማምለክ ነውና ሰው የገዛ ገንዘቡ ጣዖት ሊሆንበት አያስፈልግም። ከገንዘብ ፍቅር መራቅ ያስፈልጋል፣ ማለትም የገንዘብን መገልገያነት መቃወም ሳይሆን ገንዘብን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል እንጂ የገንዘብ ባሪያ መሆን አይገባም ለማለት ነው። ከዚህም ሌላ የገንዘብ አገልግሎትም ቢሆን ደግሞ ለአምልኮ ጣዖት መፈጸሚያና ለገቢረ ኃጢአት ከሆነ ገንዘብ አምላክ ሆኖ እየተመለከ ነው ማለት ይቻላል። በይበልጥ ደግሞ ገንዘባቸውን በአንዳች አገልግሎት ላይ ላያውሉት በማከማቸት የሚረኩ ሰዎች ለገንዘብ ያደገዙና ገንዘብን አምላካቸው ያደረጉ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች የሳንቲም ስባሪ እንድትወድቅባቸው የማይሹና በፈቃዳቸው ገንዘብን ለበጎ ምግባር የማያውሉ /የ ማይመፀውቱ/ ናቸው። እንዲህ የሚያደርጉትም ፍቅረ ንዋይ ነው። ገንዘብን ከማንም በላይ ስለሚወዱ በራሳቸው ላይ ጣዖት አድርገው ያመልኩታል። ለገንዘብ ያላቸው ፍቅርና አክብሮት ለፈጠራቸው ለእግዚአብሔርና በአርአያ ሥላሴ ለተፈጠሩ ሰዎችም ከሚሰጡት ፍቅርና አክብሮት የበለጠ ነው። ስለገንዘብ ብለው እግዚአብሔር አምላካቸውን የካዱ፣ ወንድማቸውን የሚገድሉ፣ እስከሞት ድረስም ራሳቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉ እጅግ ብዙ ናቸው። የእነዚህ ሁሉ አምላካቸው ገንዘባቸው ነውና። ለዚህ ነው ገንዘብ

መሰብሰብ ሰውን ከሃይማኖቱና ከፍቅረ ስብእ እንደሚለየው የሚያውቀው አምላክ «ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ1» በማለት ያስተማረው:: ማቴ.6+19::

ስለሆነም ከአምልኮተ እግዚአብሔርና ከፍቅረ ቢጽ የሚለይ የገንዘብ ፍቅር ወደልቡናችን እንዳይገባና እንዳይ ሠለጥንብን፣ ከፈጣሪአችንም ጋር እንዳያጣላን ልቡና ደጃችንን አጥብቀን ልንዘጋ በብርቱም ልንጠነቀቅ ይገባል:: ይሆን ክፉ ጠላት ለመቋቋም የሚያስችለውን ኃይልና ጥበብ መንፈሳዊን እንዲሰጠን ዘወትር እግዚአብሔርን መለመን ያስፈልጋል:: አንድ መንፈሳዊ አባት ልጃቸውን ሲመክሩ «ልጄ ሆይ ገንዘብ ካለህ በሥራ ላይ አውለው፣ ገንዘብ ከሌለህ ግን ምንም ገንዘብ አትሰብስብ» ማለታቸው በፍቅረ ንዋይ የተነሣ የሚመጣው የአጋንንት ጸር እጅግ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገጸሙ ቆሮንቶስ በጲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ በፍቅረ ንዋይ የመጣበትን ፈተና በፀሊእ ንዋይ / ገንዘብን በመተላት/ ድል የነሣው መሆኑን ኢያሰብን በጥንቃቄ መኖር ያስፈልገናል:: ገንዘብ ሰይጣን ሰውን ለማሰናከልና ለመጣል የሚጠቀምበት ክፉ ባላጋራችን መሆኑን ተገንዝበን በማንኛውም አጋጣሚ በእጃችን የደረሰውን ገንዘብ በማስተዋል ልንጸድትበት እንጂ አምላክ አድርገን ልናመልከው የማይገባ መሆኑን በማወቅ በጥንቃቄ እንኑር:: ማቴ.8+11::

ለ/መልካም ያደረጉልንን ማመስገን

ብዙ ሰዎች ውለታ የዋለላቸውን ሰው ከማክበርና በሚገባው መጠን ከማፍቀር አልፈው ያመልኩታል ወይም ፈጽመው ይጸየፉታል:: ይህ ባለውለታቸው የሆነ ሰው ከሚ ከፉ ይልቅ እግዚአብሔር ቢያዝንባቸው መልካም እንደሆነ ሁሉ ይሆን ተግባራቸውን እንደጽድቅ ይቆጥሩታል:: አንድ ደራሲና ገጣሚ «ለሰዎች መልካም አድርግ ልቡናቸውን የአንተ ታደርጋለህ» በማለት የተናገረው በዋሉላቸው ውለታ ወይም ከሠሩላቸው መልካም ሥራ የተነሣ በሌሎች ዘንድ /ውለታ ቢቀዋለላቸው/ የሚመለኩትን ለመተቀስ መሆኑ

ግልጥ ነው:: እኛ ግን መልካም የምንሠራው ስለሰማያዊ ዋጋ ብለን እንጂ የሌሎች ገዥዎች ወይም በሰዎች ልቡና ሚዖቅ ለመሆን ብለን መሆን የለበትም::

መልካም ለአደረገልን መልካም ውለታ መዋል ብቻ ሳይሆን ማድረግ ለሚያስፈልገው ሁሉ መልካሙን ማድረግ ከሰብእዊነታችንና ከክርስትናችን ሕግ የተነሣ ልንፈጽመው የሚጠበቅብን ከመሆኑ በቀር መከበርንና መመለክን በመኘት ሊሆን አይገባውም:: መልካም የሠሩልንንም ሰዎች ቢሆን እግዚአብሔር ውለታውን በላይ በሰማይ /በመንግሥቱ/ እንዲ ከፍላቸው ከመጸለይ በቀር እንደፍጹማን አማልክት ቆጥረን በደባልነት ልናመልካቸው የማይገባ መሆኑን ደግሞ ማስተ ዋል ያስፈልጋል:: ለመልካሙ ሥራቸው የማይጠፋውን ሰማ ያዊ ዋጋ ከፈጣሪአቸው ከእግዚአብሔር ማግኘት ሲገባቸው በውዳቤ ከንቱ ገመድ ተጠልፈው እንዲወድቁ፣ ድካማቸ ውንና ሞንነታቸውን እያሰቡ በትሕትና ከመኖር እንዲዘናጉ፣ እንዲሁም ደግሞ በምድራዊው ምስጋና ሰማያዊውን በረከት እንዲለጣጡትና በጠቅላላው በነፍሳቸው እንዲጎዱ ምክንያት ከመሆን ለመጸን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው::

ሐ/ ዝናን ማምለክ

አንዳንድ ሰዎች በሚገባ ወይም በማይገባ ነገር ለዝናቸው ወይም ለሚያውቁት ሰው ዝና ሲሟገቱ ይታ ያሉ:: የራሳቸውን ወይም የሚሟገቱለትን ሰው ስሕተት ለመሸፈን ጥፋትን ከቤተ ክርስቲያን፣ ከሕዝብ ወይም ከመን ግሥት በላይ አድርገው የእርሱን ዝና ለመጠበቅ ይጥራሉ:: መሰሳታቸውን ወይም የሚሟገቱለት ሰው ስሕተት መፈ ጸሙን ቢያውቁም ስለምድራዊ ዝና ሲሉ እውነትን ለመ ደበቅ ይሞክራሉ:: ይህ ደግሞ ለዝና መገዛትና ዝናን ማም ለክ ነው:: ጸሐፊው ስለዝና የሚሟገቱትን አስመልክቱ «የባልንጀራ ዓይን ለስሕተት የተደፈነች ናት፣ የጠላት ዓይን ግን እያንዳንዱን ጥፋት ትገልጣለች» ብሎአል:: የወላጆን ስሕተት የሚሸፍነው የዚህ ዓይነቱ ባልንጀራ ጠቃሚ አይ ደለም:: ጥፋቴን ዓይቶ ካልነገረኝ፣ እንድታረምም ካል መከረኝና ለባዶነቴ ቢሟገትልኝ በመጨረሻው ላይ ፊጣ

ፈንታዬ ከሚሆነው ውድቀቴ ሊያነሣኝ አይችልምና ምን ይረባኛል። «እውነተኛ ባልንጀራ መስተዋት ነው» ሲሉ አበው የተናገሩት መች በዋዛ ነው።

ለአንድ ሰው ዝና ተብሎ «እውነት» መሥዋዕት መሆን /አልፋ መሰጠት/ የለባትም። ለጥቅም ተብሎም የሰው ዝና መጠበቅና የሐሰት ጠበቃ መሆንም ተገቢ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድም የተጠላ ነው። ስለዚህ ነገርም መጽሐፍ «..ታዋኩን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጠያፊዎች ናቸው» ይላል። ምሳ.17÷15። እውነትን ስለሰው ወይም ስለ ራስ ዝና መለወጥ የእውነት አምላክና እውነት የሆነውን እግዚአብሔርን ክዶ ባለዝና የሆነውን ሰው ወይም ራስን ማምለክ ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድ እውነት ሕይወትም ነኝ» ብሏልና እውነትን ለዝና መለወጥ ጣዖትን በማምለክ እግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው። ዮሐ.14÷6።

ለልዑል እግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለፍጥረታዊው ሰው የሚሰጥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን የሚያመልክ ነው። እግዚአብሔርን ከማስደሰት ይልቅ ሰውን በማይገባው ነገር ለማስደሰት የተሰለፈ የሚያስደስተውን ሰው ያመልካል። ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ወደ ጎን በመተው ለሰው ፈቃድ የሚታዘዝ የሚታዘዝለትን ሰው ያመልካል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ባሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ ያክርስቶስ ባሪያ ባልሆንኩም» በማለት መናገሩ ለዚሁ ነው። ገላ.1÷10። ማንም ሰው ቢሆን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በንጹሕ አእምሮ እግዚአብሔርን ለማስደሰት እያሰበ ማድረግ አለበት። ለቸሩ ፈጣሪ ለልዑል እግዚአብሔር የሚገባውን ፍቅር አክብሮትና አምልኮት ለማንም ሳይለውጥና ማንንም ሳያወድስ፣ ጎሊናውንም ክዶ ለሌሎች ዝና ሳያሳድድ በክርስቲያንነት የሚጠበቅበትን እያደረገ በመንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሰው ሁሉ ግዴታ ነው። ይህ ካልሆነ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ያለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዴት ማክበር ይችላል?

መ/ ታላላቅ ሰዎችን ማምለክ

መጽሐፍ ቅዱስ «ለዋናዎቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፣ እነርሱ... ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ» ይላል። ዕብ.13÷17። ይህ የሐዋርያው አባባል ታዘዙለቸው፣ አታምፁባቸው ማለት እንጂ በእግዚአብሔር ፈንታ አምልኳቸው የሚል ትርጉም የለውም። የሀገር መሪዎችንም ሆነ መንፈሳውያን አባቶችን ለመሪነታቸውና ለመንፈሳዊ አባትነታቸው በማገዛው መጠንና ወሰን በመታዘዝ ልናከብራቸውና ልናገለግላቸው ከሚገባ በቀር ከእግዚአብሔር ጋር በሚወዳደር ክብር ልናመልካቸውና ከፈጣሪአችን ጋር የሚያጣላ ትእዛዛቸውን ለመፈጸም ፈቃደኞች ልንሆን አይገባም።

መሪ ወይም መንፈሳዊ አባት ከሚጠበቅበት ኃላፊነት ውጭ የሆነ እንደሆነ ከበታች ያለውም ተከትሎት በማይገባ መንገድ እንዲሄድና የማይገባ ሥራም እንዲሠራ የሚያስገድደው ሕግ አልተሠራም። መንፈሳውያን አባቶችና መሪዎች የነበሩት እነ አርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስና አውጣኪን የመሳሰሉት ሁሉ ከእውነት ባፈነገጡበት ጊዜ መንፈሳውያን ልጆቻቸው ሁሉ አብረው አላፈነገጡም። ከሃይማኖት ውጭ የሆነ ከምግባር የሚለይ ከቱ ሥራቸውን ነቅፈው አውግዘው ለዩአቸው እንጂ መንፈሳውያን አባቶቻችን ነበሩ ብለው አልተቀበሉአቸውም።

«ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ተብሏልና። የሐዋ.5÷29። ከእግዚአብሔር ይልቅ የእነዚህን መናፍቃን ትምህርት አምላካቸው አድርገው የተከተሏቸው ሁሉ ጠፍተዋል፤ ከቤተ ክርስቲያን አንድነትም ተለይተዋል።

ከጎሊና ጋር የሚቃረን ለአእምሮ የማይመች የሰውን የማንነት ሚዛን ያለፈ እንዲሁም እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋር የሚጋጭ ታዛዥነት እግዚአብሔር የሚሻው የሚቀበለውም አይደለም። ሰው ውስጣዊ ሰላሙን የሚያናጋውን፣ ከራሱ ነፃ ጎሊና ጋር የሚያጣላውን፣ ሃይማኖቱንና የክርስትና ሕይወቱን የሚፈታተነውን ትእዛዝ እንዲቀበል የእግዚ

አብሔር ፈቃድ አይደለም። መንፈሳዊ መሪና አባትም በተሰጠው መንፈሳዊ ሥልጣን የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆኑ የመንፈሳዊ ልጁን ውስጣዊ ሰላም የሚያናጋ፣ መን ፈሳዊ ቅድሰናውን የሚያደፈርስና የሚፈታተን ትእዛዝ ማዘዝ የለበትም። ይህን መሰሉ ትእዛዝ አባታዊ አይ ደለምና። ስለዚህ ታላላቆችንና መሪዎችን በሚገባው መጠን መታዘዝ እንጂ ማምለክ፣ ከእግዚአብሔር ሊያጣላ የሚችል ትእዛዛቸውንም መቀበል አይገባም። ታላቅነታቸው የል ጆቻቸውን መንፈሳዊ ሆነ አካላዊ ችግር የሚያቃልል እንጂ በራሱ ችግር መሆን የለበትም፣ ይህም ከፍርሃት የተነሣ ወደ አምልኮ ሊለወጥ ይችላልና።

ሠ/ ዓለምንና የዓለምን ፍላጎት ማምለክ

ዓለም ሊላኛዋ ጣዖት ናት። ከዓለም ጋር በፍቅር የተሳሰረ ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ለእርሱም ያለውን ታዛዥነት እና በእርሱ ያለውን እምነት ሁሉ ይረሳል፣ ይተዋልም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአ ብሔር ጠላት ሆኖአል።» በማለት ይህንን ገልጦታል። ያዕ.4+4። ፍቁረ እግዚእ ቅዱስ ዮሐንስም በመጀመሪያው መልእክቱ «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፣ በዓ ለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ። ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል።» በማለት ይህንኑ እውነታ አጉልቶታል። 1ዮሐ.2+15–17።

እስቲ አንድ ጥያቄ ለራሳችን ጎሊና እናቅርብ። የም ናመልከው እግዚአብሔርን ወይስ ዓለምንና ፍላጎቷን ነው? በእውነት እግዚአብሔርን የምናመልክ ከሆነ ዓለምን ድል መንሣት ይገባናል፣ ፈቃዷም በእኛ ላይ መሠልጠን የለበ ትም። ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ «ከእግዚአብሔር

የተወለደው ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል፣ ዓለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።» እንዳለው በዓለም ላይ ባለድል መሆን ይኖርብናል። 1ዮሐ.5+4። የዓለም ፍላጎት ባሸነፈን ጊዜ ግን እምነታችን ፈጽሞ ከውስጣችን ይጠፋል፣ ፈቃዳችንም ወደ ዓለም ይሆናል፣ እኛም የዓለምን ፈቃድ ፈጻሚዎች እንሆናለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ከባድ ፈተ ና ሲገልጥ «ዴማስ ይህን የአሁኑን ዓለም ወድዶ ትቶኛልና» በ ማለት ተናግሯል።2ጢሞ.4+10። ይህ አነጋገር የዓለም ፍላጎት ከባድ ፈተና መሆኑን የሚያመለክት ነው። የሥጋ ፍትወታት ሰዎችን ሪግጠው የሚገዙ ጣዖታት ናቸው። ለምኞታቸውና ለሥጋዊ ፍላጎታቸው የሚገዙ ሰዎችም እግዚ አብሔርን በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹም ነፍሳቸውና በፍጹም ሃሳባቸው በፍጹም ኃይላቸውም ያመልኩታል ማለት አይቻልም።

አንዳንድ ሰዎች የአካላቸውን ውበት ያመልካሉ፣ ዘወትርም ስለውበታቸው ቢናገሩ ይወዳሉ። የተፈጠሩበት ሌላ ዓላማ እንደሌለ ሁሉ ለውበታቸው ብቻ ሲጨነቁ ይታያሉ። ስለዚህ ረጋፊ ውበታቸው ሥጋር ሲሉም የ ማይከፍሉት መሥዋዕትነት የለም። ከአፈር የተሠሩና ወደአፈርም የሚመለሱ በስባሾች መሆናቸውንም ፈጽመው ይዘነጋሉ። እነዚህ ሰዎች «ከኦኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ትእዛዝ አፍርሰዋል። «በላይ በሰማይ ካለው በታች በምድር ካለው ከምድር በታች በውኃ ካለው ነገር የማንኛውንም ምስሉ የተቀረፀውንም ምስል ለአንተ አታድርግ» የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል መሻራቸውም አይታወቃቸውም። ለእነርሱ ከዚህ ትእዛዝ አንፃር የሚታየው እንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዝበው አለማምለካቸው ብቻ ነው። ነገር ግን ማንም ቢሆን እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክና ልቡናውንም ለእግዚአብሔር ብቻ አሳልፎ መስጠ ት እንጂ ራሱን እንደጣዖት ማምለክ የለበትም።

ሌሎች ደግሞ ትኩረታቸው ሁሉ በመብልና በመጠጥ ላይ ብቻ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሆዳቸው አምላካቸው ነው፣ ክብራቸው በነውራቸው ነው፣ ሃሳባቸው ምድራዊ ነው» በማለት የተናገረው እነዚህን ሰዎች

የሚመለከት ነው። ፊልጵ.3÷19። ከዚህም በላይ እነርሱ የመስቀሉ ጠላቶች መሆናቸውንና ስለዚህም በሀዘኔታ የሚያለቅስላቸው መሆኑን ጨምሮ ተናግሯል። በእርግጥ አንዲት መለኪያ አረቄ አምላካቸው የሆነ፣ ፈቃዳቸውም ሁሉ ወደ መብልና መጠጥ ያዘነበለ ብዙ ሰዎች አሉ። እሥራኤላውያንስ በአንድ ወቅት ስለሥጋ፣ዓሣ፣ዱባ፣በጢሽ፣ ቀይ ሽንኩርት አልቅሰው አልነበረምን? ዘኁ.11÷4–5። ኤሳውስ ብኩርናውን ከነበረከቱ ለምሥር ወጥ አልሸጠውምን? ዘፍ. 25÷29–34። አዳምና ሔዋንስ ለመብላት ያማረች፣ ለዓይን የምታስጎመጅ ከሆነችው ዛፍ ፍሬን በመብላት በሰው ሁሉ ዘር ላይ ርኩሰትንና መርገመ ሞትን አምጥተው የለምን? ዘፍ.3÷6።

ቅዱሳን አበው ለጣዖት ከመንበርከክ ይልቅ ሰማዕ ትነትን ይመርጡ እንደነበር ገድላቸው ይነግረናል። የዘመኑ ትውልድ ደግሞ በተቃራኒው ለጣዖት መሥዋዕት ሲያሳርግ ይውላል። የዘመኑ ሰው ያለማቋረጥ በየቀኑ መሥዋዕት የሚሠዋላቸው እነዚህ ጣዖታትም ገደብ የሌላቸውና መሰን ያል ተደረገላቸው የሥጋው ፍላጎቶችና የዓይኑ አምሮቶች ናቸው።

ሥልጣንንና ማዕረግን፣ ክብርን፣ የተለያዩ ንብረቶችን እንደአምላክ የሚመካባቸው እና የሚያመልካቸው ሰው ለእነዚህ ፍላጎቶቹ ሲል ፈጣሪው እግዚአብሔርን ይክዳል፤ ጎሊናውንም ይሸጣል። «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይ ሁኑልህ» የሚለውን ትእዛዘ እግዚአብሔር ወደጎን በመተውና በመዘንጋት ፍላጎቱን ለመፈጸም ሲል አስፈላጊ ነው የሚ ለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከመክፈል ወደኋላ አይመለስም። ለዚህ መድኃኒቱና መፍትሔው ለሥጋዊ ፍላጎት ከመገዛትና ሥጋዊ ዓለማዊ ፈቃድን ከማምለክ በመራቅ እግዚአብሔርን ብቻ በማምለክ ጸንቶ መኖር ነው።

ሪ/ ራስን ማምለክ

ከጣዖታት ሁሉ የበለጠውና አደገኛው ጣዖት ራስን ማም ለክ ነው። ሰው ከሥጋዊ ፍላጎቱ ማየል የተነሣ ሁል ጊዜ

ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ይፈልጋል። በዚህ ተግባሩ ደግሞ ራሱን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንዲያመልኩትና እር ሱነቱ በሁሉ ዘንድ የጎላ እንዲሆን፣ እንዲከበርና እንዲፈራ ይሻል። ሰዎች መልካምና ያማረ ነውየሚሉት ሁሉ በእርሱ ማንነት ውስጥ እንዲገኝና ሰዎችም ሁሉ እንዲያደንቁት ይፈልጋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ ጥያቄ እናንሳ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብን ባስገደለው ጊዜ ንጉሥ ሄሮድስ ላይ አደጋ ያመጣበት ምን ነበር? የእግዚአብሔር መልአክስ ለምን ቀሰፈው? ለምንስ በትል ተበልቶ ሞተ? ሰዎች ለአምላክ ብቻ የሆነውንና ለእርሱም የማይገባውን ክብር ሲሰጡት ባለመቃወሙና የማይገባውን ክብር በመሻት አልነበረምን? የሐዋ.12÷21–23።

ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን ጣዖታት ሁሉ ድል ነሥተው ነገር ግን ራስን ማምለክን ማሸነፍ የተሳናቸው ሰዎች የሄሮድስ መሰሎች ናቸው። በመጽሐፍ ተመዝግቦ እንደምናገኘው ክአጸምና ከሔዋን ጀምሮ ሞትን ወደ ዓለም ያመጣው፣ ቃየን ወንድሙን እስከ መግደል ያደረሰው፣ ናቡከደነፆር በባቢሎን ሕዝቡን እኔ ፈጠርኳችሁ እንዲል ያደረገው፣ ፈርዖንን ሕዝበ እግዚአብሔርን አልለቅም እግዚ አብሔርንም አላውቅም ያሰኘ ራስን የማምለክ ጣዖት ለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። እነዚህ ሰዎች ከራሳቸው በቀር ሌላ አስተዋይ፣ የተሻለ ዕውቀት ያለው፣ ከሁሉ በላይ የሆነ ያማረና የደመቀ አለ ብለው ስለማያምኑ ራሳቸውን ያመልካሉ። ሌላው ሰውም እንዲያመልካቸው ይሻሉ።

ራሱን የሚያመልክ ሰው የእርሱ ማንነት እርሱ ብቻ የሚያውቀውና በእርሱ አእምሮ የተሣለው እርሱነቱ ብቻ ነው። በምኞት ብቻ የቀረ ማንነት። ለእርሱ እንደ ሚመስለው ከእርሱ በቀር ሌላው ሰው ሁሉ ስሕተተኛ ነው። ከሌሎች ጋር ቢጋጭ እንኳ እነርሱ እንጂ እርሱ እንዳ ልተሳሳተ ያምናል። ምክንያቱም እርሱ በፍጹም ስሕተት አይሠራምና ነው። «ሰዎች ሊረዱኝ አልቻሉም እንጂ የእኔ ጠባይ ትክክለኛ ነው» የሚል የራሱ እምነት አለው።

ብዙ ጊዜ በዓለም ላይ የሚነሡትና የተነሡት እምባገሮችና ጦርነቶች በአብዛኛው ራስን የማምለክ ውጤቶች ናቸው። እንዲህም ስለሆነ ከዚህ መሰል አምልኮ ጣዖት እንድንጠበቅ የሚሻው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ» ብሏል። ማር. 8+34። ራስን መካድ ምን ማለት ነው? ሰው ራሱን ማም ለክን ከልቡናው ያጥፋ፤ ራሱንም አመድ የምድርም ትቢያ እንደሆነ ይቁጠር ማለት ነው። የትሕትና ሰው የሆነና ከውጪ ከንቱ ራሱን ያራቀ ማንም ቢሆን ራሱን ከማምለክ ተለይቷል፤ እኔ ከሁሉም በላይ ነኝ የሚል ሥጋዊ ስሜት ከእርሱ ጠፍቷልና።

ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጣላና ከአምላኩ ጋር በትዕቢት እንዲፎካከር ራሱንም እንዲያመልክ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንደኛው የራሱን ታላቅነትና ከሁሉ በላይ መሆንን መሻቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከማንም በላይ ራሱን መውደዱ ነው። ስለዚህ ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ጋር በሚጋጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ይልቅ «እርሱ እግዚአብሔር ሊልት እኔ ላንስ ያስጠፈልጋል» ያልን እንደሆነ ያን ጊዜ ራሳችንን እንደካድን በዚህ ይታወቃል። ዮሐ.3+30። በእርግጥ ራሳችንን እንድናመልክ የሚያደርገን ደግሞ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚጋጭ የተወሰነ ፍላጎታችንን ለሚሟላት ያለን ዓላማ ነው።

የመላእክት አለቃ የነበረውን ሣጥናኤልን ከነሠራዊቱ ለውድቀት ያበቃው ምንድነው? ራሱን የሁሉ የበላይ ማድረጉ አይደለምን? የተሰጠውን ትቶ ከሚገባው በላይ ታላቅና ከፍ ያለ ለመሆን የነበረው መሻት /ፍላጎት/ ከፍተኛ ስለነበረ፦ «ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ... በልዑልም እመሰላለሁ» ብሎ ተናግሮ ነበር። ኢሳ.14+13–14። ሣጥናኤል እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ከፍ ከፍ ማለትን ፈለገ። ነገር ግን ትዕቢቱ ውር ደትን እንጂ ክብርን አላስገኘለትም። አዳምንና ሔዋንንም በተመሳሳይ ፈተና እንደጣላቸው ቀደም ብሎ ተጠቅሷል።

ስለዚህ ማንም ሰው ራሱን መግዛትና ሥጋዊ ፍላጎቱን መካድ ከቻለ ዋነኛውን ጣዖት ከልቡናው ነቅሎ አጥፍቶታል ማለት ይቻላል። አሥራትን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለራሳችን ስንወስድ፣ ሰንበትን ለሥጋዊ ፈቃድ መፈጸሚያ ስንጠቀም ራሳችንን መውደዳችን አይደ ለምን? ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር በሚጋ ጭበት ጊዜ ፈቃዳችንን ከመፈጸም ይልቅ «እርሱ እግዚ አብሔር ሊልት እኔ ላንስ ያስፈልጋል» በማለት ራሳችንን በመካድ ሕይወታችንን ለዘለዓለም በእግዚአብሔር እንደ ምናስጠብቃት እርግጠኞች እንሁን። ራስን ከማምለክ ነፃ እንድንወጣ፣ ራሳችንን ለመካድ የሚያበቃ የእጋ ስጠታን የሚያድል መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቸርነቱ እንዲረዳን ዘወትር ፈቃዱን በመለመን እንተን መኖር ያስፈልጋል።

ለ/ ከሕደት

ከሕደት «ክሕደ» ከሚል የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን ፍችውም እምነትን፣ ውልን፣ መሐላን ማፍረስ፣ መሸፈጥ፣ ቃልን መለወጥ፣ መዋሸት፣ ማበል ማለት ነው። በእነዚህ የክህደት ተግባራት ላይ የተሠማሩ ሰዎች ከሐድያን ይባላሉ።

ከሕደት የመጀመሪያው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው ። ከዚህ አንፃር የእግዚአብሔርን ሕልውና የማያምን ጥበብ በሚመስለው ሥጋዊና ምድራዊ ዕውቀት በመመራመር በራ ሱ ብቻ የሚታመን ሰው ኪሐዲ ይባላል። ነቢየ እግዚ አብሔር ቅዱስ ዳዊት ይህን የመሰለውን ሰው ሰነፍ ብሎ ታል። «ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል።» በማለት እንደተናገረው። መዝ.13+1።

ፀሀብቱ፣ በዕውቀቱ፣ በሥልጣኑ፣ በወገኑ መዙተ የሚ መካና የሚታመን ሰው ሁሉ ከክሐድያን ወገን የሚቆጠር ነው። ሊታመኑበትና ሊመኩበት የሚገባው አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጥበባቸውና በዕውቀታቸው በመመካትና በመታመን የእግዚ አብሔርን ሕልውና በመካድ በገሪክ ከተማ ያስቸገሩ

ስለነበሩ ፈላስፎች ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ «የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና። ጥበበኛ የት አለ? ጸፊስ የት አለ? የዚህች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?...ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቧ ስላላወቀች» በማለት አስቀድሞ ለነቢዩ ኢሳይያስና በጓላም በጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረውን በመጥቀስ አስተምሮአል። 1ቆሮ.1÷19-21። ዝቅ ብሎም ደግሞ «እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፣ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ... ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ» ሲል ሰዎች በጥበባቸው፣ በኃይላቸውና ባብር ታታቸው እንዳይታመኑና እንዳይመኩ አስተምሯል። 1ቆሮ.1÷27-29።

ሰው ባዕውቀቱና በጥበቡ በቃይሉም የሚመካ ከሆነ የእግዚአብሔርን ሕልውና ይዘነጋል፣ የእርሱም ኃይል ይረሳል፣ በመጨረሻም ራሱን አምላኪ ይሆናል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሠውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ» በማለት የተናገረው እግዚአብሔርን ማወቅና ማመን ማምለክም ለዓለማዊው ፍልስፍናና ለገቢረ ኃጢአት ባዕውቀት ሕፃናት ለሆኑ ለየዋሆች እንጂ ዕውቀታቸውን ለሚያመልኩ አስተዋዮች ነን በማለት በሳይንሳዊ ፍልስፍናቸው ለሚመኩ የማይገለጥ መሆኑን፣ እነርሱም እግዚአብሔርን የማያውቁና የማያምኑ መሆናቸውን ለማመልከት ነው። ማቴ.11÷25። ስለዚህም እግዚአብሔርን ወደሚያስከድ ትምክህት እንዳንደርስ በዚህ ረቂቅ የትዕቢት ጣዖት ወድቀን አምላካችንን እንዳንክድ «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ» ያለው የቅዱስ ጳውሎስን ምክር እናስብ። 1ቆሮ.1÷31።

ሰዎች አፋቸውን ከፍተው ድምፃቸውን አሰምተው «እግዚአብሔር የለም» በማለት አይናገሩ ይሆናል። ነገር ግን ሕይወታቸውና ኑሮአቸው የእግዚአብሔርን ሕልውና ከካዱ ሰዎች ያልተለየ ከሆነ ከክሕድያኑ በምን ይሻላሉ? በአንደበታቸው «በእንድ እግዚአብሔር እናምናለን» እያሉ

በምግባራቸው እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ የማያደርጉ፣ በኑሮአቸውም ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለ፣ የእግዚአብሔርን ሕልውና የማያስቡ፣ የመሰላቸውን ሁሉ ሲሠሩ እግዚአብሔር የሚያያቸውና በመጨረሻው ቀን ሊፈርድባቸው የሚመጣና ዋጋቸውን የሚከፍላቸው መሆኑን ፈጽሞ የማያስተውሉ ሰዎች ከክሕድያን አምባ የሚመዘገቡ ናቸው እንጂ ሃይማኖት አላቸው እግዚአብሔርንም ያመልካሉ የሚባሉ አይደሉም። የእነዚህን መሰል ሰዎች እምነት የቃላት ወይም የሰውቀት ብቻ እንጂ በምግባር የተገለጠ የክርስትና ሕይወት አይደለም። ኑሮአቸውም ከተግባራዊ የእምነት ሕይወት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

ሰውነታቸውን በልቡናቸው ለሚመላለሰው ሥጋዊ ፍላጎታቸው አስገዝተው በምላሳቸው ብቻ እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ ቢኖገሩ፣ በኑሮአቸው አንድም የአምልኮ ሥራ ሲሠሩ ካልታዩና ሃይማኖታቸውን በምግባር ካልገለጡት በእፍ አምነው በልብ የካዱ ናቸውና እግዚአብሔርን ያመልካሉ ሊባሉ አይችሉም። በምግባር ያልተገለጠ እምነት ምውት /የሞተ/ ነው ተብሏልና። እነዚህ ሰዎች በአንደበታቸው ብቻ ስለተናገሩት በሥራም ስላልገለጡት በልቡናቸውም ስለሌለ እምነታቸው ከክሕድያን የተለየ ዋጋና ክብር ሊያገኙ አይችሉም። መዳን የሚገኘው በልብ አምኖ በአንደበት መስክሮ በተግባር ኖሮ ነውና። ያዕ.2÷14-26። ማቴ.7÷21።

ስለዚህ እኛም በአፍ መስክረን በልብ አምነን ይህንን እምነታችንንም በምግባር ካልገለጥን፣ መልካም እየሠራን እግዚአብሔርን እንደአምላክነቱ ካላመለክን ከሐዲ ከመባልና ከክሕደት የተነሣም ከሚመጣ ፍርድ ልናመልጥ አንችልም። ራሳችንን እያስመካ በራሳችንም እንድንታመን እየመከረ፣ አምልኮታችን በምግባር የተገለጠ በልቡና የታመነ እንዲሆን የሚፈትነንን ጠላት ተጠቁመን በዘመናችን ሁሉ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» የሚለውን ትእዛዝ እያሰብን ጭኖር አስተዋይነትና ለሰማያዊ ክብር የሚያበቃ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

ሸ/ አጋንንትን ማምለክ

ከአምልኮ ጣዖት መካከል አንዱ አጋንንትን ማምለክ ነው። ቅዱስ መጽሐፍ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ውጭ የሆኑትን ሰዎች ሁሉ አሕዛብ ይላቸዋል። እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ደግሞ ሕዝብ ይባላሉ። እነዚህ አሕዛብ የተባሉ አረማውያን ቡተለያየ ሁኔታ ለአጋንንት አምልኮአቸውን በመፈጸም የሚኖሩ ናቸው። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም «የአሕዛብ አማልክት ሁሉ አጋንንት ናቸውና» በማለት የተናገረው በአጋንንት የሚያመልኩ በመሆናቸው ነው። መዝ.95÷5።

አጋንንትን ማምለክ ማለት በጣዖታት ፊት ማለትም በተጠረበ እንጨትና በለዘበ ድንጋይ ፊት መንበርከክ ብቻ አይደለም። አጋንንትን ማመን፣ በአጋንንትም መታመን፣ በክፉ ሥራ ከሰይጣን ጋር በመተባበር፣ በችግር ጊዜ ከሰይጣን መፍትሔ መሻት፣ የማያውቁትን ለማወቅ ዕውቀት ፍለጋ በኃይለ አጋንንት ትጠል ወደሚበጥሱ ሥር ወደሚምሱ መሄድ፣ ስለአንዳች ጥቅም ሰይጣንንና እርሱ ያደረባቸውን ተስፋ ማድረግ፣ የሰይጣንን ፈቃድ መፈጸምና የመሳሰሉት ሁሉ አጋንንትን የማምለክ የተለያዩ ገጽታዎች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች ሰይጣን አስመስሎ ስለአደረገላቸው ጊዜያዊ የማታለያ ነገር ውለታ እንደ መክፈል ባለ ሁኔታ ይገዙለታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ሰይጣን የሚሹትን ነገር እንዲያደርግላቸው ቃልኪዳን ይገቡለታል። በዚህ መሠረትም በየወንዙ፣ በየመንደሩና በየሳፋ ሥር የደም መሥዋዕት የሚሠውለት፣ የከበረ ገጸበረከት እንዲሆነው ጌጣቸውንና ሀብታቸውን የሚገብሩለት፣ ልጆቻቸውን ሳይቀር ወስደው የሚያስረክቡትና አምልኮተ አጋንንትን ባሕል ያደረጉ ብዙ ናቸው። ለሀብታቸው በረከት ለሥራቸው ውጤት፣ ለንግዳቸው ትርፋማነት በሰዎች ዘንድ ስለሚኖራቸው ግርማ ሞገስና ፍቅር፣ በባልንጀሮቻቸው ላይ ስለሚኖራቸው የበላይነት፣ ስለብዙ ተመሳሳይ ነገሮች ሲሉ ተስፋቸውን ሁሉ በአጋንንት ላይ አድርገው በቀን ከሰው ጋር በአደባባይ

ምሽት ደግሞ ከአጋንንት ጋር ሲግግሉ የሚያድሩ ብዙ ሰዎች አሉ። አንዳች የሚያገኙ እየመሰላቸው በየጠንቋይ ቤት፣ በየቃልቻው ቤት፣ በየዛሩ ቤት፣ በየጨሌ ጣዩ ቤተ ጣዖት ገብተው አካላቸውንም ሀብታቸውንም የሚጨርሱ አእምሮአቸውን የሚያናውዙ እጅግ ብዙ ናቸው። እነዚህ ሁሉ እንግዲህ አምልኮአቸውን ለአጋንንት ሰጥተው የሚኖሩ ናቸው። አምላካቸው ጋኔን ነው፣ ተስፋቸውም በሰይጣን ነው።

በማንኛውም መንገድ ከአጋንንት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ያለጥርጥር የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይጥሳሉ። በምትሐትና በጥንቆላ የሐሰት ተአምራት እያደረገ ሰዎችን ያሳስት የነበረው የሲሞን መሠሪ ታሪክ በመጽሐፍ ተመዝግቧል። የሐዋ.8÷9-25። የሲሞን መሠሪ ቀጥተኛ ግንኙነት ከዲያብሎስ ጋር ነበር። በዚህ የጥንቆላ ሥራው በሕዝቡ ዘንድ «እኔ ታላቅ ነኝ» እያለ በኃይለ አጋንንት ከመመካቱም በላይ «ከታናናሾቹ እስከ ታላላቆቹ ድረስ ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ሁሉ ያደምጡት ነበር።»

በሐዋርያት ሥራ ታሪክ የተመዘገበው በጥንቆላ ለጌቶቿ ብዙ ገንዘብ ታስገኝ የነበረችው አገልጋይም እንዲሁም ግንኙነቷ ከአጋንንት ጋር የነበረና በኃይለ አጋንንት እየተመራች ትጠነቁል እንደነበር ተመዝግቧል። የሐዋ.16÷16/1-18። እነዚህ ታሪኮች የሚያስረዱት አጋንንት ብዙ ምልክትና ድንቅ ለማድረግ የሚችሉ መሆናቸውን ነው። በእነዚህ ጊዜያዊ ምልክቶችም አጋንንት ብዙዎችን ሲያስቱ እንደነበረና በዚህ ዘመንም ጭምር በማሳሳት ላይ መሆናቸውን የሚያስረዱ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ አጋንንትና በአጋንንት የሚመሩ ሰዎች የሚያደርጓቸው ምልክቶች ቅዱሳን በኃይለ እግዚአብሔር ከሚያደርጓቸው ተአምራት የተለዩ ናቸው። የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ እውነተኞች ክርስቲያኖችም በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ጥንቃቄና ዕውቀት ከመሳሳት ይጠብቃቸዋልና።

አንዳንድ ሰዎች ከአጋንንት ጋር በመተባበር በሰይጣን ኃይል እየታገዙ የሚያስደንቅ ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ። ሰይጣን ግን ይህን የሐሰት ተአምር በምንም መንገድ ያለ ዋጋ እያደርግላቸውም፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር የሚ ገባውን እምልኮና ክብር ለእርሱ እንዲሰጡና እንዲያመ ልኩት ለማድረግ ነው እንጂ ሊጠቅማቸው አይደለም። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎችም በሁለት ይከፈላሉ፣ የመጀ መሪያዎቹ ግንኙነታቸው ከዲያብሎስ ጋር መሆኑን የሚያውቁ ነገር ግን ከዚህ ግንኙነት ስለሚያገኙት ሥጋዊና ምድራዊ ጥቅም ብለው ለአጋንንት የሚገዙ ሲሆኑ፣ ሁለተኞቹ ደግሞ በዲያብሎስ የተታለሉ ናቸው። «ሰይጣን ደግሞ ራሱን የብርሃን መልአክ አስመስሎ ይለውጣልና» 2ቆሮ.11÷14 በዚህ መልክ ሊያታልላቸው ይችላል። ብዙ ቅዱሳንንና የዘጉ ባሕታውያንን ሳይቀር በዚህ መልክ እያሳሰተ በማታለልና ከክአታቸው በማስኮብለል ሊጥላቸው ሞክሯል፤ ያጣላቸውና ለእርሱ በመገዛት የሕይወት ዘመ ናቸውን ሁሉ እርሱን በማገልገል ያሳለፉና ጠፍተው የቀሩም ጥቂት አይደሉም።

አንዳንድ የዋሐን ሰዎች እግዚአብሔር ብቻ ከፍጹም ባሕርዩ የተነሣ የሚያውቀውን የወደፊቱን ነገር ለማወቅ ሲ ሉ የዲያብሎስ ባሪያዎች ይሆናሉ። የማይታወቀውን ለማወቅ ወደ ዲያብሎስ ማየትና እርሱን ተስፋ ማድረግ ለእግዚ አብሔር ብቻ የሚገባውን አምልኮ ለሰይጣን መስጠት ነው። በመሆኑም ከመጀመሪያው ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ሆኖ ይገኛል።

ዲያብሎስ እንደማንኛውም የሰው ዘር ሁሉ ያለፈውን ክስተትና ታሪክ ሊያውቅ ይችላል። የወደፊቱን ግወቅ ግን በእግዚአብሔር ሥልጣን ብቻ የተያዘ ነው። እርሱ እግዚ አብሔር ግወቁን ለሰጣቸው ቅዱሳንም ይህ ይሾላል። ከዚህ ሌላ ደግሞ ካለፈ ታሪክ በመነሣት በመገመትና አርቆ በግ ሰብ ሰዎች ስለወደፊቱ የተናገሩት ነገር ምናልባት እውነት ሊሆን ይችላል። ቢሆንም ከባሕርያቸው የተገኘ ዕውቀት ስላይደለ ፍጹም አይደለም። ይሁን እንጂ ዉሌ የሚ ጥሉትን፣ መጽሐፍ የሚገልጡትን፣ የቡና ስኒ የሚያዩትን፣

የሙታንን መናፍስት እንጠራለን የሚሉትን፣ ለካርታ የወደፊት ዕድልን እንናገራለን የሚሉትን፣ በአጠቋላይም የማ ይታወቀውን የሚያውቅ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ እንዳለ የሚያምኑትን በመጠበቅና በመጠየቅ መጻእያትን /የሚ መጣውን/ ለማወቅ የሚሞክሩ ሁሉ የተሳሳቱና አጋንንትን በማ ምለክ ራሳቸውን የሚያታልሉ ናቸው።

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ሁሉ ያልተጠቀሙ ነገር ግን የሚያምኑባቸው ሁሉ የመጀመሪያውን ትእዛዝ የተላለፉ ናቸው። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለሌሎች ጣዖታት ሰጥተዋልና ነው። ከርስቲያኖች ሁሉ ግን በማን ኛውም ጊዜና ሁኔታ ለአጋንንት ተገዥ ከመሆን ራሳቸውን ማራቅ አለባቸው። የእግዚአብሔር ቃልም «እነዚያ አሕዛብ የሚያደርጉትን ርኩሰት ታደርግ ዘንድ አትማር። ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ሟርተኛም፥ ሞራ ገላ ጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቁ ልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚ አብሔር ፊት የተጠላ ነው» በማለት አምልኮ ጣዖት በተለይም በአጋንንት በሚመሩ ሰዎች ተከፋ ግድረግ የረከሰ መሆኑን በመንገር ያስጠነቅቀናል። ዘዳ.18÷9–14።

መጻሕፍት በሰው ኃይል የሚታመን ሰው ርጉም ነው፣ ይልቁንም ደግሞ በአጋንንት የሚታመንና የሚመ ካባቸው የሚያመልካቸውም ምንኛ የረከሰ ነው? በማለት ይመክራሉ ይገሥጣሉ። መታመንና መመካት የሚያስፈልግ ከሆነም መመካት የሚገባው ካለመኖር ወደመኖር አም ጥቶ ዓለምን በፈጠረና በረቂቅ ጥበቡ በሚያስተዳድር ብቻውንም አምላክ በሆነ በልዑል እግዚአብሔር እንጂ በሌሎች መመካትና መታመን ጣዖትን ማምለክ ነው።

የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ

ይህ ክፍል ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ልናመልከው የሚገባ አንድ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ

ስላለን እርሱን ከማምለክ በቀር የተቀረጸውን ምስል ማምለክ የማይገባና ከጣዖት አምልኮ የሚቆጠር መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በባሕርዩ ረቂት የሆነ የማይታይ፣ የማይጸለስና የማ ይጨበጥ፣ ለዘሙኑ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው፣ ለመንግሥቱ ሽረት በባሕርዩ ሞት የሌለበት፣ ከዓለም በፊት የነበረ ዓለምን አሳልፎም ለዘለዓለም የሚኖር ፈጣሪ እግዚአብሔር ስላለን የሰው እጅ ለተጠበበባቸው ቅርፃ ቅርፅ መገዛትና እነርሱን ማምለክ የመጀመሪያውን ትእዛዝ የሚቃረን ነው።

ይሁን እንጂ ይህ ትእዛዝ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የተሣሉትን የቅዱሳን ሥዕሎችና ለእነዚህ የቅዱሳን ሥዕሎች የሚሰጠውንም ክብር የሚቃረን አይደለም። በዚህ ትእዛዝ የተነገረው የተቀረጹ ምስሎችን ማምለክና ለእነርሱ መገዛት የማ ይገባ መሆኑ ነው። «አትስገድላቸው አታምልካቸውም» በሚለው ሐረግ የተመለከተውም ሊመለክ የሚገባው የአምልኮ ስግደትም የሚሰገድለት አምላክ አንድ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፤ እርሱ ቀደም ብሎ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ብሏልና።

በየአብያተ ክርስቲያናቱ ተሰቅለውም ሆነ ተለጥፈው የምንመለከታቸው ሥዕሎች የቅዱሳንን ዜና ሕይወትና መንፈ ሳዊ ተጋድሏቸውን ጭምር በማሰብና በማስታወስ አብነት እንድናደርጋቸው ለማስቻል ነው። ሥዕሎቹን የምንሳለመው በሥዕሎቹ ለተገለጡት ቅዱሳን ፍቅራችንን ለመግለጥና ስለ ተጋድሏቸውም ስለምናከብራቸው ነው እንጂ ስለምና መልካቸው አይደለም። በዚያ በሥዕል ለተገለጠው ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ ሰማዕት ወይም መልአክ የሚገባውን ክብር እንድንሰጥ ይጠበቅብናል፤ ቅዱሳኑ እግዚአብሔር የመረጣቸውና ያከበራ ቸው ናቸውና። ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው በእነ

ልግሉትም ተጠምደው ዘመናቸውን በመንፈሳዊ ተጋድሎ አሳ ልፈዋልና ከብራቸው ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊም ጭምር ነው። የምናከብራቸውም እኛ ብቻ ሳንሆን የሰማይ መላእክትም ጭምር ናቸው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስም «የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል» በማለት የተናገረው ስለሰማያዊው ክብራቸው የሚያስረዳ ነው። ዮሐ.12+26። በዚህም መሠረት ለጸጋ ክብራቸው እንደሚገባ እናከብራቸዋልን እንጂ አናመልካቸውምና ይህ «የተቀ ረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው አታ ምልካቸውም» የሚለው ሐረግ ገድላቸውንና ቅድስናቸውን፣ ለመዘከር መታሰቢያቸውንም ለማድረግ በየቤተ ክርስቲያኑ የተለጠፉትንና የተሰቀሉትን ሥዕለ ቅዱሳንን የሚመለከት አይደለም። ሥዕልም ቢሆን፣ የተቀረጸ ምስልም ቢሆን በእግዚአብሔር ቦታ ተተክቶ ወይም ተጨማሪ ተደርጎ እንደአምላክ የአምልኮ ስግደት ሊሰገድለትና ሊመለክ ፈጽሞ የማይገባ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚህ በላይ በሰፊው እንደተብራራው ሁሉ የመጀመሪያውን ትእዛዝ በምና ነብበትና በምንሰማበት ጊዜ የዚህን ያህል ጥልቅ ትርጉም እንዳለው በማስተዋል በመኖር ሕጉን በማክበር የሚገኘውን ዋጋ ግንዘብ ለማድረግ እንድንችል እርሱ እግዚአብሔር ኃይል ጽንዕ ይሁነን።

ክፍል ሦስት

ሁለተኛው ትእዛዝ

«የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥ ፡፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠ ራውን ከበደል አያነጻምውና::» ዘጸ.20÷7::

የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ

ባለፈው ምዕራፍ የተመለከትነው የመጀመሪያው ትእ ዛዝ በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእግዚአብሔርን ስም በተመለከተ የተሰጠ ትእዛዝ ነው::

የእግዚአብሔር ስሙ ቅዱስ፣ ታላቅና ድንቅ ነው

የልዑል እግዚአብሔር ስም እንደማንኛውም ሰው ስም በልማድ የምንጠራው አይደለም:: ስለሆነም በጸሎተ ዕጣን ጊ ዜ በመኃልየ መኃልይ «ዘይትህ መልካም መዐዛ አለው፤ ስምህ እንደሚፈስስ ዘይት ነው» እንደተባለ ባማረ ቃል ስሙን እንጠራዋለን:: መኃ.1÷3:: እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጸሎቷ «ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ነገር አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው» ብላለች:: ሉቃ.1÷49:: አባቷ ኪሮ እግዚአብሔር ቅዱስ ጳውሎስም እንዲሁ «ስሙ የተ

ቀደሰና የተፈራ ነው» በማለት የእግዚአብሔርን የስሙን ቅድስና ተናግሯል:: መዝ.110÷9:: የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ በመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው ጸሎት «ስምህ ይቀደስ» እንድንለው ነግሮናል:: ማቴ.6÷9::

እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን በምናስታውስ ጊዜ ሁሉ በአክብሮትና በመፈራት ሊጠራ የሚገባውን ስሙን «ስምህ ይቀደስ» ማለት አለብን:: ስለዚህም ነው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያልን ስመ እግዚአብሔርን በጠራን ቁጥር በትጎትና ሆነን የምንሰግደው:: ካህናተ ሰማይ ሱራፌልም የሚያመሰግኑት «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚ አብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ነው:: ታላቅና ቅዱስ ስሙን በሚጠሩ ጊዜም መፍራትና በመን ቀጥቀጥ ከመገበሩ ፊት ቆመው በክንፎቻቸውም ፊቶ ቻውንና እግሮቻቸውን ሸፍነው ነው:: በዚያ ጊዜም የመድ ረኩ መሠረት ከድምፃቸው የተነሣ ይናወጣል፤ ቤቱንም ጢስ ይሞላበታል:: ይህም ነቢዩ ኢሳይያስን «እኔም ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፤ ዓይኖቼ እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ፤» እንዲል አድርጎታል:: ኢሳ.6÷1–5::

ይህን ሱራፌል በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠሩ ትን ቅዱስ፥ ስም አርባዕቱ እንስሳም በመገበሩ ፊት ቆመው ያለእንቅልፅ እረፍት «ቅዱስ ቅዱስ፥ ቅዱስ የነበረውና የሚመ ጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ፤ ያለው አምላክ» በማለት ሲያ መሰግኑት ማየቱን ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ መዝግቦታል:: ራእ.4÷8–10:: ከፍጹም ክብሩና ከቅድስናው የተነሣም «በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘለዓለምም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው፥ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ... በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ::» ራእ.4÷11::

የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ ነው:: «ስሜም በአሕዛብ

ዘንድ ታላቅ ይሆናልና» ሚል.1+11። ኤርምያስም «አቤቱ+ እንደ አንተ ያለ የለም፣ አንተ ታላቅ ነህ ስምህም በኃይል ታላቅ ነው» በማለት ተናግሯል። ኤር.10+6። ኢያሱ ወልደ ነዌም በበኩሉ «ለታላቁ ስምህም የምታደርገው ምንድን ነው?» ያለ ሲሆን ነቢዩ ዳዊትም «የሠራዊት ጌታ እግዚ አብሔር የእሥራኤል አምላክ ነው ይባል ዘንድ ስምህ ለዘለዓ ለም ታላቅ ይሁን» በማለት ዘምሯል። ኢያ.7+9። 2ሳሙ. 7+26። ነቢዩ ኤርምያስ በሌላ ሥፍራ «ተቤዣኪአቸው ብርቱ ነው+ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው» ብሎአል። ኤር.50+34። እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ምንባባት ቅዱሱ የእግዚአብሔር ስም ታላቅ መሆኑንና ይኸውም በቅዱሳን አንደበት የተመሰከረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ከዚህ ሌላም አምላካችንን እግዚአብሔርን የምና መሰግንበት እጅግ ያማረ የምስጋና ቃል በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ እናገኛለን፦ «አቤቱ ጌታችን+ ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ+ ምስጋናህ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ ብሏ ልና።... አቤቱ+ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመ ሰገነ።» የሚል ነው። መዝ.8+1–9። በእርግጥም የአምላካችን ስሙ ግሩምና ምስጉን ነው። ከዚህም ሌላ ስለወልደ እግዚ አብሔር ልደት በተናገረው ትንቢት ነቢዩ ኢሳይያስ «ስሙም ድንቅ መካር+ ኃያል አምላክ+ የዘለዓለም አባት+ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» ብሎታል። ኢሳ.9+6። በትክክልም የእግዚአብሔር ስም ድንቅ ነው እንጂ። ለዚህም ነው ድንቅ ብቻ ደግሞ አይደለም፣ የእግዚአብሔር ስም መልካምም ነው ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ክርስቲያኖች የሚጠሩበት «መልካም ስም» ያለው፣ ቅዱስ ዳዊትም «ስምህን እናገራለሁ መልካም ነውና» በማለት ምስክርነቱን ገልጧል። ያዕ.2+7።

የእግዚአብሔር ስም ቅዱስ፣ ታላቅ፣ ምስጉን፣ ድንቅ፣ መልካም መሆኑን አረጋግጠናል። እንግዲህ «የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ እግዚ አብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና» የሚለው ትእዛዝ የሚመለከተው ይህን ስም መሆኑን ግጤን

ይገባል። የትእዛዙም ዋና ዓላማ የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም ንጹሕን መላእክት እንኳን በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠ ሩት ክቡር በመሆኑ የሰው ልጆችም አክብረውት ከብርን እንዲያገኙ ነው።

የእግዚአብሔር ስም ድንቅ ተአምራትን ያደርጋል

የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በቤተ መቅደስ ደጃፍ ተቀምጠ ይለምን ለነበረው ነዳይ ሰው የሰጠው መልስ የዚህ ማረጋገጫ ነው «ብርና ወርቅ የለኝም፣ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤። በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ» ባለው ጊዜ ሰውየው ተነሥቶ ተመላለሰ። የሐዋ.3+6። ቅዱስ ጴጥሮስ የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከመጥራት በስተቀር ያደረገው እንዳችም ነገር አልነበረም። የአምላክ ስም ሽባውን ፈታው፣ ተነሥቶም ተመላለሰ። ከዚህም ሌላ የአይሁድ ሊቃነ ካህናት ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን ይዘው በመከከል አቁመው «በምን ኃይል ወይስ በማን ስም እናንተ ይህን አደረጋችሁ?» ብለው በጠየቋቸው ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ «እናንተ በሰቀላችሁት... በናዝሬቱ በኢየሱስ ክር ስቶስ ስም... ነው።» በማለት የተናገረው መልስ እውነተኛው ድንቅና ተአምራት ሁሉ ሊደረግ የሚችለው በእግዚአብሔር ስምና ኃይል መሆኑን የሚያስረዳ ነው። የሐዋ.4+7–10። ስለዚህም ነው አባቶቻችን ሐዋርያት እግዚአብሔርን «አቤ ንም ጌታ ሆይ+...ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ልጅህም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ በሪያዎች በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው» በማለት በጸሎት የጠየቁት። የሐዋ.4+29–30። ይህም የእግዚአብሔር ስም የተአምራት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

እኛ ባለንበት በዚህ ዘመን «የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» የሚለውን ያነቢዩ ኢዩኤልን ቃል በመጥቀስ ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ብቻ እምነትን

ከክሰርቲያናዊ ምግባር ጋር ሳያዋሕዱ መዳን የሚገኝ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። እነዚህ ራሳቸው ተሞኝተው ሌሎችንም የዋሆች የሚያሞኙ፣ ስሙን ከመጥራት ቃሉንም ከመናገር በቀር ፈጽመው ለአምላክነቱ በሚገባ ሃይማኖት የማያመልኩትና የሚናገሩትን ቃሉንም በምግባር ፈጽመውት የማያውቁት የስም ክርስቲያኖች ሁሉ በፍርድ ቀን በፊቱ ቆመው ምናልባት «ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህ ተአምራት አላደረግንምን?» በማለት ይከራከሩ ይሆናል+ ከንቱና ፍሬ አልባ ክርክር።

ስሙ ኃያል፣ ድንቅና ቅዱስ ነውና ተአምራት ያደርጋል፤ ይህ በእግዚአብሔር ክቡር ስም የተደረገ ተአምር ግን «ምግባር በተለየው እምነት» እንደቃሉ ሳይኖሩ «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ» ለሚሉ ግብዞች ሁሉ መዳኛ ሊሆን አይችልም። ማቴ.7+22። ማቴ.25+41–46። ያዕ.2+17። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ስም ለአጋንንት ድል መንሻ፣ ለምስጋናና በጸሎት ጊዜ ለልመና በትጎትና ሆኖ ሊጠሩት የሚገባ እንጂ ተገቢ ባልሆነ ሥፍራና ንጹሕ ፍጹምም ባልሆነ እምነት እንዲሁ በከንቱ የማይጠሩት መሆኑን በማስተዋል እንድንኖር ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር ስም ለአጋንንት አስፈሪና አስደንጋጭ ነው

በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው «ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፦ ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት» የሚለው ቃል ስሙ አጋንንትን የሚያስደነግጣቸውና የሚገሥፃቸው መሆኑን የሚያስረዳ ነው ። ሉቃ 10+17። እነዚህ ሰባ ሁለቱ አርድዕት ምንም እንኳን ለአገልግሎት አዲስ የነበሩ ቢሆንም አጋንንትን የማውጣት ሥልጣን ተሰጥቷቸው እንደነበር እንመለከታለን። ይህም ጌታ «ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ» በማለት የገባው ቃል ኪዳን ይፈጸም ዘንድ ነው። ማር.16+17።

ቅዱሳን አባቶቻችን ሐዋርያት ሁሉ በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት አጋንንትን ሲያወጡ እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ ይገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ በአጋንንት መንፈስ በመታገዝ እየጠነቆለች ለጌቶቿ ገንዘብ ታስገባ የነበረችውን ሴት ከአደረባት ጋኔን መፈወሱ ለዚህ አንድ ማስረጃ ነው። ሐዋርያው በሴቲቱ ያደረውን የጋኔን መንፈስ «ከእርሷ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዣለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት ወጣ።» የሐዋ.16+18። ይህ ሁሉ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ቅዱሳን በሙሉ የአጋንንትን ሠራዊት ሲያንቀጠቀጡአቸው የሚኖሩና ዛሬም ቢሆን ይኸው የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም የአጋንንት ፀር መሆኑን የሚያስገነዘብ ነው።

በዚህ የከበረ ስም በመጠቀም ሰዎችን የሚያሳስቱ ክፉዎች «አጋንንትን በስምህ አላወጣንምን?» በማለት በፍርድ ቀን የሚከራከሩ መሆኑ በመጽሐፍ ተመዝግቦአል። የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም በተጠራበት ሥፍራ ርኩሳን አጋንንት መጪነቃቸው ኃያል ስሙ አስፈሪና አስደንጋጭ በመሆኑ ነው እንጂ ስለነዚህ ሐሳውያን ጽድቅ አይደለም። «በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን?» በማለት የሚከራከሩት ክፉ ሰዎች በስሙ እያሳሳቱ ስለሠሩት ክፉ ሥራ ከፍርድ የማይድኑ መሆኑ የእግዚአብሔር ስም በአጋንንት ላይ የሚሠራው ኃይል ለኃጢአተኛው ሰው የጽድቅ ምስክር ሊሆን የማይችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ይህ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስም ታዲያ እንዲህ ኃይል የሚያደርግ ሲሆን በየሥፍራውና በየአጋጣሚው ሁሉ በከንቱ ስንጠራው ጥቂትም አናፍር ይሆን? ለእርሱ እንደሚገባው በመፍራትና በመንቀጥቀጥ በአክብሮት ልንጠራው የሚገባ እንጂ ለክብሩ በማይስማማ አጋጣሚው ሁሉ ልንጠራው አያስፈልግም።

የእግዚአብሔር ስም በችግር ጊዜ መጠጊያ ነው

ስለቅዱስ ስሙ በባለቤቱ በእግዚአብሔር የተነገሩት ቃላት ጣፋጮችና መጽናናትን የሚሰጡ የተወደዱም ናቸው። በመጽሐፈ ምሳሌ «የእግዚአብሔር ስም የጸና ግምብ ነው ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል።» ተብሎ እንደ ተነገረ። ምሳ.18÷10። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ደግሞ ይህን በተግባር ስለአየና ስለአረጋገጠው «አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ÷ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኳቸው፣ መከበቡንስ ከበቡኝ÷ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኳቸው፣ ንብ ማርን እንደሚከብ ከበቡኝ÷ አሳትም በእሾህ ውስጥ እንደሚነድ ነዳጹ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኳቸው» በማለት ተናግሯል። መዝ. 117÷10-12። በሌላ ቦታ ደግሞ «ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው» በማለት ነገሩን አጠቃልሎአል። መዝ. 123÷8። ቀደም ብሎም በተለምዶ አነጋገር «በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን÷ በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን» በማለት÷ የተናገረው ለዚህ ነበር። መዝ. 43÷5። «አቤቱ÷ በስምህ አድነኝ» በማለትም እግዚአብሔርን ለምኖአል። መዝ.53÷1።

እግዚአብሔር ሁልጊዜ በቅዱስ ስሙ እንድንታመን ይፈልጋል። በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ «በእግዚአብሔር ስም የሚታመን÷ በአምላኩም የሚደገፍ ማነው?» በማለት የጠየቀው ጥያቄ ይህን የሚገልጥ ነው። ኢሳ.50÷10። በሶፎንያስ ደግሞ «በመካከልሽም የዋህና ትሑት ሕዝብን አስቀራለሁ፣ በእግዚአብሔር ስም ይታመናሉ።» በማለት ስሙ መጠጊያ መታመኛም መሆኑን ገልጧል። ሶፎ.3÷12። በዳዊት መዝ ሙርም «ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርገዋለች፣ ረዳታችንና መጠጊያችን እርሱ ነውና÷ ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋልና÷ በቅዱስ ስሙም ታምነናልና» የሚል ቃል ተነግሯል። መዝ.32÷20-21።

ይህ ሁሉ የመጽሐፍ ክፍል የሚያስረዳው የእግዚአብሔር ቅዱስ ስም በችግር ጊዜ ቢጠሩት መጽናኛ፣ ቢታመኑበት መጠጊያ መሆኑን ነው። በጊዜው ሁሉ ረዳታችንና ኃይላችን የሆነውን ቅዱስ የእግዚአብሔር ስም ለባሕርዩ በሚገባው መጠን ልናከብረው እንጂ በከንቱ ልንጠራው የማይገባ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር ስም የምንባረክበትና የመንፈሳውያን ምሥጢራትን ጸጋ የምናገኝበት ነው

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት እንደተ ማርነው ሁሉ ወደምሥጢራት የሚያደርሰንን የጥምቀትን ጸጋ የእግዚአብሔር ልጅነት የምናገኘው ስመ ሥላሴን በመጥራት በስሙም በመባረክ ነው። ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ...ደቀመዛሙርት አድርጓቸው» በማለት በሰጠው ትእዛዝ ይታወቃል። ማቴ.28÷19። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር በስሙ ታጠምቅና ልጆችን ታበዛለት ዘንድ በአበው ሐዋርያት አማካኝነት ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት ሥልጣን ነው።

በዚህ ሰማያዊና አምላካዊ ሥልጣን በመጠቀም የሐዋርያት አለቃ የሆነው ቅዱስ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ዕለት የተሰበሰቡትን ሁሉ «ንስሐ ግቡ÷ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» በማለት ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ የልጅነት ጸጋ ሰጥቷቸዋል። የሐዋ.2÷38።፤ 10÷48።፤ 8÷12። ስለምሥጢረ ቀንዲል የተጻፈውንም ብንመለከት «ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽማግሌዎች /ካህናትን/ ወደ እርሱ ይጥራ፣ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸ ልዩለት» የሚል እናነባለን። ያዕ.5÷14። ይህ ቃል ለታመመ ሰው የሚፈጸምን ምሥጢረ ቀንዲል በእግዚአብሔር ስም ማከናወን እንደሚገባ የሚያስረዳ ነው። በልዑል እግዚአብሔር ስም ምሥጢራትን የመፈጸም ሥልጣን የተሰጠው ደግሞ ለካህኑ /ለቄሱ/ ነው። ዘዳ.18÷5። ካህኑም ሕዝቡን የሚባርከው «የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ ይሁን፣ በእግዚአብሔርም ስም እንመርቃችኋለን» እያለ ነው። መዝ.128÷8።

በተጨማሪም ምሥጢራትን ሁሉ የምንሳተፍባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ስሙን የተሸከመች የእግዚአብሔር ማደርያ ናት። እርሷም የከበረች የምሥጢራት ሁሉ ግምጃ ቤት ስለሆነች በስሙ ለሚታመኑ ምእመናን ሁሉ ከምሥጢራት በረከት ትናኖለች /ትሰጣለች/። በቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ስም ጸጋ የሚናኝባቸው /የሚሰጥባቸው/ ቅዱሳት ምሥጢራትን ሁሉ ለመዘርዘር ጊዜና ሥፍራ አይበቃምና በአጭሩ እንተወዋለን። እንግዲህ የእግዚአብሔር ስም የኃይል ሁሉ፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካኝነትም የጸጋ ስጦታ ሁሉ እና የበረከትም ምንጭ ከሆነ ስለዚህ የከበረ ቅዱስ ስመ መለኮት ከእኛ የሚጠበቀው ምንድን ነው?

ስለ ስመ እግዚአብሔር እኛ ግዴታ

ይህ ስም የተጠራንበት /የሐዋ. 15÷17/ እንዲሁም ከዓለም ሁሉ የተለየንበት በጌምባሮቻችንም ላይ የሚታተመው የከበረ የእግዚአብሔር ስም ነው። ራእ.22÷4። ለዚህ ሕያው ስም ልናደርግ የሚገባን ምንድን ነው?

ይህ ቅዱስ ስም የእግዚአብሔር ስም ነውና ልናከብረው በመፍራትና በመንቀጥቀጥም ልንጠራው ይገባል። ነቢዩ ሙሴ «አምላክህ እግዚአብሔር የተባለውን፣ የተመሰገነውንና የተፈራውን ስም ባትፈራ» በማለት እንዳስጠነቀቀ /ዘዳ.28÷58/ ስሙን የሚፈሩ የሚያከብሩትም የሚገባቸውን መንፈሳዊ ዋጋ ያገኛሉ፤ በራእይ «ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ» የሚል ተጽፏልና። ራእ.11÷18።

ቅዱሳን የሆኑ የሰማይ ሠራዊት በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የሚጠሩትን የእግዚአብሔርን ስም በታላቅ ትኅትና ሆነን «የተቀደሰ ስምህን ኃጢአት ባረከሰው

እንደበታችን መጥራት የሚገባን አይደለም» እያልን በክብር ልንጠራው ይገባል። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም «እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት÷ በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።» በማለት ሁሉም ሰው የእግዚአብሔርን ስም ከፍ ባለ ክብር እንዲጠራ መክሯል። መዝ.33÷3። ይህን ቅዱስ ስም ስንጠራ በመፍራትና በማከበር ብቻ ሳይሆን በፍጹም ፍቅርም መሆን ይኖርበታል፤ ይህ ፍቅርም የእግዚአብሔር ጥበቃ፣ ፍጹም መውደድና ቸርነቱ ሁሉ ከእኛ ጋር እንዲሆን ያደርጋል። በእርሱ ፍቅር የሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ ስሙን በአክብሮትና በፍቅር ይጠሩት እንደነበርና ዛሬም ቢሆን በዚህ መልክ የሚጠሩት መሆኑን ሲያመለክት «አቤቱ በቅዱሳንህ አንደበት ስምህ የተቀደሰና ጣፋጭ ነው» ሲል ቅዱስ ዳዊት ዘምሯል።

እንግዲህ የአምላካችን ስም የከበረና ቅዱስ ሲሆን በተራው ነገር ሁሉና በየአጋጣሚው ልንጠራው አይገባም፤ ምክንያቱም በሆነው ባልሆነው ስሙን በመጥራት ልማድ ወደማድረግ ደረጃ ደርሰን ክብሩንና ፍቅሩን እናጣለንና ነው። ከዚህ ይልቅ ልንጠራው የሚገባው በጸሎት ጊዜ ቸርነቱን ስንለምንና ስለተደረገልን ቸርነቱም ስናመሰግን፣ ስጠታውንም ተስፋ በማድረግ መሆን አለበት። ቅዱስ ዳዊት «በእንተ ስም እጆቼን አነሣለሁ፤ ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች» «በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ» «ለልዑል እግዚአብሔር ስም እዘምራለሁ» በማለት በተደጋጋሚ የተናገራቸው ቃሎች የሚያስረዱት የእግዚአብሔርን ስም እንዴት ባለ ጊዜና በምን ሁኔታ ልንጠራው የሚገባ መሆኑን ነው። መዝ.62÷4-5፤104÷3፤7÷7።

በመዝሙር በምናመሰግንበትና በጸሎት በምን ለምንበት ጊዜ ሁሉ እርሱ በመካከላችንና ከእኛ ጋር መሆኑን በማሰብ ቅዱስ ስሙን በትኅትና ልንጠራው ይገባናል። እርሱ ራሱ «ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።» በማለት የገባው ቃል ይሸንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ማቴ.18÷20።

ፍጹም የሆነ ልባዊ ፍቅርና አክብሮት ሳይኖር የእግዚ አብሔርን ቅዱስ ስም በልማድ መጥራት ተገቢ አይደለም። እንደ አሕዛብ ባለ ልማድ የልቡና ምንም ሳይኖር በአንደበት በመናገር ብዛት የሚገኝ አንዳችም ጥቅም የለምና። ማቴ. 6÷7። የስመ እግዚአብሔር አጠራራችንና ጸሎታችን ሁሉ ለታይታና ለክብር ወንበር ለማግኘት ይደክሙ ከነበሩት ጸፎችና ፈሪሳውያን የተለየ መሆን ይኖርበታል። ሉቃ. 20÷47። በልቡናቸው የእግዚአብሔር ፍቅር ሳይኖር በሰዎች ፊት ለመታየት ብቻ ብለው የሚጸልዩና የከበረውን የእግዚ አብሔርን ስም የሚጠሩ ሰዎች ሁሉ በዚህ ተግባራቸው ሌሎችን ያሰናክሉበታል እንጂ የሚያገኙት መንፈሳዊ ጥቅም የለም። ከዚህ የተነሣም ሰዎች የጸሎትን ዋጋና የእግዚአ ብሔርን ስም እንዲያቃልሉ ምክንያት ይሆናሉ። ለዚህ ኃጢ አት ምክንያት በመሆናቸው ደግሞ መቀጣታቸው አይቀርም። ስለሆነም እኛ ከዚህ መሰሉ ድርጊት ልንቆጠብ ይገባል።

በጸሎት ጊዜ አእምሮአችን በቆምንበት ዓላማ ላይ ተወስኖ በእርጋታና በተመስጠ ልንጸልይ ከሚገባ በቀር በተ በተነና በተረበሸ ጎሊና የምንጸልየው ጸሎትም፣ የምንጠራው ስመ እግዚአብሔርም ከልባችን ስላልሆነ በነቢዩ «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው» የተባለው በእኛ ይፈጸማል፤ እኛም ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከሚጠሩት እንመደባለን። ኢሳ.29÷13፣ ማር.7÷6። «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚሉኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማይ የሚ ገቡ አይደሉም» የተባለላቸውና በፍርድ ቀንም በከንቱ ስለጠ ሩት ስመ እግዚአብሔር ተገቢውን ዋጋ ለመቀበል በዙፋኑ ፊት በሚቆሙ ጊዜ «ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አል ተናገርንምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን?» የሚሉትና ስሙን በመጥራታቸው ብቻ ከፍርድ ያልዳኑት ሁሉ የተጠ ቀሱበት የጌታ ቃል የሚያስተምረን የእግዚአብሔርን ስም በምንጠራበት ጊዜ ሁሉ ግዴታችን ምን መሆኑን በመገንዘብ ተገቢውን ጥንቃቄ እንድናደርግ ነው። ማቴ.7÷22።

ለውይይት ተሰብስበው መርሐ ግብራቸውንም በስመ

እግዚአብሔር ጀምረው በጸሎት የከፈቱትን ጉባኤ፣ እግዚ አብሔርም የተገኘበትን ስብሰባ ለእግዚአብሔርም ስም የሚገባውን ክብር የሚያቃልሉ ሰዎች የሚንቁ፣ የእግዚ አብሔርን ስም ከብር ረስተዋልና ስሙን በከንቱ ከሚጠሩት ጋር የሚደመሩ ናቸው።መዝሙረኛው ባለቅኔ ቅዱስ ዳዊት «የእግዚአብሔርንም ስም አመሰግኑ። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ የእግዚአብሔር ስም ቡሩክ ይሁን» በማለት እንደተናገረው በጊዜው ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ማክበርና ከፍ ከፍ ማድረግ ከእኛ የሚጠበቅ ነው። መዝ.112÷1–2። ጻድቁ ኢዮብም «እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።» በማለት የተናገረው ቃል በደስታና በሰላም ጊዜ ብቻ ሳይሆን በመከራም በፈ ተናም ጊዜ ቢሆን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም በአክብሮትና በፍቅር መጥራት የሚገባ መሆኑን የሚያስተምር ነው። ኢዮ.1÷21። ከዚህ ሁሉ የምንማረው በምንሠራው ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ከፍ ከፍ ማድረግ ዓላማችን ሊሆን የሚገባው መሆኑን ነው።

በቅዱስ መጽሐፍ የምናገኛቸው ታሪኮች በጸሎትና በምስጋና ብቻ ሳይሆን በተገቢው ጊዜና ሥፍራ የእግዚ አብሔርን ስም በመጥራትና የከበረ ስሙን ከፍ ከፍ ማድረግ የሚቻል መሆኑን ያስተምሩናል። አባታችን አብርሃም በሄ ደበት ሥፍራ ሁሉ መሠዊያን እየሠራ የእግዚአብሔርን ስም ይጠራ ነበር። ዘፍ.13÷4፤26÷8። ልጁ ይስሐቅም እንደ አባቱ ያደርግ ነበር። ዘፍ.26÷25። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊትም «የመድ ኃኒትን ጽዋ አቀበላለሁ፥ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራ ለሁ» ብሏል። መዝ.115÷4 ነቢዩ ሳሙኤልም የእግዚአብሔ ርን ስም በሚገባው ሥፍራ በክብር ከጠሩት ቀደምት ቅዱሳን መካከል አንዱ ነው። ይህንንም ቅዱስ ዳዊት «ሳሙ ኤልም ስሙን በሚጠሩት ዘንድ ነው»።ሲል መስክሮለታል። መዝ.98÷6። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና» ሁላችን አግባብ ባለው ሁኔታ የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ክቡር ስም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ እየጠራን ለመዳን መዘጋጀት አለብን። ሮሜ.10÷13።

የስመ እግዚአብሔር ክብር እንዲሰበክና እንዲታወቅ በሰዎች ሁሉ ልቡናም የክብር ሥፍራ እንዲኖረው በትጎትና ሆኖ ስሙን መጥራት ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ስለስሙ መሰበክና መታወቅ ልበ ደንዳናውን ፈርዖንን እንኳ እንዳስነሣው በመጽሐፍ ተነግሮአል፤ «ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ ስሜም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ለዚህ አስነሣሁህ ይላ ልና።» ሮሜ.9÷17። በስሙ የምናምን በእርሱም የምንታመን እኛ ደግሞ እርሱን ለዓለም ሁሉ ለማሳወቅ በትጉት ልቡና ስሙን ያለማቋረጥና በክብር ልንጠራ ይገባናል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አባቱ አብን በመጥቀስ «ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው ስምህን አስታውቅኋቸው፤ አስታውቅማቸዋለሁ።» በማለት የተና ገረውና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «ስምህን ለወን ድሞቼ እነግራቸዋለሁ» ያለውም ቢሆን የሚያስገነዝበን ስመ እግዚአብሔርን በአግባቡ በመጥራት ለሌሎች ስለዚህ ክቡር ስም መስበክ የሚገባ መሆኑን ነው። ዮሐ.17÷6፤26። ዕብ. 2÷13።

ይህን የከበረ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስም መስበክ ብቻ ሳይሆን ስለዚህ ስም መከራ መቀበልም ስለ እግዚአብሔር ስም ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑን ሲያጠይቅ ስለ ቅዱስ ጳውሎስ በተናገረ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው እኔ አመለክተዋለሁና» ብሏል። የሐዋ.9÷16። ስለአባቶቻችን ስለ ሐዋርያት መከራ «እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገ ባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ» በማለት የተነገረው ቃል ስለእግዚአብሔር ስም መከራ መቀበልም ቢገባ በደስታ ማስተናገድ የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያስታውቅ ነው። የሐዋ.5÷41። ከዚህ በላይ በየፈርጁ የጠ ቀስናቸው ታሪኮች ሁሉ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቅዱሱን የእግዚ አብሔርን ስም በአምልኮ ሥርዓትም ሆነ በስብከት መካከል አስፈላጊም በሆነው ጊዜ ሁሉ በአክብሮት በመፍራትና በመን ቀጥቀጥ ሊጠራው ከሚገባ በቀር በከንቱ ያነሣው ዘንድ የማይ ገባ መሆኑን የሚያስተምሩ ናቸው። ይህ ስለ ስመ እግዚአብሔር ልንፈጽመው የሚገባ ግዴታችን ነውና በአግባቡ ልናከብረው ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት

ባገኙት ሥፍራ ሁሉ እንደቀላል ነገር በመቁጠርና ባለማክበር የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩት ከቱምቾና በልቡናቸው ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በስድብና በእርግማን በፈዝና በጨዋታቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም ይጠራሉ። በአሳለፉት የሕይወት ዘመ ናቸውም ሆነ ባሉበት ዘመን ሁሉ በውስጣቸው አንዳች ፈሪሃ እግዚአብሔር የለም። ስለዚህ በጨካኝ ልቡናቸው ልክ ባሌለው አንደበታቸው የእግዚአብሔርን ስም እንደ መጣላቸው ሲጠሩ ይውላሉ። ይህም ከኑፋቄና ከመሐላ ሌላ የእግዚአብሔር ስም በከንቱ የሚጠራበት ሁኔታ ነው።

<u>መሐላ</u>፡–በዘመነ ብሉይ በእውነት ብቻ መግል የተፈቀደ ነበር። እግዚአብሔር «በስሜም በሐሰት /በእውነት ካልሆነ በቀር/ አትማሉ» ብሎ ነበርና። ዘሌ.19÷12። ከዚህ ምንባብ በመነሣት በዘመነ ሐዲስ የተከለከለው መሐላ በብ ሉይ ኪዳን ለምን ተፈቀደ? ፈሪሃ እግዚአብሔርን ለማረ ጋገጥ መሐላ አስፈላጊ ነበርን? በማለት ሊጠየቅ ይችላል። መልሱን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

በዘመነ ብሉይ እግዚአብሔር መሐላን የፈቀደበት ምክንያት በዚያ ዘመን አረማዊነት የበዛ ከመሆኑ የተነሣ እሱ ዛብ ሁሉ በጣዖቶቻቸው ይምሉ ስለነበር፤ ሕዝበ እግዚአብሔር ደግሞ ይህን በማየትና በመስማት በጣዖታት ወደመግል እንዳያዘነብሉና እነርሱም መመኪያና መጠጊያ የሚሆናቸው የሚታመኑበት በስሙም ሊምሉ የሚችሉበት አምላክ እን ዳላቸው እንዲያምኑና ከአረማውያንና ከመሐላቸው የተለዩ ሕዝበ እግዚአብሔር መሆናቸውን ዐውቀው እንዲጸኑ ለማድረግ ነበር። ስለዚህም በሕግ «እግዚአብሔር አምላክህን ፍራ፤ እርሱንም አምልክ፤ በስሙም ማል።» የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶአል። ዘዳ.6÷13። በዚህ መጽሐፍ በሌላ ምዕራፍ ደግሞ «አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ÷ እርሱንም አምልክ፤ ከእርሱም ተጠበቅ /ከእርሱም አት ለይ/፤ በስሙም ማል» የሚል ተጨማሪ ትእዛዝ እናገኛለን። ዘዳ.10÷20።

«በስሙም ማል» ሲልም በዚያ ዘመን ሰዎች የሚምሉባቸው ብዙ ጣዖታት መኖራቸውን ከመጠቆሙም በላይ በዓለም ላይ ተሰፋፍተው በነበሩት ጣዖታት ሁሉ አትማል ማለቱ እንደሆነ ግልጥ ነው። በስሙ ሊማልበት የሚገባ መታመኛ ብቻውን አንድ የሆነ እግዚአብሔር ነው። ይህም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በኢያሱ አንደበት «በእናንተ መካከል ወደቀሩት ወደ እነዚህ አሕዛብ አትግቡ፤ የአማልክቶቻቸውንም ስም አትጥሩ፤ አትማሉባቸውም፥ አታምልኳቸውም፥ አትሰገዱላቸውም፤ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳደረጋችሁት ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተጠጉ እንጂ።» በማለት በተናገረው ቃል ይረጋገጣል። ኢያ.23÷7።

እግዚአብሔር አምላክ ለነቢዩ ኤርምያስም «በባሕል ይምሉ ዘንድ ሕዝቤን እንደአስተማሩ በስሜ፦ ሕያው እግዚአብሔርን፡ ብለው ይምሉ ዘንድ የሕዝቤን መንገድ በትጋት ቢማሩ» በማለት የተናገረው በእግዚአብሔር ስም መማል በዚያ ዘመን የተፈቀደ እንደነበረ የሚያመለክት ነው። ኤር.12÷16። ሕዝቡ በበኣልና በሌሎች ጣዖታት በማሉ ጊዜ እግዚአብሔር «ይቅር የምልሽ እንዴት አድርጌ ነው? ልጆችሽ ትተውኛል አማልክትም ባልሆኑ ምለዋል» በማለት ቁጣውን ገልጧል። ኤር.5÷7። ስለዚህም በዚያ አረማዊነት በነገነበት ዘመን በእግዚአብሔር ማምለክን ለማሳየት ሲባል በስሙ መማልና አረማዊነትን መቃወም ከብርና ጸጋ የሚያስገኝ ነበር። እግዚአብሔርም ሕዝቡን ሲያነጋግራቸው «እናንተ የያዕቆብ ቤት፦በእግዚአብሔር ስም የምትምሉ ሆይ ይህን ስሙ» ይላቸው የነበረው በእግዚአብሔር ማመን በስሙም መማል የበለጠ መሆኑን ለማስረዳት ነበር። ኢሳ.48÷1። በእግዚአብሔር ስም መማላቸውም ከአሕዛብ ሁሉ የተለዩ እንደአደረጋቸው ሲገልጥ መጽሐፍ «በእርሱ /በእግዚአብሔር/ የሚምል ሁሉ ይከብራል» ብሏል። መዝ.62÷11። ጌታ እግዚአብሔርም ራሱ ስለሃይማኖት መስፋፋት በተናገረ ጊዜ «ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከክል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።» በማለት የአምልክ ጣዖትን ከንቱነት አብሮ ገልጧል። ኢሳ.45÷23።

በዘመነ ሐዲስ ደግሞ አረማዊነት ጠፍጅል ባይባልም ወንጌል በመሰበኩና በእግዚአብሔር ስም መማሉ ባለማስፈለጉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው ሲያስተምር «ከቶ አትማሉ... ቃላችሁም አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።» በማለት ባለፉት ዘመናት ያለቦታውና ያለአክብሮት በልማድ ይጠሩት የነበረውን ስመ እግዚአብሔር እንዲፈሩትና እንዲያከብሩት አስተምሯል። ማቴ5÷34–37። አለቆቻቸው የሆኑት ፈሪሳውያንም እንግዳ ሕግ አውጥተው «ማንም በቤተ መቅደስ የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በቤተ መቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መባዕ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል» ያሉትን በመጥቀስና በመተቸት ይህ የፈሪሳውያን ሕግ ትክክል አለመሆኑንና መቅደሱና መሰዊያው ቅዱስ መሆኑን ሲገልጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንግዲህ በመሰዊያው የሚምለው በእርሱና በእርሱ ላይ በሚኖረው ይምላል፤ ...በሰማይም የሚ ምለው በእግዚአብሔር ዙፋንና በእሱም ላይ በተቀመጠው ይምላል።» ብሏቸዋል። ማቴ.23÷16–22

ሰዎች ራሳቸው ስለሠሩት መጥፎ ሥራ ወይም ስለሌሎች ሥራ ራሳቸውን ወይም ሌሎችን ሲረግሙ በእግዚአብሔር ስም የሚረግሙ ከሆነ የከበረውን ስም ያለአግባብ በመጥራት እርሱን መፍራትን የሚያቃልሉ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ለምሳሌም ነቢዩ ዳዊትን ለመጥቀስ እንችላለን። ቅዱስ ዳዊት ወደ ቀርሜሎስ ሰው ወደ ናባል መልእክተኞቹን ልኮ ምግብ በፈለገ ጊዜ ናባል በመሳደቡ ዳዊት ተቆጥቶ ሰዎቹ ሠይፋቸውን እንዲታጠቁ አዘዘ። «ለእርሱ ከሆነው ሁሉ እስከ ነገ ጠዋት ድረስ አንድ ወንድ ስንኳ ብተው እግዚአብሔር በዳዊት ላይ እንዲህ ያድርግ እንዲህም ይጨምር» በማለት ምሎ ነበር። 1ሳሙ.25÷22። የናባል ሚስት አቢግያ ብዙ ስጦታዎችን በመስጠት ለእርቅ በለመነችው ጊዜ ዳዊት ግን ደም ለማፍሰስ ምሎ ነበር። እርሷ ግን «እግዚአብሔርም ለጌታዬ የተናገረውን ቸርነት ሁሉ ባደረገልህ ጊዜ፥ በእሥራኤልም ላይ አለቃ አድርጎ ባስነሣህ ጊዜ፥ አንተ በከንቱ ደም

እንዳላፈሰስህ÷ በገዛ እጅህም እንዳልተካስህ ይህ ዕንቅፋትና የሕሊና ፀፀት በጌታዬ አይሆንልህም፣ እግዚአብሔርም ለጌታዬ በጎ ባደረገልህ ጊዜ ባሪያህን አስብ።» በማለት ዳዊት ይቅርታ እንዲያደርግ ጠየቀችው።1ሳሙ.25÷30-31። ይህም ዳዊት ለመሐላው ሲል ሊፈጽም የነበረውን ስሕተት እንዲያስተውለው አደረጎታል። ስለዚህም «ወደ ደም እንዳልሄድ÷ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን÷ አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ» በማለት አመሰገናታል። 1ሳሙ.25÷33።

<u>ሌላ ታሪክ እንጨምር፦</u> ብዙ ጊዜ በሚምል አንድ ሰው ቤት የሚሠራ አንድ ክርስቲያን አገልጋይ ነበር። ጌታው በሚምልበት ጊዜ ሁሉ እየሰገደ በመስቀል ምልክት ያማትብ ነበር። ይህም ጌታው በማለ ቁጥር የሚያደርገው የዘወትር ተግባሩ ነበር። ጌታው በነገሩ መገረም አገልጋዩን ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ጠየቀው። አገልጋዩም «በፊቱ መፍራትና መንቀጥቀጥ ከብርም ሁሉ የሚገባው የአምላኬ የእግዚአብሔር ስም ሲጠራ እንዴት አልሰግድ?» በማለት መለሰለት። ጌታውም ዘወትር ለሚጠራው ስመ እግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ባለመስጠቱ አፈረ፣ ራሱን ከዚያ ትጉት አገልጋይ ጋር አነፃፀረና ራሱንም በመውቀስ ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከመጥራት ተቆጠበ። እኛም ደግሞ እንደዚህ ሰው ስለ ስመ እግዚአብሔር ክብር የሚያስተምረን አገልጋይ ባይኖረንም ስሙ በተጠራ ጊዜ ሁሉ በፊቱ በመውደቅ የክብር አክሊላቸውንም በማውረድ ለእግዚአብሔር የአምልኮ ስግደት ከሚሰግዱት ቅዱሳን መላእክት ከሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በቂ ትምህርት ልንወስድ ይገባል። ራእ.4÷10።

ከዚህ በላይ እንደጠቀስነው እግዚአብሔር ስለ እውነት እንኳ ቢሆን ስሙን ጠርተን እንዳንምል የከለከለን ከሆነ በሐሰት በመማል የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ምን ያህል የተወገዘና ከፍተኛ ኃጢአት መሆኑን ማወቅ አያዳግትም። አንዳንድ ሰዎች ያልሆነውን የሆነ ለማስመሰል በስመ እግዚአብሔር የሚምሉ ደግሞ አሉ። በጣም

የሚገርሙት ደግሞ ከፉ የሆነውን ነገር ለመሥራት ምለው ቃል የሚገቡት ናቸው። ለእንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የገቡትን ቃል ባይፈጽሙት በተሻላቸው ነበር፤ አለበለዚያ ሁለት ስሕተቶችን ይፈጽማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ይጠራሉ፣ በቃላቸው መሠረት ክፉውን ሥራ በመሥራት ኃጢአትን ያደርጋሉ፤ በመጨረሻም ስለሠሩት ኃጢአት መጠየቃቸውና መቀጣታቸው አይቀርም። ንጉሥ ሄሮድስ የገባውን ቃል ለመለወጥ በማፈሩ የቅዱስ ዮሐንስን አንገት በማስቆረጥ የበለጠ ኃጢአትን ሠራ፤ ቀድሞውኑ የገባው ቃል አግባብነት የሌለው ከመሆኑም በላይ የኋለኛው ጥፋት ደግሞ የከፋ ሆነ። መልካም ላለማድረግ የሚምሉ ሰዎችም ደግሞ አሉ። መልካሙን ነገር ላለማድረግ መማላቸው በራሱ ጥፋት ሲሆን በመሐላቸው መሠረት መልካም አለ ማድረጋቸው ደግሞ ሁለተኛ ጥፋት ነው። ምናልባት በተለያዩ ምክንያቶች ተገፋፍቶ ቤተ ክርስቲያን ላለመሄድ ወይም ንስሐ ላለመግባት ምሎ ይሆናል። መልካም የሆነውን ነገር ላለማድረግ መማሉ ሳያንስ ቤተ ክርስቲያን አለመሄዱ ወይም ንስሐ አለመግባቱ የበለጠ ጥፋት ይሆናል።

ሌሎች ደግሞ ሰውን ካለማመናቸው የተነሣ ያላመኑትን ሰው እንዲምል የሚገፋፉ አሉ። ስለአንድ ነገር እንዲምል ሰውን መገፋፋት በራሱ ኃጢአት ነው። እግዚአብሔር የከለከለውን እንዲያደርግ የተደረገ ግፊት ነውና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጣስ ነው። ይህን የመሰለውን ግፊት ማድረግ በሰውየው መንፈሳዊ የሕይወት ጉዞ ውስጥ የመሰናክል ድንጋይ እንደማስቀመጥ ነው። ከዚህ ጋር አብሮ የሚታየው ሌላው ታላቅ ኃጢአት ደግሞ ሰው ክፉ ነገርን ለማድረግ እንዲምል መገፋፋት ነው። ስለዚህ እኛ ክፉ ነገሮችን በማድረግና በማስደረግ ስመ እግዚአብሔር በከንቱ እንዲጠራ ምክንያት ከመሆን በብርቱ መራቅ አለብን።

አንዳንድ ሰዎች ማንም ሳያስገድዳቸውና እንዲምሉም ሳይጠይቃቸው ልማድ ስለሆነባቸው ብቻ ሳይፈሩ በእግዚአብሔር ስም ይምላሉ። እነዚህን የመሰሉት ሰዎች ለስመ እግዚአብሔር አክብሮት ስለሌላቸው እጅግ ተራ በሆነው ነገር ና በመሐላ መረጋገጥ በማያስፈልገው ጉዳይ ሁሉ

ስሙን ጠርተው ይምላሉ። እንግዲህ በየምክንያቱ የእግዚ አብሔርን ክቡር ስም በመጥራት መማል ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ከትእዛዛት አንዱን መተላለፍ ስለሆነ ለስመ እግዚ አብሔር ተገቢውን ክብር በመስጠት፣ በማስተዋልና በጥንቃቄ በተገቢው ጊዜና ሁኔታም ብቻ ስሙን እየጠራን ልናመልከው ያስፈልጋል።

የሚምል ሰው ስለሚምልበት ጉዳይ ወይም በመሐላ ስለሚያረጋግጠው ጉዳይ ተአማኒነትን ያጣና ሌሎች ሰዎ ችም የተናገረውንና እርሱንም የማያምኑት መሆኑን ያመ ለክታል። ለመታመን የሚበቃ ቢሆን ኖሮ ነገሩን ለማረጋገጥ መማል አያስፈልገውም ነበር። በተናገረው ነገር ተአማኒ ነትን ለማግኘት መማሉ በራሱ በሰዎች ዘንድ በቁም ነገረኛነትና በእውነት ተናጋሪነት የማይታወቅ መሆኑን አምኖ የተቀበለው መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ስለዚህም ስለ እርሱ እውነተኛነት ለሚሰሙት ሰዎች ለማሳመን ሲል ይምላል። እውነተኛው ሰው ግን መናገር የሚገባውን ይናገራ ል እንጂ የተናገረውን ሁሉ ሰዎች እንዲቀበሉት በመጨነቅ መሐላ ሲደረድር አይገኝም። ቃሉን ሰምቶ ያመነ ይቀ በለዋል፣ ያላመነም ይተወዋል። የተናገረው እውነት በጊዜው ደግሞ መገለጡ አይቀርም፣ ዋናው ነገር እውነትን መናገሩ ላይ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ሌሎች የተናገሩአቸውን ሁሉ በመሐላ እንዲያረጋግጡላቸው ይሻሉ። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የተ ነገረውን ለማመንም ሆነ ላለማመን ሙሉ ነፃነት ያላቸው መሆ ኑን ከመናገር በቀር በመሐላ የሚፈልጉትን ለማሟላት ሲባል ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ መጥራት አይገባም። ተናጋሪው እውነተኛ እስከሆነ ድረስ እንዲሁም የሚነገረውን ነገር እውነት ከመሆኑ የተነሣ በተግባር ሲገለጥ የሚታይ እስከሆነ ድረስ አድ ማጮቹ ያለምንም የመሐላ ማረጋገጫ የተናገረውን የሚያምኑ በመሆኑ መማል አስፈላጊም አይደለም። እውነተኛ መሆናችንን ለማረጋገጥ የሚሹ ሰዎች ማረጋገጫ ቢጠይቁን እንኳ እን ዳንምል ልንጠነቀቅ ይገባል። እውነተኛነታችን መመዘን ያለበት የተናገርነው እውነት በመሆኑና በተግባር በመገለጡ እንጂ በምን ደረጃ የመሐላ ብዛት እንዳይሆን በብርቱ ጥንቃቄ ራሳን መጠበቅ ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔርን ስም ማቃለል፡- በዚህ በሁለተኛው ትእዛዝ «የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ» የተባልን በመሆኑ «በእግዚአብሔር ስም ያለአግባብ አትማል» የሚል ባለመሆኑ በእውነትም ቢሆን በእግዚአብሔር ስም መማልን የሚፈቅድ አይደለም። ይህም ትእዛዙ ሰፊና ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ ያለአግባብ መማልን ብቻ ሳይሆን ማን ኛውንም ዓይነት ያለአግባብ በስመ እግዚአብሔር መጠቀምን የሚያጠቃልልና ይኸንኑ ደግሞ የሚከለክል መሆኑን ያመለክታል።

በብዙ ሰዎች አንደበት የእግዚአብሔር ስም እንደዋዛ ሲጠራ እናደምጣለን። እነዚህ ሰዎች በሚራገሙበት፣ በሚሳደቡበት፣ በቀልዳቸውና በተረቶቻቸው፣ በብስጭታቸውና በሚያስፈራሩበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር ስም ከአፋቸው አይጠፋም። በእነዚህ ሁሉ የማይገቡ ነገሮች ክቡር የሆነውን ስመ እግዚአብሔር በየጣልቃው መጥራት ምንኛ አሳፋሪ የሆነ ነገር ነው? እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም ያለአግባብ ይጠቀሙበታል፣ ከስድብና ከእርግማን፣ ከቀልድና ከፌዋዌ ከብስጭትና ከዛቻ ጋር አስተባብረው ያለአግባብ የጠሩትን ስመ እግዚአብሔር በጸሎታቸው ጊዜ ደግሞ «ስምህ ይቀደስ» በማለት ያነሡታል። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ስም ለተቀደሰ ልዕልናው በሚገባ ክብር መጠራት ያለበት መሆኑን ዘንግተውታል። እንደእነዚህ ካሉት ሰዎች ምግባር ራስን መቆጠብና የእግዚአብሔርን ስም በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በተገቢውም ክብር መጥራት ያስፈልጋል።

ሶኖ ብዙ ጊዜ አእምሮአቸውን ሳይሰበስቡ በተረበሸና ባልተረጋጋ ልቡና፣ ባልሰከነ አእምሮ ሆነው ይጸልያሉ፣ ስመ እግዚአብሔርንም ይጠራሉ። ምንም እንኳ ሰው ደካማ ከመሆኑ የተነሣ ለእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገባውን ክብር መስጠት የማይቻለው ቢሆንም እግዚአብሔር ግን ሰው በትሕ ትና ሆኖ እንደየአቅሙ የሚያቀርብለትን ልመናም ሆነ ምስጋና ይቀበላል፣ ይሰማልም፣ እርሱ መምህረ ትጎትና ነውና። በመጽሐፍ እንደተመዘገበው እግዚአብሔር አሠርቱን

ትእዛዛት በሰጠ ጊዜ ተራራው ተናወጠ፣ በጢስም ተሞላ፣ ታላቅ ነጎድጓድ ብርሃንና የመለከት ድምፅም ተሰማ፣ ሰዎችም ከዚህ የተነሣ በፍርሃት ተዋጡ። እነዚህ ሁሉ ምልክቶችም የእግዚአብሔርን አስፈሪና አስደንጋጭ ግርማ የሚያስረዱ ናቸው። እንግዲህ በዚህ ዘመን ምሕረት እግዚአብሔር ክብሩን ዝቅ አድርጎ ራሱን በትኅትና በመግለጥ የትኅትናን ነገር አስተምሮና ፈጽሞ ካሳየን በኋላ የሚገባውን ክብር ባለመስጠታችን፣ እንድናከብረውም ሲል እንደ ቀድሞው ያድርግብን? በትሕትና ሲናገረን አላከብረውና ነገሩንም አላዳምጠው ስላልን በነጎድጓድና በሚያስደነግጥ ብርሃን ያስፈራራን? አይደለም፣ እኛ አስቀድመን ለባሕርዩ በሚገባ ክብርና ምስጋና ልናከብረው ልናመሰግነውም ያስፈልጋል እንጂ።

አንዳንድ ሰዎች የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንደቀላል ነገር ሲጠሩት ይሰማሉ። ለስም አጠራሩ ቦታና ጊዜ እንዲሁም ሁኔታ አይመርጡለትም፣ ከቶውኑም አያከብሩትም። በሆነው ሁሉ ኢየሱስ፣ ኢየሱስ እንዲህ አድርጎ፣ እንዲህ ብሎ ወዘተ እያሉ እንደአምላካቸውና ፈጣሪአቸው ሳይሆን እንደ አንድ ጓደኛቸው ሁሉ አፋቸው እንደለመደ ይጠሩታል። እንዲህ ሊሆን ግን አይገባም። ከሆነም የከበረውን የእግዚአብሔርን ስም እንደማቃለል የሚቆጠር ነው። በእርግጥ የእግዚአብሔርን ስም አክብረን በአግባቡ ብንጠራው እኛው እንከብራለን እንጂ ለእርሱ ክብር የምንጨምርለት ሆኖ አይደለም፣ እርሱ በባሕርይ ክብሩ የተመሰገነ ነውና። እኛ ስላላከበርነው ክብሩ የሚቀነስ አይደለም። ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ይህን በባሕርዩ ቅዱስ የሆነ ስም ስትጠራ «ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ» ብላ ነው። ይህ ስም አጠራርም በጋ የተገለጠው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ሁሉ በፈቃዱ የፈጠረና የሚገዛ ጌታ፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል ሆኖ በእንዲት ሕልውና የሚኖር ዘለዓለማዊ አምላክ፣ በኃጢአት ምክንያት ስለአዳም ኃጢአት/ስሕተት/ ሞት የተፈረደበትን የአዳም ዘር ሁሉ ወደ ሕይወት የመለሰ፣ በሥጋውና በደሙ ዓለምን ሁሉ ያዳነ መድኃኒት መሆኑ የሚገለጥበትና ምሥጢርን የተሞላ ነው።

ምናልባት ስሙን «ኢየሱስ» ብሎ በነጠላው መጥራት መቀራረብ የሚመስላቸው የዋህ ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ማለት የእግዚአብሔርን ባሕርይና ለባሕርዩ የሚሰማማውን ክብር በሚገባ ወደማወቅ መድረስ ማለት እንጂ የእግዚአብሔርን ስም ከማክበር ወደመለየት መሄድና ስሙን እንደተራ የተፀውኦ /የመጠሪያ/ ስም በየአጋጣሚው ሁሉ ማንሣት ማለት አይደለም። እንኳን ልዑለ ባሕርይ የሆነውን እግዚአብሔርን ቀርቶ በጣም የሚወዱትን ባልንጀራ እንኳን ከመሣሣት የተነሣ በየአጋጣሚው መጥራት ይሰቅቃል ይጨንቃል። ስለዚህ አንደበትን ልማዳዊ ከሆነ ስም አጠራር መቆጠብና የእግዚአብሔርን ቸርነቱን ከኃያልነቱ፣ ትኅትናውን ከባሕርይ ክብሩ ጋር እያነፃፀሩ በአግባብ ስሙን መጥራት ያስፈልጋል።

እግዚአብሔርን ማማረርም ራሱ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የመጥራት ሌላው ገጽታ ነው። አንዳንድ ሰዎች በተቸገሩ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርማሉ በእርሱ ያመካኛሉ፣ በሆነው ባልሆነው ሁሉ እርሱን ይከሰሳሉ። በሆነው ምክንያት ሁሉ በፊቱ ቆመው ላለመጸለይ ከእርሱም ለመለየት መወሰናቸውን በመናገር «ያስፈራሩታል»። በዚህ ጊዜ ሁሉ ስሙን እየጠሩ ነው የሚሰማቸውን ስሜት በቁጣ የሚገልጡት። ይህ ግን ፈጽሞ የሚገባ አይደለም፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ስም ልንፈራውና ልንንቀጠቀጥለት ልናከብረውም ስለሚገባ ነው። በመጽሐፍ እንደተጻፈው ወንድሙን የተሳደበ ፍርድ፣ ወንድሙን አላዋቂ ያለ የገሃነም እሳት ፍርድ የሚገባው ከሆነ /ማቴ.5÷25/ በእግዚአብሔር ላይ በክፉት የተናገረ በቁጣም የሚያጉረመርም ምንኛ የባሰ ፍርድ ይጠብቀው ይሆን? ለክርስቲያኖች በሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ከማመስገንና ረቂቅ የሆነ ሥራውን በአድናቆት ከመመልከት በቀር ማማረርና ሌሎችም እርሱን እንዲያ ማርሩት ምክንያት መሆን አልተፈቀደላቸውም፣ ራሳቸውንም ይህን ከመሰለው ምግባር ማራቅ ይኖርባቸዋል።

የእግዚአብሔርን ክብር በማቃለልና መለኮታዊ ባሕርዩን ካለማወቅ የተነሣ በሚመጣ የኑፋቄ ትዕቢት ስሙን በከንቱ የሚጠሩም አሉ። ለምሳሌ እንደ አርዮስና የዘመኑ ወሎዶደ አርዮስ «የይሖዋ ምስክሮች» ነን ባዮች ክርስቶስን ፍጡር /ሎቱ ስብሐት/ ማለት፣ እንደ መቅዶንዮስና የዘመኑ የሉተር ውላጆችና መሰሎቻቸው ክርስቶስን አማላጅ /ሎቱ ስብሐት/ ማለት የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባሕርይ ካለ ማወቅ፤ ምሥጢረ ሥላሴንም ካለመጠንቀቅ የመጣ ከንቱ አምልኮ ነው። በዚህ መልክ ስሙን መጥራት በከንቱ ስመአምላክን ከመጥራት የሚቆጠር ነውና ከዚህ ይሰውረን።

ጥንቆላና ይህን የመሰለው ተግባር ሁሉ አምልኮ ባዕድ ከመሆኑም በተጨማሪ ስመ አምላክን በከንቱ መጥራትም ነው። ልብን ለአጋንንት ሰጥቶ ለዲያብሎስ ግብር ገብቶ በሰው ፊት ግን ስሙን በመጥራት ማታለል የዋሁን ሕዝብ ማሞኘት ነው። በእግዚአብሔር ስም የሚፈጸመው ይህ ኃጢአትም ስሙን በከንቱ መጥራት ነው። በራሳቸው ፍጡራን ወደሆኑትና በአጋንንት እየተገዙ ወደሚኖሩት ወደ ጠንቋዮችና መሰሎቻቸው ሁሉ በመሄድ አንዳች መፍትሔ የሚያገኙ የሚመስላቸው ሁሉ በስመ እግዚአብሔር ከለላ የሚፈጸም የዚህ ኃጢአት ተባባሪዎች ናቸው። ስለሆነም በመጽሐፍ «ምዋርተኛም÷ሞራ ገላጭም÷ አስማተኛም÷ መተተኛም÷ በድግምት የሚጠነቁልም÷ መናፍስትንም የሚጠራ ÷ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም... ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» እንደተባለ እያስታወስን በዚህ ከመሳተፍና ስመ አምላክን በከንቱ ከመጥራት ልንቆጠብ ይገባል። ዘዳ.18÷9–12።

አንዳንድ ዘፋኞች ደግሞ በግጥሞቻቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም በመጨመር ተወዳጅነትን ያገኙ እየመሰላቸው የዘፈናቸው ማሻሻጫ ያደርጉታል። የእግዚአብሔር ስም ግን ከክብሩ የተነሣ በመፍራት በመንቀጥቀጥ የሚጠራ እንጂ መዝፈኛ አይደለም። እነዚህን በመከተል አብረው የሚያቀነቅኑና የሚከተሉአቸውም ሁሉ የኃጢአታቸው ተባባሪዎች ናቸው። ዘፋኝነት በራሱ ኃጢአት ስለሆነ ኃጢአት በሆነ ዘፈን ቅዱሱን ስመ እግዚአብሔር መደባለቅ ደግሞ

የከፋ ኃጢአት ነው። ገላ.5÷21። የሚዘፍኑም የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም ተብሏልና ከዚህ ራሳችንን ማራቅ ይገባናል።

ብዙ ሰዎች በተለይም በክርስትናዎች አካባቢ ሱቆቻቸውን፣ ድርጅቶቻቸውንና የንግድ ቤቶቻቸውን በእግዚአብሔር ስም ይሰይማሉ። ምናልባት ይህን ማድረጋቸው «የእግዚአብሔር ወዳጆች መሆናቸውን» ለማሳወቅ ወይም ደግሞ በንግዱ ብዙ ትርፍ እንዲያገኙ በማሰብ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሥራቸውን እንዲ ባርክላቸው ከመጸለይ በስተቀር በዚህ መንገድ ለመጠቀም መፈለጋቸው ትክክል ካለመሆኑም በላይ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ነው። እንግዲህ ክርስቲያኖች ሁሉ ክርስትናችን በልቡና እምነትና በምግባር የሚገለጥ ሊሆን ከሚገባው በቀር በዚህ ዓይነት ተግባር እንዳይሆን መጠበቅ ያስፈልጋል። ሌላው ከዚህ ጋር አብሮ የሚኖረው ደግሞ የክርስቶስን ስም በተለያዩ አልባሳት /ኮፍያ፣ካናቴራ ወዘተ/ ላይ በመጻፍና በማተም ለማስታወቂያ መጠቀም የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከመጥራት ጋር የሚደመር ነው። ስለሆነም ስሙን በከንቱ ከመጥራት መቆጠብ አለብን።

አንዳንዶች ደግሞ የልጆቻቸውን ስም የሚሰይሙት ባለማስተዋልና በግድየለሽነት ነው። ሰው በእግዚአብሔር ስም ሊጠራ አይገባውም፣ የእግዚአብሔር ስም የብቻው ነውና። ነገር ግን የልጆቻቸውን ስም ለምሳሌ አማኑኤል፣ ኤልሻዳይ፣ አዶናይ፣ አንዱ አምላክ ወዘተ በማለት የሚሰይሙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እየጠሩት ናቸው። አማኑኤል ማለት የወልደ እግዚአብሔር የተዋሕዶ ስሙ ነው፤ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ነው። የሚገልጠውም እግዚአብሔር ሰው የመሆኑን ምሥጢር ነው። ታዲያ በዚህ ስም ልንጠራበት ይገባናል? ፈጽሞ አይገባም። «ኤልሻዳይ» ማለትም «ሁሉን ማድረግ የሚችል» ማለት ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ከሃሊነት የሚያመለክት ነው። ማነው ሁሉን ቻይ «ከሃሌ ኩሉ» በዚህ ስም ሊጠራ የሚደፍር? ማንም ከቶ ሊኖር አይገባም። አዶናይም እንዲሁ

ነው። ወልደ አማኑኤል /የአማኑኤል ልጅ/፣ ገብረ ኢየሱስ /የኢየሱስ አገልጋይ/፣ ገብረ እግዚአብሔር / የእግዚአብሔር አገልጋይ/ እያሉ መሰየም ግን ስመ ክርስትና በመሆኑ ተገቢ ና የሚደገፍ ሞምር ነው። እንግዲህ በስማችን ኃጢአት እንዳንሠራ፣ የእግዚ አብሔርንም ስም በከንቱ እንዳና ስጠራ መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

አንዳንዶች ፈላስፎች ነን ለማለት የሚቃጣቸው ሰዎች፣ ሀወቅን፣ ተጠበብን የሚሉበትን ፍልስፍናቸውን አድ ማጭና ተቀባይነት ያለው ለማድረግ፣ የሰሚን ወይም የአን ባቢን አእምሮ ለመሳብ ሲሹ «እግዚአብሔርም እንዲህ ብሏል» እያሉ የእርሱን ሕያው ትምህርት ምዉት ለሆነው ፍልስፍናቸው ይጠቀሙበታል። ይህንኑ ፈሊጥ ብለውት በተ ራ ዲስኩራቸውና የፖለቲካ ንግግሪ ው እንደቀልድ ስመ እግዚአብሔርን የሚጠሩ የእርሱንም ቃል የሚጠቅሱ ዘመነኞችም በየሬድዮው ይደመጣሉ። በየጋዜጣው ይጽፋሉ። እነዚህም ሁሉ ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ እየጠሩት ናቸው።

በሥነ ጽሑፍ ዓለም የምናውቃቸው አንዳንድ ደራሲ ያንና ገጣምያንም የሚጽፏቸው ድርሰቶች ጆሮ ገብና ተነ ባቢ እንዲሆኑላቸው ከሚያውቋቸው መጻሕፍት የተቆነጻፉ ጥቅሶችን ከቃለ እግዚአብሔር ይጠቅሳሉ፣ ስመ እግዚአብሔ ርንም ለማሾፊያና ለመሳለቂያ ሲጠቀሙበት ይስተዋላሉ። ይህም ሁሉ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራ ት ነውና ሳያስጠይቅ አይቀርም። በራሱ ባሕርያዊ ውበትና ማራኪነት የሌለውን ደረቅና ባዶ ጽሑፍ በቃለ እግዚአብሔ ርና በስሙም ለማጣፈጥና ማስዋብ መሞከር ስመ እግዚ አብሔርን በከንቱ ከመጥራት የሚመደብ ነው።

እስከዚህ ድረስ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራ ት ምን ማለት መሆኑን ተመልክተናል። በመቀጠል ደግሞ ውጤቱ ምን እንደሆነ እንይ።

እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን አይምረውም

ሰማይ ዙፋኑ በመሆኑ፣ ምድርም የእግሩ መረገጫ በመሆኗ /ኩዋ/ በሰማይም እንዳንምል ከተነገረን በከንቱ የእግዚ አብሔርን ስም ጠርቶ መማል የቱን ያህል የማይ ገባና ከባድ ቅጣት የሚከተለው መሆኑን ልናስተውል ይገ ባል። በፍጥረታት እንዳይምል የተከለከለ ሲሆን በፈጣሪው ስም የሚምል ሰው በደሉ ይቅርታ እንደማያገኝ በእግዚ አብሔር ፊትም ምሕረት እንደማይደረግለት መጻሕፍት ይናገራሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔርን ስም የሚሰድብና የሚያማርር ይገደል ነበር። «የእግዚአብሔርን ስም የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል፣ ማኅበሩም ሁሉ ይውገሩት፣ መጻተኛ ወይም የአገር ልጅ ቢሆን የእግዚአብሔርን ስም በሰደበ ጊዜ ይገደል።» እንደተባለ። ዘፍ.24+16 የእግዚ አብሔርን ስም መስደብ ማለት ክብር ምስጋና የሚገባውን ቅዱስ ስም በአልባሌ ሥፍራ መጥራትና ልዕልናውን ዝቅ ማድረግ፣ በጠቅላላው ስመ እግዚአብሔርን በከንቱ መጥራት ማለት መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

በነቢዩ ሕዝቅኤልም «እግዚአብሔር ስለቅዱስ ስሙ ይቀናል» ተብሎአል። ሕዝ.39+25። ይህም ቃል እግዚአብሔር አምላክ ክቡር ስሙ በከንቱ እንዲጠራ የማይፈልግ መሆኑን የሚገልጥ ነው። ለዚህ ነው «ወደመጡባቸውም ወደ አሕዛብ በመጡ ጊዜ+ ቅዱስ ስሜን አረከሱ። እኔ ግን የእሥራኤል ቤት በመጡባቸው በአሕዛብ መካከል ስለአረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ ስል ራራሁላቸው፣» በማለት ስለእሥራኤል ልጆች የተናገረው። ሕዝ.36+20። የእግዚአብሔርን ስም ማርከስ ማለትም ሊሰጠው የሚገባውን ክብር መንሣትና ልዕ ልናውን ማቃለል ነው። ይህን ከመሰለው ግብር መራቅና በከንቱ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ከመከሰስ ራስን ለማዳን መጠንቀቅ ይገባል።

በነቢዩ ዘካርያስም የተነገረው የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚጠሩትን ሁሉ ስለሚጠብቃቸው ቅጣት የሚያወሳ ነው። እግዚአብሔርም በነቢዩ አድሮ የተናገረው «በሐሰት የሚምልም ሁሉ ይጠፋል... እኔ አስወጣዋለሁ» የሚል ነው። ዘካ.5÷3። በከንቱ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ መማል ዘላለማዊ ቅጣት የሚከተለው ከሆነ የራሳችንን ስም አጠራር ልንመረምርና የእግዚአብሔርን ስም በክብር መጥራት ልንለምድ ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር ለስሙ ክብር የማይሰጡ ካህናትንም አስጠንቅቋል። «ለስሜ ክብርን ትሰጡ ዘንድ ባትሰሙ በልባችሁም ባታደርጉት+ እርግማን አሰድድባችኋለሁ በረከታችሁንም እረግማታለሁ» ብሏል። ሚል.2+2።

ይህ ሁሉ ማስጠንቀቂያ እንግዲህ የእግዚአብሔር ስም ምንኛ የከበረ ገናና መሆኑን ከማመልከት ባሻገር ይህን ክቡርና ቅዱስ ስም በከንቱ የሚጠራውን ሰው እግዚአብሔር ያለ ይቅርታ የሚቀጣው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ ስሙን በማክበር የሚገኘውን በረከት እንዳናጣና እንዳንቀጣ፣ እንዳንጠፋም በጊዜው ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም በማክበር እንኑር፣ በሃይማኖተ አበውም «ስምየ መሐሪ ወመስተሣህል» እንደተባለ አቤቱ ስለቅዱስ ስምህ ብለህ ማረን ራራልን ይቅርም በለን እያልን እንለምነው። እግዚአብሔርም ይህን በማድረግ መኖርን እንዲሰጠን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

ክፍል አራት

ሦስተኛው ትእዛዝ

«የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ። ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፣ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው። አንተ+ ወንድ ልጅህም+ ሴት ልጅህም+ ሎሌህም+ ገረድህም+ ከብትህም+ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ፣ እግዚአብሔርም በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርንም+ ባሕርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፏልና፣ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም።»

ዘጸ.20÷10–11።

የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ

ሰንበት የተባረከ ቀን ነው። በጌታም ዘንድ የዕረፍት ቀን ነው። ይህ ትእዛዝት ከመጻፋቸው በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእሥራኤል የሰጠው ቀዳማዊ ትእዛዝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ይፈጽመው ዘንድ ከመሰጠቱ በፊት እግዚአብሔር ራሱ በተግባር የፈጸመው ትእዛዝ ነው ሊባልም ይችላል። እንግዲህ በዚህ መሠረት ቀዳማዊ ትእዛዝ መሆኑን ካረጋገጥን፣ እግዚአብሔርም ከሥራው ሁሉ በማረፍ ሰንበትን ለእረፍት የባረከውና የቀደሰው መሆኑን ካወቅን እኛ ደግሞ የበለጠ ልናከብረውና በሥራም ልንፈጽመው የሚገባን አይደለምን? በመጽሐፍም ደግሞ «እግዚአብሔርም

ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፣ እግዚአብሔር ሊ ያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፏልና።» በማለት የተነገረው ቃል ይህን ትእዛዝ በዓለም መጀመሪያ እግዚአ ብሔር አምላክ የሰድስቱ ቀናት ተግባሩን ከፈጸመ በኋላ በ ማረፍ ለዕረፍት የሠራልን መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ዘፍ.2÷3።

ከዚህም የምናስተውለው ነጥብ እግዚአብሔር ሕግን ወይም ትእዛዝን ከመስጠቱ በፊት ሰንበትን የባረከውና የቀ ደሰው መሆኑን ነው። በሥነፍጥረቱ እግዚአብሔር ብዙ ድንቆችን አድርጓል፣ እርሱ ብርሃናትን፣ ሰማያትን፣ ቀላያ ትን፣ ምድርን፣ ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ የሰውን ልጅ ሁሉ ፈጥሯል። እነዚህን ሁሉ ፍጥረታት ከፈጠረባቸው ዕለታት መካከል እግዚአብሔር ባርኮታል፣ ቀድሶታልም የተባለለት ከሰንበት በቀር ሌላ ቀን የለም። ስለሁሉም ዕለታት የተነገረ ቢኖር «ያ መልካም እንደሆነ አየ» የተባለው ብቻ ነው። ዘፍ.1÷12፣18፣20፣25፣31። ስለሰንበት ግን «እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም» በማለት ተነግሮአል።

ከሳምንቱ ሰባት ቀናት መካከል ለዕረፍት የተቀደሰው የተባረከውም ዕለት ሰንበት ብቻ ነው። ሌሎቹ ቀናት የተ ባረኩት ለሥራ ነው፤ እርሱ ሠርቶባቸው እኛም ልንሠራባቸው ሰጥቶናል። ይህም ሰው በየፊናው የግል ሥራውን የሚያከ ናውንባቸው ሌሎች ዕለታት ከእግዚአብሔር ጋር ከሚኑ ጋገርበት፣ በስብሐተ እግዚአብሔር ከሚጠመድበት፣ መንፈ ሳዊና ሰማያዊውን ነገር ብቻ በማሰብ ከሚውልበት ዕለተ ሰን በት ጋር የሚስተካከል ቅድስናና በረከት እንዲሁም ክብር የሌላቸው መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

በዚህ መሠረትም ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብትም ሁሉ ከተፈጠሩበት ዕለት ይልቅ አንድ ሰንበት፣ የዕረፍት ቀን የበለጠ መሆኑን እናስተውላለን። ማርታ ደስ እያላት ያለ አንዳች እረፍት የሠራችው ሥራ ማርያም ከጌታ እግር ሥር ተቀምጣ በጸጥታ ቃለ እግዚአብሔርን ከመስማቷ የበለጠ ክብር አልነበረውም። በመሆኑም ዕለተ ሰንበት ሀርፊው ቃለ እግዚአብሔርን የሚሰሙበት በተዘዘ[illegible] እግዚአብሔር

የሚያሳልፉት መንፈሳውያን ተግባራትን የሚሠሩበት በመሆኑ ከሌሎቹ ዕለታት የከበረ ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ያረፈው መቼ ነው?

መጽሐፍ «እግዚአብሔር እርሱ ሀርፎበታልና ሰባተኛውን ቀን ባረከው» ይላል። ነገር ግን «ሀርፎአልና» የሚለው ቃል ትርጉምና ፍች ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር በባሕርዩ ድካም የሚስማማውና ዕረፍትም የሚያስፈልገው አይደለም፣ ታዲያ «ሀርፎአልና» የተባለው ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? ስለ ዕረፍት የሚነገረው አድካሚ ሥራ ባለበት ነው። እግዚአብሔር ሀርፏልኖ ሲባል የትኛውን አድካሚ ሥራ ሠርቶ ነው? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ዓለ ምን በፈጠረ ጊዜ? ወይስ ዓለምን ባዳነ ጊዜ? ያረፈውስ?

እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍጠር ትእዛዝ ከመስጠ ትና ከመናገር በቀር ያደረገው አንዳች ነገር እንደሌለ መጻሕፍት ይመሠክራሉ። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት «እርሱ ተናገረና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። መዝ.32÷9። በዚህ መ ሠረት እርሱ «ብርሃን ይሁን» ባለ ጊዜ ይሆን ነበር፤ «ከሰ ማይ በታችም ያሉ ውኃች ይሰብሰቡ» ባለ ጊዜም እንዲሁ ይሰበሰቡ ነበር፤ ምድርም ዘርን ታብቅል ባለጊዜ ታበቅል ነበር። እነዚህ ሁሉ ከቃሉ የተነሣ ከመሆን በቀር በእግዚ አብሔር ላይ ያስከተሉት ድካም አልነበረም።

ከዚህ አንፃር የማዳን ሥራውን ስንመረምር በእርግጥ አድካሚ እንደነበር እናስተውላለን። ይህም እግዚአብሔር በተለየ አካሉ ሰው ከመሆኑ /ከምጢረ ሥጋዌ/ የሚጀመር ነው። እርሱ ሰውን ለማዳን ሰው መሆን ነበረበት፣ መለኮታዊ ልዕልናውን ትቶ ከብሩን በፈቃዱ ዝቅ አድርጎ በትሕትና እርአያ ገብርን መንሣት ነበረበት፣ ከኃጢአት በቀር ሰው የሠራውን ሁሉ መሥራት ነበረበት፣ መሰደብ፣ መንገላታት፣ መሰቀልና መከራን ሁሉ ለመቀበል፣ መሞትና

ከሙታን መነሣት ሁሉ በእርሱ መፈጸም ነበረባቸው። እነዚህን ሁሉ ለመፈጸም የሥጋ ገንዘብ የሆነውን ድካም ገንዘብ አድርጎ አድካሚውን የመከራ ጉዞ መጓዝ ነበረበት። አደረገውም። በዚህም አማናዊ የማዳን ሥራ ወገኖቹ የሆኑትን የሰው ልጆች አዳነ። ከዚህም በኋላ የእግዚአ ብሔር ዕረፍት ዕውን ሆናለና ዳግመኛ ድካም የለበትም። በዚህ መሠረትም ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ በሰንበት ማረፉ በኋለኛው ዘመን ለዓለም ድኅነት የሚያስፈልገውን ሁሉ ከፈጸመና ሰውን ካዳነ በኋላ ላለው አማናዊ ዕረፍት ምሳሌ የነበረ መሆኑን እናስተውላለን።

በዚያ የመጨረሻው የመከራ ቀን፣ በዕለተ ዓርብ የኃጢአትን ኃይል፣ ሞትንም በሞት ድል ነሥቶ የኃጢአት ደመወዝ የሆነውን ሞትን ፈጽሞ አስወገደው። ሮሜ.6÷23። ይህንንም በዕለተ ሰንበት /እሑድ/ በትንሣኤው ፈጸመው። በእራሱ መከራ የሰውን መከራ ሁሉ በትንሣኤው አተመው፣ ፍጹም የሆነውም የእግዚአብሔር ዕረፍት የሰው ልጆችን መዳን ማረጋገጥ ነውና። ምክንያቱም ክርስቶስ የፈጸመው የትሕትና ሥራ ሁሉ ፋይዳ የሚኖረው ሰው ዳግመኛ ወደሞትና ወደመከራ የማይሄድ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ነውና። ከትንሣኤው በኋላ እግዚአብሔር አማናዊውን ዕረፍት ዐረፈ።

ከላይ እንደተመለከትነው ሁሉ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የደከመውን ያህል ዓለምን ለመፍጠር አልደከመም። ምክንያቱም የብሉይ ኪዳኑ ሰንበት በኋለኛው ዘመን ለሚመጣው የሐዲስ ኪዳን ሰንበት ምሳሌ ነውና። ከዚህም በላይ ሰንበት ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ ዕረፍት ማለት ሲሆን እግዚአብሔር አምላክም በእርግጥ ያረፈው የኃጢአት ውጤት የሆነውን መርገም በደመሰሰበትና ሞትን ድል ነሥቶ በተነሣበት በሰንበተ ክርስቲያን ነው። ከዚህ በመነሣት ነው እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን ወይም የጌታ ቀን የተባለው። ቅዱስ ዳዊትም «ዛቲ ይእቲ ዕለት ኀረት ዕለተ መድኃኒት እንተ ባቲ ንትፈሣህ ወን ትሐሠይ፤ ይህች እንደሰተባት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘጋጃት ቀን ናት» በማለት መናገሩ ለዚሁ ነው። ይህችም ቀን ሰንበተ ክርስቲያን /ዕለተ እሑድ/ ናት። መዝ.118።

ሰንበትን የማክበር ትእዛዝ የተሰጠው መቼ ነው?

ሰንበትን ማክበር ከአሠርቱ ትእዛዛት በፊት በተግባር የነበረ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ጽላት ላይ በጻፈው ጊዜ «ትቀድሰው ዘንድ አስበው» በማለት እሥራኤል ቀድሞውኑ የሚያውቁትን ይህን ትእዛዝ እንዲያስታውሱት አድርጓል። አሠርቱን ትእዛዛት የምናገኘው በአሪት ዘጸአት ምዕራፍ 20 ሲሆን እግዚአብሔር ሥራውን ፈጽሞ /የመፍጠር ሥራውን/ በተግባር ከገለጠው በተጨማሪ በትእዛዝ መልክ ሰንበትን ማክበር እንደሚገባ የተነገረው በዘጸአት ምዕራፍ 16 ላይ ነው።

እግዚአብሔር ለእሥራኤል ጎብስተ መናን ከሰማይ ባዘነበላቸው ጊዜ በየዕለቱ የሚበቃቸውን ያህል ይሰበስቡ ነበር። በየስድስተኛው ቀን ግን በሌሉቹ ዕለታት ከሚለቅሙት በእጥፍ ይለቅሙ እንደነበር ተጽፏል። ነቢዩ ሙሴም «እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ይህ ነው፦ ነገ ዕረፍት፥ ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው፤ የምትጋግሩትን ጋግሩ፣ የምትቀቅሉትንም ቀቅሉ፣ የተረፈውን ሁሉ ለነገ እንዲጠበቅ አኑሩት አላቸው።» ዘጸ.16÷23። እንደታዘዙትም አኖሩት፣ አልሸተተም፣ ትልም አልሆነበትም፣ ሙሴም «የእግዚአብሔር ሰንበት ዛሬ ነውና ብሉት፤ ዛሬ በሜዳ አታገኙትም። ስድስት ቀን ልቀሙት፤ ሰባተኛው ቀን ግን ሰንበት ነው በእርሱ አይገኝም፤ ...እግዚአብሔር ሰንበትን እንደሰጣችሁ እዩ፣ ስለዚህ በስድስተኛው ቀን የሁለት ቀን እንጀራ ሰጣችሁ፤ ሰው ሁሉ በሥፍራው ይቀመጥ÷ በሰባተኛው ቀን ማንም ከሥፍራው አይሂድ... ሕዝቡም በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።» ዘጸ.16÷32-30። በዚሁ መሠረትም እነርሱ ሰንበትን ቀደሱት፤ በሰንበትም ምንም ነገር አልሠሩም፤ ምግባቸውን ፍለጋ እንኳ ከቤት አልወጡም፤ ምግብም አላበሰሉም፤ ዐረፉበቴ እንጂ። እግዚአብሔር ደግሞ የዓርብን እንጀራ በእጥፍ አብዝቶ ሰጣቸው፣ ባረካቸውም።

ዓርብ ዕለት ማለትም በሳምንቱ ስድስተኛ ቂን ከሰ ማይ በወረደላቸው መና የተሰጣቸው በረከት በኋለኛው ዘመን በሐዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ለዓለም ሁሉ የሚሰጠው በረከት ምሳሌ ነው። እርሱም በሥጋ በተገለጠ ጊዜ «ከሰማይ የሚወርድ ለዓለም ሕይወትን የሚ ሰጥ ነውና ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ /ኅብስት/ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ ኅብስት ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል፤ እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» በማለት ያንን ምሳሌያዊ በረከት አማናዊ አድርጎታል። በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ የዘለዓለም ሕይወት የምናገኝበትን አማናዊ ኅብስት ሥጋውንና አማናዊ መጠጥ ደሙን ሰጥቶናል። ዮሐ.6÷32–51።

ከዚህ በላይ እንዳየነው እግዚአብሔር አምላክ የሰን በትን አከባበር ከመና አሰባሰብ ጋር ነ ይዞ አዘዘ፤ ቀጥሎም የዐሠርቱ ትእዛዛት ክፍል አድርጎ ሰጠሠ። በዘጸአትና በዘዳ ግም የሕግ አንዱ ክፍል ሆኖ ተመዘገበ፣ በዘጸአትና በነቢ ያትም ብዙ ጊዜ ተወስቷል /ተነግሯል።/ እነዚህም የሚያ ስረዱን ከአሠርቱ ትእዛዛት አንዱ ክፍል ሆኖ ከመሰጠቱ አስቀድሞ ሰንበትን ማክበር በእሥራኤል ዘንድ የሚታወቅና በሥራም ላይ የነበረ መሆኑን ነው።

ሰንበትን አለማክበር ያስቀጣል

አንዳንድ ሰዎች ሰንበት ማክበርን ከሌሎች ትእዛዛት ይልቅ ቀላል አድርገው ይገምታሉ። ለምሳሌም አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ ወዘተ ከሚሉት ትእዛዛት ያነሰ ክብደትም ይሰጡታል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከተጠ ቀሱትና ከሌሎችም ትእዛዛት ሁሉ በፊት ያስቀደመው ሰን በትን ስለማክበር የሰጠውን ትእዛዝ ነው። ይህ ትእዛዝ ደግሞ ጥብቅ ነው። ይኸውም ሰንበትን ያላከበረ ሰው እንዲ ገደል በተሰጠው ትእዛዝ ይታወቃል። እግዚአብሔርም ለሙሴ «ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ፤ የሚ ያረክሰውም ሁሉ ፈጽሞ ይገደል÷ ሥራንም በእርሱ የሠራ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ።...ሰባተኛው ቀን

ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው፤ በሰንበት ቀን የሚሠራው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል።» ሲል የተናገረው ቃል የዚህን ትእዛዝ ጥብቅነት የሚያረጋግጥ ነው። ዘጸ.31÷14–15። በዚህ መጽሐፍ በሠላሳ አም ስተኛው ምዕራፍም «ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የዕረፍት ሰንበት የተቀደሰ ቀን ይሆንላችኋል፤ የሚሠራበትም ሁሉ ይገደል። በማደሪያዎቻችሁ ውስጥ በሰንበት ቀን እሳትን አታንድዱ።» በማለት የተነገረው የዚህን ትእዛዝ ክብደት የሚያመለክት ነው። ዘጸ.35÷2። ስለ ሆነም አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት ሰንበትን መሻር ቀላል ኃጢአት አይደለም፤ ምክንያቱም ሰንበትን የሻረ ይገደል፤ ከሕዝቡም ተለይቶ ይጥፋ ተብሎአልና ቅጣቱም ቀላል አይደለም። ለዚህ ማረጋገጫ እንዲሆን አንድ ምሳሌ እንጥቀስ «የእሥራኤልም ልጆች በምድረ በዳ ሳሉ አንድ ሰው በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም አገኙ። እንጨት ሲለቅም ያገኙት ሰዎች ወደሙሴና ወደ አሮን አመጡት፤ ...እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ሰውየው ፈጽሞ ይገደል፤ ከሰፈሩ ውጭ ማኅበሩ ሁሉ በድንጋይ ይውገሩት አለው። ማኅበሩም ሁሉ ከሰፈሩ ወደውጭ አወጡት÷እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ወገሩት።» ዘኁ.15÷32–36።

እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ከተማ ሰንበትን ብትሽር ተመሳሳይ ቅጣት የምትቀጣ መሆኑን በመጥ ቀስ ሲያስጠነቅቅ «ነገር ግን የሰንበትን ቀን እንድ ትቀድሱ፤ በሰንበትም ቀን ሸክምን ተሸክማችሁ በኢየሩሳሌም በሮች እንዳትገቡ የነገርኳችሁን ባትሰሙኝ÷ በበሮቿ ላይ እሳትን አነድዳለሁ÷ የኢየሩሳሌምንም አዳራሾች ትበላለች÷ አት ጠፋም።» ብሏል። ኤር.17÷27።

የይሁዳ ሰዎች ከባቢሎን ምርኮ ከተመለሱ በኋላ ነህምያም ሰንበትንም ስለማክበር አስተምሯል፤ በሰንበት ሥ ራ የሚሠሩ ሰዎችን ሲያይ «ከይሁዳም ታላላቆች ጋር ተከራ ከርሁና፦ ይህ የምታደርጉት ክፉ ነገር ምንድር ነው? የሰንበትን ቀን ታረክሳላችሁን? አባቶቻችሁ እንደዚህ አድርገው አልነበረምን? አምላካችንስ ይህን ክፉ ነገር ሁሉ

በእኛና በዚህ ከተማ ላይ አምጥቶ አልነበረምን? እናንተም ሰንበትን በማርከሳችሁ በእሥራኤል ላይ መዓትን ትጨምራ ላችሁ አልኋቸው»፡ ብሏል። ነህ.13÷17–18። እንዲሁ ደግሞ ሲሠሩ ቢያያቸው እጁን በእነርሱ ላይ እንደሚጭን /እንደሚቀጣቸው/ አስጠነቀቃቸው።"

ነቢዩ ሕዝቅኤልም ሰንበትን ስለሚሽሩ ሰዎች ብዙ ጊዜ ተናግሯል። «ልጆች ግን ዐመፁብኝ...በሥርዓቴም አልሄዱም÷ ሰንበታቴን አረከሱ፤ በዚህም ጊዜ፡– መዓቴን አፈስስባቸዋለሁ ቁጣዬንም በምድረ በዳ እፈጽምባቸዋለሁ» ሲል ተናግሯልና እያለ መልእክቱን አስተላልፏል ።

ሕዝ.20÷21።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ታሪኮች ሁሉ የጌታ ቀን የተባለችውን የተቀደሰች የእግዚአብሔር ሰንበት ማክበር እን ደሚገባ የተሰጠው ትእዛዝ ጥብቅ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው። ስለዚህ ሁላችንም የእግዚአብሔርን የተቀደሰ የሰ ንበት ቀን በማክበር ከቅጣት ራሳችንን ማዳን ይኖርብናል። ብዙዎች ግን ሰንበትን ማክበርን እንደሞኝነትና ሥራ ፈት ነት በመቁጠር ሰንበትን የሚያከብሩ ክርስቲያኖችን ሲተቹና ሲሳለቁባቸው ይታያሉ። በዚህ ዘመን ሰንበትን ባለማክበሩ የሚ ገደል በድንጋይም የሚወገር ከሰፈር ውጭም የሚጣል ላይ ናር ይችላል። ነገር ግን ሰንበትን በመሻሩ ከእግዚአብሔር ረድኤትና ጥበቃ፣ ከእምላካዊ ቸርነቱም የተጣለና በእግዚ አብሔርም ፊት የተጠላ ስለመሆኑና ሰንበትን በማክበር የሚ ገኘውን በረከት ስለማጣቱም ያስተዋለና፣ ራሱን የሚመ ረምር ብዙ የለም። እኛም ባለማስተዋልና ለዚህ ትእዛዝ ትኩረት ባለመስጠታችን እንዳንቀጣ ከእኛ የሚጠበቀውን እናድርግ።

የሰው ባሕርይ ደካማ ነውና እግዚአብሔር ሰንበትን ሠራለት

ነቢዩ ሙሴ «እግዚአብሔር ሰንበትን እንደሰጣችሁ እዩ» በማለት መናገሩ የዚህን ስጦታ ዓላማና ምክንያት አስተውሉት ለማለት ነው። ሰንበትም የእግዚአብሔር ስጦታ አንጂ በሰው ልጆች ላይ የተጫነ ሸክም ወይም ዕዳ

አይደለም። የፈጠረን እግዚአብሔር ደካማ ባሕሪያችንን ስለሚያውቅ ከሳምንቱ ዕለታት አንዱን ሰንበት አድርጎ ለዕ ረፍት ሰጠን። ከደካማችን የተነሣም በየዕለቱ መሥራት አንችልምና ሰንበትን ማክበር ለሥጋም ጠቃሚ ነው። የሰው ልጅ አቅሙ ውሱን ነው፤ ከአቅሙ በላይ ቢሠራ ይጎዳል፤ ስድስቱን ቀናት ለመሥራት የሚያስችል አቅም አሰው በሳ ባተኛው ቀን ግን ማረፍ አለበት፤ አሊያ የሚቀጥሉትን ቀናት በሙሉ አቅሙ በመሥራት የሚፈለገውን ውጤት ሰግ ኖጣት አይችልም። ስለዚህ ሰንበትን ማክበር ለሰው ልጆች ጠቃሚ ነው።

እዚህ ላይ ሰንበት የተሰጠበት ምክንያት ለሥጋ ዕረ ፍት ብቻ አለመሆኑን ማስተዋል ይገባል። እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠበት ሌላው ምክንያት ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ለሥጋዊ ፍላጎቱ ብቻ ሲታትትና ሲደክም ሥጋውንም ብቻ ሲያስብና ለሥጋዊ እርካታ ሲሠራ እንጂውል ብቻ ሳይሆን ሥጋውን አሳርፎ የነፍስ ሥራ እንዲሠራበት፣ በዚህ ዓለም ባረፈው ዕረፍት የማያልፈውን ሰማያዊ ዕረፍተ ነፍስ እንጂ ያስብ፣ እንዲመኘው፣ እንዲለምንና በሕይወት ዘመኑም ስለሰጠው መንፈሳዊ በረከት እግዚአብሔርን እንዲያመሰ ግንበት ጭምር ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ሰንበት ስለሰው ተፈጥሯል እንጂ ሰው ስለሰንበት አል ተፈጠረም» በማለት ያስተማረው ሰንበት ለሰው መጠቀሚያ /ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ/ የተሰጠ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ማር.2÷27።

እንግዲህ እግዚአብሔር ሰንበትን የሰጠን ሥጋችን ዕረ ፍት በማጣት እንዳይደክምና በምንሠራው ሥራም ውጤታ ማ መሆን እንችል ዘንድ ነውና ልናመሰግነው ይገባል። እርሱ «በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ። አንተም ልጅህ፥ ሉሊህም፣ በሬህም፣ አህያህም፣ ከብትህም፣ አንተም በግብፅ ባሪያ እንደነበርክ አስብ» በማለት ሰንበት የዕረፍት ቀንም መሆኑን አስገንዝቧል። ዘዳ.5÷14–15።

የእግዚአብሔር ቃግ ለሁሉም እኩል ነው። ጌታው ዐርፎ ሉሊው ቢሠራ አግባብ አይደለም። አዕሩግ ሲያርፉ ወራሹት

ወጣቶች መሥራታቸውም ትክክል አይደለም። መጽሐፍ እንደተናገረው ሁሉ ያርፉ ዘንድ ይገባቸዋል። እንስሳትም ድካም የሚስማማው አካል አላቸውና ማረፍ ይገባቸዋል። በመጽሐፍ «ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ፣ በሬህና አህያህ ያርፉ ዘንድ ለባርያህም ልጅ ለመጻተኛው ዕረፍት ይሆን ዘንድ በሰባተኛው ቀን ዕረፍ።» ተብሏል። ዘጸ.23÷12። በዚህ መሠረት ሰንበት በእግዚአብሔር ቸርነት ለምንፈጽመው ተግባረ ነፍስ ከሥጋ ድካማችን እናርፍበት ዘንድ የተሰጠ ጸጋ መሆኑን ዐውቀን በሚገባ ልናከብረው ያስፈልጋል።

በሰንበት ግዑዟ መሬት እንኳ ሳትቀር ታርፋለች። እግዚአብሔር በሰንበት አማካኝነት ዕረፍት የሰጠው ለግዑዟ መሬትም ነው። «ስድስት ዓመት ምድርህን ዝራ፥ ፍሬዋንም አግባ፣ በሰባተኛው ዓመት ግን ተዋት፤ አሳርፋትም» በማለት ተናግሯልና። ዘጸ.23÷10። በሌላ ሥፍራ ደግሞ «እኔ በስድስተኛው ዓመት በረከቴን በላያችሁ አዝዛለሁ፣ ምድሪቱም የሦስት ዓመት ፍሬ ታፈራለች።» ሲል የተናገረው ቃል ምድሪቱን በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ማሣረፍ የበለጠ ምርታማ የሚያደርጋትና በረከትም የሚያስገኝ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ዘሌ.25÷21–22። በዚህም ብዙ እናገኛለን መስሏቸው ያለዕረፍት ምድሪቱን ከዓመት ዓመት የሚያርሱ ሰዎች ይህን ትእዛዝ በመተላለፍ የእግዚአብሔርን በረከት ከማጣታቸውም ሌላ ምድሪቱንም ፍሬ የማትሰጥ ያደርጓታል። በመሆኑም ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር ቢመልሱና ትእዛዙን ቢከተሉ እነርሱ ከሚጨነቁት የበለጠ ሊሰጣቸው ይችላል።

ሰንበትን ብናከብር በአካልም በመንፈስም እንጠቀማለን፣ በሥጋም በነፍስም እናርፋለን፣ ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንባረካለን። እርሱ «እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን፣ ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ፥ ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ፥ በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ፣... የሚቃጠለውን መሥዋዕታቸውንና ሌላ መሥዋዕታቸውን በመሠዊያዬ ላይ እቀበላለሁ በማለት ቃል ገብቷልና። ኢሳ.56÷2–7። እንዲሁም ደግሞ «ፈቃድህን

በተቀደሰው ቀኔ ከማድረግ እግርህን ከሰንበት ብትመልስ፥ ሰንበትንም ደስታ፥ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል፥ በምድርም ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ» ሲል የተናገረው ቃል ሰንበትን በማክበር የሚገኘውን በረከት የሚያስረዳ ነው። ኢሳ. 58÷13–14።

<u>ሰንበት የተሰጠው ለምልክት ነው</u>፦–አምላካችን እግዚአብሔር እንደተናገረው ሁሉ ሰንበት የዘለዓለማዊና የመንፈሳዊ ዕረፍት ምልክት ሆኖ የተሰጠ ጸጋ ነው። «እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ ዘንድ ለልጅ ልጃችሁ ምልክት ነውና ሰንበቶቼን ፈጽሞ ጠብቁ።» ዘጸ.31÷13። ሰንበት ዘለዓለማዊ ለሆነው ዕረፍት ምሳሌ መሆኑ የተለገጠው ሰንበትን ማክበር ከአሠርቱ ትእዛዛት መካከል ተደምሮ ሕግ በመሆን ከተሰጠ በኋላ ነው።

ሰንበት የሚመጣው አማናዊ ዕረፍት ምሳሌ ሆኖ የተሰጠ የብሉይ ኪዳን ሕግ ነው። በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት በሰንበት ዕረፍተ ሥጋ ይደረጋል። ይህም በኋላ ዘመን በክርስቶስ ቤዛነት ለተገኘው ድኅነት ለዕረፍተ ነፍስ ምሳሌ ነበር። በሐዲስ ኪዳን የተገለጠው የክርስቶስ ትንሣኤ፦ በሰንበተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፤ ሰንበተ ክርስቲያንም የሰው ልጆች ለዘለዓለም ወርፈው ከእግዚአብሔር ጋር በደስታ የሚኖሩበት ምሥጢረ ትንሣኤ የተገለጠበት የድኅነት ቀን ነው።

ሰንበታውያን /መፍቀርያነ ሰንበት አይሁድ/ ሰንበት ምልክት በመሆኑ መለወጥ ወይም መቀየር የለበትም በማለት ይከራከራሉ። ይሁን እንጂ በጥምቀት የተለወጠው ግዝረትም ምልክት ነበር፤ ተቀይሯልም። ስለግዝረት «በእኔና በአንተ መካከል+ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፤ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ+ የቃልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።» የተባለው በሐዲስ ኪዳን ዘመን ከሥላሴ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን በሚገኝበት በጥምቀት ተለውጧል። ዘፍ.17÷10–11። ቆላ.2÷11–15።

እነዚህ ሁለት ምልክቶች ግዝረትና ሰንበት የተለያዩ ቢሆኑም በዘመነ ክርስትና ግለትም በሐዲስ ኪዳን ዘመን ምሳሌ የሆኑላቸው ኀማናውያን ምሥጢራት በተገለጡ ጊዜ ፍጻሜአቸውን አግኝተዋል፤ ይኸም ግዝረት በጥምቀት፣ ሰንበተ አይሁድም በሰንበተ ክርስቲያን ነው። ግዝረት ቁል ፈተ አካልን ቆርጦ መጣልና የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመባል በዚህም የእግዚአብሔርን በረከት እንዲሁም ጥበቃ ለማግኘት ዋነኛ ምልክት ነበር። በዘመነ ሐዲስ ግን ሥጋዊ ፈቃድን ከነምኞቱ በመተው በክርስቶስ አምኖ የእግዚአብሔር ልጅ ነት በሚያገኝበት ምሥጢረ ጥምቀት ተተክቷል። ሰንበትም በክርስቶስ ቤዛነት አዳም ላገኘው ዕረፍተ ነፍስ ምሳሌ ሆኖ የተሰጠ በሥጋ ዕረፍት የተገለጠ ምልክት ነው።

በሐዲስ ኪዳን ግን በመንፈሳዊ ዕረፍት በተገለጠው፣ ከኃጢአት ቁራኝነት፣ ከሞት ባርነት፣ ከዲያብሎስ ግዞት ባረፍንበት በሰንበተ ክርስቲያን ተተክቷል። በዚሁ ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘለዓለማዊ ዕረፍት የምናገኝበትን ትንሣኤ ባልሟል፤ ሰው ሆኖ ወደዓለም የመጣበትንም የማ ዳን ሥራ ፈጽሞ ድኅነታችንን አረጋግጧል።

በዚህ አንፃር አንድ ዐቢይ ነጥብ ልናስተውል ይገባል። ክርስቶስ ሰንበትን የሻረው አይደለም፣ የበለጠ የከበረ ሥራን ሠርቶበት ሰንበትንም አከበረው እንጂ በዚህም የሰንበትን ትርጉም የበለጠ አጠነከረው። እርሱም አስቀድሞ «እኔ እንደምቀድሳችሁ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ መካከል ምልክቴ ነው» እንዳለው በሰንበተ ክርስቲያን መድኃኔዓለም በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በነፍሱ ቤዛነት የኃጢ አትን ኃይልና የሞትን ሥልጣን ድል ነሥቶ ከፍርድ ተገዥነት ነፃ እንዳወጣን እናስባለን፤ የቸርነቱንም ሥራ እናስታውስበታለን። የጌታ ቀን የተባለውን ዕለተ ሰንበት በአከበርነው በቀደስነው ጊዜ ጌታችን በሞቱና በትንሣኤው ያከበረንና የቀደሰን መሆኑን እናስታውሳለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ኃጢአትን ድል ነሥቶ እንደቀደሰን እናውቃለን። በትንሣኤው የቀደሰን እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችል ይሆናል። በብሉይ

ኪዳን ሞት ቅጣት ነበር፤ በኃጢአቱ የተነሣ በሞት የተቀጣ ከነኃጢአቱ ሞቷልና የሞተውን የሚነካ ቢኖር የረከሰ ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን እንዲህ አይደለም። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶልን፦ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ ነፍሱን ከሶ የኃጢአታችንን ዕዳ ሁሉ በመደምሰስ የሞታችንን ርኩሰት በሞቱ ቀድሶታል። በመሆኑም በክርስቶስ ለምናምነው ለእኛ ሞት የሥጋ ከነፍስ መለየት ብቻ ነው፣ የሞተውንም ሰው መንካት አያረክስም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ የሞትን ኃይልና መውጊያውንም አሸንፎልናልና በሞት ወደሌላ ሕይወት መሸጋገር እንጂ ርኩሰት የለም።

ሰንበት ከባርነት ወደ ነፃነት የመውጣት ምልክት ነው። ይህም በመጽሐፍ «አንተም በግብፅ ባሪያ እንደነበርህ አስብ፤ እግዚአብሔር አምላክህ... ከዚያ አወጣህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ የሰንበትን ቀን ትጠብቅ ዘንድ አዘዘህ።» በግለት ተመዝግቧል። ዘዳ.5÷15። ይህም ምሳሌ ስለነበረች ሰንበተ አይሁድ የተነገረ ነው። ታሪኩም በራሱ ምሳሌ ነው። ግብፅ የሲኦል፣ የፈርዖን ግዞትም የአጋንንት ግዞት፣ ከግብፅ ባርነት ነፃ መውጣትም ከሲኦል ባርነት ከአጋንንት ግዞት ነፃ የመውጣት ምሳሌ ነበር። ይህ ነፃነት የተገኘውም በሰንበተ ክርስቲያን ክርስቶስ ሞትን ድል ነሥቶ መንግሥተ ፍቁልኝ መቃብር ከፈቁልኝ ሳይል በተገለጠው ምሥጢረ ትንሣኤው ነው።

ቅዳሜና ሉሉድ- ዕለተ ቅዳሜ ዛሬ ሰንበት ስለ ማሆንም ወይም በእሑድ ስለመቀየሯ /ስለመለወጧ/ የሚጠ ይቁ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ለዚህ ጥያቄ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ቃል እናስነብባለን፤ እርሱ «እንግዲህ በመብል ወይም በሞጮዋ ወይም ስለበዓል ወይም ስለወር መባቻ ወይም ሰንበትነት ማንም እይፍረድባችሁ፣ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና» ብሏል። ቆላ.2÷16–17 ይህ ቃል ጽዮንገረው በብሉይ ኪዳን ስለነበሩ ሥርዓቶች መሆኑ የታወቀ ነው፤ እነርሱንም የሚመጣው /የወንጌል ወይም የሐ ዲስ ኪዳን/ ጥላ ናቸው አላቸው። ስለመገረዝም እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ተነግሯል። የሐዋ.15÷10–29። እነዚህ ሁሉ

ምሳሌ የሆኑላቸው ነገሮች አማናዊ በሆኑ ጊዜ ተለወጡ። በመሆኑም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሁሉ ሰንበተ አይሁድ /ቅዳሜ/ የሰንበተ ክርስቲያን /እሑድ/ ምሳሌ ነበርና በእሑድ ሰንበት ተተክቷል።

እግዚአብሔር አምላክ ዓለምን በፈጠረ ጊዜ በሰባ ተኛው ቀን ማረፉ፣ የማጸን ሥራውን ፈጽሞ ሞትን ድል በ ማድረግ ለእኛ የሰጠው የሰንበተ ክርስቲያን ምሳሌ ነበር። ሰንበተ ክርስቲያን የተባለ እሑድም ለዘለዓለም የምና ርፍበትን የዕረፍት ቀን የሚያመለክት ነው። «በኋላም+ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ... ጊዜ የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው» እንደተባለው ሞት በቀሻረበት ትንሣኤ ስንነሣ ያንጊዜ እኛም የዘለዓለሙን ዕ ረፍት እናርፋለን። 1ቆሮ.15÷24–28። ስለሆነም የክርስ ቲያኖች ሰንበት ከቅዳሜ እሑድ ወደ መሆን ተቀየረ /ተለወጠ/። ሰንበተ ክርስቲያንም ተባለ። ይኸውም እሑድ ከዘረ ማለት እንጂ ቅዳሜ ፈጽሞ ተሻረ ማለት አይደለም።

በዚህ ዕለት /በሰንበተ ክርስቲያን/ የጌታ ደቀ መዛ ሙርት አንድ ልብ ሆነው ይመገቡ ነበር። የሐዋ.2÷46። በሐ ዋርያት መንፈስ ቅዱስ የወረደላቸው፣ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያንም የተመሠረተችው፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለሴቶችና ለደቀመዛሙርቱ የተገለጠውና የታየው በዚህ ዕለተ እሑድ ነው። ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን የእሑ ድ ሰንበት ከብር ከሰንበተ አይሁድ የተለየና የበለጠ ነው። መጽሐፋዊ መረጃው ይህ ይሁን እንጂ ቅድመ ክርስትና በብ ይ ኪዳን ትመራ የነበረችው ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ አይሁድ አይሁን እንጂ ቅዳሜን በሰንበትነት ታከብራለች፤ ዕለ ቲቱንም «ቀዳሚት ሰንበት» ብላ ትጠራታለች። ቀዳሚት ሰንበትን ስታከብር ግን እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን በነበረው መልክ ከዘረጉ ሳያጥፉ ካጠፉ ሳይዘረጉ፣ ከተቀመጡ ሳይነሡ አይደለም፤ በዚህች ዕለትም የወንጌልን ቃል በመፈጸም የታ መመ በመጠየቅ፣ የተቸገረ በመጎብኘት፣ በአጠቃላይ መንፈሳዊ ተግባራትን በማከናወን ነው። ዋናው ነገር ሰንበትን ስናከብር የእግዚአብሔርን ቸርነት እያሰብን፣ በተደረገልን በጎ ነገር ሁሉ እየተደሰትን፣ ከሰንበት ረድኤትና በረከትን እያገኘን መሆኑን እያስተዋልን ሊሆን ያስፈልጋል።

«በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ»

በጌታ ቀን ምንም ሥራ እንዳይሠራ በሕግ ታዝዟል። አይሁድ ሰንበትን ከምሽት እስከ ምሽት የሚያከብሩት በመ ሆኑ የበዓሉ አከባበር ከዓርብ ስለሚጀምር ዓርብን የመዘጋጃ ቀን ይሉታል። ዘሌ.23÷32። ሉቃ.23÷54። በዚህ ትእዛዝ ውስጥ «በእርሱ ምንም አትሥሩ» የሚለውን ሐረግ አይሁድ የሚፈጽሙት በደረቁ እንጂ መንፈሳዊ ትርጉሙን በመረ ዳት አልነበረም። ከዚህ የተነሣም በዕለተ ሰንበት መልካምና በጎ ነገር ማድረግም ሁሉ በእነርሱ ዘንድ ሰንበትን መሻርና ኃጢአትም ነበር። ስለዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ድውያንን በመፈወሱ አይሁድ አብዝተው ይቃወሙት ነበር።

«በዚያ ቀን ሥራ አትሥሩ» የሚለው ትእዛዝ በሰ ንበት ተኝታችሁ ዋሉ፣ ሥራ ፈታችሁ ተቀመጡ የሚል ትርጉም ያለው አልነበረም። በሌሎች ቀናት ከሚሠራው ሥ ራ ለየት ያለ መንፈሳዊና መልካም ሥራ እንዲሠራበት የተሰጠ ነው እንጂ። ሰንበትም በስንፍና ያለእንጻች ሥራ የሚያሳልፉት ሳይሆን መልካም ተግባር እየፈጸሙ በመንፈ ሳዊ ሥራ ተጠምደው የሚያከብሩት የጌታ ቀን ነው። አይ ሁድም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይከራከሩት የነበረው በሰንበት ለምን መልካምና መንፈሳዊ ሥራ ሠራህ? ለምን አስተማርክ? ለምን ድውያንን ፈወስክ? በማለት ነበር። ማቴ 12÷10። ሉቃ.14÷3። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጌታ ቀን የተባለች ሰንበትን በመንፈሳዊ ሥራ ተጠምዶ ማሳለፍ እንደሚገባ ለማስተማር በዙ ድውያንን ይፈውስና በምኩራብ በመገኘት ያስተምር ነበር።

ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር የነበረውን ሰው የፈወሰው በሰንበት ቀን ነበር፣ «ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይ ኖቹን የከፈተበት ሰንበት ቦረ።» ዮሐ.9÷14። ሰውየው የተወለደው ዓይነ ስውር ዘሮ ነው፣ ጌታችን በማንኛውም ቀን ሊፈውሰው ይችል ነበር። ጌታ ግን ስለሰንበት ሊያ ስተምርበት ወዷልና።በዕለተ ሰንበት ፈወሰው። ይህ ተአምር

አምላክነቱም ጭምር የተገለጠበተ ግሩምና ድንቅ ነበር፡ አይሁድ ግን ይህን ረቂቅ ምሥጢር አልተረዱትም ይልቁንም ሰንበትን ሽሯልና ኃጢአተኛ ነው ብለው ጮኩበት። ዮሐ.9÷16–24።

እጁ የሰለለችውን ሰው በፈወሰ ጊዜም በሰንበት መፈወስ የተፈቀደ ስለመሆኑ ሲነግራቸው «ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበትም በጉ በጉድጓድ ቢወድቅበት÷ ይዞ የማ ያወጣው ሰው ማነው? እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም? ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዷል አላቸው።» ማቴ.12÷10–13።

ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባትን ሴት ከፈወሰ በኋላ የምኩራብ አለቃውን «እናንተ ግብዞች÷ ከእናንተ እያንዳንዱ በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግሙ ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን? ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሠራት ባበንበት ቀን ከዚህ እሥራት ልትፈታ አይገባምን? አለው።» ሉቃ.13÷10–16።

በቤተ ላይዳ ለሠላሳ ስምንት ዓመታት ድውይ የነበረውንም ሰው የፈወሰው በሰንበት ነበር። ዮሐ.5÷2–11። ሆዱ የተነፋውንም ሰው የፈወሰው በሰንበት ነበር፡ ሉቃ. 14÷1–6። ከዚህም በላይ ደቀመዛሙርቱ እሸት ቀጥፈው በመብላታቸው የተነሣ ፈሪሳውያን በተቃወሙት ጊዜ «ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሯል እንጂ ሰው ስለሰንበት አልተፈጠረም» በማለት ሰው በሰንበት መልካም ሠርቶ መንፈሳዊ ጥቅም ሊያገኝ እንደሚገባ አስተምሯል። ማር.2÷23። «እኔ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም» በማለት በሰንበት ቀን ለድውያን የተደረገው ምሕረት ሰንበትን መሻር አለመሆኑን በሰንበትም ይህን መሰል መንፈሳዊ ተግባር መፈጸም የሚገባ መሆኑን አስረድቷል። ማቴ.12÷7።

በሰንበት መንፈሳዊ ሥራን መሥራት የተፈቀደ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲልም «ካህናት በሰንበት በመቅደስ

ሰንበትን እንዲያረክሱ ኃጢአትም እንዳይሆንባቸው በሕጉ አላነበባችሁምን?» ብሏቸው ነበር። ማቴ.12÷5–6። ይህም ሕግጋትን ስለመግረዝ የተናገረው ነው። ሕፃን የሚገረዘው በስምንተኛው ቀን ነው፣ ስምንተኛው ቀን ሰንበት የሆነ እንደሆነ አንገርዝም ሰንበት ይረክስብናል ብለው እይተውትም ይገርዙታል እንጂ፣ ኃጢአትም አይሆንባቸውም። በሌላ ሥፍራ ጌታችን «የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቆጡኛላችሁን?» በማለት ሞግቷቸው ስለዚህ ነው። ዮሐ.7÷21–23።

ስለሰንበት አከባበር የተሰጠውን ትእዛዝ በንባብ ብቻ ላይ ተመሥርተን ልንፈጽመው አይገባም፣ ስለዚህ ትእዛዝ ትርጓሜም ቢሆን ማጤን ያስፈልገናል። በመጽሐፍ «ፈደል /ንባብ/ ይገድላል» ተብሏልና። 1ቆሮ.3÷6። ከዚህ አንፃርም ሰንበትን ማክበር ማለት በሰንበት መልካሙን እያደረጉ የእግዚአብሔርን ቸርነት ማሰብና በመንፈሳዊ ሥራ ተጠምዶ መዋል መሆኑን ሊያስረዱ የሚችሉ ጥቂት ምሳሌ ምሾን እንመልከት።

አንድ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ የተነሣ ሰንበትን የሚያከብር ሐኪም ከሰንበቶቹ በአንደኛው ለመሞት የተቃረበና በጣር የተያዘ በሽተኛ ወደእርሱ መጥቶ ዕር ዳታውን ቢሻ ሰንበትን ለማክበር ብሉ በሽተኛውን አልረዳም ይላልን? ሰውየውን ከሚያሰቃየውና ወደሞት ሊወስደው ከሚታገለው በሽታ ከመታደግ ይልቅ ሰንበትን አከብራለሁ የሚል ሐኪም ምንም ርኅራኄና ምሕረት በልቡናው የለም። እግዚአብሔር ግን ምሕረትን ይሻል መሥዋዕትንም አይ ደለም። በሰንበት የርኅራኄና የምሕረት ሥራ መሥራት ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ በሰንበት መሥራት የተፈቀደ ነው በማለት የሥራ ዐታውን ክፍት አድርጎ ለግል ጥቅሙ የሚሠራው ሐኪም ደግሞ ሰንበትን ስለጥቅሙ ብሉ ሽሮአልና ትእዛዝን ተላልፏል። በዚያ ዕለት ሰንበት በተፈጠረው ሁኔታ የሕክምና ዕርዳታ ካልተደረገለት በሽተኛው የሚሞት ሲሆን ብዙ ነው በሰንበት ይህን አገልግሎት መሰጠት የተፈቀደው። ሰንበት ለሰው ተፈጠረ እንጂ ሰው ለሰንበት አልተፈጠረምና።

ክርስቲያኖች በሚኖሩበት ቀበሌ በዕለተ ሰንበት ድንገተኛ የሆነ የእሳት ቃጠሎ ቢነሣ ሰንበት ነውና እሳቱን አይጨሉም ብሎ መቀመጥ አግባብ አይደለም። ይህን አደጋ ለማስቀረት ሲባል የሚደረገው ሁሉ ሰንበትን መሻር ሳይሆን በሰንበት መልካም መሥራት ነው።

ከሁሉም በላይ ሰንበት ለመንፈሳዊ ሥራ እንዲውል እግዚአብሔር ማዘዙ በመጽሐፍ ተመዝግቧል፤ «ሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት ነው፣ የተቀደሰ ጉባኤ ይሆን ዘንድ ይታል።» ዘሌ.23÷3። ይህም በዕለተ ሰንበት መንፈሳውያን ሰብሰባዎች ይደረጉበታል ማለት ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር «በየሰንበቱ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ዘወትር ይመጣል» በማለት የተናገረው ሰንበት የአምልኮ መፈጸሚያ ቀን መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ኢሳ.66÷23። በሌላ ምንባብ ደግሞ የሚቃጠለው መሥዋዕትና የእህሉም ቁርባን በሰንበት ቀን እንዲቀርብ አዝዞአል። ሕዝ.46÷4። ቅዱሳት መጻሕፍትም የሚነበቡት በዕለተ ሰንበት ነው፤ «ሙሴስ ከቀደሙት ትውልድ ጀምሮ በሰንበት በሰንበት በምኩራቦቹ ሲያነቡ በየከተማው እርሱን የሚሰብኩ አሉት።» የሐዋ.15÷21። ከዚህ በላይ በመጠኑ የጠቀስናቸው ምንባባት ሰንበት የመንፈሳውያን ጉባኤዎች ማካሄጃና በቅድመ እግዚአብሔር የአምልኮ መፈጸሚያ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው።

ሰንበት የአምልኮ መፈጸሚያ ብቻም ሳይሆን የማስተማሪያ ዕለት ጭምርም ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ያስተምር እንደነበር ሁሉ ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያትም እንደ እርሱ እንደመምህራቸው በሰንበት ያስተምሩ እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ማር.6÷2። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በየሰንበቱም ሁሉ በምኩራብ ይነጋገር ነበር፡ አይሁድንና የግሪክን ሰዎች /ስለወንጌል/ ያስረዳ ነበር። የሐዋ.14÷4። በተሰሎንቄም እንዲሁ «የአይሁድ ምኩራብ ነበራ። ጳውሎስም እንደልማዱ ወደ እነርሱ ገባ÷ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበረ» የሐዋ.17÷1–2።»

እንግዲህ የሐዲስ ኪዳን የሰንበት አከባበር ይህን መምሰል የሚገባው መሆኑን ተመለከተናል። ለዚህም ነው በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በሰንበት ሁሉ ምእመናን ወደ ቤተክርስቲያን በመጉረፍ የአምልኮ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙት፣ መንፈሳውያን ጉባኤያትን የሚያደርጉት፣ ቀድሰውና አስቀድሰው በአንድነት ከቃለ እግዚአብሔር የሚማሩት። ከቤተክርስቲያን መልስም የታሠረ በመጎብኘት፣ የታመመ በመጠየቅ፣ የተራበ በማብላትና የተጠማ በማጠጣት፣ የተጣሉ በማስታረቅ ሰንበትን በምግባረ ሠናይ የሚያሳልፉትም የሰንበት አከባበር ንባቡ ብቻ ሳይሆን ትርጓሜውም ስለገባቸው ነው። ሰንበትን በዚህ መልክ ከሚያከብሩት ክርስቲያኖች ተዝረውን ትምህርት በመውሰድ በዚህ የጽድቅ ጎዳና መጓዝ ለሁላችን ጠቃሚ መሆኑን እንዘንጋ።

የጌታ ቀን የተባለ ሰንበት በሥንፍናና ሥራ በመፍታት የምናሳልፈው ቀን አይደለም፣ ይልቁንም በእግዚአብሔር መንበር ፊት በመስገድና በመጸለይ አምልኮአችንን የምንፈጽምበትና ሃይማኖታችንን የምንገልጥበት፣ ተግባረ ነፍስን የምንሠራበት፣ መንፈሳውያን ጉባኤያትንም የምናካሄድበትና የምንሳተፍበት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን የምናነብበት፣ መልካም የሆነውን ሥራ ሁሉ የምናከናውንበት የከበረ ቀን ነው። ለዚህ ነው ቀዳማት አበው «ለክርስቲያን እንደ አይሁድ ባለ ልማድ ሰንበት ማክበር አይገባም ይልቅ ለክርስቲያኖች እንደሚገባው በመንፈሳዊ ተግባራት በመጠመድና በመትጋት ነው እንጂ» በማለት በፍትሐ ነገሥት የደነገጉት። አባታችን ቅዱስ አትናቴዎስም በቅዳሴ ድርሰቱ «ዕለተ ሰንበት የዕረፍት ቀን ናት ሲባል በደዌ እንደተያዘ ሰው ከአልጋ ተጣብቆ ተኝቶ መዋል አይደለም፣ የዕለቲቱ ወዳጅ ለመሆን በመዓልትም በሌሊትም ለመንፈሳዊ ሥራ መትጋት ነው» በማለት የሰንበትን አከባበር አስተምሮአል። ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም «እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፡ ሐሴትን እናድርግ በእርሷም ደስ ይበለን» በማለት የተናገረላት ስትሆን መልካምና መንፈሳዊ የሆነውን

ሥራ በመሥራት የሚገኘውን ደስታ ለማጠየቅ /ለመግለጽ/ መሆኑን ማስተዋል ይገባል። ስለዚህም በዕለተ ሰንበት ከተግባራት ነፍስ ርቆ ተቀምጦ መዋል የሐዲቷ ኪዳንን የሰንበት አከባበር ትርጉም ካለማወቅ የተነሣ ስለሰንበት የተሰጠውን ትእዛዝ አለማክበር ነው።

ሰንበትን «መቀደስ» ማለት የተለየ ማድረግ፣ ማክበር ማለት ነው። በሌሎች ዕለታት ከሚሠሩት ተግባራት ሥጋ ሁሉ ተለይቶ በዚህ ቀን ተግባረ ነፍስን መፈጸም፣ መንፈሳዊና መልካም ሥራን ሲሠሩ መዋል ነው። ከሌሎቹ ቀናት ሁሉ ይህችን ዕለት ለእግዚአብሔር ክብር መለየት ማለት ነው።

ሰንበትን እግዚአብሔር የሚደሰትበትንና የሚወደውን ሥራ በመሥራት ማሳለፍ ነው እንጂ የሥጋን ፈቃድ ሲ ፈጽሙ መዋል ተገቢ አለመሆኑን ማጤን ያስፈልጋል። በመሆኑም በሰንበት በረከት የምናገኝበትን የምንጠቀምበትን መንፈሳዊ ሥራ መሥራት ይገባናል። ከዚሁ ጋር በየሰንበቱ ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ለእርሱ አገልግሎት፣ ከእርሱም ጸጋና ረድኤትን ለማግኘት የተቀደሰ አድርገን ከክፉ ሥራ ርቀን እንድናከብረው የሚሻ መሆኑን መዘንጋት አይገባም።

ሰንበት የወደድነውን ሁሉ ልንፈጽምበት አልተሰጠ ንም። የሰንበት ውሉአችንን ለሰንበት ጌታ ለእግዚአብሔር ሰጥተን በዚህ ቀንም እርሱ ያደረገልንን ቸርነት እያሰብን በ ማመስገን፣ መንፈሳዊ ዋጋ የሚገኝባቸውን ቅዱሳት ተግባራ ት መፈጸም ይኖርብናል። ይህም ከሰንበት ረድኤት በረከትን ለመሳተፍ ያበቃናል፡ ይህን ትእዛዝ በመተላለፍ ከመከለስም ያድነናል። ለዚህም እርሱ በቸርነቱ እግዚአ ጸጋን የሰንበት ወዳጆች የሕጉ ታዛዦች እንዲያደርገን ፈቃዱ ይሁንልን።

ክፍል አምስት

አራተኛው ትእዛዝ

«አባትህንና እናትህን አክብር፣ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲ ረዝም፤።»

ዘጸ.20÷12።

የትእዛዙ ውጫዊ ትርጉም

በመጀመሪያው ውጫዊና ጥንታዊ ትርጉሙ በሰዎች ዘንድ ታዋቂነትንና ተቀባይነትን ለሚገኙቱና አሁን ከደ ረሰበት ደረጃ በፊት ይህ አራተኛው ትእዛዝ ወላጅ እናትና አባትን ማክበር ቦሚል ብቻ የተወሰነ ትርጉም ነበረው። ይሁን እንጂ ዘመን ዘመንን እየወለደ ጊዜም በጊዜ እየተተካ በሄደ መጠን ይህ ጠባብ ትርጉም እየሰፋ ምሥጢራዊ ትንታኔውም እየበዛ የዕንሰ ሃሳቡ ወሰን እየጠለቀ መሄድ ጀመረ። ስለሆነም የዚህ ትእዛዝ ፍች ከውጫዊና ቀጥታ ትርጉም ከወላጅ አባትና እናት በተጨማሪ ወደጎን ቀጥታ ወደላይና ወደታች ያሉ የሥጋ ዘመዶችን፣ መንፈሳውያን አባቶችን፣ ካህናትን፣ መምህራንን፣ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያሉትን /ከአከባሪው በላይ የሆኑትን/ ሁሉ የሚያጠቃልል ሆነ። በዚህ ትእዛዝ ትንታኔም በጥልቀት የምንመረምረው ወላጅ እናትና አባትን በተመለከተ ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ልናውቅ የሚገባንን መሠረታዊ ጉዳይ ብቻ ነው።

በሰዎች መካከል ስላለው ግንኙነት የመጀመሪያ ትእዛዝ ነው

ይህ «አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለው አራተኛው ትእዛዝ አምላካችን እግዚአብሔር ለነቢዩ ሙሴ ከሰጣቸው ሁለት ጽላት መካከል በሁለተኛው ጽሌ ላይ ከተጻፉት የሰዎችን ግንኙነት ከሚመለከቱት ትእዛዝ መካከል የመጀመሪያው ነው። ይህም የሚያሳየው በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ሌሎች ትእዛዛት ይበልጥ ቀዳሚውን ሥፍራ የያዘና መሠረታዊ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር አምላካችንም አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አትመኝ፣ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ከማለቱ አስ ቀድሞ አባትህንና እናትህን አክብር የሚለው ትእዛዝ መስጠቱ አባትንና እናትን ማክበርና አራተኛውን ትእዛዝ በሚገባ መፈጸም ሌሎችን ትእዛዛት ከመተላለፍ የሚያድን ከመሆኑም ሌላ አባቱንና እናቱን የማያከብር ልጅ የተቀሩትን ትእዛዛት በመተላለፍ ከሚሠራው ኃጢአት የበለጠ የሚቀጣ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው። በመጀመሪያ የተቀመጠበት አንዱ ምክንያት ደግሞ ይህን ትእዛዝ ከሌሎቹ የበለጠ እንድናከብረውና አሳንሰን እንዳናየው ሙምር ነው። መግደልና ማመንዘር በእግዚአብሔር የተከለከሉ በመሆናቸው የምናከብራቸው ከሆነ ከእነዚህ በፊት እናትህንና አባትህን አክብር ብሎ ማዘዙን በእንከሮ ልናጤነው ይገባል።

ከአፀፋ ዋጋ /በረከት/ ጋር የተቆራኘ የመጀመሪያ ትእዛዝ ነው

«እናትህንና አባትህን አክብር» በማለት ካዘዘ በኋላ ይህን በሥፈጸም የሚገኘውን ጸጋ ደግሞ «እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም፣ መልካምም እንዲሆንልህ» ሲል ይገልጠዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር፤ እርስዋ የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት።» በማለት እግዚአብሔር የአፀፋ ዋጋ ለመስጠት ቃል ከመግባት ጋር የሠራልን ሕግ መሆኑን ገልጦታል። እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ዋጋም ይህን ትእዛዝ በማክበር የሚገኘውን መልካም ነገር እና ረጅም እድሜን ነው። ኤፌ.6+2–3። ዘዳ.5+16። እኛም እንግዲህ አባታቸውንና እናታቸውን አክብረው ዘመናቸው መልካም፣ ዕድሚአቸው ረዥም እንደሆነላቸው ቀደምት አበው ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ተካፋይ እንድንሆን እናቶቻችንንና አባቶቻችንን እናክብር።

እናትና አባትን አለማክበር ቅጣት አለው

በብሉይ ኪዳን የሕግ መጻሕፍት ተመዝግቦ እንደምናገኘው ይህን ትእዛዝ በመጣስ እናቱንና አባቱን የማያከብር ሰው በሞት ይቀጣ ነበር። «አባቱን ወይም እናቱን የሚመታ ፈጽሞ ይገደል።... አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል።» የሚል አለ። ዘጸ.21+15–17። በተጨማሪም ደግሞ እግዚአብሔር ይህን ጥብቅ ትእዛዝ ስለሚተላለፍ ሰው «ማናቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል፥ አባቱንና እናቱን ሰድቧልና ደሙ በራሱ ላይ ነው» በማለት ጌልሀ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል። ዘሌ.20+9።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጸሐፍት ፈሪሳውያንን ሲገሥፅ «ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። ሙሴ፡– አባትህንና እናትህን አክብር ደግሞ፡–አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሏልና። እናንተ ግን ሰው ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደፊት አትፈቅዱለትም፣ ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ» ብሏቸዋል። ማር.7+9–13። በዚህም አባትንና እናትን ማክበር የሚገባ መሆኑን አስተምሯል።

ማንንም ቢሆን መሳደብ ኃጢአት ነው፤ ለሽነመ እላት ፍርድም ያበቃል፤ እናትና አባትን መስደብማ እን ደምን የበለጠ ኃጢአት አይሆን? ከባድ ኃጢአት ነውና ውጤቱ ሞት ነው። እናቱንና አባቱን የሰደበ ሰው እርግማን ይከተለዋል፤ በመጽሐፍ « አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ በድቅድቅ ጨለማ መብራቱ ይጠፋል» ሲል የተናገረው እናት አባቱን የማያከብር ሰው ዕጣ ፈንታው ምን ያህል የከፋ መሆኑን ያሳያል። ምሳ.20÷20።

ይህ እርግማንና የሞት ቅጣት እናትና አባቱን ለተሳደበና ለማያከብራቸው ልጅ ብቻ ሳይሆን ምክራቸውን ለማይቀበል፣ ለቃላቸውም ለማይታዘዝ ዐመፀኛ ልጅም ጭምር የሚሠራ ነው። ዘዳ.21÷18-21። ስለዚህ ነገር ሌዋ ውያንም በጌባል ተራራ ላይ ቆመው ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው በመጮህ «አባቱን ወይም እናቱን የሚያቃልል ርጉም ይሁን፣ ሕዝቡም ሁሉ አሜን ይላሉ» ይሉ ነበር። ዘዳ.27÷16። በተጨማሪም ቅዱስ መጽሐፍ «በአባትዋ የምታላግጥን የእናትዋንም ትእዛዝ የምትንቅን ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጡአታል÷ አሞራዎችም ይበሉአታል።» ሲል ያስጠነቅቃል። ምሳ.30÷17።

ታሪኩ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመዘገበለት የካም ልጅ የከነዓን መረገም «ወላጁን የማያከብር ይረገም» የሚለውን ቅጣት በተግባር የሚያሳይ ነው። ካም ለአባቱ አልታዘዝ ብሎ፣ ወይም አባቱን መትቶ፣ ወይም ተሳድቦ፣ ወይም ክፉ ነገር ተናግሮ አልነበረም ነገር ግን አባቱ ኖኅ በመጠጥ ደክሞ በተመለከተው ጊዜ የተራቆተ እካሉን መሸፈን ሲ ገባው ዕርቃኑን በማየቱና ለወንድሞቹ በመናገሩ ነው እንጂ :: ዘፍ.9÷20-26። ካም ባጠፋው ጥፋት የተነሣ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ከነዓናውያን ሁሉ በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታት መርገሙን ተቀበሉ፣ ለሴምና ለያፌት ልጆች ባሪያዎች አንዲሆኑ ተረገመው ነበር። ዘፍ.9÷25-27። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋሰለ ትምህርቱ ስለ ልጅዋ ልትለምነው የመጣችውን ከነናዊት ሴት ባነጋገረ ጊዜ

«የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም» ያላት አባቱን ባለማክበሩ የተረገመውን የከነዓንን መረገም በማስታወስ ነበር። ማቴ.15÷26። ይህም አባትና እናታቸውን የማያከብሩ ልጆች ከእግዚአብሔር ጸጋና በረከት ዕጣ ፈንታ የሌላቸውና ከልጅነት ክብርም የተለዩ መሆናቸውን የሚ ያሳይ ነው። ካም አባቱን ባለማክበሩና የአባቱን ዕርቃን በድ ፍረት በማየቱ ትውልዱ እንደተረገመ፣ ይህን ላለማየት ፊታቸውን አዙረው የአባታቸውን ገላ የሸፈኑት ሴምና ያፌት ደግሞ ይህን ትእዛዝ በማክበራቸው የተባረኩ መሆ ናቸውን በማስተዋል አሠረ ፍኖታቸውን ተከትለን አባቶ ቻችንንና እናቶቻችንን በማክበር የበረከት ባለቤት ልንሆን ያስፈልጋል።

ሦስኛው የአባት የክብር ደረጃ

አባት የቤተሰብ ራስ ነው። የቤተሰቡ ራስ ነው ማለትም የሚያስተ፣ የልጆቹና የቤተሰቡ ሁሉ አስተዳዳሪ ነው ማለት ነው። «ባል የሚያስተ ራስ ነውና» ተብሏልና። 1ቆሮ.11÷3። በጥንት ዘመንም የቤተሰቡ መሪ አባት ነበር። አባት ቤተሰቡን እንደ ካህን ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር የሚ ያገናኝ፣ የቤተሰቡም ተወካይ ነበር። በተለይም ከህጎት ነለአርን ልጆች ብቻ የተወሰነበት የሙሴ ሕግ ከመሠራቱ በፊት የክህነትን ሥራ የሚፈጽመው የቤተሰቡ ኃላፊ የሆነው አባት ነው፤ ጻድቁ ኢዮብ ስለእያንዳንዱ ልጁ የሚቃጠል መሥዋዕት እንደሚቀረበና «ምናልባት ልጆቼ በድለው እግዚ አብሔርን በልባቸው ሰድበው ይሆናል ብሎ» እንደተናገረ። ኢዮ.1÷5። ስለዚህ አባት ስለልጆቹ የሚያማልድ ከእግዚ አብሔርም የሚያስታርቃቸው የቤተሰቡ አማላጅ ነበር። አባቶቻችን ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብም ሁሉ እንዲሁ ነበሩ።

የአባት በረከት ታላቅ ስጦታ በመሆኑ ልጆች ሁሉ የአባቶቻቸውን ቡራኬ ለመቀበል አብልጠው ሥራ መሥራት በዕንባም ይህን ቡራኬ መጠየቅና የሚችሉትን ሁሉ ጥረት ግድረግ አለባቸው። ምክንያቱም ከአባቱ በረከትን ያጡበለ

ማንም ቢሆን እንዲሁ ከእግዚአብሔር በረከትን ይቀበላልና። ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው ተመልከተናል፣ ምንም እንኳ ያዕቆብ በብልጠት ቡራኬውን የተቀበለ ቢሆንም በረከቱ ግን እርግጠኛና በኋላም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ነበርና አባቱ ይስሐቅ የባረከውን ያዕቆብን እግዚአብሔር ባረከው። ዘፍ.28+1114። ኤሳውም በመጮህ ይህን የአባቱን በረከት ይሻ እንደነበር ተጽፏል። ዘፍ.27+38።

የአባቶችን ቡራኬ እግዚአብሔር ካጸደቀው እርግ ግናቸውንም አጽድቆታል። ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ኖኅ ከነዓንን «ከነዓን ርጉም ይሁን፣ ለወንድሞቹም የባሪያ ዎች ባሪያ ይሁን፣ የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ ከነዓ ንም ለእርሱ ባሪያ ይሁን፣ እግዚአብሔርም ያፈትን ያስፋ፣ በሴምም ድንኳን ይደር፣ ከነዓንም ለእርሱ ባሪያ ይሁን» እያለ የልጁን ልጅ ከነዓንን ሦስት ጊዜ የረገመበት መርገም መድኃኒታችን ለከነናዊቱ ሴት በሰጠው መልስ የጸደቀ መሆኑ በቂ ማረጋገጫ ነው። አባታችን ያዕቆብም አሥራ ሁለቱንም ልጆቹን ወደእርሱ ሰብስቦ እንደባረካቸው፣ በዚ ያው መሠረትም ቡራኬው እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ የተፈጸመ መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። ዘፍ.49+1 እስከ ፍጻሜው።

እግዚአብሔር ፍቅርን በእናትና በአባት ደግነት መስሎታል

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነትና የፍቅሩን ጥልቀት ለማሳየት ሲፈልግ ይህን ፍቅሩን አባትና እናት ለልጆቻቸው ከሚኖራቸው ፍቅርና ርኅራኄ ጋር አመ ሳስሎታል። እግዚአብሔር አምላክ የፍጥረት ሁሉ ገዥ እንደ መሆኑ መጠን ሁሉ የእጁ ሥራዎች በእርሱም ሥልጣን የሚ ተዳደሩ ናቸውና እርሱንም እግዚአብሔር እንለዋለን። ለእኛ ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሣም «አባታችን» ብንለው ይወዳል። ስለዚህም ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለጸሎት ባስተማረበት አንቀጽ «በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ»

እንድንለው ያዘዘን። ሐዲስ ኪዳን ይህን የእግዚአብሔር አባታዊ ርኅራኄ በሚገልጡ ብዙ መጻሕፍት የተመላ ነው።

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገረው ብንጀምር ስለሚያስፈልገን ነገር እንዳንጨነቅ ባስተማረን ጊዜ «አት ጨነቁ ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና» ካለ በኋላ በሌላ ጊዜ ደግሞ «ከሰማይ ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገር ይሰ ጣቸው?» ብሏል። ማቴ.6+32። ማቴ.7+11። ስለመንግሥተ ሰማያትም በተናገረ ጊዜ «አንተ ታናሽ መንጋ መንግ ሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ።» ብሏል። ሉቃ.12+32። መልካም የሆነውን ሥራ በስውር መሥራት እንደሚገባ ሲያስተምርም «በስውር የሚያይ አባ ትህም ዋጋህን በግልጥ ያስረክብሃል» ሲል ተናግሯል። ማቴ.6+6። እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ራሱን በአባትነት የገለጠባቸው ቃላት ናቸው፣ እጅግ በጣም ብዙ ከመሆናቸው የተነሣም ሁሉንም ለመዘርዘር አይቻልምና ለአብነት ከላይ የጠቀስናቸው ይበቃሉ።

ልዑል እግዚአብሔር አባት ተብሎ መጠራቱ ከጥንት ጀምሮ የነበረና የሚታወቅም ቃልም እንጂ በሐዲስ ኪዳን ብቻ የተገለጠ አይደለም። በእሬት ዘፍጥረት «የእግዚአ ብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካም እንደሆኑ አዩ» የሚለው ቃልም የሚያስረዳው እርሱ የሰዎች አባት ተብሎ የሚታወቅ መሆኑን ነው። ዘፍ.6+2። የብሉይ ኪዳን ነቢያትም «አቤቱ+ አንተ አባታችን ነህ። ስምህም ከዘለዓ ለም ታዳጊአችን ነው።» «አሁን ግን+ አቤቱ+ አንተ አባታችን ነህ እኛ ጭቃ ነን፣ አንተም ሠሪያችን ነህ+ እኛም ሁላችን የእጅህ ሥራ ነን።» እያሉ የእግዚአብሔርን በአ ባትነት መገለጥ አስምተው ይናገሩ ነበር። ኢሳ.63+16፣ 64+8። እንግዲህ በጠቀስናቸው ምክንቦች ሁሉ እግዚአ ብሔር ራሱን ትሑት አድርጎ በአባትነት ፍቅር የገለጠልን መሆኑን በሚገባ ተረድተናል።

ፍጹም የሆነ ፍቅሩን ዳግም በእናት ርኅራኄ መስሎ ገልጠልናል። ይህም እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ሲወቅስ

«ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ+ ነቢያትንም የምትገድል+ ወደ እርሷ የተላኩትንም የምትወግር÷ ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ!» ባለው ቃሉ ገልጦታል። ማቴ. 23÷37። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር ዶሮ ለጫጩቶቿ ባላት ፍቅር ተመስሏል። በሌላ ምንባብ ደግሞ እግዚአብሔር «በውኑ ሴት ከማኅፀኗ ለተ ወለደው ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕግንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን? እምን÷እርሷ ትረሳ ይሆናል+ እኔ ግን አል ረሳሽም።» በማለት ፍቅሩና ርኅራሄው እንደ እናት ፍቅርና ርኅራሄ መሆኑን ገልጦልናል። ኢሳ.49÷15።

ወላጆችን የምናከብረው እንዴት ነው?

አባትህንና እናትህን አክብር የሚለው ትእዛዝ ጥልቅ ትርጉምና አስፈላጊነቱም የገባው አንድ ሰው ወላጆቼን የማ ከብረው እንዴት ነው በማለት ሊጠይቅ ይችላል። በሚከ ተሉት መንገዶች ወላጆቹን የሚያከብር መሆኑን፣ በተግባር ሊያደርግ የሚገባውንም ሊያውቅና ለጥያቄውም መልስ ሊያ ገኝ ይችላል።

ሀ. <u>ውጤታማ በመሆን፦</u> በሕይወት ዘሮ ውጤታ ማ መሆን ወላጅን ለመርዳት የመቻል አንዱ ምልክት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ልጃቸው ውጤታማ በመሆኑ ወላጆቹ ክብር ይሰማቸዋል፣ ልቡናቸውም በደስታ ይሞላል። መጽሐፍም «ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል ሰነፍ ግን ለእናቱ ኀዘን ነው» «...የጻድቅ አባት እጅግ ደስ ይለዋል፣ ጠቢብንም ልጅ የወለደ ሐሤትን ያገኛል።» በ ማለት ይህንኑ ያረጋግጣል። ምሳ.23÷24።

በትምህርቱ ብርቱ የሆነና በማዕረግ የሚያልፍ፣ በሥ ራው ታማኝና ታታሪ፣ በራሱም የሚተማመን፣ የበላዮቹም የሚወዱት፣ በሕይወት ዘመኑም ውጤታማ የሆነና የተ ላካለት፣ መልካም ዝናም ያለው ልጅ ለቤተሰቡ በተለይም

ለእናቱና ለአባቱ ከብር ከመሆኑም በላይ የደስታቸው ምንጭ ነው፣ ይኮሩበታልም። ልጁ ውጤት አልባ የሆነ እንደሆነ አባቱ ስለእርሱ ይሸማቀቃል እናቱም ታፍራለች። በመጽሐፍም ደግሞ «ሰነፍ ልጅ ለአባቱ በፀት ነው÷ ሰወለ ደችውም ምሬት ነው።» «ሰነፍን የሚወልድ ኀዘን ይሆን በታል+ የደንቆሮ ልጅም አባት ደስ አይለውም» «ሰነፍ ልጅ ለአባቱ ኀዘን ነው» በማለት ከላይ የተረበውን ሃሳብ የሚደ ግፍ ማረጋገጫ ሰጥቷል። ምሳ.17÷25። ምሳ.17÷21። ምሳ.19÷13።

ኒቂይት ሐና በልጇ በሳሙኤል ደስተኛ ነበረች፣ ዮሴፍም ለአባቱ ደስታ ነበር። በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ኤሳው የወላጆቹን የይስሐቅንና የርብቃን ልብ እንደአሳዘነ በመጽሐ ፍ ተመዝግቧል። ዘፍ.26÷35። እንግዲህ ወላጆች የሚደሰቱ በትን ነገር ለመሥራት ሌሊትና ቀን በመጣር ለውጤት ራ ስን ማሰለፍና ውጤታማ ሆኖ መገኘት ወላጆችን የማክበር አንዱ ገጽታ መሆኑን በመገንዘብ ለውጤት የሚያበቃ፣ ለበረከት የሚያደርስ ሥራን በመሥራት የተጠመዱ መሆን ያስፈልጋል።

ለ. <u>የወላጆችን ውለታ በማስታወስ፦</u> ሰው እናቱና አባቱ ያደረጉለትን ሁሉ ዘወር ብሎ መመልከትና ማስታወስ አለበት። ለዘመኗ ወራት በእርግዝናዋ ጊዜ የነበረችበትን ሁኔታ ለማወቅ የሕክምና ወይም የሥነ ልቡና ወይም የሥነ ሕይወት መጻሕፍትን ማንበብ አያስፈልግም። በእርግዝናዋ ወራት ያሳለፈችውን አድካሚ ጊዜና ከወለደች በኋላ ቤተክርስቲያን ከመግባት ለእርጎ ወይም ለሰማንያ ቀናት ተከልክላ መቆየቷን ማስታወሱ ብቻ በቂ ነው። ሕፃኑን በማሳደግ ያለባትን ኃላፊነት፣ ምግቡን በማዘጋጀት፣ ሲያለቅስ በማባበል፣ ንጽሕ ናውን በመጠበቅ፣ በጀርባዋ በማዘል በክንዷም በመታቀፍ፣ በትከሻዋ በመሸከም፣ እንቅልፍ አጥታ በመን ከባከብ ያለበትን ድካም ማሰብ የእናት ውለታዋ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል። እንዲህ ባለ ሁኔታ ከሕፃንነት ጀምራ የምትንከባከብና የምታሳድግ እናት በልጇ ደግሞ ልትረዳ ይገባታል። መከራውን ሁሉ ታግሣ ያሳደገች እናት ውለታዋ ሊከፈላት ይገባል።

እንዲሁም ደግሞ ለግላደግ ሲታገል የነበረውን፣ የቤቱን ጥሮዎች በመሸፈን፣ የልጁን ፍላጎቶች ያረካውን፣ ልጁ ሲነካ እርሱ እንደተነካ የሚሰማውን አባትም መዘንጋት አይገባም። ስለ አደረገው ነገር ሁሉ የሚቀርብለት ክብርና ምስጋና ስለገንዘብ ዕርዳታው ብቻ ሳይሆን ስለፍትሩ፣ ስለመልካምነቱና ስለርኅራኄው ጭምር ነው። የእነዚህን ጥልቅ ስሜቶች ጠቃሚነት ለማረጋገጥ እነዚህን እንከብካቤዎች በማጣት ስንቶች እንደወደቁና በከባድ የሥነ ልቡና ችግር ውስጥ እንደገቡ ማስተዋሉ በቂ ነው።

በመሆኑም ወላጆች ከዕንስ እስከ ጉልምስና ድረስ ለልጆቻቸው የሚያበረክቱት መሥዋዕትነት በእርጅናቸው ዘመን በሚደረግላቸው ዕርዳታ የሚካካስ ውለታ አይደለም፣ በሕይወት ዘመን ሁሉ በልቡና ጽላት ተቀርጾ ሊታወስ የሚኖር ነው እንጂ። ምንም እንኳ ወላጆች ቆይተው ጠ ባያቸው የሚያስቸግር ቢሆን የተደረ ውለታቸውን በማሰብ በትዕግሥት ሆኖ ከእኛ የሚጠበቀውን ማድረግ የሚገባ እንደሆነ ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም።

ሐ. በመርዳት፦ ሰው ወላጆቹ ባረጁ ጊዜ፣ በታ መሙ ጊዜና የልጃቸው ዕርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሁሉ የመርዳት ግዴታ አለበት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖቱን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።» በማለት የተናገረው ቃል ቤተሰቦችን ከሕ ግነት ዘመናችን ጀምሮ ስለአደረጉልን እንክብካቤ ሁሉ እኛ ደግሞ በዕርጅናቸው ዘመን መልካሙን ሁሉ ልናደርግላቸው የሚገባ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። 1ጢሞ.5÷8። የቤተሰቡ ቁጥር እየጨመረ በሄደ መጠን ይህ መረዳዳት አስፈላጊ መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ይህ መረዳዳትም ለቤተሰቡ ሕልውና አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች እንጂ በማይጠ ቅሙ ገቢረ ኃጣውኢ ላይ መሆን የለበትም።

ይህን በተመለከተ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመ ስቀል ላይ ሳለ እናቱ ድንግል ማርያምን ሳይዘነጋት ለሚወ ደው ደቀ መዝሙር ለቅዱስ ዮሐንስ «እነሆት እናትህ» በማ

ለት ይረዳትና ያገለግላት ዘንድ አደራ መስጠቱና ቅዱስ ዮሐንስም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደቤቱ የወሰዳት መሆኑ ልጅ ወላጆቹን በመርዳት አክብሮቱን መግለጥ እንዳለበት የሚያስተምር ነው። ዮሐ.19÷27።

የቋፍ በወንድሞቹ ተሸጦ በስደት በሚኖርበት በግብፅ ሳለ በእነዚያ የረሃብ ዘመናት ከእርሱ በብዙ ርቀት ላይ የነበረውን አባቱን አልዘነጋውም ነበር። እንዲያውም «አሁንም ፈጥናችሁ ወደ አባቴ ውጡ፥ እንዲህም በሉት፦ ልጅህ ዮሴፍ የሚለው ነገር ይህ ነው፦ እግዚአ ብሔር በግ ብፅ ምድር ሁሉ ላይ ጌታ አደረገኝ፣ ወደ እኔ ና፥ አት ዘግይ፤ በጌሤምም ምድር ትቀመጣለህ፥ ወደእኔም ትቀር ባለህ፥ አንተና ልጆችህ፥ የልጆችህም ልጆች፣ በጎችህና ላሞ ችህ ከብትህም ሁሉ። በዚያም አንተና የቤትህ ሰዎች የአንተ የሆነው ሁሉ እንዳትቸገሩ እመግብሃለሁ የረሃብ ዘመን ገና አምስት ዓመት ቀርቷልና።» በማለት አባቱን ለመርዳት ጥሪውን አስተላልፎአል። ዘፍ.45÷9–11። በዚህ ድርጊቱም ለወላጅ አባቱና ለቤተሰቡም ሁሉ ከእርሱ የሚጠበቀውን ዕር ዳታ በማድረግ ወላጆቹን አክባሪ መሆኑን በምግባር አሳይቷል። በዚህ ዘመን ያለው ትውልድም ይህን በማ ስተዋል ወላጆችን መርዳት ወላጆችን የመክበር አንዱ ገጽታ መሆኑን በውቶ በሚገባው ሁሉ ወጥሮን እየሬዳ የእግዚ አብሔርን በረከት ገንዘብ ማድረግ ይገባዋል።

መ በማፍቀርና በማክበር፦ ሰው ሁሉ የሚያው ቀው የመጀመሪያው ፍቅር የእናቱ ቀዋሎም የአባቱን ፍቅር ነው። ይህም ከእግዚአብሔር በልግሥና የተገኘ የተፈጥሮ ፍቅር ነው። ከዚህ ፍቅር ውጭ የሆነ ማለትም ወላጆቹ የማ ይወዱት እርሱም ወላጆቹን የማይወድ ሰው ጤነኛ ነው፣ ከሰዎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነትም ትክክለኛ ነው ለማ ለት ያስቸግራል። ይህ ፍቅር መልካም በማድረግ ወይም ክፉን ባለማድረግ ሊገለጥ ይችላል። ልጅ የሚያስበውን ሁሉ በማድረግ እርካታንና ምቾትንም ሁሉ መፍጠር ለወላጆቹ ያለውን ፍቅር በምግባር በመግለጥ ከእነርሱም በረከትን ለማ ግኘት ይችላል። ይህ የልጅነት ፍቅር እንዲሁም ወላጆችን

ማርካት /ማስደሰት/ በወላጆች የሕይወት ዘመን ሁሉ የ ማይቋረጥና ከሞቱም በኋላ በሌላው ዓለም ሳሉ በጸሎትና በትጻሌ እነርሱን በማሰብ፣ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ የተናገሩትን ቃላቸውንና ኑዛዜአቸውን በመፈጸም ሊቀጥል ይገባል።

ልጆች ወላጆችን የሚያበሳጩ ወይም በወላጆቻቸው የሚጨክኑ ወይም የሚጠሉአቸው ወይም ደግሞ ሃሳባቸ ውንና ምክራቸውን የማይቀበሉና የማይፈጽሙ መሆን የለባ ቸውም። ከዚህም ሌላ ወላጆቻቸውን ከአቅማቸው በላይ እን ዲያደርጉላቸው በመጠየቅ ማስጨነቅና ማሰልቸት አይገባ ቸውም። የቤተሰቦቻቸውን ንብረት ማባከንና በከፉ አመ ላቸውም የቤተሰቡን ክብርና መልካም ዝና ማዋረድ የለባቸውም። ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው የልጆች ክፉ አመል የወላጆቻቸውን ክፉ ማየትና ሞታቸውንም ለመመልከት መመኘታቸው ነው። በመጽሐፍም ማንም እናቱን ወይም አባቱን የመታ ወይም የሰደበ ፈጽሞ ይገደል ብሏል፣ አባቱን ወይም እናቱን የማያከብር ማንም ቢሆን የተረገመ ነው ብሏል። ስለዚህ ክፉ የሆነውን ነገር ሁሉ ባለማድረግ ለቤተሰብ ንጹሕ ፍቅርን መግለጥ አንዱ አክብሮት መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

ወላጆችን አለማክበር ማለት እነርሱን መናቅ ማለት ነው። ለዚህ ሃሳብ አስረጅ የሚሆነው ምሳሌ ራሱን ከወላጆቹ ጋር የሚያስተካክል ልጅ ነው። ይህን የመሰለው ልጅ ከወላጆቹ ጋር እኩል እንደሆነ ራሱን ይቆጥራል፣ ስለዚህም ወላጆቹ ሲና ገሩት መልሶ ይናገራል፣ ሲቆጡትም መልሶ ይቆጣል፣ በእር ሱና በወላጆቹ መካከል ልዩነት ያለም አይመስለውም፣ ይህ ሁሉ ታዲያ መንፈሳዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተገቢ አይደለም።

ልጅን በምክርና በተግሣፅ አስተካክሉ ማሳደግ የአባት መብት ሲሆን ልጅም መልስ ከመስጠት ይልቅ በዝምታ የሚነገረውን ማድመጥና መቀበል አለበት። እናት ወይም አባት በተቆጡ ጊዜ ልጅም በፈንታው መቆጣት የለበትም፣ የተቆጣ እንደሆነ ኃጢአትን ይሠራልና። ይህ ቁጣ ውም እናቱንና አባቱ ን ለማክበር ከተሰጠው ትእዛዝ ጋር የሚይጣጣምና የሚ ቃረንም ነው።

ሰ. <u>ፈጣን ፈቃደኝነትን</u>:- ከላይ የጠቀስነው እውነተኛው ፈቃደኝነት ፈጣንና ሳይቆይ በተግባር የሚገለጥ ከሌላ ከምንም ሁኔታ ጋር የማይያያዝ መሆን አለበት። መልካም ልጅ በወላጆቹ የታዘዘውን ለመፈጸም ወዲያው ፈቃደኛ ይሆናል። ትእዛዙ ከወላጆቹ አንደበት እንደወጣ በሥራ ላይ ያውለዋል። እንዲህ ዓይነት ልጅም በቤተሰቡ ዘንድ ተወዳጅ ነው።

ሸ. <u>ደስተኛውም ፈቃደኛ መሆንን</u>:- መታዘዝ እውነ ተኛ ከሆነ ከልቡና የመነጨና ያላምንም ማጉረምረም መሆን አለበት። አንዳንድ የታዘዙትን የ ሚፈጽሙ ነገር ግን በልባቸው የሚያጉረመርሙ ልጆች አሉ። እነዚህ ከልማድ የተነሣ ትእዛዝን ለመፈጸም እሽ አሉ እንጂ ታዛዥነታቸው ከፍቅር የመነጨ አይደለም። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የታዘዙትን ቢፈጽሙት እንኳ ልቡናቸው ፈቃደኛ ሆኖ ያዘዛቸውን ሰው ለማስደሰትና ትእዛዙንም በማክበር አይ ደለም። ሥናልባትም ትእዛዙን የፈጸሙት ከፍርሃት የተነሣ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ልጆች ደግሞ የወላጆቻቸውን ትእዛዝ ከመፈጸማቸው በፊት እጅግ ብዙ ከተጨቃጨቁና ከተነታረኩ በኋላ በብዙ ክርክር ፈቃደኛ የሚሆኑ አሉ። ወላጆቻቸውም ጨቅጫቃነታቸውን ስለሚያውቁ ምንም እንዲያደርጉላቸው ሳይጠይቋቸው ይችላሉ፣ በዚህም የተነሣ በፈቃደኝነት በመታዘዝ ሊያገኙ የሚችሉትን በረከት ያጡ ታል።

ቀ. <u>በጌታ መታዘዝን</u>:- ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፣ ይህ የሚገባ ነውና» ያለውን ማስታወስ ተገቢ ነው። ኤፌ.6+1። «በጌታ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትእዛዙ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት መሆን እንዳለበት ነው። አባት ወይም እናት ወይም ደግሞ መምህር ልጃቸው ከእግዚ አብሔር ሕግ ጋር የማይጣጣም ነገር እንዲያደርግ ቢያ ዝዙት፣ ልጃቸው ይህን ትእዛዝ ለመፈጸም አይገደድም መፈጸምም የለበትም። ነገር ግን ይህን እያወቀ አባትህንና

እናትህን አክብር ተብያለሁ በማለት ይህን የማይገባ ትእዛዝ ቢፈጽም ያዘዙት ወላጆችና እያወቀ የታዘዘው እርሱ ከተጠ ያቂነት አያመልጡም። የልጆች መታዘዝም የእግዚአብሔ ርን ሕግ እስካልተቃረነ ድረስ በማንኛውም አንፃር፣ እስከሞት ድረስም ቢሆን ራስን በማዋረድና በትሕትና የራ ስን ክብርም በመተው ሞምር ሊሆን ይገባል።

መታዘዝ በጥበብና በማመዛዘን በተለይም የታላቁን አባት የአባ እንጦንስን ምክር በማስታወስ ሊሆን ያስጠ ፈልጋል፤ «የታዘዝከው ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማ ከሆነ ፈጽመው፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነ ነገር እንድትሠራ የታዘዝክ እንደሆነ ግን ለራስህ ጎሊና ለሰው ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ የበለጠ መሆኑን ንገረው» ብሏልና። ከዚህ በተጨማሪም መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ ይከ ተሉኝማል» ሲል የተናገረውን ማሰብ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚቃረነውን ድምፅ ከመስማት ይልቅ የእግዚአብሔ ርን ድምፅ ማድመጥ የሚገባ መሆኑን የሚያስታውስ ነው። ዮሐ.10÷27።

ቀደም ብለን የጠቀስናቸው የሬካብ ልጆች ነቢዩ ኤርሚያስ ወደ እግዚአብሔር ቤት ወስዶ እንደጠየቀው በፊታቸው ወይን የተሞሉትን ዋንጫዎች አስቀምጠ «ወይ ኑን ጠጡ» ቢላቸው እነርሱ ግን «አንጠጣም» በማለት በድ ፍረትና በንጹሕ ጎሊና መልስ ሰጥተውና እንታዘዝም በማ ለታቸው ወይኑንም ባለመጠጣታቸው እግዚአብሔር ተደስቶ በበረከት ሳበኛቸው። እነርሱ ከነቢዩ ትእዛዝ ይልቅ ለእግዚ አብሔር ትእዛዝ ቅድሚያ ሰጥተው ነበርና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለመታዘዝ የተናገረው ቃልም የሚያስደንቅ ነው፤ «ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ቢሰብክ ላችሁ የተረገመ ይሁን» በማለት ከቀደመው ትምህርት ሌላ አዲስ ትምህርት አትቀበሉ ሲል ከማዘዙም በላይ ከወንጌል የሚለይ ትምህርት የሚሰብኩትን «የተረገሙ ይሁኑ» እንዳላቸው ማስተዋል ይገባል። ይህን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል በተረጉመበት ድርሳኑ ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስ

የመታዘዝን ሥርዓት ከአብራሪ በኋላ የሥርዓቱን ጥብቅነት ሲገልጥ «ከዚህ ጥቅስ ቅዱስ ጳውሎስ መላእክትንም እንኳ ለ ማውገዝ ቃጥቷል» ብሏል። መልአክም ቢሆን የእግዚአብሔ ርን ወንጌል የሚቃረን ትምህርት ማስተማር የሌለበት ከመሆኑም በላይ የዚህ ዓይነቱን መልአክ ትምህርት መቀበልን ሞምር አውግዞታል። ይህም እንግዲህ ከሕገ እግዚአብሔር የሚቃረን ትእዛዝ በመልአክም የተነገረ ቢሆን ሊፈጸም የማይገባ መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ብዙ ሰዎች ግራ የሚገቡአቸው ጥያቄዎች የፈቃ ደኝነትና የመታዘዝ መጠኑና ገደቡ ምን ያህልና የት ድረስ ነው? መታዘዝስ ፍጹም ነው? በልቡ ትእዛዙን እየተቃወመ ያለትሕትና መታዘዝ ወይም ይሉኝታን አስወግዶ ለጎሊናው መታዘዝ አለበት? የሚሉት ናቸው። ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የፈቃደኝነትንና የመታዘዝን ጥልቅ ትርጉም በጥበብና በማስተዋል መረዳት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

ከሁሉም በላይ፣ ከማንም፣ ከምንም በፊት መታዘዝ የሚገባው ብቻውን እምላክ ለሆነው ለልዑል እግዚአብሔር ነው። በመቀጠልም የእግዚአብሔር ሕግ በሚያጠቃልለው መጠን ለሰዎችም መታዘዝ ይገባል። ምንም እንኳ የሰው ጎሊና ለእግዚአብሔር በመታዘዝና ለሰዎች በመታዘዝ መካ ከል በሚፈጠር ግጭት የሚጨነቅ ቢሆንም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» በ ማለት የተናገረውን ቃል በማሰብ ጎሊናን ከውንቀት ማላቀቅ ያስፈልጋል። የሐዋ.5÷29።

ለወላጆች መታዘዝም የእግዚአብሔር ሕግ በሚፈቅደ ውና በሚያዝዘው መጠን መሆን ይኖርበታል። ከወላጆች አንዱ ልጁን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚቃረን ትእዛዝ ቢያዝዘው፣ ልጁ በንጹሕ ጎሊና ሆኖ ይህን ትእዛዝ መታዘዝ አለበት፣ የመታዘዝ ግዴታው የወላጆቹ ትእዛዝ ከሕገ እግዚአብሔር ጋር እስካ ልተቃረነ ድረስ ብቻ ነውና። ልጆቻቸው በትሕትና እንዲታዘ ዙአቸው የሚሹ ወላጆችም ልጆቻቸውን ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚጣጣምና ከዚያም ወሰን የማይወጣ ትእዛዝ ማዘዝ የሚገባቸው መሆኑን ማወቅ ኣለባቸው።

ወላጆችን የማክበር ሌላው ምልክት ሃሳባቸውን ሁሉ ማሟላት ነው። ይህም ማለት ልጅ ሊያደርገው የሚገባውን በጠየቁት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ቢሆን የጠየቁ ትንና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማሟላት ማለት ነው። ብልህ ልጅ ወላጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ራሱ ቀድሞ ያውቃልና ሳይጠ ይቁት ሃሳባቸውን በመረዳት በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይረዳቸዋል። ለምሳሌ አባቱ ደክሞት እንደቆመ የተመለከተ ልጅ አባትየው መቀመጫ ወንበር እንዲያመጣለት እስኪጠ ይቀው መጠበቅ የለበትም፣ ይልቁንም ይህ እንድሚያስ ፈልገው ተረድቶ መቀመጫ በማዘጋጀት አባቱ እንዲያርፍ በአክብሮት መጋበዝና ምቾት ሊሰጠው ይገባል። እናቱም በቤት ውስጥ ሥራ ደክማ የሚያይ ልጅ እጁን ዘርግቶ ሊደ ግፋት ይገባል እንጂ ዕርዳታውን እስክትጠይቅ መጠበቅ የለበትም። የተመገበበትን ገበታ እናቱ እንድታነሣና እንድ ታጸዳው መጠበቅም የለበትም፣ ራሱ ቀድሞ ይህን ማድረግ አለበት እንጂ። በዚህ መልክ ወላጆቹን ማክበር በወላጆችና በሰው ሁሉ ፊት ከፍ ከፍ ማለት እና በእግዚአብሔርም ዘንድ ጸጋና በረከትን ማግኘት መሆኑን ማሰብ እንጂ የሚያዋርድ አለመሆኑን ማጤን ያስፈልጋል።

በቅዱስ መጽሐፍ «ቤርሳቤህም የኤዶምያስን ነገር ትነግረው ዘንድ ወደ ንጉሥ ወደ ሰሎሞን ገባች፣ ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ ሳማትም÷ በዙፋኑም ተቀመጠ፣ ለንጉሡም እናት ወንበር አስመጣላት÷በቀኙም ተቀመጠች።» የሚለው ታሪክ ወላጆችን ስለማክበር ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። 1ነገ.2÷19። ንጉሥ ሰሎሞን ከዙፋኑ ተነሥቶ አጅ በመንሣት እናቱን በተቀበለ ጊዜ ከክብሩ የተቀነሰበት ምንም አል ነበረም ተጨመረለት እንጂ። ለሰው ልጅ የወላጅ አባቱን ወይም የወላጅ እናቱን እጅ መሳም ይበዛበታልን?

በፈርዖን ቤት ሁለተኛ ሰው የሆነው፣ የፈርዖንንም ቀለ በት በጣቱ አጥልቆ መላዋ ግብፅን የሚገዛው ባለሙሉ ሥል ጣን፣ ሰዎች ሁሉ በፊቱ የሚሰግዱለት፣ የፈርዖንና የቤቱ ሁሉ ገዥና አዛዥም የሆነው ጻድቁ ዮሴፍ በግ ጠባቂ አባቱን አልናቀም፣ ይልቁኑ የሚመጣበትን ሠረገላ በመላክ በክብር ወደእርሱ ጠርቶ ተቀበለው እንጂ። «ዮሴፍም ሠረገላ

አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው መልካሙን ያደረጉ እየመሰላቸው ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃረን ትእዛዝ ያዝዙአቸዋል። ለምሳሌ፣ በሰንበት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲ ሄድ ከማዘዝ ይልቅ ወደ ፊልም ቤት ወይም ወደ ቲያትር አዳራሽ እንዲሄድ የሚያዝዝ፣ በትንሣኤና በልደት በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ እንዲያስቀድስ ከማድረጎ ይልቅ ወደ ዳንስና ጭፈራ ምሽቶች ይዞት የሚሄድ ወላጅ ልጁ ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃረን ድርጊት እንዲፈጽም ግዘቡን ማወቅ አለበት። ልጁ መንፈሳዊ በመሆኑ የወላጁን ትእዛዝ ለመፈጸም ሊቸገር ይችላል፤ አባትም የእግዚአብሔርን ሕግ እየጠቀሰ ልጁን ሊያስገድደው ይችላል። የልጅ ኅሊናም ለእግዚአብሔር ሕግ ወይም ለአባቱ ግትር ሃሳብ መታዘዝ እንደሚገባው ለመወሰን ይጨነቃል፤ በሰማይ ለሚኖር አባቱ ለእግዚአብሔር ወይስ በሥጋ ለወለደው አባቱ ይታዘዝ?

እናትም መንፈሳዊት ምናልባትም የሰንበት ተማሪ የሆነች ልጇን ከጉልበቷ በላይ የሆነ የሴትነት አካሏን ሊያ ሳይ የሚችል የዘመኑን ፋሽን እንድትለብስና ዘመናዊት እንድትሆንላት በማሰብ የማትሻውን እንድታደርግ ልታዝዝ ትችላለች። ልጅቱ ይህን ትእዛዝ ለመቀበልና ሕገ እግዚ አብሔርን የሚቃረን ነገር ላለማድረግ በማንገራገጭ ጨርሶ ከቤተክርስቲያን ልትከለከል ትችላለች።

እነዚህ ሁለቱም ወላጆች በእግዚአብሔር ሕግ ኮተ ሰጣቸው የሥልጣን ገደብ አልፈው ልጆቹ ትእዛዘ እግዚአብሔ ርን እንዲጥሱና ከሚወዱት እግዚአብሔር ጋር እንዲጣሉ የሚያደርግ ትእዛዝ በማዘዛቸው ትክክል አይደሉም ልጆቹም ትእዛዛቸውን ባለመቀበላቸው እንደ አመፀኞች ሊቆጠሩ አይገባም። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ እንዲ ገባ ወሰቀዋልና።

ወላጆች ሁሉ ደግሞ ከልጆቻቸው ክብርንና መታዘዝን የሚጠብቁ ከሆነ ልጆቻቸውን÷ ከሕገ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረንና ኅሊናቸውን የሚፈታተን ትእዛዝ ከማዘዝ ይቆጠ ቡ ዘንድ ይገባል። «እሺታን ወይም ፈቃደኝነትን የምትጠ ብቅ ከሆነ ሊፈጸም ወይም ሊደረግ የሚችል ነገር ጠይቅ»

አዘጋጀ፥ አባቱንም እሥራኤልን ሊገናኘው ወደ ጌሤም ወጣ፤ ባየውም ጊዜ በአንገቱ ወደቀ አቅፎትም ረጅም ጊዜ አለቀሰ።» ከዚህም በኋላ ወደ ፈርዖን መስዶ አባቱና ወንድሞቹ የበግ እረኞች መሆናቸውን አስተዋወቀው እንጂ በአባቱ አላፈረም፣ አላዋረደውም። ዘፍ.41÷40–43። ዘፍ. 45÷8። ዘፍ.46÷29–31። ይህም አባቶቻቸው ድሆች ወይም ያልተማሩ መሐይማን ወይም በተናቀ ሥራ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ለሚያፍሩና አባቶቻቸውን ለሚንቁ ሁሉ ተገቢ ትምህርት የሚሰጥ ነው። ስለሆነም በመጽሐፍ «ከእና ንተ ሰው ሁሉ እናቱንና አባቱን ይፍራ» የተባለውን እያሰቡ ወላጆችን በተገቢው ሁሉ በማክበርና ቃላቸውን በመቀበል በትሕትና መኖር ያስፈልጋል። ዘሌ.19÷13።

ሠ. በፈቃደኝነት በመታዘዝ– መታዘዝ ወላጆ ችን የማክበር አንዱና ዋነኛው ጠቃሚ ክፍል ነው። መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው ለእናቱ ለእመቤታችን ለትድስት ድንግል ማርያምና ለአሳደገው ለቅዱስ ዮሴፍ አረጋዊ ይታዘዝላቸው እንደነበር በመጽሐፍ ተመዝግቧል «ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደናዝሬት መጣ፥ ይታዘዛቸውም ነበር።» ተብሏልና። ሉቃ.2÷51። ለእመቤታ ችን መታዘዙ ወላጅ እናቱ በመሆኗ ነው። ለዮሴፍ መታዘዙ ደግሞ እርሱ ምንም እንኳ ወላጅ አባቱ ባይሆን ወላጅ አባት ሊያደርገው የሚገባውን ሁሉ በማድረግ እየተንከባከበ ከልጆቹ ጋር ስለአሳደገው ነው። ይህን የዮሴፍ የአባትነት ምግባርም እመቤታችን ቅድስት ድንግል «እነሆ፥ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን» በማ ለት ትገልጠዋለች። ሉቃ.2÷48።

ይህ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ለእናቱ ለድንግል ማርያምና ለአረጋዊው ዮሴፍ እየታዘዘ ማደግ ለሁላችንም መልካም ትምህርትና መመሪያ ነው። መላእ ክትና ሊቃነ መላእክት፣ ኃይላትና ሥልጣናት ሁሉ የሚገ ዙለትና የሚታዘዙለት የሰማይና የምድር ፈጣሪ በተዋሐ ደው ሥጋ የተነሣ ለወለደችው እናቱና ለአሳደገው አባቱ ታዛዥ ሆነ። በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉ

ፍጥረታት ሁሉ የሚሰግዱለትና የሚታዘዙለት እርሱ በትሕ ትና ታዛዥ ሆነ። ፊል.2÷10። እንግዲህ በዚህ መሠረት ለወላጆች የመታዘዝን ተገቢነት መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በተግባር ፈጽሞ አሳይቶናልና ልንከተለው ያስፈልጋል።

ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅ ስ ት ከተመዘገበው ቀደምት መካከል የታዛዥነት ምሳሌ አድርገን በመጀመሪያ የምንጠቅሰው የይስሐቅን ታሪክ ነው። አባቱ አብርሃም ለእግዚአብሔር የተቃጠለ መሥዋዕት ሊያደርገው ወደ ተራ ራው ይዞት በወጣ ጊዜ ይስሐ ያሳየው ፍጹም ፈቃደ ኝነትና ታዛዥነትን ነበር እንጂ አላንገራገረም። ሌላው አስ ደናቂ ምሳሌ ደግሞ /ምንም እንኳ ስለሰቱ ስሕተት ቢሆን/ አባቷ ለእግዚአብሔር የተሳለውን ስእለት እንዲፈጽም በፈቃደኝነት መሥዋዕት የሆነችው የገለዓዊው የፎንታሄ ልጅ ታዛዥነት ነው። መሳ.11÷30–40።

እግዚአብሔርም የእሥራኤልን ልጆች በለስለመታዘ ዛቸው በወቀሰ ጊዜ በምሳሌነት የተጠቀመበት አባታቸው ያዘዛቸውን የፈጸሙ የራካባውያን ልጆች አስደናቂ የመ ታዘዝ ምሳሌ ሌላው አብነታችን ነው። አባታቸው «እናን ተና ልጆቻችሁ ለዘላለም የወይን ጠጅ አትጠጡ። በምት ኖሩባት ምድር ላይ ብዙ ዘመን እንድትኖሩ፥ በዕድሜአችሁ ሙሉ በድንኳን ውስጥ ተቀመጡ» አላቸው። ኤር. 35÷6 –10። በመታዘዛቸውም እግዚአብሔር ተደስቷልና «ለአባ ታችሁ ለኢዮናዳብ ትእዛዝ ታዝዛችኋልና፥ ትእዛ ዙንም ጠ ብቃችኋልና፥... ስለዚህ በፊቴ የሚቆም ሰው ከሬ ካብ ልጅ ከኢዮናዳብ ወገን ለዘለዓለም አይታጣም።» አላቸው። ኤር.35÷18።

ከእነዚህ ከላይ ከጠቀስናቸው ምሳሌዎች የምንማረው ወላጆችን በፈቃደኝነት መታዘዝ ምንኛ ያማረ መሆኑን ነው። ይህም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ከመሆኑም በላይ የመንፈሳዊ በረከት ምንጭ መሆኑ ሌላው ትምህርት ነው። ቅዱስ መጽሐፍም በዚህ ረገድ «ልጄ ሆይ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናትህንም ሕግ አትተው» «የወለደህን አባትህን ስማ፥

'እናትህም ባረጀች ጊዜ አትናቃት።» በማለት ወላጆችን ማክበር የሚገባ መሆኑን ያስተምረናል። ምሳ.1÷8። ምሳ.6÷20። ምሳ.23÷22። ፈቃደኝነትና ታዛዥነት ምንኛ መልካም ናቸው፤ ሁለቱም የትሕትናና የመልካም ምግባር ፍሬዎችና የፍቅር ማረጋገጫዎች ናቸውና።

በመታዘዝ ጊዜ ራስን ዝቅ ማድረግና ከራስ ሃሳብ ጋር መታገል የማይቀር ነው። በሰው ሁሉ ያለ የሥጋ ፈቃድ ታዛዥነትን እንደ ዝቅተኝነት ስለሚቆጥረው ለጎሊና ፈተና አድርጎ ይህን ስሜት ያቀርብለታል። ይህን ውጊያ ያሸነፈ ሰው ነው እንግዲህ ለመታዘዝ የሚችለው። ያለምንም ጥርጥር ሰው ሃሳቡንና የሥጋውን ፍላጎት ተቋቁሞ ፈቃደኛ በሆነ መጠን ታዛዥነቱ የበለጠ ይጨምራል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።» በማለት የተናገረው ስለመታዘዝ ካስተማረበት መካከል አንዱ ነው። ዮሐ.6÷38። በዚህም የላከውን የባሕርይ አባቱን የእግዚአብሔ ር አብን ፈቃድ ለመፈጸም ሰው መሆኑን የገለጠ ሲሆን ከዚህ በላይ እንደጠቀስነው ለአባቱም ለእናቱም በመታዘዝ ፈቃደኝነትንና ታዛዥነትን አስተምሮናል።

ፈቃደኝነት ስንል ደግሞ የሚከተሉትን ሁሉ የሚያጠቃልል መሆን አለበት፤

ረ. እውነተኛ ፈቃደኝነት:- ልጅ የወላጆቹን ሃሳብ ለመፈጸም ብቻ ብሎ ወይም ቃላቸውን ለመሙላት /ለመሥጠል/ በማለት ብቻ ፈቃደኛ መሆን የለበትም። ፈቃደኝነቱ በእውነተኛ ልባዊነት የተደረገ፣ የወላጆችን ስሜ ት ላለመጉዳት በሚደረግ ጥንቃቄ ላይ ጭምር የተመረኮዘ መሆን ይኖርበታል። የታዘዘው የማያስደስተውን ነገር ለመፈጸም ቢሆን እንኳ የወላጆቹን ደስታ በማሰብ እነርሱንም ለማስደሰት ከልቡ ፈቃደኛ መሆን ይገባዋል። ለወላጆች ትእዛዝ የሚሰጠው የፈቃደኝነት ምላሽ አፍአዊ /ውጫዊ/ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊና እውነተኛ መሆን አለበት።

እንደተባለ። እግዚአብሔርም «እናንተም ልጆች ሆይ ለወ ላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ» ሲል በሐዋርያው አድሮ መናገሩ ወላጆች በሕግ የተሰጣቸውን መንፈሳዊ የሥልጣን ገደብ እንዳ ይተላለፉና ስለ ሕገ እግዚአብሔር የሚጨነቁ የልጆቻቸውን ፍቅር እንዳያጡ ነው። ስለዚህ በልጆች ላይ የተጣለው የመ ታዘዝ ግዴታ «ከጌታ» ማለትም ከሕገ እግዚአብሔር አስካ ልተቃረነ ድረስ ብቻ መሆኑን በውቆ ምን ማዘዝ ምን ደግሞ መተው እንደሚያስፈልግ መመዘን የወላጆች ኃላፊነት ነው።

የክርስትና ትምህርት በአንዲት ጥቅስ ላይ ብቻ የተመሠረተና ቁንጽል አይደለም። ዋነኛው መሠረቱ መንፈሳዊነት ነውና። እናም ግማሹን ትምህርት ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ መጓዝ አደገኛ ነው፤ የተጓዥንም ሕይወት ግማሽ ያደርገዋል። ከዚህ አንፃር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የጻፈውን መልእክት ማስተዋል ተገቢ ነው። «ልጆች ሆይ++ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ+ ይህ የሚገባ ነውና:-... እናትህንና አባትህን አክብር» በማለት ልጆችን የሚመለከተውን ግዴታ በአንድ ወገን ካስቀመጠ በኋላ «እናንተም አባቶች ሆይ+ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።» በማለት ሁለተኛ ወላጆችን የሚመለከተውን ኃላፊነት አስቀምጦታል። ኤፌ.6÷1-4። በዚህ በመልእክቱም የልጆችንና የወላጆችን ግዴታ በየፈርጁ እንዳስቀመጠው ተመልክተናል። በተጨ ማሪም ለቀላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ደግሞ «ልጆች ሆይ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ። ኣባቶች ሆይ+ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው /አታስቆጡአቸው/»በማለት በየክፍሉ ማስገንዘቢያ ሰጥቷል። ቆላ.3÷20-25።

የእዚህ ምንባባት ጥቅል መልእክት ስናጤነው እግዚ አብሔር አምላክ ለእያንዳንዱ ወላጅ «ይህን ልጅ በጣም ብዙ በሆኑ ትእዛዛት እንዲታዘዝ በእጅህ ሰጥቻለሁ፤ ነገር ግን ይህን ታዛዥነቱን ተጠቅመህ አትጫነው፤ አእምሮውን አትጉዳው፤ ለጎሊናውም ሸክም አታብዛበት፤ ከአቅሙ በላይ የሆነ ነገርም አትጠይቀው ምናልባት ችሎዛዙን መፈጸም እንዳያቅተው፤ በትእዛዛትህ ጫናም የተነሣ የወደቀ እንደሆነ

የእርሱን ደም ከአንተ እፈልጋለሁ» በማለት የሚያስጠነቅቅ ይመስላል። ወላጆችም ይህንኑ በአንክሮ ሊጠነዘቡት ያስፈልጋል። ይህ እንግዲህ የልጆች የመታዘዝ ገደብ ብቻ ሳይሆን የወላጆችም የማዘዝ ሥልጣን ወሰን የተደረገለትና ከሕገ እግዚአብሔር ተቃርኖ የሚያቃርን በተፋለሰ የተሞላና ሞፍን እንዳይሆን ሞምር የሚያስተምር ምሥጢር የተካተተበት ነው።

ስለ ልጆቻቸው የወላጆች ኃላፊነት

ወላጆች ከልጆቻቸው ሊያገኙት ስለሚገባው አክብሮት ከእነዚህ የሚጠበቅባቸው ግዴታ ወይም ኃላፊነት ደግሞ አለ። ከዚህኑም ወላጆች የራሳቸውን ግዴታ ሳይወጡ ዘወትር መብታቸው ብቻ እንዲከበር መፈለግ የለባቸውም። ልጆችም ቢሆኑ ደግሞ ምንም እንኳ ወላጆቻቸው የሚገባቸውን ባያደርጉላቸውና ግዴታቸውን ባይወጡ ወላጆቻቸውን የማክበር ግዴታ አለባቸው። በተለይ በዚህ ርእስ ግን የወላጆችን ኃላፊነት እንመለከታለን። ከወላጆች ግዴታዎች መካከል፣ ልጆችን ፈሪሃ እግዚአብሔርን በማስተማር ማሳደግ፣ በጥሩ ሁኔታ መንከባከብ፣ ዕቅም በፈቀደ መጠን ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ ስለእነርሱ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ጥሩ አርአያነትን በማሳየት ማስተማርና ከሁሉም በላይ በፍቅርና በርኅራኄ በሥርዓትም እንዲመሩ ማድረግ ዋናዎቹ ናቸው።

ሀ. ልጆችን ፈሪሃ እግዚአብሔርን በማስተማር ማሳደግ፦

ወላጆች ልጆቻቸው ከርስትና በሚነሡበት ጊዜ እንደክርስትና አናትና አባት ሁሉ በቤተክርስቲያን እደባባይ ፊት ቆመው ልጆችን በሃይማኖትና በትድስና ለማሳደግ ቃል ይገባሉ። ስለዚህም ልጆቻቸውን በመልካም መንፈሳዊ ሥነምግባር አንፀው ለማሳደግ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ኃላፊነት አለባቸው።

አንዳንድ ወላጆች የልጆቻቸውን ሥጋዊ ፍላጎት ብቻ በማሟላት ስለመንፈሳዊ ሕይወታቸውና ስለዘለዓለማዊ ተስፋቸው የሚያስፈልጓቸውን ሁሉ ማሟላትን እንደ ትርፍ ነገር ቆጥረው በቸልታ ያልፏቸዋል። ወላጆች መጨነቅ የሚገባቸው ለልጆቻቸው ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ የአስተዳደግ ሥርዓት ነው። ከልጆች ሥርዓት አልበኝነት የተነሣ በቤተሰቡ ላይ የሚመጣው ችግር ሁሉ ቀድመው ወላጆች እንደቀላል በመቁጠር ጥንቃቄ ካላደረጉባቸው ነገሮች የሚመነጭ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋቸዋል። ያልዘሩትን ሊያጭዱ ያልበተኑትንም ሊሰበስቡ አይችሉምና።

ልጆችን ቀርፆና አስተካክሎ ለማሬምና ሥርዓት ለማስያዝ የሚቻልበትን ጊዜ በዋዛ ካለፉት በኋላ የማይቻለውን ነገር ለማድረግ መሞከር ደረቅ እንጨትን ለማቃናት እንደመሞከር ነው። በችግኝነቱ /በለጋነቱ/ ያልታረቀውን ዛፍ ከጠነከረ በኋላ እናቃናህ ቢሉት ይሰበራልና። በእርግጥ ያልተለመደ ባሕርይ ኖሮአቸው በመልካም ቤተሰብ ላይ ችግር የሚያመጡና የሚያስቸግሩ ልጆች የሉም ለማለት አይቻልም። በቅዱስ መጽሐፍ እንኳን ጥቂት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። አሳም ቅዱሱን አቢልንና ነፍሰ ገዳዩን ቃየልን ወልዷል፤ ናህ የተቀደሱ ሴምንና ያፌትን እንዲሁም የአባቱን ዕርቃን በማየት ልጁኝንና የልጅ ልጁን ያስረገመ ካምን ወልዷል፤ ይስሐቅም የተቀደሰውን ያዕቆብንና ብኩርናውን ለምሥር ወጥ የለወጠ ኤሳውን ወልዷል። ወላጆች የልጆችን መንፈሳዊ ሕይወት ለማነፅ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረጉና የመጻንን መንገድ ለማሳየት የሚጠበቅባቸውን ጥረት ሁሉ አድርገው ልጆች ግን ከሥርዓት ውጭ ቢሆኑ ወላጆች ኃላፊነታቸውን በመወጣታቸው ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው መታወቅ አለበት።

ወላጅነት ኃላፊነትና ግዴታ ሞምር እንጂ ሥልጣን ብቻ አይደለም። ወላጅነት ልጆችን የመንከባከብ፣ የማፍቀርና መልካም ሥነምግባር ያላቸው ልጆችን ለማፍራት ጥረት የማድረግና መሥዋዕትነት ሞምር የመክፈል ኃላፊነትና ግዴታ ነው። እዚህ ላይ የነቢዩ ሳሙኤል እናት ነቢ

የእርሱን ደም ከአንተ አፈልጋለሁ» በማለት የሚያስጠነቅቅ ይመስላል። ወላጆችም ይህንኑ በአንክሮ ሊገነዘቡት ያስፈልጋል። ይህ እንግዲህ የልጆች የመታዘዝ ግደብ ብቻ ሳይሆን የወላጆችም የማዘዝ ሥልጣን ወሰን የተደረገለትና ከሕገ እግዚአብሔር ተቃርኖ የሚያቃርን በተፋልሶ የተሞላና ጭፍን እንዳይሆን ጭምር የሚያስተምር ምሥጢር የተካተተበት ነው።

ስለ ልጆቻቸው የወላጆች ኃላፊነት

ወላጆች ከልጆቻቸው ሊያገኙት ስለሚገባው አክብሮት ከእነዚሁ የሚጠበቅባቸው ግዴታ ወይም ኃላፊነት ደግሞ አለ። ስለሆነም ወላጆች የራሳቸውን ግዴታ ሳይወጡ ዘወትር መብታቸው ብቻ እንዲከበር መፈለግ የለባቸውም። ልጆችም ቢሆኑ ደግሞ ምንም እንኳ ወላጆቻቸው የሚገባቸውን ባያደርጉላቸውና ግዴታቸውን ባይወጡ ወላጆቻቸውን የማክበር ግዴታ አለባቸው። በተለይ በዚህ ርእስ ግን የወላጆችን ኃላፊነት እንመለከታለን። ከወላጆች ግዴታዎች መካከል፣ ልጆችን ፈሪሃ እግዚአብሔርን በማስተማር ማሳደግ፣ በጥሩ ሁኔታ መንከባከብ፣ ዐቅም በፈቀደ መጠን ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ ስለእነርሱ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ጥሩ አርአያነትን በማሳየት ማስተማርና ከሁሉም በላይ በፍቅርና በርኅራኄ ቢሥርዓትም እንዲመሩ ማድረግ ዋናዎቹ ናቸው።

ሀ. ልጆችን ፈሪሃ እግዚአብሔርን በማስተማር ማሳደግ፦ ወላጆች ልጆቻቸው ከርስትና በሚነሡበት ጊዜ እንደከርስትና እናትና አባት ሁሉ በቤተክርስቲያን አደባባይ ፊት ቆመው ልጆችን በሃይማኖትና በትድስና ለማሳደግ ቃል ይገባሉ። ስለዚህም ልጆቻቸውን በመልካም መንፈሳዊ ሥነምግባር አንፀው ለማሳደግ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ኃላፊነት አለባቸው።

አንዳንድ ወላጆች የልጆቻቸውን ሥጋዊ ፍላጎት ብቻ በማሟላት ስለመንፈሳዊ ሕይወታቸውና ስለዘለዓለማዊ ተስፋቸው የሚያስፈልጓቸውን ሁሉ ማሟላትን እንደ ትርፍ ነገር ቆጥረው በቸልታ ያልፏቸዋል። ወላጆች መጨነቅ የሚገባቸው ለልጆቻቸው ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ የአስተዳደግ ሥርዓት ነው። ከልጆች ሥርዓት አልበኝነት የተነሣ በቤተሰቡ ላይ የሚመጣው ችግር ሁሉ ቀድመው ወላጆች እንደቀላል በመቁጠር ጥንቃቄ ካላደረጉባቸው ነገሮች የሚመነጭ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋቸዋል። ያልዘሩትን ሊያጭዱ ያልበተኑትንም ሊሰበስቡ አይችሉምና።

ልጆችን ቀርፆና አስተካክሎ ለማሪምና ሥርዓት ለማስያዝ የሚቻልበትን ጊዜ በዋዛ ካሳለፉት በኋላ የማይቻለውን ነገር ለማድረግ መሞከር ደረቅ እንጨትን ለማቃናት እንደመሞከር ነው። በችግኝነቱ /በለጋነቱ/ ያልታረቀውን ዛፍ ከጠነከረ በኋላ እናቃናህ ቢሉት ይሰበራልና። በእርግጥ ያልተለመደ ባሕርይ ኖሮአቸው በመልካም ቤተሰብ ላይ ችግር የሚያመጡና የሚያስቸግሩ ልጆች የሉም ለማለት አይቻልም። በትዱስ መጽሐፍ እንኳን ጥቂት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። አዳም ቅዱሱን አቤልንና ነፍሰ ገዳዩን ቃየልን ወልዷል፤ ኖህ የተቀደሱ ሴምንና ያፌትን እንዲሁም የአባቱን ዕርቃን በማየት ልጁንና የልጅ ልጁን ያስረገመ ካምን ወልዷል፤ ይስሐቅም የተቀደሰውን ያዕቆብንና ብኩርናውን ለምሥር ወጥ የለወጠ ኤሳውን ወልዷል። ወላጆች የልጆችን መንፈሳዊ ሕይወት ለማነፅ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረጉና የመጻንን መንገድ ለማሳየት የሚጠበቅባቸውን ጥረት ሁሉ አድርገው ልጆች ግን ከሥርዓት ውጭ ቢሆኑ ወላጆች ኃላፊነታቸውን በመወጣታቸው ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው መታወቅ አለበት።

ወላጅነት ኃላፊነትና ግዴታ ጭምር እንጂ ሥልጣን ብቻ አይደለም። ወላጅነት ልጆችን የመንከባከብ፣ የማፍቀርና መልካም ሥነምግባር ያላቸው ልጆችን ለማፍራት ጥረት የማድረግና መሥዋዕትነት ጭምር የመክፈል ኃላፊነትና ግዴታ ነው። እዚህ ላይ የነቢዩ ሳሙኤል እናት ነቢ

ይት ሐናን ማስታወስ ይገባል። እርሷ ልጇን ፈሪሃ እግዚ አብሔርን እያስተማረች ከማሳደጓም በተጨማሪ ለቤተ መቅ ደስ አገልግሎት ሰጥታው ስታበቃ «ስለዚህ ሕፃን ጸለይሁ፣ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል፣ እኔም ደግሞ ለእግዚአ ብሔር ሰጥቼዋለሁ፣ ዕድሜውን ሁሉ ለእግ ዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል።» ብላለች። 1ሳሙ.1÷28። ሐዋ ርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ «በአንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አስባለሁ፣ ይኸም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበ ረባቸው÷ በአንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቻለሁ።» በማለት የጻፈለት መልእክት የጢሞቴዎስ እናት ልጇን በተገቢው ፈሪሃ እግዚአብሔር እንደ አሳደገችው የሚያረጋግጥ ነው። 2ጢሞ.1÷5።

ከዚህም በላይ ልጆቻቸውን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በፍቅረ እግዚአብሔር ያሳደጉትንና ለእግዚአብሔርም ክብር እንዲሰጡ ሲያበረታቱ የነበሩትን የቅዱሳን ሰማዕታት እና ቶች በአድናቆት ልናስታውሳቸው ይገባል። እነዚህ ቅዱሳት አንሥት ከእናትነት ፍቅርና ርኅራኄ የሚበልጠውን መንፈ ሳዊውን ሀብት ገንዘብ ያደረጉ ናቸው። ከእነዚህ ድንቅ እና ቶች መካከል አንዷ የነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ እናት ናት። ነቢዩ ሙሴ ከእናቱ ጋር ያሳለፋቸው የልጅነት ዘመናት ጥቂት ቢሆኑም የእናቱ መንፈሳዊ ተጽእኖ ግን በልጇ በሙሴ ሕይወት ዐቢይ ሥፍራ ነበረው። እናቱ በቅር ጫት ጠቅልላ በባሕር ላይ የጣለችውን ልጇን ሙሴን የተረ ከበችው በሕፃንነቱ ከፈርዖን ልጅ ነበር፣ ከእርሷም ጋር የቆየው ጥቂት እስኪያድግና መራመድ እስኪችል፣ እናቱም የነገረችውን መቀበል እስከሚችል ድረስ ነበር፣ ከዚያም ለፈር ዖን ሴት ልጅ ልጅዋ እንዲሆን መልሳ ሰጠችው እንጂ አብ ሯት አልኖረም። ይህች አስደናቂ እናት ታዲያ በእነዚህ ዓመ ታት ውስጥ ልጇን በመንፈሳዊ መርሖዎችና በሃይማኖት ትምህርት መሠረታዊ ዕውቀት እንዲኖረውና ሥር ሰድዶ እንዲጸና ለማድረግ ችላለች፣ የአባቶቹን ሃይማኖት በሚገባ እንዲያውቅና እንዳይረሳውም በልቡናው አትማበታለች። ከዚህ የተነሣ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ በዓርባ ዓመታት

በእምልኮ ጣዖት ተከቦ መኖሩ በሕፃንነቱ ከእናቱ ካገኘው መንፈሳዊ ትምህርተ ሃይማኖት ሊያናውጠው አልቻለም። ከእናቱ ጋር የቆየባቸው እነዚያ ጥቂት ዓመታት ለወደፊት መንፈሳዊ ማንነቱ ፈር ቀዳጅና መሠረታዊ ዕውቀት ያገኘባቸው ናቸውና ወላጆች ነበሩ።

በዘመናችን የሚገኙት እናቶችስ ለልጆቻቸው የሚያስተምሩአቸው ምንድን ነው? ልጆቻቸው አብረዋቸው በሚቆዩባቸው በአማካይ ከሃያ በማይበልጡ ዓመታት ለልጆቻቸው ምን ነገረው ምንስ አስተምረው ይሆን? እንግዲ ህ ልጆችን በሚፈልጉት መልካም መንገድ ቀርፀው ለማሳደግ የሚችሉበትን ጊዜ በከንቱ እንዳያባክኑት ያስፈልጋል። ከሙሴ እናትና ከሌሎችም ቀድመን ከጠቀሰናቸው ቅዱሳት አንስት ሁሉ መማርና ራሳቸውን ለመልካምና ለመንፈሳዊ ተጋድሎ ማዘጋጀት ከዘመናችን እናቶች የሚጠበቅ ነው።

ወላጆች ሁሉ ልጆቻቸው እንዲያከብሯቸው ከመፈ ለጋቸው በፊት ልጆቻቸው ስለዚህና ስለሌሎችም ትእዛዛተ እግዚአብሔር እንዲያውቁ ያደረጉት መሠረታዊ ጥረት ስለ መኖሩ ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። በቤታችን ውስጥ ለራ ሳችንና ለልጆቻችን የምናደርገው መንፈሳዊ ነገር ምንድን ነው? በግለት ራሳቸውን መመርመርም ይገባቸዋል። ልጆ ቻቸው ከሕፃንነት ጀምሮ ጸሎትን ይለምዱ ዘንድ ወይም ስለልጆቻቸው ይጸልዩ ዘንድ በቤታቸው የጸሎት መርሐ ግብር ይኖራቸው እንደሆነ ራሳቸውን በሚገባ ሊመረምሩት ያስፈልጋል። ጻድቁ ኢዮብ በብሉይ ኪዳን ዘመን «ምናልባት ልጆቼ በድለው÷ እግዚአብሔርንም በልባቸው ሰድበው ይሆናል» ብሎ ስለልጆቹ በቁጥራቸው ልክ የሚቃጠል መሥ ዋዕት ያቀርብ እንደነበር ማስታወስ አለባቸው። ኢዮ.1÷5።

እነዚህ ወላጆች የእግዚአብሔር ቃል «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው÷ በቤትህም ስትቀመጥ÷ በመንገድ ስትሄድ÷ ስትተኛም፣ ስትነሣም ተጫወተው÷» በማለት ኃላፊነታቸውን እንደነገራቸው ማስተዋል ይኖርባቸዋል። ዘዳ.6÷6-7። ስለዚህ ሕፃ ናትን በመንፈሳዊ እንክብካቤ ማሳደግ በተለይም ፍቅር፣

ሰላምና እርእያነት ያለው መተሳሰብ ባለበት የክርስቲያን ቤ ተሰብ ውስጥ እንዲያድጉ ማድረግ በጣም ጠቃሚ ነውና ፈ ሃን በማሳየት በፍቅረ እግዚአብሔር አንፀው ሊያሳ ድጓቸው ያስፈልጋል።

እንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ለመንፈሳዊ ነገር ከማ ነሞሃትና ከማበረታታት ይልቅ ለመንፈሳዊ ዕድገታቸውና እግዚአብሔርን በመፍራት ለሚኖሩት የተቀደሰ ሕይወት መሰናክል ሲሆኑ ይታያሉ። እነዚህም ወላጆች ልጆቻቸው ጸሎታቸውን እንዲያቋርጡ በማድረግ፣ መጾም እንዳይቀጥሉ በመከልከል፣ መንፈሳውያን ጉባኤዎችን እንዳይካፈሉ በማ ድረግና ዓለማዊና ሥጋዊ የሆነውን ተድላና ደስታ ባለመፈ ለጋቸው በመተቸትና በማናናቅ መንፈሳዊነታቸውን ሲፈ ታተኑአቸው ይስተዋላሉ። እነዚህን የመሰሉ ወላጆች ሁሉ የሚያስቡት እነዚህ ሥጋውያን ተድላን ደስታዎች በልጆቻ ቸው ላይ የሚታይ ጉዳት እስካላ፦ጡ ድረስ መልካም መሆናቸውን ነው። ቆይተውና ውለው አድረው ግን የአካል ጉልምስናንና የሰውነት ዕድገትን ተከትለው ሊያመጡ የሚ ችሉትን አደገኛ ሁኔታ ልብ አይሉትም። ስለዚህ ልጆችን ማሳደግ ከባድ ኃላፊነት እንደመሆኑ መጠን ጥንቃቄ የሚጠይቅ በጸሎትም የእግዚአብሔር ዕርዳታ ሊለመንበት የሚገባ መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ተገቢ ነው። በግድ የለሽነት ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ፣ ስለመንፈሳዊ ሕይ ወታቸው የማይጨነቁላቸውና የሚገባውን የማያደር ጉላቸው ወላጆች ስለልጆቻቸው ነፍሳት በኃላፊነት መጠ የቃቸው የማይቀር መሆኑንም ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ለ. ልጆችን በፍቅርና በመልካም አያያዝ

ማሳደግ፦ ወላጆች ልጆቻቸው ያከብሯቸው ዘንድ መን ፈሳዊውን ሕይወት ቢኖሩ መልካም ነው። ወላጆች የልጆ ቻቸውን አድናቆትና በእነርሱም መተማመናቸውን በመን ፈሳዊ ሕይወታቸውና በጥሩ ጠባያቸው እንጂ በአዛዥነት ሥልጣናቸው ለማግኘት መሞከር የለባቸውም። ወላጅነት በልጆች ላይ የሚፈጸም ፍጹም ሥልጣን ነው ብለው ማሰብም አይኖርባቸውም። ከዚህ ይልቅ ወላጅነት ፍቅርና

ርኅራኄ፣ ትዕግሥትና ደግነት የሞሉት፣ ልጆችም ሮጠው የሚጠጉበት መሸሸጊያና ሰፊ ልብ መሆኑን መገንዘብ አለ ባቸው። ወላጅነት እየቀጡ እየቆነጠጡ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ስለ ልጅ ራስን አሳልፎ መስጠትም ጭምር ነው። ከፍቅርና ርኅራኄ የተለየ ወላጅነት ሕይወት የሌለውና ምጡት መጠ ሪያ ብቻ ነው። ወላጅ አባት የራሱን ሥልጣንና የበላይነት በመመልከትና ይህን ለማረጋገጥ ልጅን ይህን አድርግ ያንን አታድርግ እያለ በማዘዝና ግራ በማጋባት የሚረካ ከሆነ እርሱ ከፉ አዛዥ እንጂ አባት ሊባል አይችልም።

ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡ ምልክቶች፣ ልጆችን ከማስጨነቅ መቆጠብን፣ አቅማቸው የሚችለውን ብቻ ማዘዝን፣ አስቸጋሪና አደገኛ ስለሆነው ነገር ማስረዳትን ሁሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው። ይህን ማድ ረግ የወላጁን ክብር የሚቀንስ ሳይሆን የልጆችን ታዛዥነት ልባዊና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሚያደርግ ነው። በልጅ እንደሚታየው ልጆች ከወላጆቻቸው ይልቅ ለመን ፈሳውያን አባቶቻቸውና እዛዦቻቸው በፈቃደኝነት ይታ ዘላሉ። ምክን ያቱም፣

ሀ/ መንፈሳውያን አዛዦቻቸውን ከወላጆቻቸው ይልቅ ያምኑባቸዋል፣ የእነርሱ ትእዛዝ የእግዚአብሔርን ቃል ይወክላልና፣

ለ/ መንፈሳውያን አዛዦቻቸው እንደ ባልንጀራ በፍቅር ያነጋግሯቸዋል እንጂ በኃይልና በሥልጣን አያስፈራሯቸውም፣

ሐ/ መንፈሳውያን አባቶች ያወያዩአቸዋል፣ ከማዘዛም አስቀድመው ሃሳባቸውን እንዲረዱትና የታዘቡትንም እንዲፈጽሙት ያደርጋሉ፣ ምን ጊዜም ቢሆን አሳማኝ ቃል ተፈጻሚ ነውና፣

መ/ እነዚህ መንፈሳውያን አባቶች /አዛዦች/ የልጆቻቸው ሃሳብ ይቀበሳሉ እነርሱንም ያከብሯቸዋል፣ ግብዣው ያን «ለአዳኒ ልጅህ ወንድም ሁነው» እንዲሉ።

በእነዚህ ምክንያቶች ልጆች ከወላጆቻቸው ይልቅ ለመንፈሳውያን አበው መታዘዝን ይመርጣሉ። ታዛዥነታቸው በፈቃደኝነትና በነፃነት ነው። ስለሆነም ወላጆች ልጆቻቸውን እንቆጣጠራለን ሲሉ በመንፈሳዊም ሆነ በሥነ ልቡናዊ የሕይወት ጉዞአቸው ላይ መሰናክል እንዳይሆኑባቸው ከመጠንቀቅ ጋራ በጥሞና ሊመክሯቸው ከሚገባ በቀር በማንኛውም ረገድ ሚና እንዳያበዙባቸውና እንዳያስጨንቋቸው ያስፈልጋል።

ወላጆችን የማክበር ወሰን

ሰው ሁሉ እስከተቻለው ድረስ ወላጆቹን ማፍቀርና ማክበር አለበት፤ ነገር ግን የእናቱና የአባቱን ፍቅር ከሌሎች የተቀደሱ ተግባራት ጋር የሚቃረን መሆን የለበትም። ይህም ወላጆች በልጆቻቸው የሚከበሩ ልጆችም ወላጆቻቸውን የሚያከብሩት በተወሰነ መጠንና ይህም መንፈሳዊ ልክ ያለው መሆኑን ያመለክታል ስለዚህም፤

ከፍቅረ እግዚአብሔር የበለጠ መሆን የለበትም፤

ለወላጆች የምንሰጠው ክብር ለእግዚአብሔር ከምንሰጠው ክብር የበለጠ መሆን የለበትም። ይህን አስመልክቶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም» ብሏል። ማቴ.10÷37።

ልጆች እናትና አባታቸውን መውደድ አለባቸው፤ ይህ ለወላጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ለእግዚአብሔር ካላቸው ፍቅር የበለጠ እንደሆነ ግን እግዚአብሔር አምላክ «ማንም ወደእኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን... የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ÷ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም።» በማለት የተናገረውን ቃል ልብ ሊሉት ያስፈልጋል። ሉቃ.14÷26። ይህ እንግዲህ ወላጆች ከፍቅረ እግዚአብሔር ሊለዩት የሞከሩ

እንደሆነ፣ ፈቃዳቸውና ሃሳባቸውም እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርንም ፈቃድ የሚቃረን የሆነ እንደሆነ፣ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብሎ ሌላውን ነገር ሁሉ፣ ለወላጆቹም ያለውን ፍቅር ጭምር መተው የሚገባ መሆኑን የሚያስተምር ነው። እግዚአብሔርም ደግሞ «እውነት እላችኋለሁ ስለእኔና ስለወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን የተወ፤ አሁን በዚህ ዘመን... መቶ እጥፍ... በሚመጣውም ዓለም የዘለዓለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።» በማለት የተናገረው ቃል ከፍቅረ እግዚአብሔር ሊበልጥ የሚገባው መኖር የሌለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ማር.10÷29–30። እግዚአብሔርን ማፍቀር ምንንም ማንንም ከማፍቀር በላይ መሆን አለበት። ወላጆችን ማፍቀርና ማክበርም እግዚአብሔርን በማፍቀርና በማክበር ውስጥ ሊጠቃለል ይገባል እንጂ ከፍቅረ እግዚአብሔር የበለጠ ሥፍራ ይዞ መገኘት የለበትም። ስለአባት ወይም እናት ፍቅር ብሎ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት አንዱን እንኳ መጣስና በክፉ ሥራ ከወላጆች ጋር መተባበርም አይገባም።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተመዘገቡና አብነት ሊሆኑን የሚችሉ ወጣቶችን እንደሚከተለው እንጠቅሳለን።

1. **አባቱን የገሠፀው ዮናታን፤–** ዮናታን ዳዊትን እንደሚወደውና ንጉሥ ሳኦል ደግሞ ከቅናት የተነሣ ዳዊትን ለመግደልና ለማጥፋት እንደተነሣሣበት የሚገልጠው ታሪክ በመጽሐፍ ተመዝግቧል። ይህን ሃሳቡን ከፍጻሜው ለማድረስም ከአንድ ጊዜ በላይ ሙከራዎች በሳኦል ተደርገዋል። ይሁን እንጂ የንጉሥ ሳኦል ልጅ የሆነው ዮናታን ዳዊትን ለማዳን የበኩሉን ጥረት ያደርግ ነበር። ዮናታን እውነት በእንደኛው በኩል መኖሩንና አባቱ ሳኦል ደግሞ ለእውነት ተቃራኒ ሆኖ መቆሙን በሚገባ ስለ አስተዋለ እርሱ ከእውነት ጋር ወግኖ... አባቱን ሳኦልን ተቃወመው። የአባቱንም ክፉ ዓላማ ለማሰናከል የተቻለውን ያህል' ብዙ ሙከራ አደረገ።

በአንዱ ቀን «ሳኦልም ለልጁ ለዮናታንና ለባሪያዎቹ ሁሉ ዳዊትን ይገድሉት ዘንድ ነገራቸው» ነገር ግን ዮናታን በአባቱ ዓላማና በሃሳቡም ባለመስማማት ትእዛዙን ተቃወመው፤ ለአባቱ ለሳኦልም «እርሱ አልበደለህምና÷ ሥራውም ለአንተ እጅግ መልካም ሆኖአልና ንጉሡ ባሪያውን ዳዊትን አይበድለው፤... በከንቱ ዳዊትን በመግደልህ ስለምን በንጹሕ ደም ላይ ትበድላለህ? ብሎ ስለዳዊት መልካም ተናገረ።» 1ሳሙ.19÷1–7። በዚህም ዮናታን የአባቱን ኃጢአትና በዳዊት ላይም የፈጸመውን በደል አንዲሁም የዳዊትን መልካምነት ያለምንም ፍርሃት በመናገሩ አባቱ ክፉ ዓላማውን እንዲሠርዝና ሃሳቡን እንዲለውጥ አደረገው፤ ዳዊትም ከመገደል ድኖ በሕይወት ኖረ።

ዮናታን አባቱ ሳኦል ዳዊትን እንደጠላው እያወቀ እርሱ ግን ዳዊትን ለማዳን የሚቻለውን ሁሉ ሊያደርግለት ከዳዊት ጋር በምሥጢር ተስማሙ። የሳኦል ቁጣ ግን በዮናታን ላይ ነደደ «አንተ የጠማማ ሴት ልጅ÷ የእሴይን ልጅ ለአንተ ማፈሪያ እንደመረጥህ እኔ አላውቅምን? የእሴይም ልጅ በምድር ላይ በሕይወት በሚኖርበት ዘመን ሁሉ አንተና መንግሥትህ አትጸኑም፤ አሁንም የሞት ልጅ ነውና ልከህ አስመጣልኝ» በማለትም ተናገረው። 1ሳሙ.20÷30። ዮናታን ግን አባቱን አጠንክሮ ተቃወመው እንጂ ብስጭቱ እንዲበርድ በሃሳቡ አልተስማማለትም። ከዚህም የተነሣ በመጽሐፍ «ዮናታንም ለአባቱ ለሳኦል፦ /ዳዊት/ ስለምን ይሞታል? ያደረገውስ ምንድር ነው? ብሎ መለሰለት። ሳኦልም /ዮናታንን/ ሊወጋው ጦሩን ወረወረበት፤ ዮናታንም አባቱ ዳዊትን ፈጽሞ ሊገድለው እንደፈቀደ ዐወቀ።... ዮናታን ስለ ዳዊት ፈጽሞ አዝኖአልና እጅግ ተቆጥቶ ከሸደቃው ተነሣ በመባቻውም በሁለተኛው ቀን ግብር አልበላም።» በማለት ስለእርሱ ተጽፏል። 1ሳሙ.20÷32–34።

ዮናታንም የሆነውን ሁሉ ይነግረው ዘንድ ወደዳዊት ሄደ፤ በተገናኙም ጊዜ «እየተላቀሱ እርስ በርሳቸው ተሳሳሙ÷ ይልቁንም ዳዊት እጅግ አለቀሰ። ዮናታንም ዳዊትን፦ በደኅና ሂድ አለው።» በሕይወትም እንዲኖር አዳነው። 1ሳሙ.20÷41–42።

ጻድቁ ዮናታን የአባቱን ስሕተት በመጠቆም ከክፉ ሥራውም እንዲመለስ በመናገር ተቃወመው እንጂ ቁጣውንና ብስጭቱን በይበልጥም አባትህንና እናትህን አክብር ተብሏል በማለት በጭፍን ሃሳቡ በንጹሑ ዳዊት ላይ ክፉ በመሥራት ከአባቱ ጋር አልተባበረም። የዳዊትን ሕይወት ለማዳንም ከእውነት ወገን ተሰልፎ የተቻለውን ሁሉ አደረገ። በዚህ ድርጊቱ የአባቱን ትእዛዝና ለአባቱም ያለውን ፍቅርና አክብሮት እግዚአብሔር ከሚደሰትበት እውነት ከሆነው ነገር ሳያስበልጥ ለፍትረ እግዚአብሔር ለእውነተኛውም ነገር መሰለፍ የሚገባ መሆኑን አስተምሮናል። አባቱን ማስደሰት ከፉ ትእዛዙን ከመቀበል ይልቅ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ለእውነትም መቆምን በሚገባ መርጧልና።

2.ንጉሥ ሰሎሞንና እናቱ፦ በንጉሥ ሰሎሞንና በእናቱ መካከል የሆነው ነገር ተጨማሪ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ንጉሡ እናቱ ወደእርሱ በመጣች ጊዜ በታላቅ ክብር ተቀበላት፤ ሊገናኛት በተነሣም ጊዜ ከእንገቱ ዝቅ በማለት እጅ ከነሣት በኋላ በቀኙ አስቀመጣት፤ ከዚያም እናቲቱ ንጉሡን «አንዲት ታናሽ ልመና አለምንሻለው አታሳፍረኝ» አለችው። ንጉሡም «እናቴ ሆይ አላሳፍርሽምና ለምኚ» አላት። የለመነችው ልመና ግን ከኦባ እግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ነበር። እርሱም ሱናማዊቱ አቢሳ ለወንድሙ ለአዶንያስ እንድትዳርለት ነበር። አቢሳ ግን ለአባታቸው ለዳዊት እንደሚስት ትቆጠር ነበር።

ንጉሡ ሰሎሞን ምንም እንኳን እናቱን እጅግ የሚያፈቅራትና የሚያከብራት ቢሆን አዶንያስ አቢሳን እንዲያገባ ያቀረበችለትን ልመና ግን ሊያከብርላትና ፈቃዷንም ሊፈጽምላት አልቻለም። ይህንን ማድረጉ በእምቢተኝነት ወይም እናቱን ስለማያከብር አይደለም፤ የእናቱን ፈቃድ ፈጽሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ከመጣስ ከእግዚአብሔር ሕግ የሚቃረነውን የእናቱን ትእዛዝ መቃወም ተገቢ መሆኑን በማወቁ ነው። እናም ንጉሡ ሰሎሞን «አዶንያስ ይህን ቃል በሕይወቱ ላይ ስለመናገሩ እንደሆነ ...ሕያው እግዚአብሔርን! ዛሬ አዶንያስ ፈጽሞ ይገደላል» በማለት መሰነ። 1ነገ. 2÷18–25። ንጉሡ ሰሎሞን ስለሥጋዊ ነገር የለመነችው

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተጋፈጨ የእናቱን ልመና በመፈጸም እግዚአብሔርን ከማሳዘን ይልቅ ስለሕገ እግዚአብሔር መከበር ሲል የእናቱን ትእዛዝ አለመፈጸምን መረጠ።

3.ቅድስት ዴሚና:- በክሃዲው የዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የቦሮሱስና የዛፋራን ገዥ የነበረው ማርቆስ የዚህች የቅድስት ዴሚና አባት ነበረ። በንጉሡ ትእዛዝ ሀገረ ገዥው ማርቆስ... ለጣዖታት የዕጣን መሥዋዕት ያቀረብ ነበር። ወደሀገሩም በተመለሰ ጊዜ ያደረገውን ሁሉ ያወቀችው ልጁ ዴሚና በብስጭት ወደአባቷ በመሄድ ስለአደረገው ነገር ከተቸችው በኋላ ከእንግዲህም አባቷ አለመሆኑን እንዲሁም ለጣዖት ከመሠዋቱ የተነሣ መሞቱን ብትሰማ እጅግ የተሻለ ደስተኛ ትሆን እንደነበር ነገረችው።

ከዚህ ጠንካራ ትችት የተነሣ የአባቷ ጎሊና ተመልሶ ከራሱ ልብ ጋር መሆን ሲጀምር ወደ ዲዮቅልጥያኖስ በመሄድ የክርስቶስን ዘለዓለማዊ ንጉሥነትና አምላክነት በመመስከር በሰማዕትነት ለማረፍና ከቅዱሳን አንድነት ለመደመር በቅቷል። ዴሚና አባቷን መተቸቷ አባትህንና እና ትህን አክብር የሚለውን ትእዛዝ መጣስ አይደለም የአባቷን ነፍስ ከዘለዓለም ፍርድ የማዳን ሐዋርያዊ ሥራ ነው እንጂ።

ስለዚህ ወላጆችን ማክበር የሚያዝዙትን ትእዛዝ ከሕግ እግዚአብሔር ጋር በማነፃፀር የእግዚአብሔርን ሕግ እስካልተቃረነ ድረስ ብቻ መሆን ይኖርበታል። ወላጆችም ቢሆኑ ልጆቻቸው የሚፈተኑበትንና የሚጨነቁበትን ከሕግ እግዚአብሔር ጋር የተጣላ ትእዛዝ ማዘዝ የለባቸውም፣ ይህ ትእዛዝም ባለመፈጸሙ በልጆቻቸው ሊያዝኑ የማይገባ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።

ሌሎች የአባትነት ዓይነቶች

ከወላጅ አባት ባልተናነሰ ሁኔታ ክብር የሚገባቸው የአባትነት ደረጃዎች አሉ፤ ለምሳሌም ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን።

ቤተ ዘመድ:- አባትህንና እናትህን አክብር የሚለው ትእዛዝ ወላጆችን ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ቤተ ዘመዶችን ማለትም አያቶችን፣ አጎቶችን፣ አክስቶችን፣ የእንጀራ እናትና አባቶችን፣ ወዘተ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። በቤተዘመዱ ውስጥ በዕድሜ ታላቅ የሆኑና በማዕረግና በደረጃ የሚበልጡ ሁሉ እንደእናትና አባት ሊከበሩ ይገባል። ይህም መከበር የሚገባቸውን ታላላቅ ወንድሞችና እኅቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። ይህንን በሚገባ በማጤን በቤተዘመድ ውስጥ ላሉት ሁሉ የአባትነትና የእናትነት እንዲሁም የታላትነት ክብር መስጠት የተገባ መሆኑን ተረድቶ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሕጉን እያስታወሱ አክብሮትን መስጠት ጠቃሚና በረከት የሚያስገኝ ነው።1ጢሞ.5÷1-2።

መንፈሳዊ አባትነት:- በተፈጥሮ እንዳሉን ወላጆቻችንና ቤተዘመዶቻችን ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሳዊት እናት ቤተ ክርስቲያንን፣ መንፈሳውያን አባቶች ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሊቃውንትን፣ ሊቃነ ጳጳሳትን፣ ቀሳውስትንና ቅዱሳንን ሁሉ ሰጥቶናል።

ርእሰ አበው የተባለ አብርሃም የሁላችንም አባት መባሉ በሥጋ ስለወለደን ሳይሆን ስለመንፈሳዊ አባትነቱ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ሳይገረዙ ለሚያምኑ /አሕዛብ ለነበሩ/ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው» ካለ በኋላ በመቀጠል ምንም እንኳ እኛ በሥጋ ልጆቹ ባንሆንም «ከሕግ ብቻ ሳይሆን ከአብርሃም እምነት ደግሞ ለሆነ ለዘሩ ሁሉ የተሰፋው ቃል እንዲጸና... የሁላችን አባት ነው» ብሏል። ሮሜ.4÷11። ሮሜ.7÷16-17። ነቢዩ ኤልያስ ባረገ ጊዜ ደቀመዝሙሩ ኤልሳዕ «አባቴ ሆይ! የእሥራኤል ሠረገላና ፈረሰኞች» እያለ መጮኹና ንጉሡም ነቢዩ ኤልሳዕን በተመሳሳይ ሁኔታ መጥራቱ በሥጋ ስለተወለዱ አይደለም ስለመንፈሳዊ አባትነት ብለው እንጂ። ኤልያስም ሆነ ኤልሳዕ ሁለቱም ደናግል ነበሩና። 1ነገ.2÷12። 1ነገ.13÷14።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልሞና በላከው መልእክት «በእሥራቴ ስለወለድኩት ስለልጄ ስለኦናሲሞስ እለምንኻለሁ» ማለቱ ስለመንፈሳዊ አባትነቱ ሲናገር ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም እርሱ ድንግል ነውና። ፊልሞ.11። በሌላም ሥፍራ «በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ» በማለት የተናገረው ጢሞቴዎስን በሥጋ ስለ ወለደው ሳይሆን በትምህርት ስለወለደውና መንፈሳዊ አባቱ ስለሆነ ነው። 1ጢሞ.1÷2። 2ጢሞ.1÷2። ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ደግሞ «ልጆቼ ሆይ በእናንተ እስኪሳል ድረስ ዳግመኛ ስለእናንተ ምጥ ይዞኛል» ማለቱ፣ ለቆሮጠንቶስ ሰዎችም «እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥፃችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልጽፍም። በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የላችሁም፣ እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና። ስለዚህ የም ወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ» በማለት መናገሩ መንፈሳዊ አባትነቱን የሚያመለክት ነው። ገላ.4÷19። 1ቆሮ.4÷14-17።

ድንግሉ ሐዋርያ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም «ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ» ደግሞም «ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመስማት ይልቅ የሚበልጥ ደስታ የለኝም» ማለቱ ስለመንፈሳዊ አባትነቱ የተናገረው መሆኑ ግልጥ ነው። 1ዮሐ.2÷1። 3ዮሐ.ቁ 4።

እንዲሁ ሁሉ የሥርዓት መጽሐፋችን ጲድስቅልያ በምዕራፍ ስድስት «ከእግዚአብሔር በታች አባትህ ሊቀጳጳሱ ነው» በማለት ሕግ ሠርቷል። ቤተክርስቲያንም ደግሞ በቅዳሴዋ ሰዓት ቅዱሳንን «ቅዱሳን አባቶቻችን» ትላቸዋለች። «በተጨማሪም ስለሙታን የሞቱትን አባቶቻችንን፣ አባቶቻችንን ቅዱሳንንና ሊቃነ ጳጳሳትን፣ አባቶቻ ችንን ጳጳሳትን፣ አባቶቻችንን ቀሳውስትን፣ አባቶቻችንን መነኮሳትን» በማለት ትጸልያለች። ቤተክርስቲያን አባትነትን ከማክበሯ የተነሣ የበላይ መሪዎቿን ሁሉ አባ፣ አቡነ እያለች ትጠራቸዋለች፡ አባት ማለት ነው። ለዚህ ምክንያቱም በመጠሪያው ውስጥ የሚገለጠው ፍቅር የመንፈሳዊ አገልግሎቱና የመንፈሳዊ መሪነቱ መሠረት ስለሆነ ነው።

መንፈሳዊ አባትነት ከሥልጣን በጣም የበለጠና ሰፊ ትርጉም አለው። በዲድስቅልያ በተጻፈው መሠረት ፓትርያርኩ፣ ሊቀጳጳሱና ጳጳሱ የበላይ፣ አዛዥና ጠባቂ /እረኛ/ መሆኑን የምንቀበለው ቢሆን እንኳ የሚያሸንፈን ይህ ሥልጣኑ ሳይሆን ፓትርያርክ አባታችን፣ ሊቀጳጳስ አባታችን እያልን በምንጠራው ጊዜ ከመንፈሳዊ አባትነቱ የሚመነጨው ጥልቅ መንፈሳዊ ፍቅርና የምንሰጠው አክብሮት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በእኛ ላይ ጠባቂ እንዲሆን የሰጠን መንፈሳዊ አባት ነው ብለን ስለምናምን ጭምር ነው።

ጳጳሱ አባትም፣ አለቃም፣ አዛዥም፣ የበላይም በመሆኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ባለመርሳት ሜጨቶጅን በክንፎቿ ሥር እንደምትሰበስብ ዶሮ ልጆቹን የመሰብሰብ ግዴታውን ያስታወሰ እንደሆነ ከማንኛውም ሥልጣን በላይ ከልጆቹ ጋር በሚያስተሳሥር ጽኑ መንፈሳዊ ፍቅር የሚኖር መሆኑን ማወቅ አለበት። የሚታዘዙለት ሁሉ ከመንፈሳዊ አባትነቱ የተነሣ እንጂ ሥልጣኑን ፈርተው እንደታዘዙለት ማሰብም የለበትም። ከፍቅር የተነሣም በብዙ መልክ ታማኝነትንና ታዛዥነትን ከልጆቹ ሊያገኝ ይችላል። ይህን አስመልክቶ ቅዱስ መጽሐፍ «ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን ብትገዛላቸውም÷ መልሰህም በገርነት ብትናገራቸው÷ በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል» ይላል። 1ነገ. 12÷7። ስለዚህም የካህኑ አባትነት የማዕረግ ወይም የሥልጣን መጠሪያ ብቻ ሳይሆን ከፍቅር፣ ከእንክብካቤና ከደግነት የመነጨና መንፈሳዊ መሆን አለበት፣ በመንፈሳዊነቱም የሁሉ አዛዥ ለመሆን ይችላል።

እውነተኛ ካህን ወደ አገልግሎት ትምህርት ቤት ከመግባቱ በፊት ወደ ፍቅር ት/ቤት መግባትና ፍቅርን መማር አለበት። የፍቅር ሰው የሆነ እንደሆነ ሕዝቡ ሁሉ ሥልጣኑን ሳይመለከቱ ከፍቅሩ የተነሣ በጥሩ ስሜት ልጆቹ ይሆናሉ፣ ምንም እንኳን ጸጋው ውሱን ቢሆን ሁልጊዜ ለፍቅር ቅድሚያ ይሰጠዋልና። ካህኑ እውነተኛ አባትና አለቃ እንዲሆን የልጆቹን ልቡና በፍቅር ዋጋ የሚገዛና

የሥልጣንና የታላቅነትን ስሜት ከሚያመጡበት ዓለማዊ ሁኔታዎች መራቅ አለበት። ዓላማውም ነፍሳትን ለእግዚአብሔር መንግሥት መማረክ እንጂ ሰዎችን ለእርሱ ማስገዛትና ማዘዝ አለመሆኑን ማወቅ ይገባዋል። ምናልባትም ካህኑ «ስለራሴ ክብር አይደለም ስለክህነት ክብር ነው እንጂ» ቢል እንኳ ከክርስቶስ እንዲማር እንነግረዋለን። እርሱ ክርስቶስ እንኳ ዝቅ ብሎ የደቀመዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ክብሩ አልተቀነሰም፣ ይልቅ ትሕትናውን ሰናይ የበለጠ ወደድነው አከበርነው እንጂ።

እውነተኛ አባት የሆነ ካህን በልጆቹ ተገዥነትና ታዛዥነት እንዲሁም በሚያጋጥማቸው መንፈሳዊ ድካም የተነሣ ስለሚጨነቅላቸው ከቶውኑ እንቅልፍ አይወስደውም። መታዘዝ ቀላል ነገር ነው፣ ከዚህ የሚበልጠው ግን ፍጹም ፍቅርና አክብሮትን ማግኘት ነው። አፍቃሪ ካህንም ጌታችን ያደርግ እንደነበረው ሁሉ ልጆቹ ትእዛዙን እንዲያስተውሉ ያስጠናቸዋል፣ ያስተምራቸዋል፣ ያሳምናቸዋል እንጂ ሥልጣን አለኝ ብሎ አያስጨንቃቸውም። በሥልጣኑ በመጠቀም ለአጭር ጊዜ ማስተካከል ይችል ይሆናል፣ በፍቅርና በአክብሮት አልታዘዙለትምና። ትእዛዙ ከፍቅርና ከልባዊ አክብሮት የመነጨ መንፈሳዊ የሆነ እንደሆነ ውጤቱ አዛዡን የሚያረካ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ለልጆቹም የነፍስ መዳኛ ይሆናል። ማዕረጋቸው ትንሽ ወይም ዝቅተኛ ቢሆንም በልጆቻቸው ልቡና ሲታወቁ የሚኖሩት ክብር የእግዚአብሔርን ፍቅር ገንዘብ በማድረጋቸው በምእመናን ዘንድ የታወቁትና የተመሰከረላቸው ናቸው።

የካህኑ አገልግሎት መፈቀርን /መወደድን/ ካጣ ዋናውን ድጋፍ አጥቷል። ልጆቹ ልቡናቸውን ከፍተው ሊሰሙትና እርሱም የሚያስፈልጋቸውን መንፈሳዊ ነገር ሊያውቅላቸው የሚችለው ከእነርሱ ጋር የሚያስተሳሥረው ፍቅር ያለ እንደሆነ ብቻ ነው። ከዚህ ፍቅርም የተነሣ የሚመክራቸውንና የሚሰጣቸውን አስተያየቶች፣ ልጆቻቸው የሚነግራቸውን መፍትሔዎች በፈቃደኝነት ይጠቀሙባቸዋል። ይህም አገልግሎቱን ቀላልና ተግባራዊ ያደርገዋል። ከዚህም የተነሣ የካህኑ አባታቸው ተግሣፅ፣ ምክርና ቅጣትም ቢሆን ለመቀበል ታዛዦች ይሆናሉ። ግንኙነታቸው በእውነተኛ

የአባትና ልጅ ፍቅር ላይ የተመሠረተ ከሆነ ልጆቹ ከእርሱ ጋር በግልጽ ለመነጋገር፣ እርሱንም ለመተቸት ወይም ለማመስገን ቢሆን፣ እንዲሁም ሰይጣን ስለሚያመጣባቸው ፈተናና ችግርም ሁሉ ሳያፍሩት ሊነግሩት ይችላሉ። ምክን ያቱም ልበ ሰፊና በሚነግሩት ነገር ሁሉ የማይሰላቹና በትዕግሥት ሰምቶ ተገቢውን የሚመክር መሆኑን ያውቃሉና። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል» ብሏልና። 1ዮሐ.4+8።

ይህ ፍቅር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዬ እመሰክርላችኋለሁ» በማለት የተናገረለትም የመንፈሳውያን ልጆቹ ፍቅር ነው። ገላ.4+15። በፍልስጥኤም በነበረው ታላቅ የአሸናፊት ስነ ሥርዓት ላይ የተገለጠው ሁኔታ ይህን መንፈሳዊና አባታዊ ፍቅር የሚያስረዳ ነበር። መጽሐፍም «ሁሉም እጅግ አለቀሱ፥ ጳውሎስንም አንገቱን አቅፈው ይስሙት ነበር፤ ይልቁንም፦ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን አታዩም ስላላቸው ነገር እጅግ አዘኑ።» ሲል መዝግቦታል። የሐዋ.20+38። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች ስለፍቅር የጻፈላቸው መልእክትም እጅግ ጥልቅ ነበር፤ «በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ እነርሱም ስለነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥... ከአስያ ለክርስቶስ በኩራት ለሆነው ለምወደው ለኤጴኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።... በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ... ለምወደው ለስንጣክን ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ በጌታ እጅግ ለደከመች ለተወደደች ለጠርሲዳ ሰላምታ አቅርቡልኝ።» ብሏል። ሮሜ.16+3–16።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ሁሉተኛውን መልእክቱን «እኔ ሽማግሌው በእውነት ለምወዳቸውና እኔ ብቻ ሳልሆን እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ደግሞ ለሚወዷቸው ለተመረጠች እመቤትና ለልጆቿ» በማለት መጀመሩና በሦስተኛው መልእክቱ ደግሞ «ሽማግሌው... በእውነት እኔ ለምወደው ለጋይዮስ፥ ወዳጅ ሆይ ነፍስህ እንደሚከናወን በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።» ግለቱ የሚያመለክተው የመንፈሳውያን አበውን የአባትነት ፍቅር ነው። 2ዮሐ. 1+2። 3ዮሐ.1–3።

አባቶቻችን ሐዋርያት ይህን የመሰለውን መንፈሳውያን ልጆችን የመውደድ ፍቅር የተማሩት ከመምህራቸውና ከአምላካቸው ከመድኃኔዓለም ክርስቶስ ነው። እርሱ በዚህ ዓለም የወደዳቸውን እስከ መጨረሻው የወደደ ደግ አባት ነውና። ዮሐ.13÷1። ከዚህ ፍቅሩም የተነሣ ራሱን ስለ ወደዳቸው አሳልፎ ሰጥቷልና። ከትንሣኤው በኋላም ሃይ ማኖታቸውን ያጸና ዘንድ ለሚወዳቸው ራሱን ገልጧልና። እርሱ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ሕፃናት ሁሉ እንዲንጫጩና የገሊላዋንም ሴት እንድትከተለው ያደረጋት ይህ የአባትነት ፍቅር ነው። ማቴ.27÷55። የኢየሩሳሌምን ደናግልም ዋይ ዋይ እንዲሉና ሙሾ እንዲደረድሩ ያደረጋቸው ይኸው ፍቅር ነው። ሉቃ.23÷27። ይህን መሰሉ መንፈሳውያን አበውንና መንፈሳውያን ልጆቻቸው ምእመናንን የሚያስ ውንና መንፈሳውያን ልጆቻቸው ምእመናንን የሚያስ ተሣሥርና የሚያዋሕድ እውነተኛ ፍቅር ለክህነት አገልግሎት የማይናወጽ የመሠረት ድንጋይ ነው።

እንግዲህ «አባት» የሚለውን ቃል ስናወሳ ማንኛውንም ዓይነት የአባትነት ፍቅር ማውሳታችን ሞሆኑ ይታወቅ ዘንድ ይገባል። በፍቅር ያልተረጋገጠው አባትነት ሕይወት አልባ የሆነ መጠሪያና ትርጉም የሌለው ማዕረግ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ሰዎችም ከመንፈሳውያን አባቶቻቸው ተስፋ የሚያደርጉት እውነተኛ ፍቅርንና አባታዊ ርኅራኄን ነው። ስለሆነም ከመስጠት ይልቅ የሚጠይቅ፣ ከመምከር ይልቅ የሚረግም፣ ከመጠገን ይልቅ የሚያቆስል አባት አጽሙን ሊመረምርና ርኅራኄን፣ ደግነትን፣ ጥንቃቄንና ራስን አሳልፎ መስጠት የሆነውን ፍቅር ገንዘብ ለማድረግ መጣር ይኖ ርበታል።

ቅዱሳን አበውን ማክበር

በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ጸንተውና ተጠምደው ሳሉ ዐረፍተ ዘመን ለገታቸውና በክብር ላረፉት ቅዱሳን አበውም ክብር ይገባቸዋል። ቅዱሳን ስንልም ስለሃይ ማኖታቸው በመጋደል የተሰዉ አበው ሰማዕታትን፣ በየበረሃው በእት ወስነው ሲጸልዩ የወደቁ ቅዱሳንን፣ በገዳማት ተወስነው በንጽሕና በቅድስና ያለፉ አበው መነኮሳትንና ቀላውስትንም፣ በሕግ ተወስነው ለቅድስና የበቁትንም ሁሉ ማለታችን ነው።

እነዚህን ቅዱሳን የምናከብራቸው በስማቸው ጽላት ቀርጸን፣ ቤተክርስቲያን አንጸን፣ ገዳም ገድመን፣ በዓሉቻቸውን በማክበር፣ በመዝሙራችንና በጸሎታችን ስማቸውን በማንሣት፣ ገድላቸውን በማንበብ፣ ሥዕሎቻቸውንም በቤተ ክርስቲያን በማኖርና ታሪካቸውን ለምእመናን በማስተማር ነው። የልጆቻችንን፣ የማኅበሮቻችንን ስም በእነርሱ በመሰየም መታሰቢያቸውን በማድረግና በአማላጅነታቸው በመማፀን ወዘተ ልናከብራቸውም እንችላለን። በሕይወተ ሥጋ በነበሩ ጊዜ ያስተማሩትን ትምህርታቸውን በመከተልና በማስፋፋት ያሳለፉትን የተጋድሎ ሕይወት አብነት በማድረግና የሕይወት ጎዳናቸውን ተከትሉ በመኖር ልናከብራቸውም እንችላለን። በዚህ ብንጸና በረከታቸው ረድኤታቸውና አማላጅነታቸው ከእኛ ጋር ይሆናል።

በዕድሜ ታላቆችን ማክበር

ከቤተሰብ መካከል በዕድሜ ታላቅነታቸው ሊከበሩ የሚገባቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ግንም ሰው ቢሆን በዕድሜ ከእርሱ የሚበልጡትን ማክበር አለበት። በመጽሐፈ ኢዮብ የተመዘገበው ታሪክ ለዚህ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ኤልፋዝ፣ በልዳዶስና ሶፋር የተባሉት ሦስት የኢዮብ ጓደኞች ከጻድቁ ኢዮብ ጋር ያደረጉት ክርክር ሃያ ስምንት ምዕራፎችን ያጠቃለለ ነው። አራተኛው የኢዮብ ወዳጅ ኤሊሁ ግን የሁሉም ታናሽ ስለነበረ አንዲት ቃል እንኳ ሳይናገር በጸጥታ ክርክራቸውን ያዳምጥ ነበር። ክርክራቸው ውጤት አልባ እንደሆነ ባየ ጊዜ ግን እንዲህ አለ «እኔ በዕድሜ ታናሽ ነኝ፥ እናንተ ግን ሽማግሌዎች ናችሁ፤ ስለዚህም ሰጋሁ፤ ዕውቀቴን እገል ጥላችሁ ዘንድም ፈራሁ።» ኢዮ.32÷6–7። ኤሊሁ ታናናሽ በዕድሜ ታላቆቻቸው ባሉበት ከመናገር ይልቅ ስለታላቆቻቸው ክብር ዝም ማለት እንደሚገባቸው ያስተምራል። ለታናሹ የሚገባው ተቀምጦ በጸጥታ ማድመጥ፣ ማስተዋልና መማር ነውና። ከመነኮሳት ሕይወትም ፍጹሙ፣ ማዕከላዊው ባሉበት ወጣኒው ይናገር ዘንድ አይፈቀድለትም፤ ሕጋቸው

ትሕትናና አክብሮት ነውና። በዚህ ረገድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለልጁ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ «ሽማግሌ የሆነውን አትገሥፀው÷ እርሱን ግን እንደአባት÷ ጎበዞችን እንደወንድሞች÷ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናቶችም፣ ቆነ ጃጅቱን እንደ እኅቶች ባፍጹም ንጹሕና ለምናቸው።» በማ ለት መመሪያ መስጠት በዕድሜ ታላላቅ የሆኑ መከበር እንደሚገባቸው የሚያስተምር ነው። 1ጢሞ.5÷1–2። ከዚ ህም ሌላ ለሮም ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «በጌታ ሆኖ ለታ ወቀ ለሩፎንን፣ ለእኔና ለእርሱም እናት ሰላምታ አቅርቡልኝ» ሲል የሩፎንን እናት እንደ እናት በማክበር መሆኑ ግልጥ ነው። ሮሜ.16÷13። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ቅዱስ ማር ቆስን ልጄ ማለቱ በዕድሜ ስለሚበልጠውና ታላቁ ስለሆነ ነው፣ «..ልጄም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል።» 1ጴጥ.5÷13።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሠርጉ ቤት ስለሆነው ነገር ሲናገር «ማንም ለሠርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፣ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና» ማለቱ ታላላቆችን ማክበርን የሚያስተምርና በታላላቆች መካከል በተቀመጥን ጊዜ ሁሉ ልንዘነጋው የማ ይገባ መመሪያ ነው። ሉቃ.14÷10። መጽሐፍም ደግሞ «በሽ በታሙ ፊት ተነሣ÷ ሽማግሌውንም አክብር» በማለት ያዝዛል። ዘሌ.19÷32።

በዕድሜ ታላቁ ከሆነ ሰው ጋር የሚጓዝ ማንም ቢሆን ታላቅየው የተሸከመውን ተቀብሎ ማገዝ ይገባዋል፣ ይህም የአክብሮት ሌላው ገጽታ ነውና። ከታላላቆቹ ጋር የሚነ ጋገርም ሰው ሁል ጊዜ የሚበልጠውን ክብር ለታላቁ በመ ስጠትና እርሱንም በማስቀደም ትሕትና በተሞላበት ሁኔታ አክብሮቱን መግለጥ አለበት።

ከዚህም ሌላ ከዕድሜ መስፈርት ውጭ የበለጠ መንፈሳዊ ጸጋና ዕውቀት ላላቸው መንፈሳውያን አባቶች ክብርን መስጠት ተገቢ ነው። ስለዕድሜአቸው ብቻ ሳይሆን ስለመንፈሳዊ ጸጋቸውም ልናከብራቸው ይገባል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ቢሆን በዕድሜ ታላላቆች ሆነው የሚያጠፉና እግዚአብሔርንም ሰውንም የሚያሳዝኑ /ለምሳሌ 1ነገ. 2÷6–9። መዝ.118÷100። መክ.4÷13።/ የመናፍቆችን

ያህል በዕድሜ ወጣቶች ሆነው መንፈሳዊ ጸጋቸው ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦች ሊኖሩ ይችላሉና፤ ለምሳሌም ዮሴፍ፣ ዳንኤል፣ ቅዱስ አትናቴዎስ ወዘተ። እነዚህ ወጣቶች በነበሩ በት ዘመን ስለመንፈሳዊ ጸጋቸው ክብር የተገባቸው ነበሩ።

ባለ ማዕረጉን ማክበር

በማዕረግና በከፍተኛ የሥልጣን ኃላፊነት ላይ የተሾመውም ሰው ክብር ይገባዋል። ቅዱስ መጽሐፍም ስለዚ ህ በግልጽ የሚያስተምረን ነገር አለ። ደጉና ጻድቁ ኢዮብ ከ ማዕረጉና ከሀብቱ የተነሣ «ለድህው አባት ነበርኩ» አለ። ኢ ዮ.29÷16። ጻድቁ ቅዱስ ዮሴፍ በፈርዖን ቤት ላይ አዛዥ ሆኖ በተሾመ ጊዜ «እግዚአብሔር ለፈርዖን አባት አደረገኝ» ማለቱ ስለማዕረጉ ከፍተኛነት ሲሆን ከዚህም የተነሣ ክብር የተገባው መሆኑን ሲናገር ነው። ዘፍ.45÷8። ሶርያዊው ንዕ ማን ከለምፁ ይድን ዘንድ በዮርዳኖስ ውኃ ለመጠመቅ ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ባሮቹ «አባት ሆይ÷ ነቢዩ ታላቅ ነገርስ እንኳ ቢነግርህ ኖሮ ባደረግኸው ነበር» ያሉት ስለወለዳቸው ሳይሆን ከማዕረጉ የተነሣ ስላለው ክብር ነው። 2ነገ.5÷13። እንዲሁ ዳዊትም የሚያሳድደውን ንጉሥ ሳኦልን «ደግሞም÷ አባቴ ሆይ÷ የልብስህ ዘርፍ በእጄ እንዳለ ተመልከተህ ዕወቅ» ሲል አባት ሆይ ያለው በማዕረግም በዕ ድሜም የሚበልጥ ስለሆነ ነው። 1ሳሙ.24÷11።

እንግዲህ ይህ አራተኛው ትእዛዝ በጣም ሰፊ ትርጉም ያለውና ብዙ ምሥጢራትን የሚያጠቃልል እን ደመሆኑ ወላጅ አባትንና እናትን ማክበር ብቻ ማለት እንዳልሆነ ሁላችንም በአንክሮ ልናጤነው ይገባል። የአባ ቶችና የእናቶችን፣ በዚህ ደረጃም ሊከበሩ የሚገባቸውን ሁሉ በረከት ለማግኘትና በእግዚአብሔርም ዘንድ ተወዳጅ ለመ ሆን ትሕትናን ገንዘብ አድርጎ ክብርን ለሚገባው ክብርን መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህ ዕድል እንድንበቃ እግዚአብሔር ይርዳን።

ክፍል ስድስት

አምስተኛው ትእዛዝ

«አትግደል»

ዘጸ.20÷13።

«አትግደል» የሚለው ትእዛዝ ወንጀለኞችንና ነፍሰ ገዳዮችን ብቻ የሚመለከትና ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ያልሆነ የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በዚህ ርእስ ሥር የዚህን ትእዛዝ አስፈላጊነት ና ጠቀሜታ በማሳየት በሕይወታችን ላይ ያለውን ተጽ እኖ፣ ምን ያህል እየተላለፍነው ወይም እያከበርነው መሆኑን ለመዳሰስ እንሞክራለን። ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ጥያቄ እናነሣለን፣ እግዚአብሔር መግደል ፈጽሞ ከልክሉ ይሆን ወይም እንደኃጢአት ወይም እንደወንጀል የማይቆጠር የተፈቀደ መግደል ይኖር ይሆን?

የተፈቀደ መግደል

እግዚአብሔር አምላክ አትግደል የሚለውን ትእ ዛዝ ሕግ አድርጎ የሰጠ ሲሆን በአንዳንድ ሥፍራዎች ደግሞ መግደል የፈቀደበት ሁኔታ መኖሩን እናስተውላለን። መፍ ቀድ ብቻ ሳይሆን መግደልን አስፈላጊ ያደረገባቸው አን ዳንድ ሥፍራዎችም አሉ። በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ ምናገኘው ኃጢአት የሠራ ሰው እንዲገደል ሕግ ተሠርቷል።

ትእዛዛትን የተላለፈውን በሞት መቅጣት

ለምሳሌ «አታመንዝር» የሚለውን ትእዛዝ የተላለፈ ሰው በሞት ይቀጣ ነበር። በመጽሐፍ «አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽሞ ይገደሉ።» ይላልና። ዘሌ.20÷10-16። በዝሙት ያገኟትን ሴት በጌታ ፊት በከሰሷት ጊዜ ጻሐፍት ፈሪሳውያን የጠቀሱት ይህን ሕግ ነበር። ዮሐ.8÷5። ከዚህም ሌላ ማንም ይህን ትእዛዝ ተላልፎ ሰውን ቢገድል በተን ኮልም በባልንጀራው ላይ ቢሸምቅበትና ቢገድለው ፈጽሞ ይገደል የሚል ትእዛዝ አለ። ዘጸ.21÷12-14። በቀጥታ የገደለ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ለአንዱ ሰው መሞት ተጠ ያቂ የሚሆን መገደል እንደነበረበት በሕግ ተደንግጎ ነበር፤ «በሬው ግን አስቀድሞ ተዋጊ ቢሆን÷ ሰዎችም ለባለቤቱ ቢመ ሠክሩለት ባይጠብቀውም÷ ወንድንም ወይም ሴትን ቢገድል÷ በሬው ይወገር፣ ባለቤቱ ደግሞ ይገደል።» ተብሎ ነበርና። ዘጸ.21÷29።

በብሉይ ኪዳን እንደተጻፈ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚጠራ እንዲገደል ሕግ ይናገራል፤ ከትእዛዛት አንዱን ተላልፏልና። ዘሌ.24÷16። የመጀመሪያውን ትእዛዝ በመተላለፍም ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ያመለከ ለማያችንም የሰዋ ሁሉ እንዲገደል እንዲጠሩም እግዚአብሔር አዝዞአል። የበኣልን ካህናት ነቢዩ ኤልያስ ያስገደላቸው በዚሁ ትእዛዝ መሠረት ነበር። ዘጸ.22÷20። 1ነገ.18÷40።

በሌላ ሥፍራ ደግሞ አረመኔዎች፣ ምትሐተኞ ችና ጠንቋዮች የሐሰት ነቢያትና ሐሰተኛ ሕልም አላሚ ዎች እንዲገደሉ ሕግ መኖሩን መጻሕፍት ያረጋግጣሉ። ዘሌ.20÷27። ዘኍ.22÷18። ዘዳ.13÷15።ዘዳ.13÷5።

ከፍ ብለን ከጠቀስናቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደተረዳነው አመፀኞችንና ሕግ ተላላፊዎችን መግደል የተ ፈቀደ በመሆኑ እንደኃጢአት ተቆጥሮ ወይም «አትግደል»

የሚለውን ትእዛዝ እንደመሻር ተወስዶ የሚያስቀጣ አይደ ለም። በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» በማለት ሲናገር የጠቀሰው ሕግ በዘ ጸአት «አትግደል» የተባለውንና በዘሌዋውያን ደግሞ «ሰውን እስኪሞት ድረስ የሚመታ ፈጽሞ ይገደል» የሚ ለውን ነው። ዘጸ.29+13። ዘሌ.24+17። ከዚህም በላይ መግ ደል ብቻ ሳይሆን በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ወንድ ሙንም የሚሰድብ የሸንጎ፣ የገሃነምም ፍርድ የሚገባው መሆኑን በመግለጥ ይህን ሕግ እንደአጠበቀው እንመለከታለን። ማቴ.5+21–23።

የትእዛዙ ጠቃሚነት

በዚህ ምድር በምንኖርበት ዘመን በምንሠራው በማን ኛውም ኃጢአት በምንም መንገድ ይሁን በምን አንድን ወይም ብዙ ሰዎችን እንጎዳለን። የገደልነው እንደሆነ ግን እናጠፋዋለን። በምድር ላይ የመኖር ዕድሉም ፈጽሞ ይወድ ማል። መግደል የሰውን ሕይወት በእጅጉ ይጎዳል። የሰው ሕይወት የራሱ ባለመሆኑና የሰውን መድረሻና ፍጻሜ ሊወስነው የሚችለው ፈጣሪው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ መግደል በእግዚአብሔር ሥልጣን ገብቶ በደል መፈጸምም ጭምር ነውና ያስጠይቃል። የሰውን ሕይወት ሊቆጣጠርና ከጠፋም በኋላ ሊተካው የሚችል ማንም የለም፣ እግዚአብሔርም እርሱ እስከወሰነው ዘመን ብቻ እንዲኖር ነው የፈጠረው። የሕይወትና የሞት ቁልፍ በእግዚአብሔር እጅ ብቻ የተያዘ ነው።

በመግደል የሚፈጸም ኃጢአትም ሊጠገን የማይችል በመሆኑ ከባድ ነው። ሰው በሌላ ሰው ላይ ስለሠራው በደል ሊክስ ይችላል፣ የሰደበውን ሰው ክብር ለመግለጥ ይቅርታ ሊጠይቀው ይችላል፣ የነጠቀውን ንብረትም ሊመልስለት ይችላል። መግደል ግን ከዚህ የተለየ ነው፣ ማንም የገደለውን ሰው ሕያው ሊያደርግ አይችልምና። ንስሐ

ያልገባውን ሰው መግደል ደግሞ የመግደልን ኃጢአት የበለጠ ያከብደዋል፣ምክንያቱም ሟቹ በንስሐ ስለዘለዓለ ማዊ ሕይወቱ የነበረውን ተስፋ ፈጽሞ የሚያጨልምበት ስለ ሆነ ነው። የሞተው ሰው ሞቱ በሥጋም በነፍስም በመሆኑ ሰ ማ ፈንታውም ወደ ሲኦል መጣል ነውና የገዳዩ ኃጢአት እጅግ ከባድ ይሆናል። ይህን እንግዲህ መግደል ምን ያህል የከፋና የሚያስጠይቅ ከባድ በደል መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

ነፍሰ ገዳይ ሰው የራሱም ገዳይ ነው፣ የሠራው ኃጢ አት ራሱንም ቢሆን ወደ ሞትና ወደሲኦል የሚያደርሰው ነውና። ይህ ሁሉ የተነገረው፣ መግደልም እጅግ ከባድ ነው ያልነው ለንስሐ ያልበቁ በኃጢአት ዓለም ወይም በክፉ ሥራ የሚኖሩ እግዚአብሔርም በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት የመዳን ተስፋ ያላቸውን ሰዎች በተመለከተ ነው። ንስሐ ገብቶ የሚጠራበትን ቀን የሚጠብቀውንና የዘለዓለም ሕይ ወት ተስፋው የተረጋገጠለትን ሰው የገደለውስ የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም።

ማንም ይሁን ማን ሰውን መግደል ኃጢአት ነው። በተለይም በሕይወቱ ቅድስና፣ በአገልግሎቱ፣ በተሰጠው ማንኛውም ጸጋ ቢሆን ወገኖቹን ሊረዳ፣ የተቻለውንም ለጎረቤተሰቡ ሊያበረክት የሚችለውን ጠቃሚ ሰው መግደል የእግዚአብሔርን ሕንፃ ከማፍረስ በተጨማሪ በዚያ ሰው ለሚጠቀመው ሕዝብ ጉዳት ነው። የበደሉ መጠንና የኃጢ አቱ ክብደትም በሚቹ ጠቃሚነትና አስፈላጊነት መጠን የሚመዘን ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ነቢ ያትን የምትገድል ወደእርሷ የተላኩትንም የምትወግር» በማ ለት ኢየሩሳሌምን የወቀሳት በእግዚአብሔርም በሕዝብም ዘንድ ከፍተኛ ጠቃሚ አገልግሎት ሊያበረክቱ የሚችሉት ቅዱሳን በክፋት ልጆች በመገደላቸው ነው። ማቴ.23+37።

በሌላም ቃል «ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራ ክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ» በማለት የተናገረው በግፍ ስለተገደሉት ደጋግ አበው ነው። ማቴ.23+35። በዚህ

ምንባብ ውስጥ «የጻድቅ ሁሉ ደም» የሚለው ሐረግ የደጋግ ሰዎችን ደም ማፍሰስና መግደል ከባድ ኃጢአት መሆኑንና የሚያስከትለውንም የተጠያቂነት አደጋ የሚያመለክት ነው።

ቃየን ወንድሙን አቤልን በገደለው ጊዜ እግዚአብሔር ቃየንን «የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደእኔ ይጮኻል።» ማለቱ የቃየን በደል ከባድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ዘፍ.4÷10። አቤል ስለመገደሉ የተናገረው ነገር አልነበረም፣ ቢሆንም ሰማያዊ ፍርድ ይህን ይሻል፣ እግዚአብሔር ደም የሚያፈሱትን ይበቀላልና። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ የተበቀለው ስለአቤል ብቻ አይደለም፣ በጭካኔ ወንድሙን የገደለው ቃየን እግዚአብሔርን «እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ፣... የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል።» ባለው ጊዜ እግዚአብሔርም መልስ «እንግዲህ ቃየንን የገደለ ሁለ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል» በማለት ቃየንን ያገኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገበት። ዘፍ.4÷14–15። ይህን ያደረገበት ምክንያት ሰው ሁሉ ነፍሰ ገዳዩን ለመበቀል እጁን እንዳያነሣ ነው፣ በቀል የእርሱ የልዑል እግዚአብሔር ነውና። ነፍሰ ገዳዩን በመግደል መልካም ያደረገ እንዳይመስለውም ነው። የተገደለው ሰው ደግሞ ደግም ሆነ ክፉ ነፍሰ ገዳዩን ከተጠያቂነት የማ ያድነው ከመሆኑም በላይ መግደል ደግሞ ከባድ ኃጢአት ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ደም የሚያፈሱትን በራሱ መንገድ ሳይበቀላቸው አይቀርም።ሰዎቹ ደጋግ እንኳ ቢሆኑ ሰው የገደሉ ከሆነ እግዚአብሔር በሆነው ነገር ይበቀላ ቸዋል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ቅዱስ ዳዊት ነው። እርሱ ከመንፈሳዊ ቅናት በመነሣት ቤተ መቅደሱን ለማነፅ በወሰነ ጊዜ እግዚአብሔር የነገረውን እንመልከት። «ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ፦ እጅግ ደም አፍስሰኻል፣ ታላቅም ሰልፍ አድርገሃል፣ በፊቴ በም ድር ላይ ብዙ ደም አፍስሰሃልና ለስሜ ቤት አትሠራም።» አለኝ ሲል ተናግሮአል። 1ዜና.22÷8። እግዚአብሔር ዳዊ ትን ደግ መሆኑን ቢያውቅ እንኳ በእጁ ስለፈሰሰው እጅግ

ብዙ ደም ይህን ክብር ሊሰጠው አልፈቀድም፣ በዚህም ተበቀለው፣ ቀጣው። ቸሩ እግዚአብሔር በሚወደው ዳዊት እንዲህ አደረገ። እርሱ እግዚአብሔር ስለዳዊት «ዳዊትን ፈተንኩት፣ ልቡንም እንደልቤ ሆኖ አገኘሁት» በማለት ተና ግሯል። ልጁ ሰሎሞንም ሲጸልይ «ስለባሪያህ ስለዳዊት ብለህ ፊትህን ከእኔ አትመልስ» ብሏል፣ ፈጣሪው እግዚአብሔርም «ስለባሪያዬ ስለዳዊት» እያለ ብዙ መልካም ነገሮችን ለሰው ልጆች አድርጓል። ዳዊት እንደዚህ ደግና ጻድቅ ሲሆን ባፈሰሰው ደም የተነሣ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንዳይሠራ ተከለከለ። ቤተመቅደሱንም ከእርሱ አብራክ የተገኘውና በዘመኑ ሰላምና ጸጥታ የሆነለት ንጉሡ ሰሎሞን ሠርቶታል።

እግዚአብሔር «በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመ ልሳለሁ» በማለት የተናገረውን ቃሉን የሚያጥፍ አይደለም። ስለቃሉ ክብር ብለው በመታገሥ መከራን ተቀብለው በሰ ማዕትነት ስለሞቱት እንኳን ሳይቀር እግዚአብሔር በፍርድ ወንበር ተቀምጦ የሚበቀልላቸውና እውነተኛውን ፍርድ የሚ ሰጥ መሆኑን በቃል ኪዳን ገልጦአል። ራእ.6÷10። ስለዚህ እጅን ከደም አካልንም ከመግደል መከልከል ተገቢ ነው።

የአግዳደል ዓይነቶች

«አትግደል» የሚለው ትእዛዝ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው። እግዚአብሔር አምላክ አትግደል በማለት ሲያዝዝ ማንም ሰው ራሱንም ሆነ ሌላውን ሰው መግደል የማይችል መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህም በማንኛውም ምክንያት የትኛውንም ዓይነት ግድያ የሚከለክል ትእዛዝ ነው። ኃጢ አት በማሰብ፣ በመናገርና በማድረግ እንደሚፈጸምና ሁሉም ኃጢአት እንደሆነ ሁሉ ግድያም የሚጀመረው በማሰብ በመፈለግና በመመኘት ነው። ሰማያዊው ሕግ ከምድራዊው፣ መንፈሳዊው ሕግ ከሥጋዊው/የወንጀል/ ሕግ የሰፋ በመሆኑ ለግድያ የሚሰጠውም ትርጉም ጥልቅና ሰፊ ነው። በዚህ ዓ ለም በወንጀል ሕግ የግድያ ሙከራና ግድያው የተፈጸመ እንደሆነ ብቻ የሚያስቀጣ ሲሆን ሌላውን ሰው ለመግደል

የሚያስበውና የሚመኘው ግን ምኞቱና ሃሳቡ በተግባር እስካልተገለጠ ድረስ የሚያስቀጣ አይደለም። እግዚአብሔር ግን ስለክፉ ምኞቱና ሃሳቡ በዚህ ሰው ይፈርድበታል እርሱ ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ነውና።

በአንዱም ሆነ በሌላው ሁኔታ የተለያዩ የአገዳደል ዓይነቶች አሉ። አካልን መግደል፣ መንፈስን መግደል፣ ሥጋን መግደል፣ ነፍስን መግደል፣ በቀጥታ መግደል፣ በተዘዋዋሪ መግደል፣ በግል መግደል፣ ተባባሪ ሆኖ መግደል ወዘተ ሁሉም መግደል ነውና ሕግን በመተላለፍ የሚያስቀጣ ነው።

ጦርነት መግደልን በሚከለክለው በአምስተኛው ትእዛዝ ይጠቃለላልን? የሚሉ ጠያቂዎች መኖራቸው አይቀርም። ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ በሁለት መልክ የሚታይ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር አንድ ሰው እንዲይገደል ከከለከለ የብዙዎችን መገደልም የማይፈቅድ መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህ አንፃር የብዙዎች ነፍሳት እንዲጠፉ የጥፋት መሣሪያዎችን በማምረት እነዚህን መሣሪያዎች ለመሞከሪያ ወይም አምባገነንነታቸውን ለማሳየት ጦርነት በመክፈት በሌሎች ላይ ዘምቶ የብዙዎቹን ሕይወት መቅጠፍ የአምስተኛው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው። የዚህ ዓይነቱ ጦርነት የፈጠረውን የሕዝቡን ሰላማዊ ሕይወት በሚፈልገው በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነው። በእግዚአብሔር ሕግ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ መንግሥታትም ይህንን የሚከለክል ስምምነት መፈረሙ በግፍ በሚነሡ ጦርነቶች የሚጠፋው የሰው ሕይወት እንዲተርፍ ሰላማዊ ኑሮ አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር ሰው ራሱን ከሚደርስበት ማንኛውም አጥፊ አደጋ እንዲከላከል ፈቃዱ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን በመሰለ ሁኔታ እሥራኤልን እንዴት ከፍልስጥኤማውያን ጥቃት ራሳቸውን መከላከል እንደሚገባቸው ያስተምር እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ መዝግቦታል። ከዚህ አንፃር ራስን ከአብሪተኞች ጦርነት መከላከል ከል ሕዝቡን ከጥፋት መከላከል በመሆኑ ይህ የአምስተኛው ትእዛዝ ተቃራኒ አይደለም። ገዳዮችን መከላከል ተገቢ ነውና እግዚአብሔርም ይህን የመሰለውን እርምጃ የወሰዱ ብዙ ሰዎችን እንዳልተቃወማቸው መጽሐፍ ምስክር ነው።

ዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተራቀቀ ሁኔታ በአገልግሎት ላይ የዋሉበት መሆኑ በሁላችን ዘንድ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ይህን የጥበብ ውጤት ለጥፋት መጠቀም በተለይም የእግዚአብሔርን ሕንፃ ለማፍረስ መጠቀም ከፍተኛ ኃጢአት ነው። ለምሳሌ በአንዳንድ የሕክምና ተቋማት ወሊድን ለመቆጣጠር በሚል ሰበብ የወንዴውን የዘር ምንጭ ከሰውነቱ በማስወገድ የሚደረግ ቀዶ ጥገና ተተኪ የሰው ዘር እንዳይፈጠር የተደረገ የረቀቀ የግድያ ወንጀል በመሆኑ አትግደል ለሚለው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው።

በሌላም በኩል ያልተወለደውንና ወደፊትም በሕይወት የመኖር እድል ያለውን ፅንስ የማናሩም ሆነ የመግደሉ ሥልጣን የእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ በውርጃ እንዲወጣ ማድረግና ማስወገድ ራሱ የአምስተኛው ትእዛዝ ተቃራኒና የግድያ ወንጀልም ነው። በሕገ እግዚአብሔር አትግደል ከመባሉም ሌላ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግም የዚህን ተግባር ፈጻሚዎች ወንጀለኞች የሚያደርጋቸው ድንጋጌ አለ። «በእግዚአብሔር ፈቃድ ከተፀነሰ በኋላ ሕልውናው በሰው ባልተፈለገ ፅንስ ላይ በሚደረግ የማስወረድ ወንጀል የተሳተፉት ሁሉ በምድራዊ ሕግም በወንጀል በእግዚአብሔር ሕግም በኃጢአት ተጠያቂዎች ናቸው። ውርጃን በማንኛውም መንገድ የሚያግዙ ሰዎች የግድያ ወንጀል ተባባሪ መሆናቸውን ማወቅና ከዚህ ኃጢአት መከልከል ይኖርባቸዋል።

ሰው እስከ አሁን ከገለጥናቸው ተግባራዊ የግድያ ዓይነቶች ሌላ በሃሳቡም ሌላውን ሊገድል ይችላል። አንድን ሰው ለመግደል ወይም በሌሎች ተገድሉ ለማየት ይፈልግና ይህንኑ ያውጠነጥን ይሆናል። በሰውየው መሞት የሚያገኘውን ዕርካታ /ደስታ/ እያሰበ ይደሰት ይሆናል። በዚህ ሁሉ ድርጊቱ በፍላጎቱና በሃሳቡ ያንን ሰው ገድሎታልና ተጠያቂ ነው። የአንድን ሰው መሞት ማሰብና መመኘት ከፍቅር የተነሣ ለባልንጀራ በጎ ነገር ከማሰብ ጋር የሚቃረን ነውና በልቡና ውስጥ ተደብቆ የሚሠራ ኃጢአት ነው። ይህን መሰሉ ጥላቻም የግድያ ዓይነት ነው። ሐዋርያው

ቅዱስ ዮሐንስ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው» በማለት ማስተማሩ ለዚሁ ነው። 1ዮሐ.3÷15። ከዚህ በመ ነሣት አትግደል የሚለው ትእዛዝ በተግባር የገደሉትን እንጂ እኛን አይመለከተንም የሚሉ ሰዎች ይኖሩ አይ ችልም።

ከዚህ ሌላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራ ስብከቱ «ለቀደሙት፦ አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፣ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ÷ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል» በማለት መቆጣትን ከግድያ ጋር አስተካክሎ ተናግሮአል። ማቴ.5÷21–22። በመሆኑም ሰው የሚወደውን ወንድሙን ሊገድለው ቀርቶ ክፉም ሊያስ ብበት አይገባውም የፍቅር ሕግ ይከለክለዋልና።

በሌላ በኩልም ተዘዋዋሪ የግ ድያ ዓይነቶች አሉ። እነዚህ በቀጥታ ለጊዜው ለሞት የሚያ ደ ሳይሆኑ ቀስ በቀስ ግን ወደሞት የሚያደርሱ ናቸው። ለጊዜው መግደል በጥይት ወይም በዱላ መትቶ ወይም በጩቤ ወግቶ ወይም በድንጋይ ወግሮ ብቻ አይደሉም። ሰውን የሚያሳዝን ንግግር፣ አስጸያፊ ጠባይ፣ ሰውን መናቅና መስደብም ሁሉ የሰውን ኅሊና የሚያቆስሉና ዕረፍትና ሰላም የሚነሡ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ቀስ በቀስ የሚጎዱ እንጂ በአንድ ጊዜ ለሞት የሚያበቁ አይደለም። ከጊዜ በኋላም ሲገድሉ የሞቱን ምክንያት ሰዎች አያውቁትም እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል። ከዚህ ሰው ግድያ ውስጥ በማበሳጨትም ሆነ በመሳደብ ወዘተ የተሳተፉ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሥራቸውን ያገኛሉ በተዘዋዋሪ የግድያው ተሳታፊዎች ናቸውና።

በመጽሐፍም «እነሆ÷ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራ ተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፣ የአጫጆችም÷ ድምፅ ወደጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል።» እንዳለው ለቀጠ ረው ሠራተኛ ከአገልግሎቱ ጋር የሚመጣጠን ዋጋ የማይከ ፍለው አሠሪ በተዘዋዋሪ ሠራተኛውን ወደሞት እየነዳው መሆኑን ማወቅ አለበት። ያዕ.5÷4። ሊያገኝ የሚገባውን የደመወዝ ጭማሪና ዕድገት መከልከል ሠራተኛውን በተዘ ዋዋሪ መግደል ነው። መጽሐፍ «የሞያተኛው ዋጋ እስከ ነገ ድረስ በአንተ ዘንድ አይደርብህ።» «ድሀና ችግረኛ የሆነውን

ምንደኛ÷ ከወንድሞችህ ወይም በምድርህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚቀመጡት መጻተኞች ቢሆን÷ አታስጨንቀው። ድሀ ነውና÷ ነፍሱም ጠንክራ ትፈልገዋለችና ወደ እግዚ አብሔር እንዳይጮኽብህ፣ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ደመወዙን ፀሐይ ሳይገባ በቀኑ ስጠው።» በማለት ይመክራ ል። ዘሌ.19÷13። ዘዳ.24÷14። ያለበቂ ምክንያት ሠራ ተኛን ከሥራ ማባረርም በእርሱና በቤተሰቡ ሁሉ ላይ በተዘዋዋሪ የግድያ ወንጀል መፈጸም ነው።

በበሽታ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት ሞት ጥላውን አጥልቶበት ዕርዳታ ለሚሻ ሰው ተገቢውን ዕርዳታ አለ ማድረግ በተዘዋዋሪ መንገድ መግደል ነው። መጽሐፍም ይህን በተመለከተ «የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው÷ እርሱ ራሱ ይጮኻል፣ አይሰማለትም።» በማለት ያስገነዝባል። ምሳ.21÷13። መልካም ማድረግ ሲቻል አለ ማድረግ የሚያስጠይቅ መሆኑን ሲገልጽ «በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው» ይላል። ያዕ.4÷17። በዓለ ማችንም የሰዎችን ዕርዳታ ሲሹ በሞት አፋፍ ሆነው የሚያጣጥሩ እጅግ ብዙ ነፍሳት እንዳሉ ይታወቃል። እነዚ ህን ድሆች በተቻለ መጠን አለመርዳት በተዘዋዋሪ መግደል መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። በግቢው ደጃፍ ወድቆ ፍርፋሪ ለለመነው አለዓዛር ያልራራለት ነዌ የሚገባውን ቅጣት ከመቀበል አላመለጠም። ሉቃ.16÷19። በመንገድ የወደ ቀውን በሽተኛ መርዳት ሲገባቸው ጥለውት የሄዱት ካህኑና ሌዋዊው ሰው የየራሳቸውን ምክንያት ያቀርቡ ይሆናል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ምክንያታቸውን አይቀበላቸውም። እርሱ «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም» በ ማለት ምሕረት በሌለበትና ክፉት በሞላበት ልብ የምታ ቀርቡልኝ መሥዋዕት አያስደስተኝም ብሏልና። ማቴ.9÷13። እግዚአብሔር ግን ደጉን ሣምራዊ ልኮ ታድጎታል። ካህኑና ሌዋዊው ግን በተዘዋዋሪ ለሞት ጥለውት በመሄዳቸው አም ስተኛውን ትእዛዝ በመጣስ ከመጠየቅ አይድኑም። ይኸውም የሥጋን ግድያ በተመለከተ ነው።

ነፍስን መግደል

ነፍስን መግደል በተለያዩ መንገዶች ይፈጸማል። ነፍስ ከእግዚአብሔር እንድትለይ ማድረግ መግደል ነው። ይኸውም ነፍስ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተለይታ በገቢረ ኃጢአት ጸንታ እንድትኖር ማድረግ ነው። ስለዚህም ለኃጢአት የተገዛች ነፍስ ምጡት ናት። እግዚአብሔር በሰሎሞን አድሮ ኃጢአት «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፤ እርስ ዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው» በማለት የተናገረው የዚህ ማረጋገጫ ነው። ምሳ.7÷26።

ጌታችን ከአይሁድ ጋር ሲነጋገር «እናንተ ከአባ ታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታ ደርጉ ትወዳላችሁ» በማለት ሰይጣናዊ ስለሆነውና ከእግዚ አብሔር በመለየትም ገዳይ ስለሆነው ክፋታቸው ተና ገሮ አቸዋል። ሰይጣንም ሰውን በተለመደው መንገድ በሥጋ እንደገደለ አልሰማንም፤ ነገር ግን «እርሱ ከመጀመሪያው ጀምሮ ነፍስ ገዳይ ነበረ» የሚለው ሀረፍተ ነገር ሰይጣን የሰውን ነፍስ እንደሚገድልና ለዘለዓለም በገሃነም እንዲጣል የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል። ዮሐ.8÷44።

«ፊደል ይገድላል» የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት የእግዚአብሔርን ቃል፣ ትእዛዛቱንም በጥሬው እየቆነጻጸሉ በተሳሳተ ትርጉም ሰዎችን በማይገባ መንገድ መምራትና መንፈሳዊ ሕይወትን ወይም ነፍስን ከእግዚ አብሔርና ስለእርሱ ከሚነገረው የቀና ትምህርት በመለየት መግደል መሆኑን የሚያመለክት ነው። 2ቆሮ.3÷6። ሰው እውነተኛና ትክክለኛውንም እምነት ከመረዳት የራቀና ከሃይማኖት የወጣ እንደሆነ መንፈሳዊ ሞት /ሞተ ነፍስ/ ደርሶበታል ማለት ነው። በዚህ መልክ ነፍሳትን እያጠመዱ ከእግዚአብሔር ሕግ በመለየት የኃጢአት ባሪያ ለማድረግ ቀንና ሌሊት የሚደክሙ ዓለማውያን በየዕለቱ ስንት ነፍሳትን እየገደሉ ይውሉ ይሆን? የዚህ ወንጀልና ኃጢአት ተሳታፊና ተባባሪ ከመሆን ይሰውረን።

ከዚህም ሌላ የተሳሳተ ትምህርተ ሃይማኖት በማስተ ማር የሰው መንፈሳዊ ሕይወት በኑፋቄ የሚመርዙና በተዛባ መንገድ የሚመሩ ሰዎችም ነፍሰ ገዳዮች ናቸው። በቀጥተኛ ሃይማኖት ጸንቶ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ የዘለዓለምን ሕይ ወት እንዳይወርስ እንቅፋት ሆነዋልና። ይህም በሥጋ ከመግደል የከፋ ነው። በሥጋው የሞተ በነፍሱ የመዳን ዕድል ሊኖረው ይችላል፤ በነፍሱ የሞተ ግን የሚጠብቀው የዘለዓለም መከራ ነው። በዚህ አንባር በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትን ምእመናን ከእውነተኛው የሃይማኖት መንገድ በማስወጣት ለመናፍቅነት የዳረጉአቸው እነአርዮስ፣ መቅዶንዬስ፣ ንስጥ ሮስ፣ ሉተር፣ የይሖዋ ምስክሮች መሥራች ቻርልስ ራስል ወዘተ እና የእነዚህ ሁሉ ኑፋቄ የወለዳቸው መናፍቃንና ሌሎችም ሁሉ በነፍሰ ገዳይነት ከሚጠየቁት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፤ የግድያውን መንገድ የከፈቱት እነርሱ ናቸው።

ስለዚህ ነገረ ሃይማኖትን የሚያስተምር ሁሉ ቀደምት አበው ካስተማሩት የተለየ እንዳይናገር መጠንቀቅ ይገባዋል። መጽሐፍም «አባቶችህ የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ።» ብሏልና። ምሳ.22÷28። ሃይማኖት በሰው ፍልስፍና ያልተመሠረተ በሰው በጎ ፈቃድም የማይጸና ሰማያዊ ነውና በምድራዊ ዕውቀት እንደተፈለገ የሚነዳ አይደለም። እንደተገኘ የሚዘነጠልም አይደለምና እነዚያ «እንደፈለግን እንተረጉማለን» የሚሉ ሁሉ ለብዙዎች ስሕተት ምክንያት በመሆናቸው በነፍሳት መንፈሳዊ ሞት ከመጠየቅ አያመ ልጡም።

የንስሐ ልጆቻቸው የሆኑ ምእመናንን ኑዛዜ ብቁ በተሰጣቸው የክህነት ሥልጣን ባለመጠቀምና መንፈሳዊ ትምህርትን ባለማስተማር ልጆቻቸውን ለጠላት ዲያብሎስና ለመናፍቃን አሳልፈው የሚሰጡ ካህናትም ከነፍሰ ገዳይ የሚመደቡ ናቸው። እነዚህን ካህናት እግዚአብሔር «ለእሥራ ኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፣ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው። እኔ ኃጢአተኛውን፡- በእርግጥ ትሞታለህ ባልኩት ጊዜ፡ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ ለኃጢ

አተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ::» በማለት ስለኃላፊነታቸው አስገንዝቦአቸዋል:: ሕዝ.3÷16–18::

በመቀጠልም ኃጢአት ምን ያህል የከፋ መሆኑን ሲገልጥ «ነገር ግን አንተ ኃጢአተኛውን ብታስጠነቅቅ እርሱም ከኃጢአትና ከክፉ መንገዱ ባይመለስ÷ በኃጢአቱ ይሞታል÷ አንተ ግን ነፍስህን አድነሃል::» በማለት የካህኑን የመጠበቅ ኃላፊነት ዘርዝሮአል:: ሕዝ.3÷19:: በመሆኑም ካህኑ ሕዝቡን ችላ በማለቱና እያንዳንዳቸውን ባለማስተማሩ ፣ ባለመጠበቁና ባለመከታተሉ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምውታን ስለሚሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ስለእነዚህ ነፍሳት ከመጠየቅ አያመልጥም::

ካህኑ የምእመናንን ነፍሳት ከፍርድ ለማዳንና ለጽድቅ እንዲበቁም ለማድረግ በቀንም በሌሊትም ስለ እነርሱ ሕይወት በመጸምና በመጸለይ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣት ይጠበቅበታል:: በራሱ ብቻ የግል ሕይወቱ መል ካም መሆኑ በቂ አይደለም:: ስለዚህም በአደራ ይጠብቃ ቸው ዘንድ ለተሰጡት የምእመናን ነፍሳት ግድ የሌለው ካህን ለውድቀታቸውና ለዘለዓለማዊ ሞታቸው ምክንያት በመሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ በዕዳ መጠየቁ አይቀርም:: በተለይ የምእመናንን ሕይወት ከእውነተኛው ሃይማኖት ለመለየት የሚጥሩ መናፍቃን ባሉበት የካህኑ ኃላፊነት የከበደ ከመሆኑም በላይ በምእመናን ሞተ ነፍስ የተነሣ ተጠያቂነቱም ከፍተኛ ነው::

የክህነት አገልግሎቱን በሚገባ ባለመወጣቱ የተነሣ ቢያስተምራቸው ኖሮ በሃይማኖት ጸንተው በምግባር ተጠ ብቀው በፍርድ ቀንም ዘለዓለማዊ ሕይወትን ማግኘት ሊችሉ በነፍሳቸው ለዘለዓለም ሞት እንዲጸሩ ምክንያት የሆነው ካህን ነፍሰ ገዳይ ነውና እግዚአብሔርም ይፈርድበታል:: ስለሆነም ለክህነት አገልግሎት የሚመረጠው ሰው በብርቱ ጥንቃቄ የተፈተነና ብቃቱም የተረጋገጠለት መሆን ይኖርበታል:: በሚመራቸው ምእመናን ጉባኤ በመገኘት የማ ይጎበኛቸውና የማያስተምራቸው ቁስ የነፍሳቸው /የመንፈ ሳዊ ሕይወታቸው/ ገዳይ ነውና ነፍሰ ገዳዮች እንዳይሾሙ

ቤተክርስቲያን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባት:: እግዚ አብሔርም «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቷል» በማ ለት የተናገረው ቃል፤ የማያስተምር ሕዝቡንም ወደ እውነት መዳንም ወደሚገኝበት የተቀደሰ ሕይወት የማ ያደርስ ካህን ስለጠፉት ነፍሳት ተጠያቂ መሆኑን የሚያመለክት ነው:: ሆሴ.4÷6:: ልጆቹን ከማስተማርና ከማ ስጠንቀቅ ችላ በማለቱ ካህኑ ኤሊም በእግዚአብሔር መቀ ጣቱ የዚሁ ምሳሌ ነው:: 1ሳሙ.2÷29–34::

ከካህኑ በተጨማሪም ማንም ሰው ለወለዳቸው ልጆቹ መንፈሳዊውን ሕይወትና ፈሪሃ እግዚአብሔርን በያስተምራ ቸውና ሥርዓት አልባ እንዲሆኑ ቢተዋቸው ስለእነርሱ መን ፈሳዊ ጉስቁልና፣ ስለነፍሳቸውም ሞት ከተጠያቂነት ሊድን እንደማይችል ማወቅ አለበት:: ልጆችን ስለማሳደግም «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ:: ለልጆችህም አስተምረው÷ በቤትህም ስትቀመጥ÷ በመን ገድም ስትሄድ÷ ስትተኛም÷ ስትነሣም ተጫወተው /ተነጋ ገረው/» በማለት መነገሩ የወላጆችን ኃላፊነት የሚያሳይ ነው:: ዘዳ.6÷6–7::

ማንም የቤተሰብ ኃላፊ እግዚአብሔርን በመፍራትና በጥንቃቄ ልጆቹን ማሳደግ አለበት:: እርሱ የቤተሰቡ ራስ ነውና ስለሚስቱም፣ በቤቱ ስለሚኖሩ ሁሉ ኃላፊነት አለ በት:: የሁሉንም መንፈሳዊ ሕይወት በሚገባ ካልመራና ማኅበራዊ ኑሮውን ብቻ የሚመለከት ከሆነ እንደ ኢያሱ «እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን» ለማለት አይች ልም:: ኢያ.24÷15:: ስለእነዚህ በግድየለሽነት ስለሚ ያስተዳድራቸው የቤተሰቡ ነፍሳትም እግዚአብሔር ይጠ ይቀዋል÷ በነፍስ ገድሏቸዋልና:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጋብ ቻና ትዳር መንፈሳዊና ሰማያዊ መሆኑን ዘንግቶ ቤቱን «አነስተኛ ሲኦል» አድርጓታል:: ከልጆቹ አንድ እንኳን የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል ቢፈልግ ብዙ መከራ መቀበል አለበት:: ይህን የመሰለው አባት በፍርድ ቀን ከመጠየቅ አይድንም:: ከሁሉ ነገር በፊት ጋብቻ መን ፈሳዊና ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ ፍሬዎች የሚገኙበት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው:: ይህን

በመገንዘብ ልጆቻቸውን በቀና ሃይማኖት አጽንተው በሥነ ምግባር አሳድገው በመንፈሳዊ የሕይወት ጎዳና የሚመሩትን አባቶች ሁሉ በአድናቆትና በታላቅ ክብር እንመለከታቸዋለን። እነርሱ ሬቂቁንና ከእነርሱ የሚጠበቀውን መንፈሳዊ ግዴታ የተረዱና የጋብቻቸውን ዋና ዓላማም ጠንቅቀው ያውቁ ናቸው።

ለልጆቻቸው የመጥፎ ሥራ፣ የክፉ ምግባርም ምሳሌ የሚሆኑ፤ በቤት ውስጥም ዘወትር የሚጨቃጨቁና ክፉ ቃላትን በመመላለስ የሚነጋገሩ፤ በቤታቸውም ሰላም የሌላቸው ወላጆች የልጆቻቸውን የኑሮ አቅጣጫ በማበላሸት ለውድቀታቸው ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ ያደርጋሉ። እነዚህ ወላጆችም ልጆቻችንን አልገደልንም ለማለት አይችሉም። እነርሱም የልጆቻቸውን የመንፈሳዊ ሕይወት ተስፋ ገድለውታል፤ አጨልመውታል፤ ለልጆቻቸው ያሳዩአቸውና በአእምሮአቸው ውስጥ የቀረፁት እግዚአብሔር የማይወደውንና የትእዛዛቱም ተቃራኒ የሆነውን ዓለማዊና ሥጋዊ ምግባር ነውና።

ስለዚህ ወላጆች በአነጋገራቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በኑሮአቸው በአመጋገባቸው፣ በሥርዓትና በምግባራቸው ሁሉ የልጆቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት በማበላሸት የገሃነም ባሮች በማድረግ ለዘለዓለም እንዳይገድሏቸው መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። መግደል የአንድን አካላዊ ሕይወት ሕልውና ማጥፋት ብቻ ወይም ምድራዊ ሕይወቱን ማሳለፍ ብቻ እንዳይመስለን፤ የአንድን ሰው ሃሳብ ማጥፋት መንፈሳዊ ሕይወቱ ለዘለዓለም ወደማይወጣበት የሞት ኑሮ መጨመርም ነፍሰ ገዳይነት መሆኑን ማወቅ ይገባል።

አንድ ሰው ኃጢአትን እንዲሠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ማሰናክልም የነፍስ ግድያ ነው። ሰው በእኛ ምክንያት በኃጢአት የወደቀ እንደሆነ በኃጢአቱ የተነሣ ምጢት ነውና ይህን ሰው የገደልነው እኛ መሆናችንን ማወቅ ያስፈልጋል፤ ለውድቀቱ ምክንያት ነንና። ስለዚህም እግዚአብሔር ይጠይቀናል። በመጽሐፍም «በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታሥሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር፤ ወዮ ለዓለም ስለማሰናከያ፣ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፦ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።» በማለት ጌታችን የተናገረው የሚያመለክተው ይህንኑ ነው። ማቴ.18÷6-7።

በመሆኑም ሰዎችን ከመንፈሳዊ ጉዞአቸው እንዳናሰናክልና በፍርድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት እንዳንጠየቅ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ክርስቶስ ስለፍርድ ቀን ባስተማረበት አንቀጽ ኃጢአት ከሠሩ ይልቅ ለኃጢአት ምክንያት የሆኑትን አስቀድሞ አውስቷቸዋል፤ «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ ወደ እቶን እሳትም ይጥሏቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» በማለት የሚያሰናክሉ ቅጣታቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጧል። ማቴ.13÷41-42።

ራስን መግደል

ራስን መግደል ሌሎችን ከመግደል እኩል ነው። ሰው የነፍሱ ባለቤት አይደለም፤ በነፍሱም ላይ የወደደውን ሊያደርግ ሥልጣን የለውም። የሰው ነፍሱ የእግዚአብሔር ገንዘብ ናት፤ በክርስቶስ ደም፣ በቤዛነቱ ወደቀደመ ክብሯ ለመመለስ የበቃች የእግዚአብሔር ሀብት ናት። የፈጠራትም እርሱ እግዚአብሔር ነው። ሰው እንደፈለገ ሊያደርጋት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ለስሙም ክብር የተፈጠረች እርሱንም በማመስገን አንታ እንድትኖር የተሰጠች ስጦታ ናት። ስለዚህ ነው ራሱን የገደለ ሰው በቤተ ክርስቲያን አሉተ ፍትሐት የማይደረግለት። ይህ ሰው በንስሐ ሊፈወስ /ሊድን/ የማይችል ኃጢአት ሠርቶ ነው የሞተው።

ተስፋ መቁረጥም ደግሞ ራስን እንደመግደል የሚቆጠር ነው። አስተዋይ ሰው ተስፋ አይቆርጥም፤ እግዚአብሔር ፈጽሞ እንደማይተወው ያውቃልና። ራሱን የሚገድል ሰው ተስፋው የተሟጠጠ ነው። ተስፋ መቁረጥ ደግሞ በራሱ ኃጢአት ነው፤ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት ቸል ማለት ነውና። ይህም በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ጥበቃና ታዳጊነት ላይ እምነት በማጣትና በመጠራጠር የሚመጣ ነው።

ራስን መግደል ትዕግሥት ማጣትንም ያመለክታል። ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት አለማመንንም የሚያመለክት ነው። ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት የሚያምን ቢሆን ኖሮ ራሱን ከማጥፋት ከመከልከሉም በላይ ራሱን በመግደሉ ወደዘለዓለም ስቃይ ወደገሃነም እሳት መውረዱን ያስተውል ነበር። ከችግር እላቀቃለሁ በማለት ራሱን የሚገድል ሰው ከችግሩ አይገላገልም፣ ይልቁኑ ወደባሰና ወደተወሳሰበ ሌላ ችግር ነው የሚገባው «ከድጡ ወደማጡ» እንዲሉ። ራስን መግደል ችግርን ለማቃለል መንፈሳዊም ሆነ ተግባራዊ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ራሱን የሚገድል ሰው የአእምሮ በሽታ ያለበትና አስተሳሰቡ የተዛባ ነው። ራስን መግደል ነፍስን በተግባር ማጥፋት ነውና አትግደል ለሚለው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው።

ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ውን ጤናማና ንጹሕ ሰውነትና ሙሉ አካል በማጎሳቆልና እግዚአብሔርም ለማ ይደሰትበት ተግባር በማዋል በተዘዋዋሪ ራሳቸውን ይገድ ላሉ። ክርስትና እግዚአብሔር የፈጠረልንን አካላችንን እን ድናጎሳቁል አይፈቅድም። ክርስትና የሚያዝዘው የሥጋ ፍላ ጎትን በማሸነፍና በመቆጣጠር ለሕገ እግዚአብሔር ማስገዛ ትና በዚህ ሂደት ምግባር ትሩፋትን እየሠራን የእምነት ጥንካሬን ገንዘብ እንድናደርግ ነው። በመጽሐፍ እንደ ተጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለአንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን» እንዲሁም «ስለዚህ ሞቱ በእኛ... ይሠራል» ያለውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደግሞ «የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።» በማለት መናገሩ አካ ልን ስለማጎሳቆል ሳይሆን የሥጋን ፈቃድ ስለመግደል የተነገረ ነው። ሮሜ.8÷36። 2ቆሮ.4÷12። ዮሐ.12÷24። የሥጋ ፍላጎትን መግደል ማለትም ከፈቃደ ነፍስ ጋር የሚ ቃረነውን ፍትወተ ሥጋ ማስቀረት ነው እንጂ ሞተ ሥጋ ማለት አይደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።» በማለት ያስተማረው ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ስለማስገዛት ነው። 1ቆሮ.9÷27።

በቅዱስ መጽሐፍ ሰው ሥጋውን «ይመግበዋል ይከ ባከበውማል» ተብሎ እንደተጻፈ፣ በዚያ ቀን እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን እንድንሠራ ስለሰውነታችንም ዕረፍት የሰንበትን ሕግ ሰጥቶናል። ኤፌ.5÷29። መድኃኒታችንም ብዙ ድውያንን የፈወሰው ስለሰው አካል ጤንነት የሚያስብ በመሆኑ ነው። ስሙን ለማመስገን ክብሩንም ለመግለጥ እን ድንችል እግዚአብሔር ጤናማ አካላችንን ይፈልጋል። ጤናማ አካል ቆሞ ለመጸለይ፣ ለመስገድ፣ ነቅቶ ለመቆየት፣ ሰዎችን ለማገልገል፣ ለመጾም፣ ይረዳል። ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ አገልግሎትን ለመፈጸምና የዘለዓለምን ክብር ለመውረስ ሰው ሁሉ አካሉን በጤና መጠበቅ አለበት እንጂ በግድየለሽነትና በቸልታ አካሉን እያጎሳቆለ ሽባ ሊያደርገው አያሰፈልግም አካሉ የእግዚአብሔር ገንዘብ ነውና። 1ቆሮ.6÷20።

በዚህ መልክ ሰዎች አካላቸውን በማጎሳቆል ራሳቸውን ከሚገድሉባቸው መንገዶች መካከል በመጠጥ ብዛት በመስ ከር፣ በማጨስ፣ የሱስ ምንጮች የሆኑ ዕፅዋትን በመብላትና የመሰለሉት ይገኙበታል። እነዚህ ሁሉ ቀስ በቀስ የሰውን አካል በማጻከም ለጽድት ሥራ ቀርቶ ቆሞ ለመሄድ ከማ ይቻልበት ደረጃ በማድረስ ወደሞት የሚያጓጉዙ ናቸው።

ከሁሉ የከፋው ራስን የመግደል ዓይነት ግን ኃጢ አትን መሥራት ነው። ኃጢአት ሞት ነውና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በበደላችን ምውታን ነበርን» «የኃጢአትም ደሞዝ ነው» «ስለሥጋ ማሰብ ሞት ነውና» እንዳለ። ኤፌ.2÷5። ሮሜ.6÷32። ሮሜ6÷8። በዚህ መሠረትም ሰው ኃጢአትን በመሥራት መንፈሳዊ ማንነቱን ይገድላል። ይህ ሞትም ነፍሱን ከእግዚአብሔር በመለየት ወደ ሲኦል ቀጥሎም ወደገሃነም እሳት እንድትጣል፣ ለዘለዓለምም ያለተስፋ እንድትቀር ያደርጋታል።

ስለሆነም ኃጢአት ሰው ራሱን የሚያጠፋበት መንፈሳዊ /ረቂት/ ግድያ ነው። ሰው ከኃጢአት የተነሣ ከመንፈሳውያን ምግባራት፣ ከጸም፣ ከጸሎት፣ ከመስገድ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመመልከት፣ከኑዛዜ፣ ከሥጋውና ከደሙ፣ ከሌሎችም ጸጋና ድኅነት ከሚገኝባቸው ምግባራት የተለየ እንደሆነ መንፈሳዊ ማንነቱን /ነፍሱን/ ገድሏል።

የራሱን ሥጋዊ ፍላጎት ተከትሉ ለጊዜያዊና ምድራዊ ለሚያልፍም እርካታ ብሉ ወደዓለም ያጋደለ ፈቃደ ነፍሱንም የተወ ሰው አምስተኛውን ትእዛዝ በመተላለፍ የራ ሱን ነፍስ ገድሏል። በወንጌልም «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል» ተብሉ የተነገረው ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ነው። ማቴ.10+39። ለምድራዊ ተድላ ሲርጥ፣ ለሚያልፍ ጊዜያዊ እርካታ ሲደክም የዘለዓለም ሞትን ገንዘብ አድርጓልና። ስለዚህ «አትግደል» የሚለውን ሕግ ስፋትና ጥልቀት ከራሳችን ማንነት ጋር በማገናዘብ ከመግደል ተጠብቀን ልንኖር ይገባናል።

ክፍል ሰባት

ስድስተኛው ትእዛዝ

«አታመንዝር»

ዘጸ.20+14።

ዝሙት በሚባልበት ጊዜ ሰፊ ትርጉም ያለውና በሁለት ዋና ዋና መንገዶች የሚፈታ ነው። በአጠላ ስንመለከተው ዝሙት ማለት ፍትረ ተራክቦ ማለት ነው። የሥጋ ፍላጎቱን መግታትና ራሱን መግዛት ካለመቻሉ የተነሣ ሰው በዝሙት ሊፈተን ይችላል። ይህ ዝሙትም በሁለት መንገድ በተግባር ይፈጸማል። አንዱ ሴሰኝነት ሲ ሆን ሁለተኛው ደግሞ አመንዝራነት ነው። አንድ ሰው ሴሰኛ ነው የሚባለው በሕግም ሆነ ከሕግ ውጭ ያለማጸረጥ ተራክቦን የሚፈጽም እንደሆነ ነው። ሴሰኛ ሰው በውስጡ ካደረው የዝሙት መንፈስ የተነሣ የተራክቦ ሱሰኛ ነው ለ ማለት ይቻላል። ስለዚህም በአጽዋማት፣ በበዓላት፣ እንዲ ሁም / በሰንበት ያለዕረፍት ተራክቦን ይፈጽማል። ይህ እንግዲህ ገደብ የሌለው ዝሙት ነው። ሴሰኝነት የግድ ወደ ብዙ ሴቶች ወይም ወንዶች መሄድን የሚሻ ላይሆን ይችላል። አንድ ሰው ከሚስቱ /ከባሏ/ ጋር የሚያደርገው /የምታደርገው/ ተራክቦ የተወሰነ ጊዜ ከሌለውና እንደመብላትና መጠጣት ያለማጸረጥ የሚፈጸም ከሆነ ሴሰኝነት ነውና ዝሙት በባልና ሚስት መካከልም ሊኖር ይችላል።

ስለሆነም ኃጢአት ሰው ራሱን የሚያጠፋበት መንፈሳዊ /ረቂት/ ግድያ ነው። ሰው ከኃጢአት የተነሣ ከመንፈሳውያን ምግባራት፣ ከጸም፣ ከጸሎት፣ ከመስገድ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመመልከት፣ከኑዛዜ፣ ከሥጋውና ከደሙ፣ ከሌሎችም ጸጋና ድኅነት ከሚገኝባቸው ምግባራት የተለየ እንደሆነ መንፈሳዊ ማንነቱን /ነፍሱን/ ገድሏል።

የራሱን ሥጋዊ ፍላጎት ተከትሉ ለጊዜያዊና ምድራዊ ለሚያልፍም እርካታ ብሉ ወደዓለም ያጋደለ ፈቃደ ነፍሱንም የተወ ሰው አምስተኛውን ትእዛዝ በመተላለፍ የራ ሱን ነፍስ ገድሏል። በወንጌልም «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል» ተብሎ የተነገረው ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ነው። ማቴ.10+39። ለምድራዊ ተድላ ሲርጥ፣ ለሚያልፍ ጊዜያዊ እርካታ ሲደክም የዘለዓለም ሞትን ገንዘብ አድርጓልና። ስለዚህ «አትግደል» የሚለውን ሕግ ስፋትና ጥልቀት ከራሳችን ማንነት ጋር በማገናዘብ ከመግደል ተጠብቀን ልንኖር ይገባናል።

ክፍል ሰባት

ስድስተኛው ትእዛዝ

«አታመንዝር»

ዘጸ.20+14።

ዝሙት በሚባልበት ጊዜ ሰፊ ትርጉም ያለውና በሁለት ዋና ዋና መንገዶች የሚፈታ ነው። በጠባ ስንመለከተው ዝሙት ማለት ፍትረ ተራክቦ ማለት ነው። የሥጋ ፍላጎቱን መግታትና ራሱን መገዛት ካለመቻሉ የተነሣ ሰው በዝሙት ሊፈተን ይችላል። ይህ ዝሙትም በሁለት መንገድ በተግባር ይፈጸማል። አንዱ ሴሰኝነት ሲ ሆን ሁለተኛው ደግሞ አመንዝራነት ነው። አንድ ሰው ሴሰኛ ነው የሚባለው በሕግም ሆነ ከሕግ ውጭ ያለማጽረጥ ተራክቦን የሚፈጽም እንደሆነ ነው። ሴሰኛ ሰው በውስጡ ካደረው የዝሙት መንፈስ የተነሣ የተራክቦ ሱሰኛ ነው ለ ማለት ይቻላል። ስለዚህም በአጽዋማት፣ በበዓላት፣ እንዲ ሁም / በሰንበት ያለዕረፍት ተራክቦን ይፈጽማል። ይህ እንግዲህ ገደብ የሌለው ዝሙት ነው። ሴሰኝነት የግድ ወደ ብዙ ሴቶች ወይም ወንዶች መሄድን የሚሻ ላይሆን ይችላል። አንድ ሰው ከሚስቱ /ከባሏ/ ጋር የሚያደርገው /የምታደርገው/ ተራክቦ የተወሰነ ጊዜ ከሌለውና እንደመብላትና መጠጣት ያለማቋረጥ የሚፈጸም ከሆነ ሴሰኝነት ነውና ዝሙት በባልና ሚስት መካከልም ሊኖር ይችላል።

አንድን ሰው አመንዝራ ነው ለማለት የሚቻለው ከሕግ ሚስቱ ወይም ባሏ ውጭ ከሌላ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ሰው ጋር ተራክቦ ያደረገ/ች/ እንደሆነ ነው። ከብዙ ሴቶች የደረሰ ወንድ ወይም ከብዙ ወንዶች የሄደች ሴት ሁለቱም አመንዝራ ይባላሉ። የዝሙትን ፍላጎት ለማርካት የሚፈጸመው ይህ ተራክቦ አመንዝራነት ይባላል።

እንግዲህ ሴሰኝነትና አመንዝራነት የዝሙት ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች ናቸውና ዝሙት በሚባልበት ጊዜ ሁለቱንም ወይም ከሁለቱ አንዱን ሊያመለክት እንደሚችል ማስተዋል ይገባል።

በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «አታመንዝር» ያለውን ስድስተኛውን ትእዛዝ የግእዙ ንባብ «ኢትዘሙ» ይለዋል። የአማርኛው ምንባብ ትርጉሙን ጠባብና ውሱን ሲያደርገው ግእዙ ግን በሰፊው ልንመለከተው እንድንችል ሰድል ይሰጣል። ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ስለስድስተኛው ትእዛዝ ስንጽፍ «ዝሙት» እያልን በየርእሱ የጠቀስነው አመንዝራ ነትንና ሴሰኝነትን ለማጠቃለል በማሰተዋል እንድናነብ ይሁን።

የዝሙት አስከፊነት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከዝሙት ሽሹ፣ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።» ብሏል። 1ቆሮ.6÷18። ሰው በገዛ ሥጋው ላይ የሚሠራው ኃጢአት አደገኛነቱ ከምን ላይ ነው? እንደ ሐዋርያው አገላለጥ ይህ አደገኛነት በሁለት ምክንያቶች ላይ የተመሠረተ ነው፤

1/ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስ ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን?» 1ቆሮ.6÷15።

2/«የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?... ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። 1ቆሮ.6÷19–20። «እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነንና።» 2ቆሮ.6÷16። «የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ... አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር አርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና+ ያውም እናንተ ናችሁ።» 1ቆሮ.3÷16–17።

ስለእነዚህ ከላይ ስለተጠቀሱት ምክንያቶች ማንም ዝሙትን ቢያደርግ በክርስቶስ ብልቶች ላይ ኃጢአትን ይሠራል፤ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ፣ የመንፈስ ቅዱስን ማደሪያ ያረክሳል። ምንኛ አስከፊ ኃጢአት ነው? ዝሙት የተቀደሰውን ንጹሕ አካል ማሳደፍ /ማቆሸሽ/ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በደለኞችንም ይልቁንም በርኩስ ምኞት የሥጋን ፍትወት እየተከተሉ የሚመላለሱትን... እየቀጣቸው ለፍርድ ቀን እንዴት እንዲጠብቅ ያውቃል።» በማለት ዝሙትን የርኩሰት ምኞት ሲል ገልጦታል። 2ጴጥ.2÷9–10።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሴኬም ዲናን ያስነወረበት ታሪክ በተነገረበት ክፍል «ያዕቆብም ሴኬም ልጁን ዲናን እንዳስነወራት ሰማ»ይላል። ዘፍ.34÷5። የያዕቆብ ልጆች ግን እጅግ ከመናደዳቸው የተነሣ ሴኬምን ለመግደልና ክተማውንም ለማጥፋት ዕቅድ አዘጋጁ ምክንያቱም አርሱ «እኅታቸውን ዲናን አርክሶአታልና።» ዘፍ.34÷13–27። ነቢዩ ሕዝ ቅኤልም ዝሙት ስለሠራው ሰው ሲናገር «የጎረቤቱን ሚስት አረከሰ» ሲል ሐዋርያው ይሁዳ ደግሞ «ሰዎች እያለሙ ሥጋቸውን ያረክሳሉ» ብሏል። ሕዝ.18÷11። ይሁ.8። ባለራእዩ ቅዱስ ዮሐንስም «የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ የሚያስጸይፍ ነገር፣ የዝሙትም ርኩሰት» በማለት የዝሙትን አስከፊነት ከመግለጡም በላይ የመቶ አርባ አራት ሺዎቹን ሕፃናት ከብር፣ ያለእነርሱም እዲሱን ቅኔ ሊማር የሚችል እንደሌለ ባብራራበት ክፍል «ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው። ድንግሎች ናቸውና በጉ ወደ ሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው።» በማለት ከዝሙት የራቁት የከበሩ መሆናቸውን ተናግሯል። ራእ.17÷1–4። ራእ.14÷4። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ምንባብ ሁሉ የዝሙት ኃጢአት ርኩ[illegible] መሆኑን፣ አመንዝራዎችም ከዝሙት

የተነሣ ሥጋቸውን ያረከሱ መሆናቸውን በመግለጥ የዝሙትን አስከፊነት የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አድሮ «በግልሙትናሽና በኃጢአትሽ ምድሪቱን አረከስሽ» በማለት ዝሙት ከሰው አልፎ ምድርን የሚያረክስ አስከፊ ኃጢአት መሆኑን ተናግሯል። ኤር.3÷1–2።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክታቱ ዝሙትን ርኩሰት ብሎታል። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህልም የሚከተለውን እንመልከት፦«የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም፡ ዝሙት÷ ርኩሰት÷ መዳራት» ገላ.5÷19። ለቆላስ ይስ ሰዎች በጻፈው መልእክትም «በምድር ያሉትን ብልቶ ቻችሁን ግደሉ÷ እነዚህም ዝሙት ርኩሰት ፍትወትም... ነው» ብሏል። ቆላ.3÷5። እንዲሁም ደግሞ ለኤፌሶን ሰዎች «ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኩሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤... ከዚህ የተነሣ በማ ይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና» በማ ለት ዝሙት ርኩሰትና አስከፊ ኃጢአት መሆኑን ገልጧል። ኤፌ.5÷3–6።

ጣዖት ማምለክም በሃይማኖት ዝሙት መፈጸም ነው። ከአንድ ፈጣሪአቸው ከእግዚአብሔር በተጨማሪ ጣዖ ትን የሚያመልኩ ሰዎች በሃይማኖት ላይ አመንዝረዋልና ዘማ ውያን ናቸው። በዘመነ መሳፍንት እሥራኤል እግዚአብሔ ርን ትተው ጣዖትን ባመለኩ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ «ሌሎች አማልክትን ተከትለው አመነዘሩ ሰገዱላቸውም እንጂ መሳፍንቶቻቸውን አልሰሙም፤» በማለት ቅዱስ መጽሐፍ መዝግቦታል። መሳ.2÷17። ይህን የመሰለው አገላለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ ነው። ለም ሳሌም የእሥራኤል መንግሥት በይሁዳ በተተካና በጣዖት አምልኮ በተዘፈቀ ጊዜ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አድሮ «ከዳተኛይቱ እሥራኤል ያደረገችውን አየህን? ወደ ረዘመው ተራራ ሁሉ ከለመለመ ዛፍም ሁሉ በታች ሄደች በዚያም ገለሞተች። ...አታላይ እኅቷ ይሁዳ ግን እንዳልፈራ ች እርስዋም ደግሣ ከግንድ ጋር አመነዘረች» ብሏል። ኤር.3÷6–9። በሆሴዕም «በዚያ በኤፍሬም ውስጥ

ግልሙትና ተገኘ÷ እሥራኤልም ረከሰአል» በማለት ተነግሯ ል። ሆዕ.6÷10። በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ጣዖትን ማምለክ በ ማመንዘር የዝሙትን ኃጢአት መፈጸም እንደሆነ የተነገ ረባቸውን ምንባባት ቁጥር ለመፈጸም አይቻልም። በአጠ ቃላይ ግን ዝሙት በአንዱም ሆነ በሌላኛው ገጽታው ርኩሰት ተብሏል። ርኩሰ ከማለት በቀር የዝሙትን አስከፊነት ለመ ግለጥ የተሻለ ቃል አልተገኘም። ይህ ኃጢአት አስከፊ መሆ ኑን ከሚገልጡት ገጽታዎቹ አንዱ በዝሙት የተነሣ እግዚ አብሔር ከፍተኛውን መቅሰፍት በዓለም ላይ ማምጣቱ ነው። አስኪ ዝሙት በዓለም ላይ በሚኖሩ ሰዎች ያመጣባቸውን ጥፂት መቅሰፍቶች እንመልከት።

1/ ብሉይ ኪዳን እንደሚነግረን በመጀመሪያ እግዚ አብሔር ዓለምን ሁሉ የቀጣበት መቅሰፍት የጥፋት ውኃ ነው። እግዚአብሔር «የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠ ፋለሁ የሥጋ÷ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሷል፤ መንፈሴ ለዘለዓ ለም በእርሱ ላይ አይኖርም» ብሏል። ዘፍ.6÷37፤13 ። ይህም የጥፋት ውኃ ከዚያ በፊት ሆኖ የማያውቅ ምሳሌም የሌለው ቅጣት ነው። የዚህ ቅጣት ምክንያቱ ዝሙት ነው። በመጽሐ ፍ «ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።» የሚል ተጽፏል። ዘፍ.6÷1–2።

2/ እግዚአብሔር ከዝሙት የተነሣ ሰዶምንና ገሞራን አቃጥሏል። «እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአ ብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተ ሞች÷ በዙሪያቸው ያለውንም ሁሉ÷ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሁሉ÷ የምድሩን ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ።» ዘፍ.19÷24–25። ሐ ዋርያው ቅዱስ ይሁዳም ይህንን አሳዛኝ ክስተት በማስታወስ «እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።» ብለዋል በማለት ተናግሯ ል። ይሁዳ.7።

3/ ከዝሙት የተነሣ የብንያም ነገድ ሁሉ ሊጠፋ ነበር። መሳ.20። እግዚአብሔርም ከእነርሱ መካከል ከሞዓባውያን ጋር ያመነዘሩ ብዙዎችን አጥፍቷቸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከእነርሱም አንዳንዶቹ እንደሴሰኑ በአንደ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደወደቁ አንሴስን።» ብሏል። 1ቆሮ.10÷8።

4/ ከዘማዊነቱ የተነሣ በአመነዘረው የቆሮንቶሱ ሰው ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጠንከር ያለ ውሳኔ አስተላልፏል። «መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።» ሲል መናገሩ ዝሙት ምንኛ የከፋ ኃጢአት እንደሆነ የሚገልጥ ነው። 1ቆሮ.5÷5።

ከላይ ከተጠቀሱት ምድራውያን ቅጣቶች በተጨማሪ የመከራ ፍርድ ይጠብቀዋል። በዘህ አንባር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አትሳቱ፤ ሴሰኞች ሆኑ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም... ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ብሏል። 1ቆሮ.6÷9–10። ሐዋርያው በዚህ ትምህርቱ ሴሰኞችን ከጣዖት አምላኪዎች አስቀድሞ ማስቀመጡ ዝሙት ምን ያህል የከፋ ኃጢአት መሆኑንና አደገኛነቱን እንድናስተውል ያደርገናል።

ዝሙት እጅግ ከባድና አደገኛ ኃጢአት በመሆኑ የኃብቻን አንድነት ያፈርሳል። ይህን ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት /ኤፌ.5÷22–23/ ምሳሌ የሆነ ታላቅ ምሥጢርና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ደግሞ «እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው» ብሎ የተናገረለትን /ማቴ.19÷6/፤ በማንኛውም ምክንያት ቢሆን ሊፈርስ የማይችለውን የተቀደሰ ጥምረት ኃብቻን ዝሙት ሊያፈርሰው ይችላል። በዝሙት ጠንቅ በኃብቻ የተዋሐደው አንድ አካል ይፈርሳል፤ ተጋቢዎችም አንድ ሥጋ መሆናቸው ቀርቶ ሁለት የተለያዩ ግለሰቦች ይሆናሉ፤ ከዚያ በኋላም አንድ ሊሆኑ አይችሉም።

ይህን በመሰለ ሁኔታ አስከፊና አደገኛ ስለሆነው ዝሙት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ... እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳ አትብሉ። ...ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።» በማለት ይመክረናል። 1ቆሮ.5÷9–13። ስለሆነም አመንዝራ ሰው በዝሙት የተዳደፈና በኃጢአት የረከሰ፣ ተሳላፊ የሆነውን የኃጢአት ተሐዋሲ የተሸከመ ነውና ከክርስቲያኖች አንድነት የተለየ ነው። ይህም የዝሙትን አስከፊ ገጽታ የሚያመለክት ነው። በዚህ አንፃር የቆሮንቶሱ ኃጢአተኛ በዝሙት የተነሣ ከክርስቲያኖች አንድነት መለየት በደረሰበቅ ጊዜ ከልክ በሚበዛ ጥልቅ ኅዘን ተውጦ ነበር። 2ቆሮ.2÷7።

የዝሙት ኃጢአት ውስብስብ ነው። ዝሙት አንድ ሰው በሌሎች ላይ በሚፈጽመው ኃጢአትና ርኩሰት እንጂ ሁም ፈተና ብቻ የሚወሰን አይደለም። ሰው በራሱ ሥጋ ላይ የሚሠራውን ኃጢአት፣ ራሱን ማርከሱንና ንጽሕናውን ማጣቱን፣ ራሱንና ጤናውንም ማጥፋቱን ጭምር የሚያጠቃልል ነው። ከዚህ በተጨማሪም ዘማዊ ሰው እግዚአብሔርን ይበድላል፣ የክርስቶስን አካል የመንፈስ ቅዱስንም ማደሪያ አርክሷልና። ቅዱስ ዳዊት በኦርዮ ሚስት በቤርሳቤህ ላይ ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ፊቱን በመመለስ «አንተን ብቻ በደልሁ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ» በማለት መጸለዩ ለዚሁ ነው። መዝ.50÷4።

ዝሙት ወደተለያዩ የኃጢአት ደረጃዎች ሊያድግና ልዩ ልዩ ውጤቶችን ሊያስከትል የሚችል ነው። ከገደብ የለሽ የሥጋ ፍላጎት ተነሥቶ ከብረገጽሕናን ማጣት፣ እርግዝና፣ ውርጃ፣ ፍቺ፣ ሃይማኖትን መካድ፣ በመጨረሻም እግዚአ ብሔርን ወደመካድ ሊያድግ ይችላል። በዘመናችን ብዙዎች ሃይማኖታቸውን የሚለውጡት ከእግዚአብሔር ሕግ ከልክላዎች ለመለየትና በነፃነት ለመሴሰን እንዲመቻቸው የሚሹትን የሥጋ ፍላጎታቸውን ሁሉ ያለገደብ ለመ ፈጸም እንዲችሉ ነው።

ዝሙት የሰውን አካል ሙሉ በሙሉ የሚያላትፍ ኃጢአት ነው። ሰው ዝሙትን በሚፈጽመበት ጊዜ

አእምሮው፣ የስሜት ሕዋሳቱ፣ ልቡናው መንፈሱ፣ አካሉ ሁሉ ተሳትፎ በማድረግ በኃጢአት ይመረዛል። በተለይም መመኘትና መሳምጀት ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ይቆጣጠሩ ታል። ዝሙት አስከፊና ከባድ ኃጢአት ከመሆኑ የተነሣ «እግዚአብሔርን መጥላትና ዓለምን ማፍቀር ነው» ተብ ሏል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ይህን አስመልክቶ «አመ ንዝሮች ሆይ+ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲ ሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል።» በማለት አስተምሯል። ያዕ.4+4።

ከአሕዛብ ወገን ወደክርስትና ሲመጡት ምእመናን እንዳይከብዳቸው በማሰብ ሐዋርያት ከሠሩላቸው ሕግጋት አንዱ ዝሙትን የሚመለከት መሆኑ የዝሙትን አስከፊነት የሚገልጥና ከዚህ ኃጢአት መከልከልም አስፈላጊና ጠቃ ሚም መሆኑን የሚያመለክት ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የሆኑ ትን እንዳናስቸግራቸው+ ነገር ግን ከጣዖት ርኩሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቀርጣለሁ።» በማለት የተናገረው። የሐዋ.15+19–20።

ዝሙት እጅግ አደገኛ ኃጢአት ከመሆኑ የተነሣ ብዙ የተቀደሱ ሰዎችን ለመውደቅ አጋትቷቸዋል። ጥበበኛው ሰሎሞንም ከገጠመኙ በመነሣት /የዝሙት ኃጢአት/ «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸው፣ አርሷ የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው» በማለት የዝሙትን ክፋትና አደገኛነት ተናግሯል። ምሳ.7+26። ዝሙት ኃይለኛ ኃጢአት በመሆኑ እርሱን ለመቋቋም ብርቱ ጥንቃቄና የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ያስፈ ልጋል።

ሴትን ከእርሱ ጋር ዝሙት እንድትፈጽም ያስገ ደዳትና የደፈራት ወንድ ሩብአዊነቱ ወደ አውሬነት የታለ ወጠ ሆኖአልና ኃጢአቱ እጅግ የከፋ ነው። ከጭካኔውም የተነሣ የሴቲቱን እምቢታና ጩኸት ወደጎን በመተው ለጊ ዜያዊ የሥጋ ፍላጎት ዕርካታ ሲል አስገድዶ ስለደፈራት ስለአራቱም ሆነ አብራው ዝሙት ስለፈጸመችው ሴት ተጠ

ያቂ ነው። ስለዚህ ሕግ «ያ የደረሰባት ሰው ብቻውን ይገጠ ደል። ...በብላቴናይቱ ላይ ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት የለባትም፣ ሰው በባልንጀራው ላይ ተነሥቶ እንደሚገድለው ይህ ነገር ደግሞ እንደዚሁ ነው» በማለት አስገድዶ መድፈር የነፍስ ግድያ ያህል የከፋና ከባድ መሆኑን ይናገራ ል። ዘዳ.22+25–26። ከዚህም ሌላ ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ ለሮማውያን በተናገረው ሁኔታ ከተፈጥሮአዊ ልማድ ውጭ በሆነ ተራክቦ የተፈጸመ ዝሙት የበለጠ አስከፊና አስጠያፊ ነው። ሮሜ.1+26።

የዝሙት አፈጻጸም ዓይነቶች

የዝሙት ኃጢአት በተለያዩ መንገዶች ሊፈጸም ይችላል። እነዚህን የዝሙት የአፈጻጸም ዓይነቶች ከመዘ ርዘር አስቀድሞ ስለያዩ የዝሙት መጠሪያዎች መናገር ይገባል። ዝሙት የተለያዩ መጠሪያዎች የተሰጡት ኃጢ አት ከመሆኑም በላይ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቅ ነው። ባለትዳሮች ሲፈጽሙት አመንዝራነት፣ በመበለቶች ሲፈጸም ሴተኛ አዳሪነት፣ ግልሙትና እና ርኩሰት፣ ተመሳሳይ ፆታ ባላቸው ሲፈጸም ግብረ ሰዶም ይባላል። ከአፈጻጸም ሁኔታዎች በመነሣት የተለያዩ መጠሪያዎች ይሰጠው እንጂ ያው ዝሙት ነው።

ዝሙት በልዩ ልዩ መንገድ ሊፈጸም የሚችል በመ ሆኑ ከአፈጻጸሙ በመነሣት የሚከተሉትን የዝሙት ዓይ ነቶች ለመዘርዘር ይቻላል። ዝሙት በተራክቦ ምኞት /ሃሳብ/፣ በስሜት፣ በልቡና በማመላለስ፣ በአካል፣ በሕልም ወዘተ ሊፈጸም ይችላል። ዝሙት በተለያዩ መንገዶች ሥጋዊ ፍትወትን ለማርካት የሚደረጉ ሙከራዎችንም ያካትታል፣ ከዚህም ሌላ በመናገር፣ በመሰማትና በመጻፍም ሊፈጸም ይችላል። ሌሎችን ወደ ዝሙት ለማስገባት በማባ በል፣ በመጻራት፣ በሽርሽር ሰበብ ይዞ በመከብለል፣ በማታ ለል፣ በመተሻሸት ወዘተ ሊፈጸምም ይችላል። በፈቃድና በእ ቪታ፣ በኃይልና በማስገደድም ሊፈጸም ይችላል። ይህ ሁሉ የዝሙት ዝርያና «አታመንዝር» የሚለው ትእዛዝ ተቃራኒ ነው።

በስሜት የሚፈጸም ዝሙት

ሰው በማየት ስሜቱ የተነሣ በዝሙት ሊወድቅ ይችላል። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ «ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመ ንዝሮአል» ብሏል። ማቴ.5÷28። ጻድቁ ኢዮብም በዘመነ ብሉይ «ከዓይኔ ጋር ቃልኪዳን ገባሁ፤ እንግዲህስ ቆንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ?» በማለት የተናገረው ግሩም ቃል ማየት የዝሙት ስሜትን ሊያመነጭ የሚችል መሆ ኑን የሚያመለክት ነው። ኢዮ.31÷1።

ስለሆነም በከርስቲያኖች ዘንድ ዓይን አፋርነት የጥበብና የማስተዋል ምልክት ሲሆን ዓይኑን በአካላዊ ውበትና ቁመና ላይ ተክሉ በመጎምጀት መመልከት የልብ ንጽሕና አለመኖሩንና የዝሙት መርዝ በስሜቱ ውስጥ መኖሩን ያሳያል። ይሁን እንጂ ማየት ሁሉ ኃጢአት ነው ማለት አይደለም፤ በተለይ የመጀመሪያ ዕይታ ኃጢአት ሊሆን አይችልም። ሰው አፍአዊ ዓይኑን ጨፍኖ አይኖርምና። መጨረን የሚገባውስ ውስጣዊ ዓይንን ነው። የሰው ዓይኖች ከራሱ ቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ለዝሙት በሚጋብዝ ነገር ላይ ሊያርፉ ይችላሉ። እስከዚህ ድረስ ኃጢአትን አል ሠራም። ነገር ግን በመጀመሪያው ዕይታ ተማርኮ ለሁለተኛ ጊዜ ለማየት ዓይ ኖቹን የወረወረ እንደሆነ ኃጢአት ይሆንበታል፤ ዓይቶ የመርካት ፍላጎት አድሮበታልና። ኃጢ አቱ በተግባር ላይፈጸምና ሰውየውም ራሱን ሊቆጣጠር ይችላል፤ የኃጢአቱ ምንጭ ግን በመጀመሪያ ዕይታው የታወከው ውስጣዊ ማንነቱ /ልቡናው/ ነው።

ከማየት በተጨማሪ ሰው በመስማትም ዝሙትን ሊፈጽም ይችላል። ይህ ደግሞ ሰውየው በተራከቦ ሥጋ ላይ ያተኮሩ ነገሮችን በመስማት የመደሰትን ልምድ ያዳበረና በሰማውም ቁጥር ወይም ከሰማ በኋላ ጥቂት ቆይቶ በጎሊ ናው እያመላለሰ ሊዝናናበት የሚፈጸም ነው። ሰው በሚነካውና በሚያሸትተው ነገር የተማረከና የረካበትም እንደሆነ በዚህ ስሜት ዝሙትን እንደፈጸመ ይቆጠራል።

በማሰብ የሚፈጸም ዝሙት

የስሜቶች ሥራ አፍአዊ ውጫዊ ነው። ሃሳብ ከተበከለ ግን ዝሙት ውስጣዊ ተግባሩን ይጀምራል። በት ንሹ የተጀመረው ሃሳብም ሲያድግ ወደ ምኞት ይለወጣል። ኃጢአትም የዝሙትን ሃሳብ በልቡና ውስጥ በሚያመነጨው ምኞት ይጀመራል። እነዚህ የዝሙት ሃሳቦች ከምኞት የተነሣ ለመርካት የሚሹ ስሜቶችን በመማረክ መቆጣጠር ይጀምራሉ። ይህ ከማሰብ የሚገኝ የዝሙት ዕርካታ ብዙ ሕል ምና ግምት በሚመላለስበት ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለተራከቦ ማሰብ ከማንበብ፣ ከማየት፣ ከመስማት፣ ወይም ከማንኛውም በፍትወት የሚማርክ ክስተት ሊመነጭ ይችላል።

ቢሆንም የሃሳብ ጦርነትንና በማሰብ ኃጢአትን መሥራት ለየትል ማየት አለብን። ሰይጣን ሰውን በዝ ሙት ሃሳብ ሊፈታተነው ይችላል፤ እናም ውጊያው ውጫ ዊና የማያቋርጥ ከሆነ ሰውየው ኃጢአትን አልሠራም፤ እየተከላከለና ራሱን ለማዳን እየጣረ ነውና። በሃሳብ ኃጢ አትን መሥራት ደግሞ የኃጢአትን ሃሳብ መቀበልና ማጣ ጣም፣ ሌሎች አዳዲስ ሃሳቦችንም ለመፍጠር በልቡና ውስጥ መርካት ነው። ስለዚህ ሰውየው ከጥላቻ የተነሣ በሚዋጋውና ከእርሱም ዘንድ ሊያርቀው በሚታገለው የዝሙት ሃሳብና፤ ሰውየው ተቀብሎ በሚያስተናግደውና በሚያጣጥመው የዝሙት ሃሳብ መካከል ያለው ልዩነት በዚህ መልክ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል።

በልቡና ምኞት የሚፈጸም ዝሙት

ውጊያው በሀሳብ ብቻ ከሆነና በልቡና ውስጥ ሥፍራ የሌለው ከሆነ የሚነሳ አይደለም። ነገር ግን ስሜት የተቀ ሳቀለበትና በየደረጃው እያደገና እየጨመረ የሄደ እንደሆነ እየ ከደና ኃያል እየሆነ ወደ አካላዊ ዝሙት ሊደርስ ይችላል። ይሁን እንጂ በልቡና ምኞት የሚፈጸም ዝሙት የጨለ ነገር ተጨማሪ እገዛ የሚያስፈልገው ፍላጎት ብቻም በመሆኑ ሰውየው በቀላሉ የሚያስወግደው ሊሆን ይችላል።

በመናገር ወይም በጽሑፍ የሚፈጸም ዝሙት

ይህ ዓይነቱ ዝሙት በተራክቦ ላይ ያተኮሩ ቀልዶችን ስለተራክቦ የሚያወሱ ጨዋታዎችን፣ በፍትወተ ተራክቦ ላይ ያተኮሩ ዘፈኖችን፣ ለስላሳና በፍትወተ ሥጋ የተሞሉ ንግግሮችን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህን ሁሉ አንድ ሰው በራሱና በሌሎች ሰዎች ላይ በፈጸማቸው ጊዜ ኃጢአት ይሆናሉ። በጽሑፍ የሰፈሩና ለመነበብ የበቁ እንደሆነ ደግሞ ወደ ተመሳሳይ ኃጢአት የሚመሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ የሚመሩባቸው ሁሉ ደግሞ ኃጢአትን ይሠራሉ።

ከዝሙት አንፃር የወላጆች ኃላፊነት

በቤተሰብ ውስጥ ጥፋት የሚፈጸመው ከወላጆች የልጅ አስተዳደግ ዘዴ ጉድለት በሚመነጩ ሁኔታዎች ነው። የቤተሰቡ ኃላፊ ልጆቹን ይዞ ወደፊልም ቤት ሊሄድ ይችላል። ይህ ፊልም ደግሞ የልጆችን መንፈሳዊ ንጽሕና የሚያሳድፍ፣ ዓይኖቻቸውም ለኃጢአት የተከፈቱ እንዲሆኑ በማድረግ በአመለካከታቸው ላይ ተጽእኖ የሚኖረው ሊሆን ይችላል። በአባትየው አመለካከት ግን ፊልሙ በልጆቹ አለምሮ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽእኖ ሥፍራ ሳይሰጠው ስለመልካምነቱ ብቻ ሊናገር ይችላል። ይህን ያስብ እንጂ ይህ ወላጅ አባት በእርሱና በልጆቹ መካከል ያለውን የዕድሜ ልዩነት የዘነጋና ልጆቹም በደመነፍስ ከሚመሩበት የዕድሜ ደረጃ ላይ መሆናቸውን የረሳ ነው።

ከዚህም ሌላ እርሱ በትዳር የሚኖር በመሆኑ በጊዜው የሚፈታተነው የተራክቦ ፈተና የሌለበት ሲሆን በልጆቹ ላይ ሊደርስባቸው የሚችለውን ከባድ ስሜታዊ ፈተናም ዘንግቶታል። እናም መልካም ያደረገ እየመሰለው ልጆቹን በዝሙት ስሜት እያቃጠላቸው፣ ሊያውቁትና ሊያ

ዩት የማይገባቸውን ያለጊዜው እንዲያዩና እንዲያውቁ በማድረግ ለፈተና ይዳርጋቸዋል። ስለሆነም ወላጆች ከዚህ መሰሉ ድርጊት በእጅጉ ሊቆጠቡ ይገባል።

ሌላው ዓይነት የቤተሰብ ኃላፊ ደግሞ ቤቱን ዘመናዊና ባለጥሩ ደረጃ ለማድረግ ከመፈለግ የተነሣ በቪዲዮ ፊልምና በመሳሰሉት ማደራጀት ሚስቱንና ልጆቹን ዘወትር የሚያስደስትና የሚያዝናና የመሰለው ነው። የሚያዩትንም የሚሰሙትንም በመቆጣጠር ሊያደርገው እንደሚችል በመተማመን ይናገራል፤ ነገር ግን «መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም+ መሰናክሉን ለሚያመጣው ነገር ግን ወዮለት» ተብሎ እንደተጻፈ ማስታወስ ይኖርበታል። ሉቃ.17+1።

በዘመናዊነት ሰበብ ልጆቹን ወደ ኃጢአት እደባባይ የሚጋብዝና የሚገፋፋ፣ ሃይማኖተኛነታቸውንም የሚያናንቅና የሚያጣጥል አባት ደግሞ ተጠያቂነቱና ኃላፊነቱ እጅግ ከፍተኛ ነው። ሴት ልጁን በተለያዩ ጌጣጌጥና ትባቶች በማስጌጥ የሰዎችን ሃሳብ በፍትወት እንድትማርክ የምታሰናብት እናትም ከተጠያቂነት የምታመልጥ አትሆንም፤ ምክንያቱም ይህን መሰሉ ግፊት ልጅቱ በኃጢአት እንድትወድቅ ያደርጋታልና ነው።

ከዚህ ጋር ቢተያያዝ ሊነሣ የሚችለው ሌላው ነጥብ ዝሙት ከመጥፎ ባልንጀርነትም ሊመጣ የሚችል ኃጢአት መሆኑ ነው። በመጽሐፍም «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል።» ተብሎ መነገሩ ይህን ሁሉ የሚመለከት ነው። 1ቆሮ.15+33። ይህ ክፉ ባልንጀርነት የተባለ ግንኙነትም ከሌሎች ጋር በመሆን ስለኃጢአት መነጋገርን፣ የጥፋት ስብሰባዎችን፣ አብሮ መዋልን ወዘተ የሚያጠቃልል ነው።

ይህ ኃጢአት ዝሙት ከተለመደበት ማኅበረሰብ እና ከተቃራኒ ፆታ ፈተና ሊመጣም ይችላል። የምንገኘው አስባበስንና ጌጣጌጥን በተመለከተ የተለያዩ አስተሳሰቦች በሚንፀባረቁበት ትውልድ መካከል ነው። አለባበስ ከጓላ ቀርነት ጋር ያልተያያዘ ከሆነና፤ ሰዎችም ከሃይማኖትና ከጎሊናቸው

ፍርድ ውጭ ሆነው የሚለብሱና የሚያጌጡ ከሆነ ይህን የሚያደርጉት ከዘመኑ ጋር ለመጣጣም ወይም እንዳይተቹ ብለው ሊሆን ይችላል።

ብዙውን ጊዜ ሴቶች ከሰዎች አድናቆትና ከማይጠቅም ከንቱ ውዳሴ የተነሣ ይደሰታሉ፤ በመሆኑም ራሳቸውን በቤት ላሉት ሳይሆን በውጭ ለሚገኙት ለማሳየት ሲሉ አብዝተው ያጌጣሉ። ከሁሉ ይልቅ ከአለባበሳቸውና በጌጣጌጣቸው ወንዶችን ለመማረክና ለማጥመድ በመቻላቸው አብዝተው ይደሰታሉ። ይህ ድርጊትም በጎሊናቸው ካለ ባቸው ኃላፊነት ውጭ በራሳቸው እንዲተማመኑና በወንዶችም ላይ በሚያሳድሩት ተጽእኖ እንዲኮሩ ያደርጋቸዋል። ይህን ሁሉ ሲያደርጉ በግላቸው በምኞት ላይወድቁ ይችላሉ፤ ቢሆንም ምድራዊና ዓለማዊ ለሆነ አለባበሳቸውና ጌጣጌጣቸው የተገዙና የተንበረከኩ መሆናቸውን ያውቁታል።

እነዚህን የመሰሉ ሴቶች ሁሉ በዝሙት አልወደቅንም ሊሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን በእነርሱ የተነሣ ስለ ወደቁት ነፍሳት እግዚአብሔር ይጠይቃቸዋል። ስለእነዚህ ነፍሳትም በፍርድ ቀን ቅጣታቸውን ይቀበላሉ። በዚህ አንፃርም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት። የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታሥሮ ወደጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።» በማለት የተናገረው በእነርሱ ይፈጸማል። ማቴ.18÷6–7። እንደሴቶቹ ሁሉ ራሱን በማስጌጥና በአለባበሱም ሁሉ ሴቶችን የሚማርክና ለኃጢአት የሚጋብዝ ወንድ ከፍ ብሎን በጠቀስነው የመጽሐፍ ቃል መሠረት ከመጠየቅና ቅጣቱን ከመቀበል ሊያመልጥ አይችልም።

በክርስትና ተቀባይነት የሌላቸው ግንኙነቶች

በክርስትና የሃይማኖት ሕግ የተወገዙና ተቀባይነት የሌላቸው ነገር ግን በምድራዊውና ዓለማዊው ሕግ ዘንድ ዕውቅና የተሰጣቸው ግንኙነቶች አሉ። እነዚህ ግንኙነቶች በእግዚአብሔር ሕግ ሲመዘኑ የዝሙት ግንኙነቶች ናቸው። እነርሱንም እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

1. ከሕገወጥ ፍቺ በኋላ የተመሠረተ ጋብቻ

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ፍቺ ሕግ ሲናገር «ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል» «ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላ ይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል» እያለ በመደጋገም አስገንዝቧል። ማቴ.19÷9። ሉቃ.16÷18። ስለሆነም በቤተክርስቲያን ከተፈቀደው መጽሐፋዊ ፍች ውጭ ከፍትሐ ብሔር ሕግ አንፃር የፈለገውን ዓይነት ውሳኔ ቢያገኝና በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሰው ፍችው በክርስትና ሕግ ዘንድ ተቀባይነት የለውምና በጋብቻ እንዳለ ይቆጠራል። ቢያገባም በሚስቱ ላይ ሁለተኛ እንደደረበና ኃጢአትን እንደሠራ ይቆጠራል። እግዚአብሔርም በቃሉ «ሚስቱን ፈትቶ ሌላ የሚያገባ ሁሉ በእርስዋ ላይ ያመነዝራል» ብሏል። ማር.10÷11።

ብዙ ሰዎች ፍችን ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ስለዚህም ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት ካላቸው አንድነት የላቸውም የሚለውን ለመጠቀም ሲሉ ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ፤ ይፋታሉም። በክርስትና ሕግ መሠረት ቀድሞ ወድዶ ያገባትን ሚስቱን ምክንያት ፈልጎ ይፈታት ዘንድ አይፈቀድለትም። ለሴቲቱም ቢሆን እንደዚሁ። በዝሙት ምክንያት በቀር ትዳር እንዲፈርስ ቃለ እግዚአ ብሔርም አልፈቀደምና ሁለቱም የሚታወቀት በቀድሞ ትዳራቸው እንዳሉ ነው። ለዚህ ነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።» በማለት ያስገነዘበው። ማቴ.19÷6። ሰውየው በቀድሞ ሃይማኖቱ በሕግ ያገባትን ፈትቶ ሌላዋን ለማግባት ሲል ሃይማኖቱን ቢቀይርና ቢያገባት የፈጸመው ዝሙት እንጂ ጋብቻ አለመሆኑን መጽሐፍ ተናግሯል።

ቀሳውስትም ቢሆኑ የተፈታችውን ከማግባት ሊቆጠቡና በሕገ ቤተ ክርስቲያንና በቃለ እግዚአብሔር መሠረት ሊመሩ ይገባቸዋል። በዚህ ረገድ ሕግን በተላለፈ ጊዜም

ለከፍተኛው የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ውሣኔ መቅረብ ይኖርበታል። በማንኛውም ሰው ቢሆን ከሕገወጥ ፍቺ በኋላ የሚደረግ ጋብቻ ሕገወጥና ዝሙትም መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው።

2. የተፈታችውን /የተፈታውን/ ማግባት

በክርስትና ሕግ ከሚከለከሉት ግንኙነቶች አንዱ ፈትን ማግባት ነው። እግዚአብሔርም «የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።» «እርሷም ባልዋን ፈትታ ሌላ ብታገባ ታመነዝራለች» በማለት ተናግሯል። ማቴ.5÷32፣ ሉቃ.16÷18፣ ማር.10÷12። ይህን በመሰለው ጋብቻ የተጠ ገናኙት ሁለቱም (ሴቲቱም ሆነ ወንዱ) አመንዝረዋል፤ ምክ ንያቱም ፍቺ ሊፈጸምና ጋብቻ ሊፈርስ የሚችለው ብዙ ሙት ወይም በሌላ ሕጋዊ ምክንያት ብቻ ነውና። ፍቺ ከዝሙት በስተቀር በሌሎች ምክንያቶች ቢደረግ ሕጋዊ አይደለም፣ የቀደመው ጋብቻም በሕጋዊነቱ የታወቀ ሆኖ ይቀያል። በዚህ ረገድ ሴቲቱ ለሁለት ባሎች ተዳረች ማለት ነውና አመንዝራ ሆናለች።

3. ዘመድን ማግባት

ሰው እንዲያገባት በሕግ መንፈሳዊ የተከለከለውን ሴት ቢያገባ አመንዝራ ይሆናል። በዚህ መሠረት ዘመዱን እንዲያገባ ለማንም አልተፈቀደምና ይህን የሚያደርግ አመ ንዝራ ነው። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ከሄሮድስ ጋር የተጋፈጠበት ታሪክ ለዚህ ትምህርት ጥሩ ምሳሌ ሊ ሆነን ይችላል። «የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም» በማለት ሄሮድስን እንደነቀፈው በዚህም የተነሣ በሰማዕትነት ማለፉን ቅዱስ መጽሐፍ መዝግቦታል። ማር.6÷18። በዘሌዋውያን የተዘረዘረው ሁሉ ደግሞ ተጨ ማሪ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል። ዘሌ.18÷6–18። ዛሬም ቢ ሆን ቤተክርስቲያን ይህን የመሰለውን ጋብቻ አትፈቅድም የዝሙት ግንኙነት ነውና።

4. ከአንድ በላይ ማግባት

በቤተክርስቲያናችን ሕግ መሠረት ከአንዲት ሚስት በላይ ማግባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ከአንዲት ሚስት በላይ የሚያገባ ሰው አመንዝራ ይባላል፤ ይህን የመሰለው ግንኙነትም አመንዝራነትና ዝሙት ነው።

የዝሙትን ጸር እንዴት እንቋቋመው ?

ይህን የዝሙት ኃጢአት የምንከላከልባቸው ዘዴዎች በሁለት ሁኔታዎች ማለትም በአሉታዊና አዎንታዊ ሁኔታዎች ዙሪያ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው። ዝሙትን ለመከላከል ትኩረት የሚደረግባቸው አሉታዊ ሁኔታዎች ለኃጢአት የሚያነሣሡ ማናቸውንም ነገሮች ኃጢአትንና ሥ ራፈትነትን መሸሽ ናቸው። አዎንታዊ የተባሉት ሁኔታዎች ደግሞ ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የኃጢአትን ፍቅር በማ ስወገድ ስሜትን ሁሉ ለመንፈሳዊና ለተቀደሰ ነገር በማዋል በፍቅረ ቢጽ እንዲጠመድ ማድረግ ነው። ስሜትን በማ ነሣሣት ወደ ኃጢአት የሚመሩ ነገሮችን ሁሉ ማስወገድና መሸሽ የዝሙትን ኃጢአት ለመከላከል ግሩም ዘዴ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም መጽሐፍ «በጉያው እሳትን የሚታቀፍ+ ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? በፍሕም ላይ የሚሄድ+እግሮቹስ የማይቃጠሉ ማነው? ወደሰው ሚስት የሚገባም እንደዚሁ ነው» በማለት ዝሙት ሊሸሹት የሚገባ ክፉ ኃጢአት መሆኑን በእሳት መስሎ እያደነቀ ተናግሯ ል። ምሳ.6÷27–29።

ሰው በተለያየ ሁኔታ ለኃጢአት ሊጋለጥ ይችላል፤ ይህም ፍላጎቱ በውስጡ አለ ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም። ነገር ግን ለኃጢአት መጋለጥ ብርቱ ጥንቃቄ ካልተደረገ እጅግ አደገኛ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። በሆነው አጋጣሚ ለኃጢአት በተመቻቸ ሁኔታ የተገኘ ሰው በልቡናው የዚያ ኃጢአት ፍላጎት ያለው እንደሆነ ልቡናው ንጹሕ ነው ለማለት አይቻልም። እንዲህ ዓይነት አጋጣሚ የተፈጠረበት ጥበበኛ ሰው ግን ከኃጢአት በመሸሽ ራሱን ለማ

ዳን ይጥራል እንጂ በድፍረት ከኃጢአት ጋር አይጋፈጥም። በዚህ መሠረትም ለዝሙት ከሚገፋፉና ውድቀትን ከሚያስከትሉ ግናኙውም ነገሮች መሸሽና መጽሐፍም «እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ» ያለውን ቃል ማስታወስ ይገባል። ራእ.2+5።

ወደ ኃጢአት ከሚጋበዙና በራሳቸው ኃጢአት ከሆኑ ስብሰባዎች፣ ጉብኝቶች፣ ምንባቦች፣ ጽሑፎች፣ ድምፆች እንዲሁም ዕይታዎች ሁሉ መሸሽ ያስፈልጋል። ከማይገባና ከክፉ ባልንጀርነትና ግንኙነት ሁሉ መሸሽ ይገባል። ባልንጀራ ሊሆን የሚገባው ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ የሚያቀርብ መሆን ይኖርበታል። በሌሊት የሚያስቸግሩ መጥፎ ሕልሞችን በቀን እያስታወሱና ስለእነርሱም እያሰላሰሉ ጎሊናን ከ ማስጨነቅ መቆጠብ ጠቃሚ ነው፣ ይህን ከራስ ለይቶ ለመ ማስወገድ እንደመውደቅ ይቆጠራል።

ሰው ኃጢአቱን እያሰበ ራሱን በሚወቅስበት አጋጣሚ ወደጎሊናው ከሚመጡበት የኃጢአት ሃሳቦች መጠንቀቅ አለበት። ስለእነዚህ የቀደሙ ኃጢአቶች በጥቅል በጥቅሉ ከማ ውሳት በቀር በተልቀት ስለ እያንዳንዱ ኃጢአት ማሰብ የለበችም፣ ምክንያቱም ልቅ ሃሳብ የምኞት ኃጢአትን ወደ ማስከተል ደረጃ ሊያድግ ስለሚችል ነው። በመሆኑም ኃጢ አትን በማሰብ የተጀመረው መፀፀት ወደሌላ አደገኛ ስሜት እንዳይለወጥ ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ከኃጢአት አካባቢና ከራሱም ከኃጢአት በአካል መሸሽ ያስፈልጋል። ቅዱሳን አበው «ወደ ኃጢአት የቀረበ ሁለት ውጊያ አለበት፣ እንዱ ውስጣዊ ሁለተኛው ደግሞ አፍአዊ» በማለት ተናግረዋልና ፈጽሞ ወደኃጢአት አለመቅረቡ አግ ራጭ የሌለው ነው። ወደኃጢአት የቀረበ በቀላሉ ይወድቃል። በጉድጓድ አፍ ላይ እንደቆመና ጠላት በቀላሉ ገፍትሮ ወደጉድጓድ ሊጥለው እንደሚችል ሰው ነው፣ ከጉድጓድ ሩቅ ቢሆን እግዚአብሔር ከጠላቱ በፊት ደርሶ የሚያድነው ታዳኒ ይልከለትና ያድነው ነበርና።

ብቻችነት ለመውደቅ የሚያበቃ ከሆነ ከራስም መሸሽና ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ብቻ ችነት እንዳይመስለን ያስፈልጋል። ብቻችነት ሰው ከሰይጣንና

ከርኩስ ሃሳብ ጋር በመሆን ከእግዚአብሔር የሚለይበት ሁኔታና ጊዜ ነው። እንዲህ ባለው ሁኔታ ብቸኛ መሆን እደገኛ ስለሆነ ከራስ ብቸኝነት ሸሽቶ ከሰዎች ጋር መሆን ይመረጣል።

ዝሙትን ከማሰብ መሸሽ

በመጀመሪያ ደረጃ ይህን የዝሙት ሃሳብ ከሚያመጡ ሁሉ መሸሽ ያስፈልጋል። ይህ የኃጢአት ሃሳብ ወደ አእምሮ በመጣ ጊዜ በጽኑ መቃወምና ቦታም አለ መስጠት ተገቢ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን» ሲል የተናገረውን ቃል ዘወትር ማስታወስ ያስፈልጋል። 2ቆሮ. 10+5። አእምሮን በመንፈሳዊ ሃሳብ ማለትም በጸሎት፣ በማ ንበብ፣ በተዘከሮተ እግዚአብሔር፣ በማንኛውም ምክኒ ህብታዊ ወይም ማኅበራዊ ጉዳይ እንዲጠመድ በማድረግ የኃጢአትን ሃሳብ መቋቋም ይቻላል። የጎለኛው ሃሳብ ጠቃ ሚና ትኩረትን የሚጠይቅ በሆነ መጠን የቀድሞውን የኃጢ አት ሃሳብ ከጎሊና የማጥፋት ኃይል ይኖረዋል።

ክፉውን የኃጢአት ሃሳብ በሌላ የተቀደሰ ሃሳብ በመ ተካት መቋቋም ካልተቻለ በሥራ ራስን በመጥመድ ወይም ደግሞ ጊዜን በማይጎዳ ሌላ ተግባር ላይ ማዋል ጠቀሜታ አለው። ይህም የሰውየው ጎሊና ብቻውን ለክፉ የዝሙት ሃሳብ እንዳይጋለጥና እንዳይጠቃ ይከላከለዋል። የኃጢአት ሃሳብ በጎሊናው እየተመላለሰ የሚያስጨንቀው ሰው ከሌ ሎች ሰዎች ጋር በተለያዩ አርእስት ላይ በመነጋገር ሊያ ስወግደው ይችላል፤ አእምሮው በአንድ ጊዜ ስለዝሙት ሊያ ስብና ከሌላ ሰው ጋር ለመነጋገር አይችልምና።

ከዝሙት ማዕበል ጋር ከመጋፈጥ መሸሽ

በመዝሙረ ዳዊት «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ፥» እንደተባለው ከመውደቅ ይልቅ ሊጥል ከሚችለው የኃጢአት ማዕበል መሸሽ ያስፈልጋል። መዝ.

1÷1–2:: ምናልባት ቀልደኞች ባልንጀሮቹ ሰውየውን አብሯ ቸው እንዲጫወት ሊጋብዙት ይችላሉ፤ እምቢ ቢላቸው ሊተ ቹት ይችሉ ይሆናል፤ ቢሆንም ብቻውን ወደእነርሱ በመሄድ በሃ ላባቸው ማዕበል የተነሣ እንዳይሸነፍና አብሮም እንዳይጠፋ ጠን ከሮ ሃላባቸውን መቃወም ይኖርበ ታል:: ዐዋቂ ሰው ማንም ስለእርሱ የፈለገውን ቢናገር መን ፈሳዊ ዓላማውን በጽኑ ሊጠብቅ ይገባል:: ሰዎች ስለእርሱ የሚናገሩትንም በመፍራ ት ለኃጢአተኝነት በሩን መክፈት የለበትም፤ ምክንያቱም የሰው ትችት የሚፈልገውን ፍጹም ነት ሊያመጣለትና በፍርድ ቀንም ይቅርታን ሊያስገኝለት አይችልምና:: ዓለምን በማንኛውም ገጽታዋ ቢሆን መከተልና ለፈቃዷም መን በርከክ የማይገባ መሆኑን ሲገልጽ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ይህን ዓለም አትምሰሉ» በማለት አስገንዝቧል:: ሮሜ. 12÷2:: በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ሰው ንጽሕናን ገን ዘብ ማድረግ እንጂ ዓለምን መስሉ ለዓለም ተገዝቶ መኖር አይገባውም::

ከመረታት መጠንቀቅ

እያንዳንዱ የኃጢአት እርምጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚመራ በመሆኑ ከመጀመሪያው እርምጃ አንሥቶ መጠ ንቀቅ ይገባል:: ምናልባት ከመጀመሪያው እርምጃ ራስን በመቆጠብ የመጀመሪያውን እርምጃ ውጤት ለማስቀረት ይችላልና:: ለራሱም «አሁን ወድቄአለሁና ዋጋ የለኝም» አይበል:: ተስፋ መቁረጥ የሰውን ሃሳብ ደካማ በማድረግ ለውድቀትና ለመረታት እንዲበቃ ያደርገዋልና ከዚህ መጠ ንቀቅ ያስፈልገዋል::

ኃጢአት ሂደቱን በመቀጠል በተግባር እስኪፈጸም ድረስ መፈታተኑን አያቋርጥም:: ስለሆነም ኃጢአትን በመፈጸም በመጨረሻው የውድቀት ደረጃ እስኪያደርስና እስኪረታ ድረስ ዕድል መስጠት አይገባም:: በማየት ወይም በመስማት ዝሙትን የፈጸመ ሰው ንስሐ መግባትና ዳግመኛ በሃላቡ ወደ ዝሙት ከመጓዝና ዝሙትን በጎሊና ከማ መላለስ

መቆጠብ ይኖርበታል:: በሃሳብ ዝሙትን ቢሠራ በልቡ ወደ ማመላለስ፣ ወደመሳሙትና ወደመመኘት እንዳይደርስ መሸሽ አለበት:: በምኞት ቢወድቅ «...እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከማፍሰስ አልተቃወማችሁም» ያለውን በማስ ታ ወስተጋድሎው ከባድ መሆኑን ዐውቆ በጽኑ ሊጋቻ ወመው ይገባል:: ዕብ.12÷4:: ቅዱስ ይስሐቅ የተባለው የቤተ ክርስ ቲያን አባት «ድል ያደረጉት ወታደሮች እነዚያ አክሊል የተቀዳጁት ብቻ አይደሉም፤ ጠላት የደበደባቸውና አጥን ታቸውን የሰበረባቸውም ጭምር ናቸው እንጂ፤ እነርሱ ሳይሸነፉና እጃቸውን ሳይሰጡ በጽናት ይታገሉና ይዋጉ ነበ ርና» ሲል እንደተናገረው ሰው ሁሉ በጽናት ዝሙትን ሊቃወመው ይገባል::

ከሥራ ፈትነት መሸሽ

ሥራ ፈትነት የወጣቶች ጠንቅና የነፍሳቸው ጠላት ነው:: በተቃራኒው ደግሞ ባተሌ /የሚሠራ/ ሰው ስለዝሙት ለማሰብ ጊዜ የለውም:: በማይጠቅሙ ስብሰባዎች ለመሳተ ፍም የሚያባክነው ጊዜ የለውም:: ስለሆነም የዕረፍት ጊ ዜውን እንኳን ለዕረፍት በሚስማማ ሥራ ስለሚያሳልፈው በአብዛኛው በኃጢአት አይጠቃም::

ስለሚጠብቀው የወደፊት ተስፋ የሚያስብና ከዚያም ለመድረስ ተግቶ የሚያጠና ተማሪ ስለዝሙት የሚያስብበት ጊዜ የለውም:: አእምሮውም ኃጢአትን ከማሰብ በማራቁ በጥናቱ ውጤታማ ሊሆን ይችላል:: ከዚህም በመነሣት የጊ ዜንና የሕይወትን ትርጉምና ዋጋ ዐውቆ እያንዳንዷን ደቂቃ በሚጠቅም ነገር ላይ በማዋል ለኃጢአት ጊዜ ከመስጠት መቆጠብ ያስፈልጋል::

ጊዜን በሥራ፣ በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ስብሰባዎች፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ፣ መንፈሳዊ ዕውቀትን በመ ገብየት የተያዘ በማድረግ በሥራ ፈትነት ጠንቅ ከሚመጣ የኃጢአት ሃሳብ ለማምለጥ ይቻላል:: እነዚህ ሁሉ አእምሮን ስለኃጢአት እንዲያስብ ዕድል ይነፍጉታል:: ከዚህም በላይ አብዝቶ በመሥራት ለተራቡ ፍላጎት የሚቀሰቅሰውን የሰው ጉልበትና ኃይል በመቀነስና ሥጋን በማድከም ከዝሙት

ማዕበል ለማምለጥ ይቻላል። የእነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሁኔታዎች ሁሉ ድምር ወደአምንታዊ የዝሙት መከላከያ ዘዴ ያደርሰናል።

ፍቅረ እግዚአብሔር

ፍቅረ እግዚአብሔር ያደረበት የሰው ልቡና የኃጢአት ማደሪያ ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔር ፍቅር ሰው ኃጢአትን እንዲጠላውና እንዲንቀው ያደርገዋል። ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ መንፈሳዊ ስሜቱ ስለሚበረታ ኃጢአትን ለመቋቋም ኃይል ያገኛል። ሰውም የዝሙትን ኃጢአት ለማስወገድ ከዝሙት ምክንያቶች መሸሽ ብቻውን በቂ አይደለም፣ ውስጣዊ ልቡናው ኃጢአትን በሚያስወግድለት ፍቅረ እግዚአብሔር የታነጸና የጸና መሆን አለበት።

ይህን ፍቅረ እግዚአብሔር ማ ትም የጸጋ ምንጭ በሆኑት በጸሎት፣ በጾም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመርመር፣ ቃለ እግዚአብሔርን በማንበብ፣ የቅዱሳንን የተጋድሎ ታሪክ በማጥናት፣ ያለማቋረጥ በማስቀደስ፣ መንፈሳዊ ጉባኤያትን በመከታተል፣ ራስን በመመርመርና በመውቀስ፣ በመናዘዝ፣ ንስሐ እየገቡ ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል፣ መንፈሳዊ ግንኙነቶችን በማጠንከርና መልካም አርአያዎችን አብነት በማድረግ የሚመጣ ነው።

እነዚህ ሁሉ መንፈሳውያን መንገዶች ልቡናን ከፍቅረ ኃጢአት በማንጻት ውስጣዊ ጥንካሬ እንዲያገኝና በፍቅረ እግዚአብሔር እንዲሞላ ያደርጉታል። ስለዚህም የዝሙትና የሌሎች ኃጣውእ ጸር ቢያጋጥመው እንኳ ታግሉ ያሸንፋል፣ የሚጥለው መሰናክል ቢመጣበትም ወዲያው ነቅቶ በመነሣት በንስሐ ሳሙና ከራሱ ያስወግደዋል። ፍቅረ እግዚአብሔር ኃጢአትን ለማስወገድና ውጊያውንም ተቋቁሞ ለማሸነፍ የልቡና ብርታትንና ጽናትን የሚሰጥ በመሆኑ በፍቅረ እግዚአብሔር ጸንቶ መኖር ይገባል። የዝሙትን ጸር ለመከላከል እውነተኛው ዘዴና መሣሪያ በፍቅረ እግዚአብሔር ጸንቶ መኖር መሆኑን ዐውቆ ይሽንኑ ገንዘብ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

ኃይልና ስሜት

የዝሙት ጸር /ውጊያ/ በሁለት ሥጋውያን ገጽታዎች ላይ ያነጣጥራል። እነዚህም የሰውነት ኃይልና ስሜት ናቸው። ከተጠራቀመ አካላዊ ሙቀት የሚወጣው ኃይል በወጣትነት ውስጥ በጉልህ ሲንፀባረቅ ይታያል፣ የወጣትነት ምልክትም ነው። ይህ የወጣትነት ኃይል ከእምቅና ያተጠራቀመ ስብ የሚወጣ በመሆኑ በተገቢው መንገድ በትዕግሥትና በጥንቃቄ ካልተያዘና ራስን በመግዛት ካልተመራ በቀላሉ ሊያጠፋ እንደሚችል እሳተ ገሞራ ከፈነዳ መመለሻው ከባድ ነው። ይህ አደገኛ የሥጋ ኃይልም በአምልኮ ተግባራት ማለትም በጸም፣ በጸሎት በስግደት፣ በመንፈሳዊ አገልግሎትና በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚከናወን የትሩፋት ሥራ በመታገዝ በቁጥጥር ሥር ካልዋለ ወይም ካልተወገደ ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ ፍትወተ ሥጋ በማደግ በዝሙት ሊጥል ይችላል። ይህን ኃይል ለመቋቋም አማራጭ የማይገኝለት መፍትሔ በሃይማኖት መኖርና ለሕግጋተ እግዚአብሔር መገዛት ነው። በዚህ የሥጋን ፈቃድ ሁሉ ለመቆጣጠርና ውጊያውንም ለመቋቋም ይቻላል።

ስሜታዊነትም የወጣትነት ዕድሜ ዋነኛ ነፀብራቅ ነው። ይህ የወጣትነት ስሜትም በአግባቡ ካልተያዘ፣ በቃለ እግዚአብሔር ካልተሞረደና ካልለዘበ በወጣቱ የወደፊት ሕይወት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል። ከዚህ ተፈጥሯዊ ስሜታዊነትና ችኩልነት ውጭ በሆኑ ሌሎች ምክንያቶችም ወጣቱ ፍቅር፣ መልካም ምግባር፣ ርኅራኄና አምንታዊ የሆነ የስሜት ለውጥ ሳይኖረው ይችላል። የዚህን አሉታዊ ውጤት በወጣትነት ሰበብ ለማካካስ መሞከር የተሳሳተ ነው።

ስሜታዊነት መፍትሔ ካልተሰጠው ሰውየውን በቀላሉ በኃጢአት ሊጥለው ይችላል። ለምሳሌ የተራከቦ ፈቃድ ለሚዋጋው ሰው ይህንን ስሜቱን የሚቋቋምበት መፍትሔ ካልተሰጠው ይህን ስሜቱን ለማርካት ,ሲል በዝሙት ሊወድቅ ይችላል። የወጣቶች ስሜት በፍጥነት መርካት

የሚፈለግ ስለሆነ ጊዜ ሰጥቶ ከመተው ይልቅ በጠንካራ መንፈሳዊ ዘዴ እንዲሰክንና እንዲረግብ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ለማድረግ የሚመረጠው ፍቅረ እግዚአብሔር በወጣቱ ልቡና ውስጥ ሥፍራ እንዲኖረው የሚያስችል ዘዴን መጠቀም ነው። ይህ ፍቅረ እግዚአብሔር ም ሰዎች ገንዘብ ባደረጉት ጊዜ ቤተሰባቸውን፣ ባልንጀራ ዎቻቸውን፣ ሀብታቸውን፣ ሥልጣናቸውንና ማንኛውንም ነገር በመተው ሰማያዊውን ምሥጢር ብቻ በማሰብ እንዲ ኖሩ የሚያደርግ ታላቅ መንፈሳዊ ኃይል ነው።

ከዚህ ፍቅረ እግዚአብሔር ጋር ፍቅረ ቤተክርስቲያን ለቤተክርስቲያን መቆርቆር፣ ለሰው ልጆች ዘለዓለማዊ ድኅነት በጽኑ መጨነቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቃቸውንና የእርሱ ገንዘብ መሆናቸውን መሻት አለ። ስለዚህ የወጣቶች በአገልግሎት መጠመድ ከአካላዊው ይልቅ ጥልቅና ከፍተኛ ለሆነው የመንፈሳዊ ስሜት እርካታ ምክንያት ነው። በጠ ቅላላው አጋን ለማግኘት የሚተጉ፣ ባእግዚአብሔር ፍቅር የተጠ መዱ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚያበረክቱ ሰዎች ለዝሙትና ለተራክቦ ስሜት በቀላሉ ሊሸነፉና ሊወድቁ አይችሉም።

ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ በደከመ ጊዜ ኃጢአት በእርሱ ላይ ጦሩን መሰበቅ ይጀምራል። ስለዚህ ስሜትን ለመቆጣጠር እንዲቻል በሚረዳ መንፈሳዊ አገልግሎት ራስን ጥሙድ በማድረግ በፍቅረ እግዚአብሔር ጸንቶ መኖር የዝሙትን ኃጢአት ለመቋቋምና በአሸናፊነት ለመወጣት ጠ ቃሚ ነው።

የንጽሕናን ሕይወት ገንዘብ ለማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ያስፈልጋል። ይህን የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ማግኘት የሚቻለው ደግሞ በጽኑ መንፈሳዊ ኑሮና በማያቋርጥ የጸሎት ሕይወት ነው። ቸሩ ፈጣሪአችን እግዚአብሔርም በኃጢአት የወደቁትን በመታደግ ለቅድስና እንደአበቃቸው ሁሉ ዛሬም ቢሆን በትሕትና የሚጋደሉትንና ረዳትነቱን የሚሹትን ሁሉ ለመታደግ ፈቃዱ ፍጹም ነውና እርሱን ጥ በማድረግ የዝሙትን ኃጢአት ለመቋቋም መዘጋጀት ያስፈ ልጋል። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን።

ክፍል ስምንት

ሰባተኛው ትእዛዝ

«አትስረቅ»

ዘጸ.20÷15።

ሌብነት ምንድን ነው?

በአጠቃላይ ሲታይ ሌብነት የሌላውን ሰው ንብረት ሙሉድ ብቻ ሳይሆን የሌላውን ንብረት ያለባለቤቱ ፈቃድ መስረቅ ነው። መጽሐፍ «ወደባልንጀራህ ወይን ቦታ በገባህ ጊዜ እስክትጠግብ ድረስ ከወይኑ ብላ፣ ወደ ዕቃህ ግን ከእርሱ ምንም አታግባ። ወደ ባልንጀራህ እርሻ በገባህ ጊዜ እሸቱን በእጅህ ቀጥፈህ ብላ፣ ወዳልታጨደው ወደባልንጀራህ እህል ግን ማጭድ አታምጣ።» በማለት የተናገረው ይህንን የሚያብራራ ነው። ዘዳ.23÷24-25። ሙሉድ በባለንብረቱ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እን ደሆነ ሌብነት ሊባል አይችልም። ስለዚህ ሌብነት ባለ ንብረቱ ሳይፈቅድና ሳያይ የሰውን ንብረት ለራስ ማድረግ ወይም መስረቅ ነው። ሌብነት ባለንብረቱ ሳያይና ሳይ ፈቅድ በድብቅ የሚደረግ ዘረፋ ነው ለማለት ይቻላል። ይሁዳ ደቀመዛሙርቱ ሳያውቁ ደብቆ ከሙዳየ ምጽዋቱ ይሰርቅ እንደነበር። ዮሐ.12÷6። ሌባ የሚሰርቀው ባለቤቱ ተኝቶ ወይም ሳይኖር ወይም ደግሞ በምሥጢርና በድብቅ ነው። ከሌብነት ጋር አብሮ ተደራቢ ኃጢአት ደግሞ አለ። መዋሸት። በአጠ ቃላይ ሌብነት ሌሎች ሰዎችንና ንብረታቸውን ካለማክበር የመነጨ በሰዎች ላይ የሚፈጸም ጥፋት ነው።

ሌብነት የሚገልጠው ሌባው ሰው የማይታመን መሆኑና አስጠያፊ ተግባር ላይ መሠማራቱን ነው። በዚህም የተነሣ በክፉ ጠባዩ ሰዎች ያገልሉታል፣ ከእርሱም ይጠነቀቃሉ፣ እርሱም ደግሞ ራሱን በሰዎች መካከል የማይጠቅምና የተጠላ አድርጎ በማሰብ ይሸማቀቃል። ሌብነት ሌባው ሰው ያለውን ነገር እንኳ ሳይቀር የሚያቃጥል እሳት ነው። ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሰርቆ ያገኘው ንብረት በሕጋዊነት ያገኘውንም ንብረት የተሰረቀ ሊያስመስልበት ይችላል። የተበከለ ምግብ ወደ ሆድ ውስጥ ገብቶ ንጹሑን ምግብ ይዞት እንደሚወጣ፣ ሌብነትም የተበከለ ጠባይ በመሆኑ በሰዎች ዘንድ የተጠላና የረከሰ የእግዚአብሔርንም ሕግ የሚፃረር ከባድ ኃጢአት ነው። «አትስረቅ» ተብሎ ሕግ መሠራቱም ስለዚህ ነው።

አትስረቅ የሚለው ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊትም ስርቆት የተከለከለና የተወገዘ የተጠላም ክፉ ምግባር ነበር። ላባ ወደ ያዕቆብ ወጥቶ «ጣዖቶቼን ለምን ሰረቅህ?» ብሎ በጠየቀው ጊዜ ያዕቆብ በመበሳጨት» «ማንም የአንተን ጣዖት ቢ ወስድ ይዞም ቢገኝ በሕይወት አይኑር» ብሎ የመለሰው ስርቆት የተጠላ ስለነበር ነው። ዘፍ.31+30–32። የሰረቀ ሰው መኖር አይገባውምና እንዲገደል መደረጉን መጽሐፍ መዝግቦታል። በዮሴፍና በወንድሞቹ ታሪክም ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ክስተት ተፈጽሟል። ወንድሞቹ የእርሱን ዋንጫ ሰርቃችኋል በመባላቸው እጅግ ተበሳጭተው በመ ርህ «ጌታዬ እንደዚህ ያለውን ቃል ለምን ይናገራል? ባሪያዎችህ ይህን ነገር የሚያደርጉ አይደሉም። ...ከጌታህ ቤት ወርቅ ወይም ብር እንዴት እንሰርቃለን? ከባሪያዎችህ ጽዋው ዮተገኘበት እርሱ ይሙት፣ እኛም ደግሞ ለጌታችን ባሪያዎች እንሁን።» ብለው የተናገሩት ሌብነት በዚያ ዘመን የተወገዘ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ዘፍ.44+7–9።

ስርቆት አሳፋሪ ኃጢአት ነው። የጨለማ ሥራና ኃጢአተኛውም የሚናቅበት ስለሆነ ከሰው ዘንድ ወጥቶ ሊጣል ይገባዋል። ሌባው ስርቆቱን ለመፈጸም ሲል መዋሸቱ የማይቀር ቢሆንም የሰረቀ መሆኑን የማይዋሽ ሌባ የለም።

በዚህ መልክ ባለንብረቱን ለማታለል ሲል ከመስረቁ በፊት ወይም በኋላ ሊዋሽ ይችላል። ለሚያየው ወይም ለሚጠረጠረው ለማንም ቢሆን ሊዋሽ ይችላል። ውሸት የስርቆት ጠለያ ነውና ሌባው ኃጢአቱን በሚናዘዝበት ጊዜ መስረቁን ብቻ ሳይሆን ለመስረቅ ሲል ወይም መስረቁን ለመደበቅ ሲል መዋሸቱንም ጭምር መናዘዝ አለበት።

የተሰረቀው ከማን ነው?

የድህውን ወይም የእጓለማውታን ወይም የመበለቲቱን ልጅ፣ ገንዘብ ወይም ንብረት መስረቅ እጅግ የከፋ ኃጢአት ነው። ተስፋ ከሌላቸው መስረቅ የጎረሱትን ከአፍ እንደመንጠቅ ያለ የከፋ ጭካኔ ነው። በቅዱስ መጽሐፍም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሐፍት ፈሪሳውያንን «እናንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን... የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ ወዮ ላችሁ፥ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ።» በማለት መና ገሩ ከድህውና ከመበለቲቱ መቀማት የከፋ ኃጢአት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ማቴ.23+14። ከድህው መስ ረቅም ከዚህ የተለየ አይደለም። የስርቆት ከባድነት የሚ ለካው በተሰረቀው ዕቃ ዋጋ ሳይሆን የተሰረቀው ዕቃ ለባለ ንብረቱ በሚሰጠው ጥቅም ነው። ከችግረኛው መስረቁ በሌ ባው ልቡና ምንም ዓይነት ሰብአዊነትና ርኅራኄ የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

የዕለት ጉርሱን ማግኘት ከማይችለው ችግረኛ አራጣ መጠየቅም የሰውየውንና የልጆቹን የዕለት ጉርስ እንደ መስረቅ ይቆጠራል። ይህን ሰው ከመርዳት ይልቅ አራጣ እንዲከፍል መጠየቅ ጭካኔ የተሞላበት ኃጢአት ነው። አራጣ መቀበል ከጭካኔ የመነጨ የሌብነት ዓይነት ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔርም እንደመያዣ ሁሉ አራጣንም የከለከለው «ከአንተ ጋር ለተቀመጠው ለወገኔ ለድህው ገንዘብ ብታ በድረው፥ እንደባለ አራጣ አትሁን፥ አራጣም አትጫ ንበት።» «ወንድምህ ከአንተ ጋር ይኖር ዘንድ ከእርሱም ምንም ወለድ ወይም ትርፍ አትውሰድ፣ ነገር ግን

አምላክህን ፍራ፤ ብርሀን በወለድ አታበድረው፣ መኖሀንም በትርፍ አትስጠው::» በሚል መናገሩ አራማና ወለድ ከደሀው እንደመሰረቅ የሚቆጠሩ ስለሆነ ነው:: ዘጸ.22÷25–26:: ዘሌ. 25÷35–37:: እንግዲህ በአራጣ ማበደር የሌብነት ሌላ ገጽታና ርኅራኄ የጎደለው ድርጊት ከሆነና ከተከለከለ የሰው ቤት ሰብሮ ገብቶ ዉስጤ ሳያይ መስረቅማ ምንኛ የከፋና አሰቃቂ እንደሚሆን ግልጽ ነው::

ድህውን ሰው መዝረፍና ሀብቱን መስረቅ ይህን ያህል የጭካኔ ተግባር ከሆነ የእግዚአብሔር የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ንብረት መስረቅና ንዋየ ቅድሳቷን መዝረፍም ምንኛ የባሰ ጭካኔ ይሆን? የሚጸልይ ሰው መስሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገባ በኋላ ንዋየ ቅዱሳቱን፣ ታቦቱን፣ ሥዕሎቹን ወዘተ መስረቅ እጅግ አሳዛኝና የሚዘገንን ኃጢአት ነው:: ማንም ሰው ወደቤተ እግዚአብሔር ገብቶ ይሰርቃል ተብሎ አይገመትም፣ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሁሉ ንዋይ ቅዱስ ነውና ወደዚያ የሚመጣውም በፈሪሃ እግዚአብሔርና በት ኅትና ሆኖ ድኅነቱን ፈልጎ ነውና በዚህ ሁኔታ ተመሳስሎ ወደ ተቀደሰው ቤተ ጸሎት ከመጣ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ሻ ማ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ አልባሳትንና ንዋያተ ቅድሳትን የሚሰርቀው ሰው ምን ይባላል? የቤተ ክርስቲያንን ንብረት ሰርቆ ለራሱ ቤትና ኑሮ የሚያደርገውን ሰውስ ምን እንለዋለን? ዕውቀት ፍለጋና ከፍቅራችን ጽናት የተነሣ ነው በሚል ሽፋን ከየገዳማቱና አድባራቱ ንዋየ ቅድሳትን በድብቅ እያወጡ ለባዕዳን የሚሸጡትንና ከሀገር የሚያሸሹትን ሌቦችስ ምንድን ነው የምንሳቸው? እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች እንግዲህ በየደረጃው የተወሳሰቡ ኃጢአቶች ናቸው::

ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚሰርቅ ሰው ነው:: ይህም አሥራት በኩራትና ቀዳምያትን በታዘዘው መሠረት ባለማውጣት የሚፈጸም ነው:: ይህን በተመለከተ ነቢዩ ሚልክያስ «ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: እናንተ ግን:– የምንመለሰው በምንድር ነው ብላችኋል:: ሰው እግዚ አብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም:– የሰረቅንህ በምንድር ነው ብላችኋል:: በአሥራ

ትና በበኩራት ነው፤ በቤት ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራ ቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ ...በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚ አብሔር::» በማለት የተናገረው ይህንኑ የሚያብራራ ነው:: ሚል.3÷7–10:: ይህ ከእግዚአብሔር የተሰረቀ ገንዘብ፣ ከድሆች የተሰበሰበ፣ ለተገቢው ባለቤቱ ያልተሰጠ የዓመፃ ገንዘብ ነው::

በዚህ ዓይነት የእግዚአብሔር ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያንና ከሰዎች እንደሚሰረቅ ሁሉ የእግዚአብሔር ጊዜም ይሰረ ቃል:: ሰው በሕይወት ዘመኑ ሲኖር ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ሊያውለው የሚገባ ነገር ግን ለሌላ ጉዳይ የሚጠቀምበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰረቀ ነው:: በሳ ምንቱ ውስጥ የእኛ ያልሆነ አንድ የእግዚአብሔር ቀን አለ፤ ይህም ዕለተ ሰንበት ወይም የጌታ ቀን ነው:: ይህ ቀን ለእግዚአብሔር ክብር ለአምልኮቱ ካልሆነ ለሌላ ተግባር እንዳይውል የተከለከለ ነው፤ ለራሱ ጉዳይ የሚጠቀምበት ማንም ቢኖር የእግዚአብሔርን ጊዜ ሰርቋል:: በየዕለቱ የተወሰነው ሰዓት ለጸሎት፣ ለመንፈሳዊ ተግባር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመመርመር፣ ጉባኤያትን ለመካፈል ወዘተ መዋል ይኖርበታል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ቀኑን ሙሉ ተግባረ ሥጋችንን ስንፈጽም ብንውል ከእግዚአብሔር ጊዜ ሰርቀናል ማለት ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ሀብት አሥራቱን በኩራቱን ቀዳምያቱን የማግኘት መብት እን ዳለው ሁሉ ከጊዜው የመጀመሪያውን ማግኘት ይገባዋል፤ ይሽውም የአምልኮና የምስጋና ጊዜ ነው:: ነቢዩ ዳዊት «አምላኬ አምላኬ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች» በማለት የተናገረው ለዚህ ነው፤ የእግዚ አብሔርን ጊዜ ለእርሱ መስጠት ይገባልና:: መዝ.62÷1:: ማለዳ ተነሥቶ ዕለቱን በአምልኮ ሥራ፣ በጸሎትና በምስጋና መጀመር ሲገባ ቀኑን ሙሉ በተግባረ ሥጋ መዋል የእግዚ አብሔርን ጊዜ መስረቅ ነው::

ከዚህ ጋር በየዓመቱ አንድ ጊዜ የሚመጡት የበዓላት ቀናት ለምሳሌ ልደት፣ ጥምቀት፣ ሰሙነ ሕማማት፣ ትንሣኤ ፍልሰታ የመሳሰሉትና ሌሎችም እግዚአብሔርን

የምናመለግንባቸው በጸሎት፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመ
ልከት፣ ወዘተ የምንጠመድባቸው ቀናት ናቸውና እንዳ
ንሰርቃቸው መጠንቀቅ ይገባል።

ሌብነት ትርጉሙ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ ከዚህ በላይ በጠቃቀስናቸው የስርቆት ዓይነቶች ብቻ የሚወሰን አይደለም። ግድግዳ ሰርሥሮ ከመሰረቅ ጀምሮ በሐሰትና በማ ምታት እስከተገኘ ገናና ስም ያሉትን ሁሉ የሚያጠ ቃልል ነው። ከእነ ዚህ ጋር አድራጊው ራሱን እንደጥፋተኛ የማይቆጥርባቸው፣ ያለማፈርም የሚፈጽማቸው ከግምት ውስጥ የማይገቡ የሚመስሉ የስርቆት ዓይነቶችም የማይዘ ነጉ ናቸው። *ለምሳሌ፦*

1. ብዙ ሠራተኞች ለመሥሪያ ቤታቸው ሥራ የተገዛላቸውን ወይም የተሰጡአቸ የጽሕፈት መሣሪ ያዎች ለግል ጥቅማቸው ያውሏቸዋል፣ አንዳንድ ባለ ሥልጣኖችም ለሥራ ብቻ እንዲጠቀሙባቸው የተሰጡአቸ ውን መኪናዎች ለግል ጉዳያቸው መፈጸሚያ ያደር ጉአቸዋል፣ ሁሉም በዚህ ተግባራቸው በመስረቅ መሥሪያ ቤቱ ያለጊዜው ከመጠን ያለፈ ወጪ እንዲያወጣ ምክንያት ይሆናሉ።

2. የተዋሱትን ዕቃ በጊዜው ባለመመለስ ባለንብረቱ በረሳው ጊዜ የራሳቸው የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ይህ ንብረት ባለቤቱ ስለረሳው ብቻ የተዋሰው ሰው ንብረት የሚያደርገው ሕግ የለም። ከተዋሰ በኋላ የሚያረሳሳ ወይም ባለንብረቱ የረሳውን ዕቃ አስታውሶ የማይመልስ ሰው እንደሌባ ይቆጠራል።

3. የተበላሸውን ዕቃ ደህና በማስመሰል መሸጥ በማጭ በርበር የተፈጸመ ስርቆት ነው። ብልሽቱን ደብቀው የሚሸጡ ነጋዴዎች ታማኝነት የሌላቸው ናቸው። ይህ አሮጌውን እንደአዲስ፣ መጥፎውን እንደጥሩ አስመስለው የሚሸጡትን ይመለከታል። አንድን ዕቃ መልካም ዝናና ተፈላጊነት ባለው ሌላ ዕቃ ስም መሸጥ፣ ቅቡን ወርቅ ነው

ብሎ መሸጥ ሁሉ በማጭበርበር የሚፈጸም ስርቆት ነው። ትክክል ባልሆነ መለኪያ፣ ከብደት፣ ሜትር ወይም በሌላ በመጠቀም መሸጥም ሌብነት ነው። ዕቃውን ከገበያ በመሰወር ፈላጊው በበዛ ጊዜ ከሚገባው በላይ ዋጋ በመጠየቅ ብዙ ለማትረፍ መጣር ራሱ ሌብነት ነው፣ የማይገባ ጥቅም ማግኘት ነውና።

4. ለሠራተኛው ከሚገባው በታች እየከፈሉ ጉልበቱን በነፃ መበዝበዝም አንዱ የሌብነት ገጽታ ነው። ፈርዖን በነፃ የሚበዘብዘውን የእሥራኤልን መከራ የተመለከተው እግዚአ ብሔር «በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ» በማለት መናገሩ ያለዋጋ በነፃ ስለተሰረቀው ጉልበት ነው። ዘጸ.3÷7። ቅዱስ ያዕቆብም «እነሆ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል» ያለው ከሠሩበት በታች ስለተከፈላቸው ሠራተኞች ነው። ያዕ.5÷4።

5. ጉቦም የሰውን ገንዘብ ያለአግባብ መበዝበዝ በመሆኑ ከሌብነት ይቆጠራል። ደመወዝ የሚከፈለው ሠራተኛ ሌላ ከፍያ ሳይጠይቅ አገልግሎቱን ለሕዝብ ማበርከት አለበት። ጉቦ የተቀበለ እንደሆነ ሌብነትን ፈጽሟል። ጉቦ በስጠታ መልክ ቢፈጸም እንኳ አብሮ የተያያዘ ጥቅም ስላለ ከሌብነት ተለይቶ አይታይም።

6. በሥራ ጊዜ በሰዓት አለመገኘት፣ በሥራ ቦታ የተቀጠሩበትን ሥራ ትቶ የግል ሥራን ማከናወን፣ የሥራ ጊዜን ለመዝናናትና ለጨዋታ ማዋል፣ ሕጋዊ ያልሆነ የሕ መም ፈቃድ በማምጣት ከሥራ መቅረት ወዘተ የሥራ ሰዓ ትን መስረቅ ናቸው። ሥራውን በተገቢው ሁኔታ አለመሥ ራት፣ ጥራቱን፣ መጠኑን አለመጠበቅ፣ ከሥራ ገቢታ ጠፍቶ መሄድ ወዘተ ሁሉ ጊዜን መስረቅ ነው። እንዲውሬብት የተ ሰጠውን መሣሪያ ማበላሸት፣ በማድየለሽነትም ለሥራ ላይ ማ ዋል፣ አሠሪውን ለአላስፈላጊ ወጪ የሚጨርግ ነውና ይህ ተጨማሪ ወጪ በሠራተኛው እንደተሰረቀ ገንዘብ ይቆጠራል።

7. ባልንጀራው እንዲያስቀምጥለት በአምነት የሰጠውን ዕቃ አልተቀበልኩም ብሎ መካድ ሌብነት ነው። እንዲህ የሚያደርገውም ሰው ሌባ ነው። መጽሐፍም ስለዚህ ነገር «ማናቸውም ሰው ኃጢአትን ቢሠራ፥ እግዚአብሔር ንም ቢበድል፥ ያኖረበትን አደራ ወይም ብድር ወስዶ ባልንጀራውን ቢክድ፥ ወይም ቢቀማ፥ ወይም በባልንጀራው ላይ ግፍ ቢያደርግ፥ ወይም የጠፋውን ነገር ቢያገኝ፥ ያንን ሸሽጎ በሐሰት ቢምል፥ እርሱ ኃጢአትን ሠርቶ በደለኛ ቢሆን በቅድሚያ የወሰደውን ወይም በግፍ የተቀበለውን ወይም የተሰጠውን አደራ ወይም ጠፍቶ ያገኘውን፥ ወይም በሐሰት የማለበትን ነገር በሙሉ ይመልስ» ብሏል። ዘሌ.6÷2–4።

8. ከሌባ ጋር መተባበር በራሱ ሌብነት ነው። መጽሐፍም «ማንም የሌባ ባልንጀራ ቢሆን ወንጀለኛ ነው። ይላል። ምሳ.29÷24። እንዲሁ ሁሉ ለሌባው ከለላ ወይም መጠጊያ የሰጠ ወይም ያበረታታ ወይም ድርጊቱን ያሞካሸና በሌብነቱ እንዳይፀፀት ያደረገ የሌባ ተባባሪ የሌብነቱም ተካፋይ ነው።

9. የሌላውን ሰው ሃሳብ እንደራስ አድርጎ ማቅረብ፣ ከሌላ የተወሰደውን ጥቅስ ራስ የተናገሩትና የፈጠሩት በ ማስመሰል ማቅረብ የሃሳብ ሌብነት ነው። ይህ በድርሰት፣ በዜማ፣ በሥነ-ጽሑፍ ወዘተ የተለመደ ስርቆት ነው። ይህ ዓይነቱ በዓለማዊውም ሕግ ቢሆን የተከለከለ ተግባር ነው። የራስ ያልሆነውንና ያልደከሙበትን ሥራ እንደ ደከሙበት አስመስሎ ማቅረብ በእግዚአብሔርም ፊት ሌብነት ነው።

10. ሰውን በመሰለልና ያልተፈቀደለትን ምሥጢር በመስማት፣ የሰውን የግል ማስታወሻ ወይም ደብዳቤ በማ የት ምሥጢር ሊሰረቅ ይችላል። ሰው የሌላውን ምሥጢር ለማወቅ መሞከር የሌለበት ከመሆኑም በላይ ያወቀውንም ምሥጢር አክብሮ ሊጠብቀው ያስፈልጋል። ከዚህ ውጭ የሚያደርግ የምሥጢር ሌባ ነው።

11. ነፍሳትን መስረቅም አንዱ የሌብነት ዓይነት ነው። ይህን ዓይነቱ በኑፋቄና በእንግዳ ትምህርት እያታለሉ ምእመናንን ከአናት ቤተክርስቲያናቸው በማስከብለል ሃይ ማኖታቸውን እንዲክዱ የሚያደርጉትን የሚመለከት ነው። በዚህ ተግባር የተሠማሩት ሁሉ ምእመናንን ድኅነት ከሚያገ ኙበት እውነተኛ ሃይማኖት የሚያስኮበልሉና የሚያሳስቱ በመሆኑ ይህ ተግባራቸው ነፍሳትን መስረቅ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእኔ በፊት ቀመጡት ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው» በማለት የተሳሳተ ትምህርት ያስተማሩ የነበሩትን መምህራን ሐሰት ሌቦች ብሏቸዋል። ዮሐ.10÷8። የሕግ መምህር የነበረው ገማልያልም ስለእነዚህ ሲናገር «ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ ፡-እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና÷አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ፤ እንደምንምንም ሆኑ።» በማለት የጠቀሰው ሐሰተኛ ትምህርት ስለአስተማ ረው ቴዎዳስና ደቀመዛሙርቱ መሆኑ ግልጥ ነው። የሐዋ.5÷36–37። ይህን በመሰለ የነፍሳት ስርቆት ከመወሰድ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ሲናገር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐ ንስ «ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤ ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና።» በማለት አስጠ ንቅቋል። 2ዮሐ.1÷10–11።

የመስረቅ ምክንያትና መፍትሔው

ምክንያቶች፡-

ምኞት፣ ስስት፣ ፍቅረንዋይ፣ ራስወዳድነት፣ ጭካኔ፣ ጥላቻ፣ የሌሎችን መብትና ክብር መድፈር፣ ሕገወጥነትና የመሳሰሉት ሁሉ ለመስረቅ የሚያነሣሡ ምክንያቶች ናቸው። የሌብነት አመል ከሌሎች በመውረስ፣ በመኮረጅ ወይም በተዛባ አመለካከት የተነሣም ሊመጣ ይችላል። ድህነት፣ ችግርና ጉስ ቁልናም የሌብነት ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ተስፋ ለቆረጠችና ለተዋረደች ነፍስ ሌብነት ምናልባት በሽታ፣ ወይም ልምድ፣ ወይም የደስታ ምንጭ ይሆን ይሆ ናል። ጠቢቡ ሰሎሞንም «የስርቆት ወኃ ይጣፍጣል+ የተሸሸገ እንጀራ ደስ ያሰኛል» በማለት ተናግሯል። ምሳ.9÷17። ከዚህ በተጨማሪም «ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ፣ ባሕሩ ግን አይሞላም» በማለት ሀብት ንብረት እያላቸው በቃኝ ከማ ለትና ከስስት የተነሣ በፍቅረ ንዋይ ፈረስ እየጋለቡ ስለሚሰርቁት ሃብታም ሰዎችም ተናግሯል።መክ.1÷7–10። የእነዚህ ሰዎች የስርቆት ምክንያት ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ካለማወቅና ከፍቅረ ንዋይ የመነጨ ነው።

ስርቆት ተቸግሮ በሚሰርቀው ድህም ሆነ አልጠግብ ብሎ በሚሰርቀው ሀብታም ቢፈጸምም ይቅርታ የሌለው ኃጢ አት ነው። መጽሐፍም «ሌባ በተራበ ጊዜ ነፍሱን ሊያጠግብ ሲሰርቅ ቢያዝም ሰባት እጥፍ ይከፍላል፣ በቤቱም ያለውን ሁሉ ይሰጣል» ማለቱ ደህ ነውና ቢሰርቅም ይቅርታን ያገኛል ማለት አለመቻሉን ያመለክታል።

<u>መፍትሔው፡-</u>

የመጀመሪያው መፍትሔ በሰው ልጅ ልቡና ውስጥ የታማኝነትን ፍቅር መትከልና የተዋረደውን ግብር የሌብ ነትን ችግኝ መንግሉ /ነቅሉ/ መጣል ነው። ሰዎች ሌሎችን መውደድና የሌሎችን መብት ማክበር መልመድ ይገባቸዋል። ሰዎች እርስ በርስ የተዋደዱ እንደሆነ አንዱ የሌላውን ንብረት አይፈልግም፣ አንዱም ሌላውን አይከዳም። አንዱ የጣለውን ንብረት እንኳ ቢያገኝ በቅንነት የጠፋበትን ሰው ለ ማግኘትና ለማወቅ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል እንጂ ወድቆ ያገኘውን የባልንጀራውን ንብረት እንደራሱ አየቆጥረውም።

በሕጋዊነት ያልተገኘ ገንዘብ ሕጋዊውን ጨምሮ የሚበላ እላት መሆኑን ሰዎች ሁሉ መገንዘብ አለባቸው። ከዚህም የተ ነሣ ደህውም በአቅሙ ሠርቶ ከችግር ኑሮ መውጣትን ሌሉ ችም ሰዎች በታማኝነት ላይ የተመሠረተ ትርፍ ማግኘትና ጠ ንክሮ በመሥራት ራሳቸውን ማሻሻል የሚገባቸው መሆኑን ማወቅና ጠንክሮ መሥራት እንጂ መስረቅ የለባቸውም።

በወጣቶች ዘንድም ቅንጦት፣ ልቅ የሆነ መዝናናት፣ ያለጊዜውና አስፈላጊ ሳይሆን ከተቃራኒ ፆታዎች ጋር መወ ዳጀትና መሳሳትን፣ የምሽት ፖርቲዎችና ጭፈራዎች፣ ቁማሮችና መጠጦች ሁሉ ሊወገዱ ይገባቸዋል። ምክንያቱም ሁሉ ለአፈጻጸም የሚያበቃቸውን ገንዘብ ለማግኘት ሲባል ወደ ስርቆት የሚገፋፉ ገቢረ ኃጣውእ ናቸውና ነው። ለእ ነዚህ ሁሉ ማሟያ የሚፈልጉትን ለማግኘት ቤተሰቦቻቸ ውን ወደማስገደዱ፣ ካልተሳካ ደግሞ ወደ ሌብነት እንዲ ያዘነብሉ የሚያደርጉ ናቸውና ከወጣቶች አእምሮ መሠረዝ አለባቸው መባሉ ተገቢ ነው።

ከሁሉም ይበልጥ ሌብነትን ለማስቀረት የሚጠቅ መው ወሳኝ መፍትሔ ንስሐ ነው። ንስሐ ሌባውን ስለ ቀደመ በደሉ እንዲፀፀትና ዳግመኛ ሌላ ስርቆት ላለመ ፈጸም እንዲወስን ስለሚያደርገው ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ሌባው በንስሐው ወቅት መስረቁን ከመናዘዙና ቀኖናውን ተቀብሎ ከመፈጸሙ በተጨማሪ የሰረቀውን ሁሉ በምሥጢርም ሆነ በግልጥ ለተሰረቀበት ሰው መመለስ አለበት። በዘሌዋውያን «በቅሚያ የወሰደውን ወይም በግፍ የተቀበለውን... ነገር ይመልስ» የሚል ሕግ የተሠራ ሲሆን በዘጸአት ደግሞ «ሰው በሬ ወይም በግ ቢሰርቅ÷ ቢያርደው ወይም ቢሸጠው÷ በበሬው ፈንታ አምስት በሬዎች፣ በበጉም ፋንታ አራት በጎች ይክፈል» ተብሎአል። ዘሌ.6÷4። ዘጸ.22÷1–2። ምሳ.6÷30–31። ዘኬዎስ ደግሞ «ጌታ ሆይ ግንባም በሐሰት ከሰሼ እንደሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ» ማለቱ ይህንኑ በማስታወስ ነው። ሉቃ.19÷8።

ስለዚህ የሰውን ንብረት የሰረቀው ሌባ በብሉይ ኪ ዳን እንደተሠራው ሕግ እጥፍ ለመመለስ ባይችል እንኳ የሰረቀውን ንብረት ለባለቤቱ መመለስ ይገባዋል። ይህም በትምህርተ ንስሐ፣ የበደሉትን መካስ፣ የቀሙትን መመለስ እንዲገባ ከተሠራው ሥርዓት ጋር በመጣጣም የተነሳሒውን ንስሐ ዋጋ ያለው ያደርገዋል።

ክፍል ዘጠኝ

ስምንተኛው ትእዛዝ

«በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር»

ዘጸ.20÷16::

በሐሰት መመስከር መዋሸት ነው:: በቅዱስ መጽሐፍም ስለሐሰት የተነገሩት ቃላት የመዋሸትን አስከፊ ገጽታ የሚያሳዩ ናቸው:: ስለዚህም ነገር ጠቢቡ ሰሎሞን «ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው» በማለት ተናግሯል:: ምሳ.12÷22:: መዋሸት በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ በመሆኑም ቀደም ብሎ በዘሌዋውያን «እናንተም እርስ በርሳችሁ ሐሰት አትነጋገሩ»የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር:: ዘሌ.19÷11:: ይህም በሰዎች ዘንድ ሐሰት መናገር ያለተፈቀደ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: ከዚህ በመነሣት ሐሰት ወይም ውሸት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠቱ አስፈላጊ ነው:: ሐሰት /ውሸት/ የሆነውን አልሆነም፣ ያለሆነውን ሆነ ብሎ ለሌላው ሰው መናገር ወይም አሉታዊውን አምንታዊ አምንታዊውን ደግሞ አሉታዊ አድርጎ በማቅረብ የተሳሳተ መረጃ መስጠት ማለት ነው:: ሐሰት የእውነት ተቃራኒ ነው::

በዚህ ላይ በመመሥረት ነው መምህረ አሕዛብ የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ምእመናን በላከው መልእክቱ «ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ÷...እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ::» በማለት የመከረው:: ኤፌ.4÷25:: በዚህ ምንባብም ቢሆን እውነትን መናገር የክርስትና መሠረት መሆኑ በግልጥ ነው የተመለከተው:: ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት ተባብረው ሐሰትን አውግዘውታል፤ ክፉ ነውና::

መዋሸት በሰውም በእግዚአብሔርም ዘንድ መጠላቱ ኃጢአት ስለሆነ ነው:: ውሸት ከፍርሃትና ከደካማ ባሕርይ የሚመነጭ ሊሆን ይችላል:: በራሱ የሚተማመንና እውነተኛ ሰው አይዋሽም፣ የተሰጠውንም ኃላፊነት በሚገባ ይወጣል:: በራሱ የማይተማመን ደካማና ሰነፍ ሰው መዋሸትን የስንፍናው መሸፈኛና ቀላል የመፍትሔ አማራጭ አድርጎ ይጠቀምበታል:: አልፎ አልፎም ውሸትን ለቀደመ ሐሰት መሸፈኛ ሲጠቀሙበት የሚታዩም አሉ:: እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ከአንዱ ውሸት ወደሌላው እየቀጠሉ ሲዋሹ ይኖራሉ፣ መዋሸታቸውን ለመሸፈን መዋሸትን ለምደዋልና::

የሐሰተኛ ሰው ቃሉ አይታመንም÷ የሚያምነውም የለም፤ እውነትን እንኳ ቢናገር፣ እውነተኛነቱንም ለማረጋገጥ ቢሞክር፣ ከቀደመው ውሸቱ የተነሣ ነገሩን አምኖ የሚቀበለው አያገኝም፤ አንድ ጊዜ ተአማኒነቱን አጥቷልና:: መዋሸት በጀርባ ሌላ ኃጢአትን የከለለ፣ ያለፈውን መሸፈኛ ወይም የሚመጣውን መከለያ እጥፍ ኃጢአት ነው:: ስለሆነም እንደ ዋሸ ያመነውን ተነሳሒ የሚያናዝዘው ካህን ለመዋሸት የገፋፋው ምን እንደሆነ ይነግረው ዘንድ ሊጠይቀው ይገባል፤ ከውሸት በስተጀርባ ሌላ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርምና::

ሐሰትን ወደዓለም ያስገባው የመጀሪያው ውሸተኛ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው:: እርሱ በሥጋ ከይሲ በእባብ ተሰውሮ የመጀመሪያ ወላጆቻችንን አዳምንና ሔዋንን «ሞትን አትሞቱም» በማለት በሐሰት በተናገራቸው ጊዜ ዋሸ:: ዘፍ.3÷4:: ለዚህ ውሸት ያነሣሣውም ከፋቱና እንርሱን ለማጥፋት የነበረው ፍላጎቱ ነው:: እግዚአብሔርም ስለዚህ ክፉ ጠላታችን ሲናገር «እርሱ ...ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና::» ማለቱን ባወንጌል ተጽፎ እናገኘዋለን:: ዮሐ.8÷44:; እነዚህ ምንባባት ሐሰተኛ ሰው በግብሩ የዲያብሎስ ልጅ መሆኑን ያስተምሩናል::

ሐሰት ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ሊሆን ይችላል። የሐ ሰት መልእክትን የሚያስተላልፍ ሰው ሁሉ በተዘዋዋሪ ስለ ሚዋሸና የውሸትም ተባባሪ ስለሆነ ሐሰተኛ ነው። አንዳንድ የዋህ ሰዎች መድኃኒታችን «እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ» ያለውን በመዘንጋት የሰሙትን ሁሉ እውነት መሆኑን ሳያረጋግጡ መልሰው በማውራት የሐሰት ተባባ ሪና ሐሰተኞች ይሆናሉ። የክርስቲያኖች የዋህነት ግን በማ ስተዋልና በጥበብ ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል። ሳያረ ጋግጡ መናገር ሳያውቁ መመስከር በተለይ ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ አይደለም።

ዓለማችን እውነትም ሐሰትም፣ እውነተኛም ሐሰተኛም የመላባት በመሆኑዋ በውስጧ የሚኖር ሰው ሁሉ የሚሰማውን በደፈናው ከማመን አስቀድሞ መመርመርና እውነተኛውን ነገር ማረጋገጥ ግዴታው ሊሆን ይገባል። በብሉይም ሆነ በሐ ዲስ ኪዳን ነገር ሁሉ በምስክር የተረ ጋ ሲሆን እንደሚጸና መነገሩ ስለዚህ ነው። ዘዳ.17÷6። ማቴ.18÷16። 2ቆሮ. 13÷1። በዚሁ የተነሣም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ «ነገር ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር ይጸናል» የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ተጽፎ እናገኘዋለን። ስለአንድ ነገር ምስክርነቱን የሰጠ ወይም የሰማውን ለሌላ ሰው የተናገረ ሰው ስለነገሩ እውነቱን ላያውቀው ስለሚችል፣ ስለተናገረው ነገር የተረ ጋገጠ ዕውቀት ላይኖረው ስለሚችል፣ ነገሩም የተጋነነ ሊሆን ስለሚችል፣ የተሳሳተ ነገር ሰምቶ ሊሆን ስለሚችል፣ ስለሰ ማው ነገር የማይታመን ወይም አጠራጣሪ መረጃ ሊያገኝ ስለሚችል፣ በግል ምክንያት የሰውን ዝና ለመጉዳት ብሎ ሊ ያደርገው ስለሚችልና በመሳሰሉት ምክንያቶች እንደ እርግጠ ኛ ምስክር ሊቆጠር አይገባም።

ባልንጀራ ወይም ጠላት የተናገረውን ነገር ከማጣራ ትና ከማረጋገጥ በፊት በጥላቻ መመልከትና በክፉ መጠርጠ ር ተገቢ አይደለም። ስለሆነው ነገር ሁሉ እርምጃ ከመውሰድ አስቀድሞ መመርመርና በቂ መረጃ ማግኘት ያስፈልጋል። ያልተጣራና ያልተረጋገጠን ነገር መናገርና ባልተረጋገጠ ነገር ላይ ተመርኩዞ መወሰን ከሐሰተኛነት አይለይም። የዚህ ዓ

ይነቱ ተግባር በጥንቃቄ ላይ ካልተመሠረተ እውነተኛውንና ጻድቁን ወደመክሰን ሊያደርስ ይችላል፤ በመጽሐፍም «በድፍ ረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ /በእውነተኛው/ ላይ የሚናገሩ የሸንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።» የተባለው ሳይረጋ ገጥ ስለሚነገር ነገር አደገኛነት ለማመልከት ነው። መዝ. 30÷18። ይህም የተባለበት ምክንያት ብዙዎች የአይሁድ ሊቃነ ካህናት እንደአደረጉት ሁሉ በቅዱሳን ላይ በሐሰት ስለሚመሰክሩ ነው። እነዚህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበርና።» ማቴ.26 ÷59።

በቅዱሳን ላይ በሐሰት መመስከር

በመጽሐፍ እንደተመዘገበው ቅዱስ እስጢፋኖስን አይ ሁድ ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ብዙ ሰዎች በሐሰት መስክ ረውበት ነበር። በሐሰት ቃላቸው «ይህ ሰው በዚህ በተቀ ደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይ ተውም» በማለት እነርሱን ትክክለኛ፣ እርሱን ደግሞ ተሳዳቢ ና ሕግን ተላላፊ አድርገው በመናገር መስክረውበት ነበር። የሐዋ.6÷13። ቀደም ብሎም በብሉይ ኪዳን ንግሥቲቱ ኤልዛቤል በኢይዝራኤላዊው በናቡቴ ላይ ያቆመቻቸው የሐ ሰት ምስክሮች «ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድበአል ብለው በናቡቴ ላይ መሰከሩ። የዚያን ጊዜም ከከተማ አውጥተው እሰኪሞት ድረስ ወገሩት»። 1ነገ.20÷13።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «በክብርና በውርደት÷ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናሳጥናለን፤ አሳቾች ስንባል እውነተኞች ነን» በማለት የተናገረው በሐዋርያዊ አገልግሎታቸው ላይ በሐሰት ይናፈስ የነበረውን አሉባልታ የሚመለከት ነበር። 2ቆሮ.6÷8። ከዚህም በላይ በቅዱሳን ላይ ስለተነገረው የሐሰት ምስክርነት ሁሉ እንጻፍ ቢባል ጊዜም አይበቃም። ብዙ ቅዱሳን በሐሰት ምስክርነት የተነሣ ያለ በደላቸው መከራን ተቀብለዋል፤ የነፍስ መሥዋዕትነትም ጭምር ከፍለዋል። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ኦትናቴዎስ ሐዋር ያዊ በዝሙትና በነፍስ ግድያ ሶርያዊው ቅዱስ አብርሃም፣

ታላቁ መቃርዮስ፣ አባ መሪና በዝሙት የተከሰሱት በሐሰት እንደነበር ቅዱሳት ድርሳናት ያስረዳሉ። እነዚህ ቅዱሳን አበው በሐሰት ከተከሰሱበት ኃጢአት ነፃ መሆናቸው ተረ ጋግጧል። ስለዚህ እንግዲህ በሐሰት ለሚነገር ክስም ሆነ ወሬ ጆሮን ከመስጠት መቆጠብ ለሰው ሁሉ ጠቃሚ ነው።

«በሐሰት አትመስክር» የሚለው ትእዛዝ ዋሽቶ የሚናገረውንና ሐሰተኛ ወሬን የሚሰማውንም ሰው ሁሉ የሚመለከት ነው። ሐሰት ወሬን የሚሰማና የሚቀበል ሰው ውሸተኛውን የበለጠ እንዲዋሽ ይገፋፋዋልና በኃጢአት ላይ ኃጢአት እንዲሠራ ምክንያት ይሆንዋል። በዚህ መሠረትም በሐሰት ኃጢአት ተናጋሪውና አድማጩ ሁለቱም ተሳ ታፊዎች ናቸው። በቅዱስ መጽሐፍ የምናገኘው የመጽሐፍ ቃል የሚያስተምረው ሐሰተኛ ወሬን መስማትና ማስተ ጋባትም ተገቢ አለመሆኑን ነው። ምሳ.29÷12። የቤተ ክርስቲያን ሕግም ከዚሁ በተመሳሳይ ካህኑ ሐሰተኛ ነገርን እንዳይሰማ ያዝዛል።

ቃላት ለአድማጩ እስኪደርሱ ድረስ ስለመበረዛቸው

አንዳንድ ሰዎች ስለአንድ ነገር የሰሙትን እንዳለ ከማስተላለፍ ይልቅ የራሳቸውን ሃሳብ ጨምረው፣ በራሳቸው መደምደሚያ አበጅተውለት፣ የራሳቸውንም ፍላጎት እንዲ ያስተላልፍላቸው ካመቻቹ በኋላ ልክ እንደተናጋሪው ቃላት አስመስለው ለሰሚው ያቀርባሉ። እነዚህ ሰዎች ሐሰተኞች ናቸው። የዓባይን ወንዝ እንደ ምሳሌ እንውሰድ፣ መልኩ ቡናማ ቀለም ነው፣ ቡናማ የሆነበት ምክንያት ከመነሻው ጀምሮ በሰበሰበው የተሸረሸረ አፈር የተነሣ ነው። ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ ተራራዎች ላይ በዘነበው ንጹሕ ውኃ የተሞላ ነበር፣ በረኻሙ ጉዞው ግን ከአፈር ጋር ተደባልቆ ቡናማ መልክ ኖረው። የመጀመሪያ መልኩም ለመለወጥ በቃ። እንዲሁ ሁሉ ከመነሻቸው ንጹሐን የነበሩት ወሬዎች በመጨረሻ በሚሰማቸው ሰው ጆሮ ሲደርሱ ከብዙ ሃሳብ

ጋር ተደባልቀውና ማንነታቸው ተለውጦ ነው። ሐሰት የተጠ ደባለቀባቸውና የተበረዙ ሆነው ለጆሮ ይቀርባሉ። ከንጹሕ ንግግር ጋር የተቀላቀለ ሐሰት በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሻክር ይሆናል። በዚህ የተነሣም የተናፈሱትን የሐሰት ወሬዎች መሠረት በማድረግ ባልንጀራን ወይም ወዳጅን ወይም ማንኛውንም ሰው ቢሆን ከመቀየምና ስለጉዳዩም ከመናገር አስቀድሞ ስለሆነው ነገር ሁሉ እርግጠ ኛ መሆን ይገባል።

አንዳንድ ሰዎች በሐሰተኛ ወሬ የተነሣ ስማቸው ሲጎ ድፍና ሲታሙ እየሰሙ ራሳቸውን ከመከላከል ተቆጥበው ይኖ ራሉ። እነዚህ ንጹሐን ቁጥብነትን በመምረጣቸው እንደ ጥፋተኛ መቆጠር የለባቸውም። የአንድን ሰው ንጽሕና ለማረ ጋገጥ የሚደረገው ጥረት ስለሰውየው ሊታወቅ የማይገባውን የግል ምሥጢሩን የሚያጋልጥ፣ የሌላውን ሰው ወንጀለኛነት የሚያጋልጥ፣ ወይም የሰውየውን ስሕተቶች የሚያጋልጥ ሊ ሆን ስለሚችል ራሱን ለመከላከል ላይመርጥ ይችላል። የአንድን ሰው ንጽሕና ማረጋገጥ በክሳሾቹና በስም አጥፊዎቹ ላይ ችግር የሚያስከትል ሲሆን ንጹሑ ሰው ነገሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት መከላከሉን ሊተው ይችላል።

ይሁን እንጂ ሐሰተኛው ሰው ንጹሑን ጥፋተኛ፣ ጥፋ ተኛውን ደግሞ ንጹሕ አድርጎ የሰዎችን ጎሊናና አመ ለካከት ሊበርዝ ይችላል። ይህን በተመለከተ በቅዱስ መጽሐፍ «ኃጥ ኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ የሚፈርድ÷ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው።» የሚል ተጽፎ እናገኛለን። ምሳ 17÷15። ንጹሑን ሰው የሚኮንን ኃጢአተኛውንም ጻድቅ እንደሆነ የሚመሰክር ሰው ሐሰተኛ ነው። በሌላም በኩል በአንድ የሥራ መስክ በቂ ችሎታና ዕውቀት ሳይኖረው እንደ አንድ ዐዋቂና ብቁ ባለሙያ ሆኖ ሥራ እንዲያገኝ ማድረግም ራሱ ሐሰት ነው፣ ይህን ያደረገውም ሐሰተኛ ነው። ይህ ውሸት /ሐሰት/ ችግረኛውን ወይም ድህውን ለመርዳት ተብሎ የተደረገ ቢሆንም የዋሸውን ሰው በኃጢአቱ ከመጠየቅ ሊያድነው አይችልም።

ውዳሴ ከንቱ

ከመጠን ያለፈ ምስጋናና የተጋነነ አድናቆት እውነተኛ መሠረት የሌለውና ሐሰት በመሆኑ ተወዳሽን ሰው ስለራሱ የተሳሳተ እምነት እንዲኖረው በማድረግ ይጎዳዋል። ብዙ ሰዎች ይህን ቀላል ዘዴ በመጠቀም ከሌሎች የሚፈልጉትን ያገኛሉ፤ ከሚሹት ሥፍራም ይደርሳሉ። ይህንን ኃጢአት አስጠያፊ የሚያደርገው ነገር አወዳሽ የሚያደንቀውን ሰው ሲያገኘው ማወደሱና በሌለበት ሥፍራ ደግሞ የሚተቸው በመሆኑ ነው። ስለዚህም ሰውን ባልዋለበት እንደዋለ፣ ያልሠራውን እንደሠራ፣ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ምስጋናና ውዳሴ አየሰጡ ማሞካሸት እውነተኛ መሠረት የሌለውና ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ስለሆነ ከሐሰት ተነጥሎ አይታይም።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ስለ አንድ ሰው ጠንካራ ጎን ሊነገሩ የሚገባቸውን በመተው ድካሙን ብቻ አጉልቶ በማሳየት ሌሎች ስለእርሱ ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥ መሞከር ግማሽ እውነት በመሆኑ እንደሐሰት የሚቆጠርና በኃጢአትነቱም የሚያስጠይቅ ነው። ሐሰት የተሰኘበት ምክንያትም ስለ ሰውየው የተሳሳተ መረጃ መስጠት ስለሆነ ነው።

ሐሰተኛ ሰው በሕብረተሰቡ መካከል ያለው ሥፍራ የተናገረው ነገር ተአማኒ እንዳይሆን ያደርገዋል። እንዲህ ያለው ሰው የሚናገረው ሐሰት አስጠያፊ ነው። ስለሆነም ሐሰትን የሚናገረው ሰው ደረጃው ከፍ ያለ መሆኑ የተናገረውን ሐሰት የበለጠ አስጠያፊ ያደርገዋል። በዚሁ አንፃር ሐሰተኛውን ወሬ የተናገረው ሰው ሥልጣንና ደረጃ ሐሰትን አስጠያፊ ያደርገዋል። ለማንኛውም ተራ ሰው የተነገረና ለባለሥልጣን ወይም ለመንፈሳዊ አባት የተነገረ ሐሰት የሚመዘንበት ሚዛን እኩል አይደለም። ለምሳሌ ያህልም የዮሴፍ ወንድሞች ለአባታቸው እንደዋሹት፣ አንድ ሰውም ለንስሐ አባቱ እንደሚዋሽ፣ ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋሹና እግዚአብሔር እንደቀጣቸው። የሐዋ.5÷3–4።

በሕዝቡ መካከል ከያዙት መንፈሳዊ ሥልጣንና ሥፍራ የተነሣ ሕዝቡን የሚያስቱትን ሐሰተኞች ነቢያት፣ ሐሰተኞች ክርስቶሶች፣ እግዚአብሔር ያልነገራቸውን ነገርን የሚሉ ሐሰተኞች መምህራንንና የመሳሰሉትን ሁሉ እግዚአብሔር «እኔም ሳልናገር፦ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል ስትሉ÷ ከንቱ ራእይን ያያችሁ፣ ውሸተኛንም ምዋርት የተናገራችሁ አይደላችሁምን? በማለት ስለጥፋታቸው ነቅፎአቸዋል። ሕዝ.13÷7። ስለሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ «በስሜ ሐሰትን የሚናገሩትን የነቢያትን ነገር ሰምቻለሁ።» በማለት ቅሬታውን ገልጧል። ኤር.23÷25። ሕዝቡ ለመንፈሳውያን መምህራን፣ በእነርሱ ለሚደረጉት ተአምራትና ድንቆችም የሚሰጠውን እውነታዊ ግምት ተገን አድርገው የተሳሳተ ትምህርት የሚያስተምሩት ሐሰተኞች ሐዋርያት እንዲሁም ለማሳሳት የሚጠቀሙባቸው «ሐሰተኛ ድንቆች» የእነርሱን ሐሰተኛነት አስከፊና ተጠያቂነታቸውንም ከፍተኛ ያደርጉታል። ራእ.2÷2። 2ተሰ.2÷9።

የመዋሸት ምክንያትና መፍትሔው

አንዳንድ ሰዎች መዋሸት ከፈጸሙት ጥፋት የሚያድናቸው እየመሰላቸው የሠሩትን ኃጢአት ለመደበቅ ይዋሻሉ። ይሁን እንጂ የሐሰት መንገድ አጭርና የትም የማያደርስ ብዙ ጊዜም መገለጡ የማይቀር በመሆኑ ሰዎች ከሐሰት ይልቅ የሚያድናቸውን እውነተኛና ተገቢ መንገድ መጠቀም ይኖርባቸዋል። በተገለጠ ጊዜ የሚያሳፍርና ማኅበራዊ ከበሬታውና መንፈሳዊ ተአማኒነትን የሚያሳጣ ሐሰትን በመጠቀም ምንም ነገር መሥራት ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ጉዳቱ ያመዝናል። ለሁሉም የሚበጀው ደግሞ ልቡናን ከክፋት አእምሮን ከሐሰት ነፃ በማድረግ ማንኛውንም ኃጢአት ለማስወገድ የሚቻል መሆኑን ማመን ነው።

አንዳንድ ሰዎች ከመበሳጨት ወይም ከመፍራት ወይም ስለአንድ ነገር የሚጠይቃቸው ሰው ከሚያ ሳድርባቸው ጫና የተነሣ ሊዋሹ ይችላሉ። ከመዋሸት ይልቅ ግን በእንደዚህ ያለ ጊዜ ዝምታ ሞልካም መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። በሐሰት ራስን ለማዳን ከመሞከር ምንም ይሁን ምን የንግግርን አቅጣጫ በመቀየርም ቢሆን፣ መልስ ላለመስጠት ይቅርታ በመጠየቅም ቢሆን፣ በተቻለ መጠን በማስተዋልና እውነትን በመናገር ራስን መከላከልና ስለተሠራው ስሕተት ይቅርታ መጠየቅ መልካም ነው።

አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ እንደዐወቁ፣ ሳይሆኑም እንደሆኑ በማስመሰል የሚኩራሩ በመሆኑና አለማወ ቃቸውንም እንዳይታወቅባቸው ስለሚዋሹ መዋሸትን እንደመሸፈኛ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። አንዱን ኃጢአት ለመሸፈን በመዋሸት ተጨማሪ ኃጢአት ከመሥራት አላውቅም በማለት እውነት መናገሩ የተመረጠና ተገቢም ነው።

ለማጠቃለልም ሐሰት በአንደበት በመናገር የሚፈጸም ኃጢአት ነው። በሰው ዘንድ በምሥጢር መጠ በቅ ያለባቸው ብዙ ጉዳዮች ስላሉ በዚህ ረገድ የ ማይናገረው ሰው ሐሰተኛ ሊባል አይችልም። እንዲህም ስለሆነ ባለመናገር የሐሰትን ኃጢአት መዋጋትና መከላከል ይኖርብናል።

ክፍል አሥር

ዘጠነኛው ትእዛዝ

«የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፣ የባልንጀራ ህን ሚስት ሉሊውንም ገረዱንም በሬውንም አህያ ውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።»

ዘጸ.20÷17

የምኞት አደገኛነቱና ዕድገቱ

«አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ የብሉይ ኪዳኑን ሕግ ውበት የሚገልጥ ነው። በጥልቀት ሲተረጉምና ሲጤን ኃጢ አቶችን ሁሉ የሚመለከት ሆኖ መገኘቱ «አትመኝ» የሚ ለው ትእዛዝ የበለጠ ጠቃሚ መሆኑን ለመረዳት አስች ሏል። በቀድሞ ጊዜ የሰዎች ልቡና በክፋት የደነደነ ነበርና ይህ ሰማያዊና ታላቅ ሕግም በሰዎች ዘንድ የታወቀና ትኩ ረትም የተሰጠው አልነበረም። ትኩረት በተሰጠው ጊዜ ነው ውበቱና ጠቃሚነቱ የታወቀው። መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስም «ሕግና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይም ሰላችሁ፣ ልፈጽም እንጂ...» በማለት የተናገረው የሰውን አእምሮ ወይም ዕውቀት ስለ ሕግ ፍጹም ላደርገው ነው ማለቱ ነበር፤ ቀድሞ ፍጹም አልነበረምና። ማቴ.5÷17።

በወንጌልም «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያንጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል» የሚለው ትምህርት በውስጡ የብሉይ ኪዳንን ሕግ የያዘ የብሉይ ኪዳን ሕግ

ትርጉም ነበር፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ በአሪት «የባልንጀራህን ሚስትም አትመኝ» ብሎ ሕግ ሠርቶ ነበርና። ማቴ. 5+28። ዘዳ.5+21። እግዚአብሔር አምላካችን «አትመኝ» የሚለውን ትእዛዝ ሲሰጥ የኃጢአትን መነሻ /ሥር/ ስለ ሚያውቅ ነው። የኃጢአት ሁሉ መነሻ ምኞት ነው። ለምሳሌ ግመንዘር የሚጀመረው በሥጋዊ ምኞት ነው፤ ሌብነት ሀብታም ለመሆን ወይም ገንዘብ ለማግኘት ከመመኘት የሚመጣ ነው፤ ሐሰትም እውነተኛ ለመምሰል ወይም አንዳች ነገርን ያለአግባብ ለማግኘት ከመመኘት የተነሣ የሚፈጸም ነው፤ መግደል ከመበቀል ምኞት ወይም ወደዚያ ከሚያመራ ስሜት የሚመጣ ነው። ሰው እንግዲህ ምኞትን ከተዋጋውና ድል ካደረገው ኃጢአትን ሁሉ ድል ያደርጋል። ለዚህ ነው «አትመኝ» የሚለው ትእዛዝ የኦሪትን ውበት የሚገልጥ ያ ማረ ነው የተባለው።

አንድን ሰው «ምኞተኛ ነው» ማለት የሌላውን በመ መኘት የሚኖር ነው ማለት ነውና ስድብ ነው። መሳደብም ደግሞ ኃጢአት ነውና ሰውን እንዲህ ከማለት መቆጠብ ይገባል። ሰው ከምኞት ጋር በተፋጠጠ ጊዜ ከምኞት ከመ ታገል ይልቅ የሚበጀው ምኞትን መሸሽ ነው፤ ምክንያቱም ምኞትን ከማሸነፍ ይልቅ ልቡ በምኞት ጦር ሊወጋና በምኞት መርዝ የተነደፈ ሊሆን ይችላልና ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ «ከክፉ የጎል ማሳነት ምኞት ግን ሽሽ» በማለት የመከረው። 2ጢ ሞ.2+22።

ምኞት እስኪፈጸም ድረስ ያለማቋረጥ የሚዋጋ በመሆኑ ከምኞት መሸሽ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። በመሸሽ ምኞት የሚያሳድረውን ተጽእኖ ለመቋቋም ከተቻለ ለምን ከምኞት ጋር ወደመታገልና ወደመጯገት ይኬዳል? ምኞት በሰው ልቡና ውስጥ ሥፍራ በተሰጠው መጠን የሰውን ፈቃደኝነት ያገኛል፤ ስለእርሱ /ምኞት/ በታሰበ መጠንም በልቡና ውስጥ ያድጋል፤ ከዚያም ስለ እርሱ በማሰብ ወደ መደሰት፣ ለመፈጸም ወደ ማለጎምጀት፣ ቀጥሎም በተግባር ወደ መፈጸም ያደርሳል። ስለዚህ ምኞትን በመፈጸም ከመውደቅ መጀመሪያውኑ ከመመኘት መሸሽ እጅግ ጠቃሚ

ነው። የሰው ባሕርይ ደካማ ነውና ከሥጋው የተነሣ ስለሚመኘው ኃጢአት ከማሰብ ጀምሮ በእርሱ ወደ መመራ ት፣ ወደመፈጸም፣ ወደመደጋገም፣ በእርሱ ወደመለከፍ፣ ለሚመኘው ነገር ወደመገዛት ሊደርስ ይችላልና ጠንቀኛ ከሆነው ምኞት አብዝቶ ራስን መቆጠብ አስፈላጊ ነው።

ምኞት የሚያስከትለው አደጋ እስከአሁን በተጠ ቀሰው ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ሰው ምኞቱን ለመፈጸም ሲል በሌላ ኃጢአት ሊወድቅ ይችላል። ለምኞቱ ብሎ ሊ ዋሽ፣ ሊያታልል፣ ሊሰርቅ፣ ሊገድል፣ ምናልባትም ከዚህ የበለጠ ኃጢአት ሊሠራ ይችላል። ከዚህ ሁሉ ምኞትን ከሥሩ ነቅሎ ከልቡና ማውጣት ተገቢ ነው።

ምኞት ዘለርካታ የሚገታ አይደለም

ሰው ምኞት ባደከመውና ተገዥ ባደረገው ጊዜ «ዳግመኛ እየጓጓሁ ከምቸገር ይህን ምኞቴን ፈጽሜው ባርፍ ይሻለኛል» በማለት ራሱን ያታልል ይሆናል። ምኞት ግን በአንድ ጊዜ እርካታ ከልቡና የሚነቀል ከጎሊናም የሚጠፋ አይደለም። የተጠማ ሰው ሁሉ አንድ ጊዜ ጠጥቶ ዳግመኛ እንደሚጠማ፣ ምኞትም እንደዚህ ነው። በዚህ ረገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሣምራዊቷ ሴት «ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል» በማለት የነገራት ቃል መሠረታዊ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው። ዮሐ.4+13። ውኃን የጠጣ ሁሉ ዳግመኛ እንደሚጠማ፣ ምኞቱን በመ ፈጸም ደስታን የሚያገኝ የሚመስለውና ፈጽሞ እንደሚረካ በማሰብ የተመኘውን የፈጸመ ሰው እንደገና ደግሞ ይመኛል፤ ለምኞቱም ማብቂያ የለውም። ምኞቱን መፈጸም ሰውን ዳግመኛ ከመመኘት አያድነውም፤ የበለጠ የምኞት ጸርን ይጨምርበታል እንጂ። ለምሳሌም በዓለማችን እንደምናየው ገንዘብን ተመኝቶ ገንዘብን ያገኘ ሰው በዚ ያው መጠን የበለጠ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይመኛል እንጂ የሰበሰብኩት ይበቃኛል አይልም። በአንጹ ደረጃ ያለውን የዝሙት ኃጢአት የፈጸመ ደግሞ ሌላኛውን ለመፈጸም ይመኛል።

አባታችን አዳም በገነት ያሉትን ዛፎች ሁሉ ከአንዲቱ በቀር እንዲያዝዝባቸው ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። በዚህ ባለመርካቱም ያቺን አንዲቱን ደግሞ ፈለገ ተመኛት÷ ከፍሬዋ ለመብላትም ጓጓ። ሁሉን ያለው ንጉሡ አክዓብ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን መሬት ተመኘ፤ ሰባ ሚስቶች የነበሩት ዳዊት የአገልጋዩን የኦርዮንን ሚስት ተመኘ፤ ንጉሥ ሰሎሞንም ምኞቱን ለማርካት እስከ መጨረሻው ተጓዘ «ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኋቸውም» በማለት መጨረሻ የሌለው ምኞቱን ተናገረ። መክ.2÷10። በዚህ ውጤትም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚስቶችን ለእርሱ አደረገ፤ በማይ ሞተው ቃልም « ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባሕር ይሄዳሉ÷ ባሕሩ ግን አይሞላም ዓይን ከማየት አይጠግብም፣ ጆሮም ከመስማት አይሞላም፤» በማለት ምሳሌውን ትቶልን አልፏል። መክ.1÷7-10።

በዚህም ምኞትን ፈጽሞ እርካታን ማግኘት ጊዜያዊ በመሆኑ ከመመኘት የሚገላግል መፍትሔ ምኞትን አለመፈጸም መሆኑን አስተምሮናል። ለዚህ ችግር መፍትሔው የሚመኝ ሥጋን ራስን በመግዛት ልጓም መቆጣጠር ነው።። ያገባው፤ ብዙም ሚስቶች የነበሩት ዳዊት እርካታን በፈለገ መጠን በምኞት ድል እንደተመታና ያላገባው ዮሴፍ በንጽሕና ሆኖ ምኞትንም በመሸሽ እንደአመለጠውና ድልም እንደ አደረገው ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ምኞትን ያሸነፉት የሸሹት ናቸው እንጂ የተጋፈጡት አይደሉምና በጥበብ ሆኖ ከክፉ የሥጋ ምኞት መሸሽ መድኃኒት መሆኑን እንወቅ።

የምኞት ዓይነቶች

የምኞት ዓይነቶች ብዙ ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «ሥጋ በመንፈስ ላይ ይመኛል...» በማለት ምኞት ከሥጋ ፈቃድ የሚመነጭ መሆኑን ተናግሯል። ገላ.5÷17። ምኞትን የሚያስከትል የሥጋ ፈቃድም ተዘርዝሮ

የሚያበቃ አይደለም። በዚህ የሥጋ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ በሰው ልቡና ስለሚመላለሰው ምኞት ሲናገር ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት፣ ስለገንዘብም መመካትሯ» በማለት የተመለከታቸውን ዘርዝሮአል። 1ዮሐ.2÷16።

በዚሁ መሠረትም የዓይን አምሮት፣ የገንዘብ ፍላጎት ሌሎችም ሁሉ የምኞት ዓይነቶች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ» በማለት በክርስቲያኖቹ ዘንድ ምኞት በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተረታ ገልጧል። ገላ.5÷24። ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር በመስቀል የሚገኘው ደስታ መንፈሳዊ እርካታን የሚሰጥ ከፍተኛ ድል ነው።

የሥጋ ምኞትም ለዝሙት፣ ለመብላት፣ ለዓይን አምሮት፣ ለመስግት ወይም ለማሸተት የሚደረገውን ጉጉት ሁሉ ያጠቃልላል። እግዚአብሔር «የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ» ማለቱ አታመንዝር ሲል ነው። ኤሳው ብኩርናውን ለምሥር ወጥ እንዲለውጥ ያስገደደው የመብል ምኞቱ ነው። ዘፍ.25÷29-34። የእሥራኤላውያንም መሳም ጀትና «የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል? በግብፅ ያለ ዋጋ እንበላው የነበረውን ዓሣ፣ ዱባውንም ፣ በጢኽንም÷ በኩራቱንም÷ ...ሽንኩርቱንም እናስባለን» በማለት ማልቀስ ከዚህ የሥጋ ምኞት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ዘኁ.11÷4-5። እሥራኤል የተመኙትን ሥጋ እግዚአብሔር ሰጣቸው፤ ነገር ግን በከባድ መቅሰፍት መታቸው፤ ይህም ስለክፉ ምኞታቸው መቀጣጫ ነው። የጎመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋል።» የዚያ ሥፍራ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ። ዘኁ.11÷34።

የገንዘብ ምኞት ንብረትን የማደራጀት ምኞትን የሚያጠቃልል ነው። ንጉሥ አክዓብ የናቡቴን መሬት ለመውሰድ እንደበቃበት ያለምኞትም አለ። ስለዚህ እግዚአብሔር «የባልንጀራህን ቤት አትመኝ» በማለት አዘዘአል።

የክብርና የታዋቂነት፣ የሥልጣንና የማዕረግ፣ የታላቅነት፣ የውበትና የጌጥነት ወዘተ ምኞቶችም አሉ። እነዚህ ሁሉ ወደ ውድቀት የሚያደርሱ የጥፋት መንገዶች ናቸው። ዲያብሎስም የወደቀው «ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥... በልዑልም እመሰላለሁ» በማለት የማይገባውን ለማግኘትና ለመሆን ካደረበት ጽኑ ምኞት የተነሣ ነው። ኢሳ. 14÷13-14። በዚህ ተመሳሳይ ዲያብሎስ «እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ... ትሆናላችሁ» ባላቸው ጊዜ አዳምና ሔዋን ለመውደቅ የበቁት ባደረባቸው ከፍተኛ ምኞት የተነሣ ነበር። ዘፍ.3÷5።

ከሁሉም የበለጠ አደገኛው በሰይጣን ልቡና የነገሠው የሰውን ልጅ የማጥፋት ክፉ ምኞት ነው። ከመጀመሪያው አንሥቶ ዓላማው ሰውን በየምክንያቱ በማሰናከል ከእግዚአብሔር ለማጣላትና በነፍሱም እንዲሞት ለማድረግ ነበርና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለእርሱ «እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ» ብሎአል። ዮሐ.8÷44። የበቀል ስሜትም ከዚህ ምኞት ጋር የሚደመር ነው።

የሰው ልጅ ከዚህ ክፉ ኃጢአት ከምኞት ተለይቶ ሊኖርና ውጊያውን ለመቋቋም የሚችለው ለዚህ ዓለም እንግዳ መሆኑን በመገንዘብና ከንቱ የሆነውን የምኞት ምንጭ መናቅና መተው ሲቻለው ነው። «ሁሉ ከንቱ ንፋስን እንደመከተል ነውና» እንዲሁም ደግሞ «ዓለሙም ምኞቱም ያልፋልና።» መክ.1÷10። 1ዮሐ.2÷17።

የራስን ጥቅምና እርካታ በማሰብ ብቻ ላይ ተመሥርቶ በምኞት እሳት ከመቃጠል ይልቅ ሳያቋርጡ ስለሌሎች ሰዎች ማሰብን፣ ለሰው ማፍቀርን፣ እንዲሁም ሌሎችን በቸርነት መርዳትን ገንዘብ በማድረግ ከምኞት የተነሣ የሚፈጸመውን ኃጢአት ለመቋቋም ይቻላል።

ክፍል አሥራ አንድ

አሥረኛው ትእዛዝ

«ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ»

ዘሌ.19÷18

በዚህ መጽሐፍ በመጀመሪያው ክፍል እንደተገለጠው ሁሉ በዘሌዋውያን 19÷18 የተጻፈው «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለው ትእዛዝ በዘጸአት 20÷3-17 ከተዘረዘሩት ጋር ተዳምሮ ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል አንዱ ነው። ይህን ትእዛዝ ከአሥርቱ ትእዛዛት ነጥለው የሚመለከቱ ቢኖሩም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለትእዛዛት በተና ገረበት እንቀጽ ሕግ ሁሉ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ሃሳብ፣ በፍጹም ነፍስም በመውደድ በፍቅረ እግዚአብሔር እና ባልንጀራን እንደራስ አድርጎ በመውደድ /በፍቅረ ቢጽ/ የሚጠቃለል መሆኑን በሚገባ አስተምሯል።

ይህንን የጌታችንን ትምህርት መሠረት በማድረግም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አሥርቱን ትእዛዛት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመፈረጅ የመጀመሪያውን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት /ፍቅረ እግዚአብሔርን/ የሚመለከት፤ ሁለተኛውን ደግሞ በሰዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ግንኙነት /ፍቅረ ቢጽን/ የሚመለከት ነው ብለውታል። ይህም የሆነበት ምክንያት የትእዛዛት አሥረኛው «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» የሚለው በመሆኑ ነው። ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል የዚህን ትእዛዝ አተረጓጎምና ተግባራዊ አፈጻጸሙ እንመለከታለን።

ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ

በብሉይ ኪዳን «ባልንጀራ» የሚለው ቃል በጉር ብትና የሚኖር አሥራኤላዊን የሚመለከት ፍቺ የተሰጠው ነበር። «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት የተሰጠው ትእዛዝም በመልካም ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ጉርብትናን ብቻ የሚመለከትና በጎረቤታሞች መካከል ንጹሕ ፍቅር እንዲኖር የሚያስችል ዓላማ ያለው ነበር። በዚሁ መሠረ ትም እያንዳንዱ ሰው ባለበት ደረጃና የኑሮ ሁኔታ ባልንጀ ራውን መውደድ እንደሚገባው ቅዱሳት መጻሕፍት ያሰተ ምራሉ። ለምሳሌ ጠቢቡ ሰሎሞን «ባልንጀራውን የሚንቅ ይበድላል» በማለት የተናገረው ሰውን መናቅ ኃጢአት ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የሚያስጠይቅ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ምሳ 14÷21።

በቅዱስ ወንጌልም እንደተጻፈው የዘለዓለምን ሕይ ወት ለመውረስ ምን ማድረግ እንደሚገባ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለጠየቀው ጎልማሳ የተሰጠው መልስ ትእዛዛትን እንዲፈጽም ነበር። ትእዛዛቱ እንዲዘረዘሩለት በመጠየቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አትግደል፣ አታ መንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ እናትህንና አባትህን አክብር» በማለት ከዘረዘረለት በኋላ «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለቱ ባልንጀራን መውደድ እም ላካዊ ሕግና በተለይም ደግሞ የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ መሠረታዊ መስፈርት መሆኑን የሚያመለክት ነው። ማቴ.19÷19።

በብሉይ ኪዳን ከነበረው አንፃር ባልንጀራ የሚለው ቃል በሐዲስ ኪዳን ሰፋ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን። በዕለተ ዓ ርብ በመስቀል የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ለዓለም ሁሉ ማለትም ለደቂቀ አዳም ድኅነት በመሆኑና ይህ ቤዛነ ትም ሕዝብንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ስለሆነ ባልንጀራ የሚለው ቃል ፍቺ በክርስቶስ አንድ አካል የሆኑትን ሁሉ የሚያጠቃልል ወደመሆን ሰፍቷል። በዚህ ትርጉም መ ሠረትም ባልንጀራን መውደድ ማለት ሰውን ሁሉ መውደድ ሆኖ እናገኘዋለን።

በቅዱስ ወንጌል ታሪኩ የተጻፈለት ደጉ ሣምራዊ በመንገድ ላይ ወድቆ ያገኘውን ቁስለኛ አንሥቶ መልካም ነገር ስለአደረገለት፣ ከወንበዴዎችም እጅ ስለአዳነው፣ ምሕ ረትም ቸርነትም ስለአደረገለት ባልንጀራው እንደተባለ ተገልጧል። ሉ.ቃ.10÷25–37። በደዌ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በደዌ ነፍስም ተይዘው ለሚቃትቱና ዕርዳታን ለሚሹ ሁሉ ደርሶ ከቃለ እግዚአብሔር ተመግቦው፣ በንስሐ ታክመው፣ ጸጋና ረድኤትን ተጎናጽፈው በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲ ኖሩ ማድረግ ባልንጀራን መውደድ ነው። ወንበዴ ዲ ያብሎስ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚያንገላታቸውን ደቂቀ አዳም ለመንፈሳዊ የሕይወት ትንሣኤ ማብቃትና ነፍሳ ቸውን በኃጢአት ከመሞት መታደግም ባልንጀራን መውደድ ነው።

በጥቅሉ ስንመለከተው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ የሰውን ዘር ሁሉ ማንንም ከማን ሳያበላልጡ እኩል በሆነ ፍቅር መመልከትና ማክበር ባልንጀራን መውደድ መሆኑን ግጤን ያስፈልጋል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «ነገር ግን መጽሐፍ፦ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን የእግዚአብሔርን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራ ላችሁ፥ ሕግም እንደተላላፊዎች ይወቅሳችኋል።» በማለት የተናገረው ባልንጀራን መውደድ ማለት ሁሉን እኩል አድርጎ በእኔድ የፍቅር ዓይን መመልከት እንደሆነ ለማ ስረዳት ነው። ያዕ.2÷8–9።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው የመጽሐፍ ክፍሎች ባልንጀራን መውደድ ማለት ሰውን ሁሉ መውደድ እን ደሆነ አረጋግጠውልናል። አሥረኛው ትእዛዝ ደግሞ ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ መፈጸም የሚገባው ትእዛዝ ነው። «እንደራስ መውደድ» ሲባል ምን ማለት መሆኑን መመልከት አስፈላጊ ነው። እንደራስ መውደድ ሰፊ ትርጉም ያለው ነው። እንደሚከተለው እንመ ለከተዋለን።

እንደሚታወቀው ሁሉ ማንም ቢሆን በራሱ ላይ ክፉን የሚመኝ፣ የሚያደርግም የለም፣ ሞትን የሚወድ የሚሻውም የለም፤ ማንም መዋረድን፣ ርኩሰትን፣ ውድቀትንም የሚፈልግ የለም። ደግሞ ማንም ድኅነትን፣ ጸጋና በረከትን የማይሻ የለም። ማንኛውም ሰው ዓይነቱ የተለያየ ይሁን እንጂ ለራሱ መልካም የሆነውን ሁሉ ይሻል። መልካሙን ለማግኘት የተቻለውን ያህል የማይጥር የለም። እንዲህ ከሆነ ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ለራስ የሚሹትን መልካም ነገር ሁሉ ለባልንጀራ ማድረግ ማለት ነው። በወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።» በማለት ያስተማረው ይህንኑ የሚያመለክት ነው። ማቴ.7÷12። በዚህ ትምህርት መሠረትም ሕግ በተባሉት አሪት የታዘዘና በነቢያት ትንቢት የተሰበከው ፍቅር ይህ ነውና ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ለራስ ቢያሻኑት የሚወዱትን ለባልንጀራ ማድረግ ነው።

በሐዲስ ኪዳን ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ከዚህም የበለጠ ትርጉም ተሰጥቶት እናገኛለን። የዚህ ማረጋገጫ የሚሆነውም ሐዋርያው ጳውሎስ «እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ሰንኪ የራሱን ጥቅም አይፈልግም። ሲል» የተናገረው ነው። 1ቆሮ.10÷24። በዚህ ትምህርቱም የባልንጀራን ጥቅም ከራስ አስበልጠ መመልከት የሚገባ መሆኑን ገልጧል። ይህንንም ለፊልጵስዩስ ሰዎች በላከው መልእክት «ብእንድ ሃሳብ ተስማሙ፣ አንድ ፍቅር፣ አንድም ልብ፣ እንድም ሃሳብ ይሁንላችሁ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትኅትና ይቁጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት÷ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።» በማለት አጠናክሮታል። ፊልጵ.2÷2-4። በዚህም ባልንጀራን እንደራስ መውደድ ማለት ፍቅርን በትሕትና መግለጥ መሆኑን እናስተውላለን።

ስለሆነም ሰው ባልንጀራውን እንደራሱ፣ ከራሱም አብልጦ የሚወደው ከሆነ የተቀደሰ የባልንጀራውን ሰውነትና መንፈሳዊ ሕይወቱን ያጠፋ ዘንድ አይገድለውም፤ አካሉን በዝሙት አያረክሰውም፤ ሀብቱንም ሆነ ንብረቱን አይ

ሰርቅበትም፣ በሐሰት አይመሰክርበትም፣ ንብረቱንና ቤቱን በመመኘትና በመቅናት አይመቀኘውም። ከአሥርቱ ትእዛዛት መካከል የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከቱትን ሁሉ የሚተላለፍ የፍቅርን ሕግ ይጥሳል። ባልንጀራውንም የማይወድ ሰው ትእዛዛትን እንዳይጥስ፣ ሕግም እንዳያፈርስ የሚከለክለው ገደብ የለም።

ስለዚህ ለሰው ፍቅር የሌለው ማንም ቢሆን ጎሊናውን የሚከብደውና በወንድሙ ላይም ክፉን እንዳያደርግ የሚቃወመው ውስጣዊ ሃሳብና ስሜት ስለሌለ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመተላለፍ ኃጢአትን እየፈጸመ የዲያብሎስ ባሪያ ሆኖ ይኖራል። ይህ እንዳይሆን ነው አምላካችን እግዚአብሔር «ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ» በማለት ያዘዘው። ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል «በኩሉ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት÷ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።» ያለው የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም የከበረ መንፈሳዊ ዋጋ ያለውና እግዚአብሔርንም የሚያስደስት መሆኑን ለማስረዳት ነው። 1ሳሙ.15÷22።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ትምህርቱ ባልንጀራን እንደመውደድ እግዚአብሔርን የሚያስደስተው ነገር የሌለ መሆኑን ሲገልጥ «በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ እግዚአብሔርን÷ባልንጀራንም እንደራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው» በማለት አስተምሯል። ማር.12÷33።

እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራንም እንደራስ መውደድ የሕግጋት ማሠሪያ ነው፤ ሕግጋትና ትእዛዛት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ይጠቃለላሉ። ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንኑ ያረጋግጡልናል። ከነዚህም ማረጋገጫዎች መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዛት ሁሉ እግዚአብሔርን በማፍቀርና ባልንጀራን እንደራስ በመውደድ የሚጠቃለሉ

መሆኑን ከገለጸ በኋላ «አሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ» በማለት የተናገረው አንዱ ነው። ማቴ.22+37–40።

ቅዱስ ጳውሎስም በዚህ ቃለ ወንጌል መሠረት ለሮሜ ክርስቲያኖች በላፈው መልእክት «ሕርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ+ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና። አታመንዝር+ አትግደል+ አትስረቅ+ በውሸት አትመስክር+ አትመኝ የሚለው ከሌላ ይቀ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሉአል። ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም» በማለት ተናገሯል። ሮሜ.13+8–10። ይህም ፍቅር የእግዚአብሔርን ሕግ ፈጸመው አማናዊ ውኃ የክርስትና ሕይወት በተግባር የመገለጥ የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ መሆኑን የሚያስረዳ ትምህርት ነው። ስለዚህ በዚህ ፍቅር ትእዛዛትን ፈጸመው የሚኘውን መንፈሳዊ ከብርና ለማያዊ አክሊል ገንዘብ ለማድረግ መዘጋጀት ያስፈልጋልና።

ፈሪሐኢችን መልዶ እግዚአብሔር ኢያዕሰ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስተምር «ወትእዛዛቱ ውሱ ሬተቸይቱ» እሥራኤል ሆይ+ በግ ጌታ አምላክኽን አንድ ጌታ ነው+ አን ተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ሃሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፈተቸይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የምትል እርሷን የምትመስል ይህች ናት» ብሏል። ማር.12+29–31።

ይህ ምንባብ ቀደም ብለን እንደተመለከትናቸው ትእዛዛት በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ መጠቃለላቸውን ከ ማ ሳየቱም በላይ «ባልንጀራህን እንደራስ መውደድ» የሚለውም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። እያንዳንዳችንንም በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በሥራ ቦታ፣ በማ ኅበራዊ ኑሮ ይህን በመሳሰለው ሁሉ ባልንጀራ የሆነውን የሰው ዘር በመውደድ ትእዛዛትን መፈጸምና ሰማያዊውን መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት እንድንዘጋጅ የሚመክር አምላካዊ ቃል ነው።

በዚህ በአሥረኛው ትእዛዝ መሠረት ወንድምን መውደድ ወይም ባልንጀራን እንደራስ የመውደድ ፍቅር የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን በሚገባ ዐውቀናል። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።» ሲል የተናገረው ወንድምን መውደድ የእግዚአብሔር ልጅነት ማረጋገጫም ጭምር መሆኑን ሲገልጥ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች መንፈሳውያን ናቸውና በመንፈሳዊ ምግባራቸው፤ ሰውንም በመውደዳቸው ይታወቃሉ። 1ዮሐ.3+10። በመቀጠልም «እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እና ውቃለን፤ ወንድሙን የ ማይወድ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው+ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ። ...ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን +የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ+ በሥራና በእውነት እንጂ በቃ ልና በአንደበት አንዋደድ።» በማለት ፍቅር በተግባር መገለጥ የሚገባው መሆኑን አበክሮ አስገንዝቧል። 1ዮሐ.3+14–18።

በሌላ ምንባብም ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙን የሚጠላ እስከአሁን በጨለማ አለ። ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል ማሰናከያም የለበትም፤ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ+ በጨለማም ይመላለሳል+ የሚሄድበትንም አያውቅም+ ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮ ታልና።» በማለት ያስተማረው ባልንጀራን መውደድ ብሩህ የሆነ አምላካዊ ስጦታ መሆኑን የሚገልጥ ነው። 1ዮሐ.2+9–11።

ባልንጀራን መውደድና እግዚአብሔርን መውደድ የማይ ነጣጠሉ ናቸው። የአንዱ መኖር የሌላኛውን ሕልውና እየገለጠ የሰውን ልጅ ከውድቀትና በኃጢአት የተነሣ ከሚመጣው ሞተ ነፍስ የሚታደጉ ሰማያውያን ስጦታዎች ናቸው። ስለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ «እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን።» ያለው። 1ዮሐ.5+2–3። በመሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች የተባልን ሁሉ ባልንጀሮቻችንን በመውደድና ትእዛዛቱንም በመፈጸም የፍቅር ልጆች እውነተኞም አፍቃሪዎች ለመሆን እንችል ዘንድ እንበርታ። በዚህ ሰማያዊ ሕግ በፍቅረ ቢጽ አጊድ ሆነን የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት ልንችል ዘንድ እርሱ ልዑል አምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን፤ አሜን።

ክፍል አሥራ ሁለት

ሕግጋተ ወንጌል

በመግቢያችን ለመግለጥ እንደሞከርነው ሁሉ ስለሕ ግጋተ ወንጌል በሰፊው የመተንተን ዓላማ የለንም። የዚህ መጽሐፍ ርእስ «ሕግጋተ እግዚአብሔር» የሚል በመሆኑና ከሕግጋተ እግዚአብሔርም ሶስተኛው ክፍል ሕገ ወንጌል ስለሆነ የመጽሐፉን ይዘት የተሟላ ለማድረግና ለአንባብ ያንም የሕግጋተ እግዚአብሔርን ምንነት ለማስተዋወቅ እንዲ ቻል ሕገ ወንጌልን ማትረቡ አስፈላጊ ሆኗል። ስለዚህም በዚ ህ ክፍል የሕግጋተ ወንጌልን ዝርዝርና ስለእያንዳንዳቸውም በአጭሩ ለማብራራት እንሞክራለን።

ለሕግጋተ ወንጌል ዝርዝር በቤተክርስቲያን መምህራን ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። አንደኛው ወገን በማ ቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ከቁጥር 22–45 የተዘረዘሩ ትን በመውሰድ እነዚህ ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ናቸው በማ ለት የሚያስተምሩ ሲሆኑ፣ በሁለተኛው ወገን ያሉት ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አምስት ከቁጥር 35–36 የተዘረዘሩትን ስድስት ጥያቄዎች በመውሰድ ሕግጋተ ወን ጌል እነዚህ ናቸው በማለት ያስተምራሉ። በሶስተኛ ወገን ያሉት ደግሞ ሕግጋተ ወንጌልና ቃላተ ወንጌል የተለያዩ መሆናቸውን በመተቀስ በማቴዎስ አምስት ያሉት ሕግጋተ ወንጌል ሲሆኑ በማቴዎስ ሃያ አምስት ያሉት ደግሞ ቃላተ ወንጌል ናቸው የሚል አመለካከት ያላቸው ናቸው።

የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ያለው አመለካከት ከሶስ ተኛው ወገን የሚስማማ ነው። ሕግ ሲባል ለማድረግ የማ ዘዝና ከማድረግ የመከልከል ባሕርይ ያለው ከመሆኑ የተን ሣና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት የተዘረዘሩት ሁሉ

የሕግ ባሕርይ ያላቸው በመሆኑ ሕግጋተ ወንጌል ሊባሉ ይችላሉ። በማቴዎስ ሃያ አምስት የተዘረዘሩትን ስንመለከት ደግሞ ከላይ የተጠቀሰውን የሕግ ባሕርይ አያንፀባርቁም። ከዚህም ሌላ በዕለተ ዮጽዓት ክርስቶስ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት በይባቤ መላእክት በተገለጠና በፍርድ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ ኃጥአንና ጻድቃን ተገራና በቀኙ ቆመው እንዲመልሱ የሚያቀርብላቸው ጥያቄዎች ናቸው እንጂ በግዘዝ ወይም በመከልከል የተሰጡ ሕግጋት አይደሉም። ስለሆነም ሕግጋት ከማለት ይልቅ ቃላተ ወንጌል ቢባሉ የበለጠ ተስማሚነው ቢሌላም በኩል እነዚህን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት የተዘረዘሩትን በተናገረ ጊዜ ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግጋተ አሪትን እያስታወሰ እየጠቀሰ መሆኑ ከሕግ ወገን ሕግጋት ለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫ ነው። ስለሆነም ሕግጋተ ወንጌል የሚከተሉት ናቸው፦

1.«በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቆጣ»

ማቴ.5+22–26፦ ይህ ሕግ ወንድም ናቸው የሰው ልጆችን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን ልብ ማለት ያስመ ለጋል። በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በመስቀል ላይ የተቸረጠ ሰውና የፈሰሰው የመድኃኔዓለም ሥጋና ደም ሕገብንና ኤሕ ዛብን አንድ ያደረገ የክርስትና መሠረት በመሆኑና በዚህ ቤዛነትም ሰው ሁሉ ድኅነት በመሰጠቱ ሁሉም ወንድማ ማቾች ሆነዋል። በመሆኑም ክርስቲያኖች አንዳቸው የሌላ ኛው አካላት ናቸውና አንዱ በሌላው ወንድሙ ላይ እን ዳይቆጣ ታዝዟል። ከፍትርና ከመተላለፍ በቀር ቁጣ የእግዚ አብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።

መቆጣት የሌላውን ሰው ስሜት የሚነዳና ከቁጣው ድንገተኛነት የተነሣም ወደሌላ ከፍተኛ የስሜት ለውጥ ሊቀ የር ስለሚችል ከመቆጣት መቆጠብ ተገቢ ነው። ያል ታሰበና ያልተጠበቀ ቁጣ የደረሰበት ሰው በድንጋጤ ሊሞ ትም ይችላል። ከዚህም ሌላ በድንጋጤ ራሱን ለመከላከል በሚያደርገው ድርጊት የተነሣ ነፍስ እስከ መግደል ሊደ

ርስም ይችላል። እንግዲህ ቁጣ በአንደበት የሚነገርና ቀላል ይምሰል እንጂ ውጤቱ አደገኛና አሳዛኝም ሊሆን እንደሚችል በግሌን ከመቆጣት መቆጠብና ቁጣንም ከራስ ማራቅ ይበጃል።

መቆጣት በሰው ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላና ኃጢአትም በመሆኑ ከተ ፈጸመ በኋላ የሚከተለው ቅጣት አለ። መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ «ለቀደሙት፦ አትግደል እንደተባለ ሰምታ ችኋል÷ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላች ኋለሁ÷ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፣ ወን ድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባ ዋል፣ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባ ዋል።» በግለት ቁጣንና መሳደብን ከመግደል ጋር አስተ ካክሉ መግለጡ መቆጣት ከፍተኛ ኃጢአትና ቅጣቱም ታላቅ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ማቴ.5÷21–33። ስለዚህ ቁጣን ከራስ አርቆ በትዕግሥትና በመተሳሰብ መኖር ለክር ስቲያኖች ሁሉ የሚገባ ነውና ሁላችን ገንዘብ እናድርገው።

2.«ወደ ሴት አትመልከት በልብህም አታመንዝር»

ማቴ.5÷27። ይህ ወይ ሴት በመመልከት በልቡና የሚያድረው ፍትወተ ሥጋ ኃጢአት መሆኑን የሚያ መለክት ነው። ሴትን ማየት ሳይሆን ባዩአት ጊዜ ለፈቃደ ሥጋ መመኘትን ነው እግዚአብሔር የማይፈቅደው። ለዚ ህም ነው በወንጌል «ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛ ትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል» በማለት የተነገ ረው። «ዓይቶ የሚያሰናክል ዓይን» የተባለውን ፍትወተ ተራ ክበን አውጥቶ መጣልና መንግሥተ ሰማይን ገንዘብ ማድ ረግ በማየት የሚመጣ ምኞትን በመፈጸም በገሃነም ከመጣል ይሻላል፣ ይበልጣልም። ማቴ.5÷28።

ዓይን ሁሉን ይመለከታል፣ ወደልቡና መዝገብ የሚ ልከው ግን ቀልቡ ያረፈበትን ነው። በዚህ አንጻር ሴትን በክፉ የኃጢአት ምኞት መመልከት አይገባም፣ በልቡናም

ለዝሙትና ለተራከቦ ማሰብ ታላቅ በደል ነው፣ የሃሳብ መድረሻ ተግባር ነውና እርሱም ዝሙት። ስለዚህ በማየት መዘዝ ከሚመጣ ውድቀት ለመዳን ይህን ሕገ ወንጌል በሚገባ መረዳትና ዓይነ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ዓይነ ልቡናንም መቆጣጠር ያስፈልጋል።

3. «ሚስትህን ያለዝሙት ምክንያት በሌላ ነውር አትፍታት» ማቴ.5÷32

ይህ ሕግ ጋብቻ የከበረና መንፈሳዊ አንድነት ፍጹ ም ተዋሕዶ ስለሆነ በተገኘው አጋጣሚና በተፈጠረ ችግር ሁሉ ሰበብ ሊናጋ የማይገባው መሆኑን የሚያመለክት ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል÷ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ...ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።» በግለት ያስተማረው ትምህርት የጋብቻን ታላቅነትና ምሥጢራዊ ትርጉም የሚያስረዳ ነው። ማቴ.19÷5–7። በዚህ ትምህርት መሠረት ማንም ሰው ሚስቱን ለመፍታት አንዳች ምክንያት የለውም። በሥጋ ፍጥረትም ቢሆን ለአንድ አዳም አንዲት ሔዋን፣ ለአንዲ ት ሔዋን አንድ አዳም ብቻ የተፈቀደ መሆኑን ስንመለከት የምናስተውለው ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚደረግ አንድነት መሆኑንና በቀላሉና በሰው ፍላጎት እንዳይፈርስ ሰማያዊና አምላካዊ ጥበቃ የሚደረግለት መሆኑን ነው።

ይህን የከበረ አንድነት ማፍረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ በደልና ኃጢአት ነው። ስለዚህ በፈቃደ እግዚ አብሔር አንድ የሆኑ ባልና ሚስት አንድነታቸውን አክብረው ሊጠብቁትና ከተቀደሰ ጋብቻ የሚለቀመውን መልካም ፍሬ በረከት ገንዘብ ለማድረግ መትጋት ይኖርባቸዋል።

ፈጣሪአችን እግዚአብሔር ኃጢአት በሆነ በዝሙት ምክንያት ካልሆነ በቀር ጋብቻ እንዳይፈርስ አዝዟል። መፋታት በተረጋገጠ የዝሙት ኃጢአት ምክንያት ካልሆነ በቀር የተወገዘ ነው። ምክንያቱም ፍቺ ቤተሰብን ከመበተን አልፎ ከዚያ ጋብቻ የተገኙትን ሕፃናት የሚያሳቅል፣ ተስፋ ቢስ፣ ሰላምና ማኅበራዊ ፍቅርም የሌላቸው፣ በመጨረሻም ወደ

ኃጢአት ሥራ እንዲያዘነብሉና በነፍሳቸውም እንዲ ጎዱ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ነው። በዚህም የተነሣ ተስ ማምተው የተጋቡ ባልና ሚስት መፋታትም ሆነ መለያየት እንደማይገባቸው ዐውቀው በጋብቻቸው መጽናት አለባቸው።

4. «ፈጽመህ አትማል» ማቴ.5÷34፡-

መሐላን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ስለመጥራት በተዘረዘረበት ክፍል ቤ.ሬው የተመለከትነው ስለሆነ ጸጋመኛ ወደዚያ መመለስ አያስፈልገንም አልታ መነበትም። በአጭሩ ማንም ሰው በማንኛውም ጉዳይ ማረጋገጫ ለመስጠትና ባላንጣውን ለመርታት ወይም ተጯጋቹን ለማሳመን በማሰብ ቢምል ሕገ እግዚአብሔርን ያፈርሳል። በማንኛውም ምክንያት ቢሆን መማል ኃጢአት ነው። እንኳን ሲሐሰት በእውነት ነገርም ቢሆን መሐላ ፈጽሞ የተከለከለ ነው። የሚምል ሰው የእግዚአብሔርን ስም ከንቱ ያደርጋል። ዘሌ.19÷12።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን፣ ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።» በማለት ያስተማረው ትምህርት መሐላን በጥብቅ ከልክሏል። ማቴ. 5÷33-37። የሚምል ሰውም ከቶ የተባለ የጠላት ዲያብሉስ ወገን መሆኑን በመግለጥ ከመማል እንድንቆጠብና ነገራችንን ሁሉ አዎን ወይም አይደለም በማለት እንድናጸና አስገንዝቦናል።

5.«ክፉን በክፉ አትመልስ»_ማቴ.5÷39።

የዚህ ሕግ ዋና መልእክት ትዕግሥት ነው። በመታገሥ ወደኃጢአት ተግባር ሊያመራ የሚችለውን ሁኔታና ወደ ውድቀት የሚያደርሰውን የሥጋ ግፊት መቆጣጠር ይቻላል። ለሚያጋጥም ክፉ ፈተና በችኩልነት በግልፍተኝነት የሚደረግ አፀፋ ወይም ክፉን በክፉ መቃወም በዚህ ሕግ መሠረት የተከለከለ ነው።

በሌላ በኩል ይህ ሕግ በቀልን የሚቃወም ነው። «አትበቀሉ÷... በቀል የእኔ ነው÷ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ» በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች የጻፈው በወንጌል መድኃኒታችን «ክፉውን በክፉ አትቃወም» በማለት ካስተማረው በመነሣት ነው። ክፋውን በክፉ አለመቃወም ማለትም ክፉውን ነገር በክፉ ድል ለመንሣት አለመዘጋጀት፣ ክፉውን ግብር በክፉ ግብር አለመቃወም በጠቅላላው አለመበቀል ማለት ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ተወዳጆች ሆይ÷ራሳችሁ አትበቀሉ÷ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ» በማለት የተናገረው። ማቴ.5÷39። ሮሜ. 12÷17-19። ስለዚህ ክፉን በመልካም ማሸነፍ እንጂ በክፉ እንዳንሸነፍ ክፉውን ሃሳብ ከእኛ ማራት ይገባናል።

6.«ጠላትህን ውደድ»

ማቴ.5÷45፡- የዚህኛው ሕግ ዋና መልእክት ደግሞ ፍቅር ነው። ይህን ሕግ የሰጠን ክርስቶስ ጠላቶቹን በመውደድ እኛም እንዲሁ እንድናደርግ አስተምሮናል። ሰውን ሁሉ መውደድ የክርስትና ሕግ ነው። ይህ ሕግ ፍጹም የሚሆነው ደግሞ የሚያውቁትን ወዳጅን በማፍቀር ብቻ ሳይሆን ጠላትን ጨመውደድ በተግባር የተገለጠ

እንደሆነ ነው። ክርስቶስ ሁሉንም በመውደድ በፍጹም ፍቅር እንደተገለጠ ክርስቲያኖች, ሁሉ ደግሞ ሁሉን በመውደድ ፍጹማን እንድንሆን ይህ ሕግ ግድ ይለናል። ማቴ.5÷44–46።

ከዚህም በላይ በአጭሩ የቀረቡት ስድስቱ ሕግጋተ ወንጌል ሲሆኑ በዕለተ ምጽዓት ክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ የሚመዝንባቸው ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ የተራበን ማብላት :– ማቴ.25÷35።

ለ/ የተጠማን ማጠጣት:– ማቴ.25÷35።

ሐ/ እንግዳን መቀበል :– ማቴ 25÷35።

መ/ የታረዘን ማልበስ :– ማቴ.. 25÷36።

ሠ/ የታመመን መጎብኘት :– ማቴ.25÷36።

ረ/ የታሠረን መጠየቅ:– ማቴ.25÷36።

በእነዚህ ስድስቱ ቃላት አንገር ክርስቶስ ለሌሎች የተደረገውን ሁሉ ለእርሱ እንደተደረገ፣ ለሌሎች ያልተደረገውን ለእርሱ እንዳልተደረገ በመቁጠር የምእመ መናንን ምግባር የሚመዝን መሆኑን እንገነዘባለን። በክርስቶስ ክርስቲያኖች የተባሉ የሰው ልጆች ሁሉ ግንኙም ከማን ሳይለዩና ሳያስበልጡ፣ ሳይንቁም እነዚህን ስድስቱን ምግባራት ለሁሉም በእኩል ሚዛን መፈጸም ይኖርባቸዋል። እነዚህን የፈጸሙትን መድኃኔዓለም ክርስቶስ «እናንተ የአባቴ ቡሩካን÷ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።» በማለት ዘለዓለማዊ የሆነውን የጽድቅ ዋጋ ይሰጣቸዋል። ማቴ.25÷34።

ስለዚህ እኛም ሕግጋተ ወንጌልን በመጠበቅና ቃላተ ወንጌልን በመፈጸም የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች, ለመሆን እንድንበቃ በቸርነቱ ይርዳን። አሜን።

ክፍል አሥራ ሦስት

ማጠቃለያ

እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ሕግጋተ እግዚአብሔርን ለመመርመር ስንነሣ የዚህን ያህል ጥልቅ ትርጉም ያላቸውና ሁለንተናዊ የክርስትና ሕይወታችንን የሚመለከቱ አልመሰለን ይሆናል። ቀስ በቀስ ወደእያንዳንዱ ሕግ ይዘት ስንገባ ግን የሕግጋቱን ጥልቀት፣ ስፋትና ከብደት በሚገባ ተመልክተናል። በእነዚህ ሕግጋት ትንተና ፍጻሜ ደግሞ የበለጠ ያስተዋልነው በአንድ ሳይ ተደምረው ሕግጋቱ ሁሉ ቢጨመቁ የሚወጣቸው ፍቅር ሆኖ ነው የተገኘው። የሁሉም ሕግጋት የመጨረሻ ግባቸው ፍቅር ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በላከው መልእክቱ «የትእዛዝት ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው» ያለው። 1ጢሞ.1÷5 ለሮሜ ሰዎች።በጻፈው መልእክቱ «ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው» ብሏል። ሮሜ 13÷8–10።

ሕግጋት ሁሉ በፍቅር የሚፈጸሙ ከሆነ ስለፍቅር ጥቂት በመጻፍ ማጠቃለሉ የሚመረጥ ሆኖ ተገኝቷል።

ፍቅር ምንድን ነው?

ፍቅር አንድ ሰው ከሌላው ጋር በየዕለቱ የሚያደርገው ግንኙነት የሚመራበት በሞተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ልባዊ መዋደድና ጥልቅ መንፈሳዊ ጸጋ ነው። በሰዎች መካከል በሚኖረው መልካም ግንኙነት የተነሣ አንዱ ለሌላው የሚያደርገው መልካም ነገር ሁሉ ፍቅር ነው።

አንዱም ለሌላው የሚያደርገው ይህ መልካም ነገር /ፍቅር/ በልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው። በዚህ የዕለት ተዕለት ግንኙነት ለተራበ ማብላት፣ ለተጠማ ማጠጣት፣ የተቸገረን መርዳት፣ ያዘነን ማጽናናት ይህን የመሰለው መልካም ምግባር ሁሉ ሰው ለሰው ካለው ፍቅር የሚመነጭ ነው። በዚህ መሰል ተግባር ለሌሎች መልካም ያደረጉትን ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመጣ ጊዜ «የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ...ከሁሉ የሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስለአደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት» በማለት የከበረ ዋጋ እንደሚሰጣቸው በወንጌል ተናግሯል። ማቴ.25÷34–40። ሰዎችን መውደድና ሰውን መርዳት ፍቅር ነውና ከፍቅር አምላክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊ ዋጋን ያስገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ... መልካም እናድርግ» ያለው በፍቅር የሚደረግ መልካም ነገር የሚያስገኘውን መንፈሳዊ ዋጋ በሚገባ ስለተረዳ ነው። ገላ.6÷10።

ይህ ፍቅር የተባለው ለሰው መልካም መሥራት የሰውን ድካሙን ሳይቀር በመሸፈን መገለጥ የሚገባው ተግባር ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን በተመለከተም «ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲህም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።» በማለት የክርስቶስ ሕግ የሆነው ፍቅር በተግባር እንዲገለጥ አስተምሯል። ገላ.6÷2። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጽኑ ፍቅሩ የተነሣ የሰው ልጆችን ሸክም ተሸክሞ ሞት የማይሰማውን ሲሆን መዋቲ ሥጋን ተዋሕዶ ሞትን ድል እንደአደረገልን ሁሉ፤ የወገኑን ጉድለት ሁሉ በመታገሥ ወደ ድኅነት እንዲደርስ ማድረግም ፍቅርን በተግባር መግለጥ ነው።

ፍቅር በመላእክት ልሳን ከመናገር በላይ የከበረ ነው። እውነተኛ ፍቅር ከዕውቀትና ከልግሥና ሁሉ ይበልጣል። ፍቅር የተባለው ሰውን መውደድ የክርስትና ሕይወት መሠረት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፍቅር ያልተቀመመና ያልጣፈጠ ገድልና ትሩፋት ሁሉ የማይጠ

ቅም መሆኑን ከገለጠ በኋላ «ፍቅር ያስታግሣል፤ ፍቅር ያስተዛዝናል፤ ፍቅር አያቀናናም፤ ፍቅር አያስመካም፤ ፍቅር አያስታብይም፤ ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም፤ አያበሳጭም፤ ክፉ ነገርን አያሳስብም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል፤ እንጂ ስለ ዓመፅ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም።» በማለት ስለፍቅር ጠባይዓት ዘርዝሯል። 1ቆሮ.13÷1–10።

በዚህ መሠረት ሰው ለሚያፈቅረው ቸርነትን ያደርግ ለታል፤ የሚወደውን ይታገሠዋል፤ አይንቀውም፤ አይቀናበትም፤ አይመቀኘውም፤ ያምነዋል፤ ስለዚህ የራሱን ሳይቀር ይተውለታል /ይሰጠዋል/። የሚወደውን ሰው እንዳያጣው በትሕትና፤ በየዋህነትና በትዕግሥት በጥንቃቄም ያፈቅረዋል። ኤፌ.4÷2። ሰው ሁሉ ለሚወደው ቸርና ርኅሩኅ ነው፤ ካለው ሁሉ በልግሥና ያካፍለዋል፤ በማንኛውም ነገር ቢሆን አይጨክንበትም። ኤፌ.4÷32።

በእግዚአብሔር የሚታመን ክርስቲያን ሁሉ የፍቅር ሰው መሆን ይጠበቅበታል። በመሰቀል ላይ ለቤዛ ዓለም የተሰቀለው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ሰውን ሁሉ መውደድ እንደሚገባ ነው። አማናዊው የክርስትና መሠረት እምነትና ትምህርትም በዚህ ፍቅር መጽናት ይኖርበታል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ «በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ወይም አለ መገረዝ አይጠቅምምና።» ሲል ያስተማረው ለዚህ ነው። ገላ.5÷6። ይህም እምነትን የሚያንቀሳቅሰውና በምግባር እንዲገለጥ ሥራም እንዲሠራ የሚያደርገው ሞተር ፍቅር መሆኑን ያስረዳል።

ከዚህም ሌላ ለመንፈሳዊ ነፃነት የተጠሩበት የክርስትና እምነታቸው በተለያዩ የሥጋ ፈቃዳትና ፈተናዎች እንዳይሰናከልና ፍሬ አልባ እንዳይሆን ሲያስጠነቅቅ «ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።» በማለት እምነታቸውን በመዋደድ

እንዲገልጡት መከሯቸዋል። ገላ.5÷13። ሃይማኖትን በም ጭር ለመግለጥ ፍቅር እጅግ አስፈላጊ መሣሪያ መሆኑን ሲያሰገ ነዝብም «ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብት በላሉ እርስበርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።» ብሏል። ገላ.5÷14። ከዚህ ሁሉ በመነሣት ፍቅር የእምነት ተግባራዊ መግለጫ ነው ለማለት ይቻላል።

በሰዎች መካከል ፍቅር አለ ማለት በመካከላቸው ፍጹም የሆነ አንድነትና መናበብ አለ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ሰዎች በአንድ ፍቅር ይኖራሉ፣ አንድ ነገር ያስባሉ፣ በአንድ ዓላማ ይሠራሉ፣ በአንድ መንገድ ይጓዛሉ፣ በጠቅላላው አንድ ልብ ይሆናሉ። በአንድ ወንጌል ለአንድ ሰማያዊ አገልግሎት የተጠሩት ሐዋርያት ሃሳባቸው፣ ዓላማቸውና ግባቸው አንድ ነበርና ተስፋቸውን ሲጠባበቁ «በአንድ ልብ ሆነው ይተጉ ነበር»። የሐዋ.1÷14፣ 2÷42፣4÷32።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «በመጨረሻው ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ÷ የሌላው መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ÷ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ» በማለት ማስተማሩ በፍቅር መካከል መለያየትን የሚያመጣ አንዳች ነገር እን ዳይኖር ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያመለክት ነው። 1ጴጥ.3÷8። ስለዚህ ፍቅር ስንል የሚዋደዱትን ሰዎች ልባዊ አንድነት የሚያመለክት መሆኑን እናስተመ ውል። የዚህ ዓይነቱ ፍጹም የልቡና አንድነት ወይም ከልብ መዋደድ በጽኑ እምነት ላይ ከተመሠረተ ፍቅር የሚገኝ መንፈሳዊ ፍሬ ነው። የእግዚአ ብሔር ማደሪያ ካልሆነው ልብ ይህንን እውነተኛ ፍቅር ማግኘት አይቻልም። ሐ ዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፍቅርን ከመንፈስ ፍሬዎች መካከል የፈረጀው በዚሁ ምክንያት ነው። ገላ.5÷22።

ፍቅር ከፍ ብሎ የተመለከትነውን ትርጉም ያዘለ ከሆነ የእግዚአብሔር ሰዎች በእምነት የሚኖሩትን ኑሮ በፍቅር መሠረትነት ላይ የተገነባ ሊያደርጉት ያስፈልጋል። መዋ ሀረ አሕዛብ የተባለው ቅዱስ ጳውሎስ «በፍቅር ተመላለሱ» ካለ በኋላ «ፍቅርን ተከታተሉ» ማለቱ ይህንኑ የሚያጠናክ

ነው። ኤፌ.5÷2። 1ቆሮ.14÷1። ሽንገላ የሌለበት ፍጹም ፍቅር የኃጢአት ጠላትና እንቅፋት ነው። በሰዎች መካከል ፍቅር ካለ አንዱ በሌላው ኃጢአትን እንዳይሠራ የፍቅር ሕግ ያግደዋል። ፍቅር በሰዎች መካከል ያለውን ክፋት የሚ ያስወግድ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን «ጥል ከርከርን ታስነሣለች፣ ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለጠ ች።» በማለት የተናገረው ይህን የሚደግፍ ነው። ምሳ. 10÷12። ቅዱስ ጴጥሮስም «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍ ናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።» ማለቱ ፍቅር በኃጢአት ላይ ያለውን የበላይነት የሚያሳይ ነው። 1ጴጥ.4÷8።

እንግዲህ የፍቅር መንፈሳዊ ጠቀሜታ ወሳኝ ከሆነ ሰሎሞን እንዳለው «የጎመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል።» ምሳ. 15÷17። በፍቅር ካልጣፈጠ ኑሮም ትርጉም አይኖረውም። ተድላንም፣ ደስታንም የሚያጣፍጣቸው፣ ችግርንም መከራ ንም የሚያቀልላቸው፣ ኑሮን ሁሉ ትርጉም የሚሰጠውና የሚያጣፍጠው የፍቅር ቅመምነት ነው። ስለሆነም የፍቅር ሰው መሆን በፍቅርም መኖር ተገቢ ነው። ሰው ሁሉ በፍቅር በመኖር የጠላት ዲያብሎስን ምሽግ ማፍረስና መሣሪያው ኃጢአትንም ኃይል አልባ ማድረግ ይችላል።

ፍቅር በተግባር መተርጎም አለበት

ከዚህ በላይ ባሉት ክፍሎች የፍቅርን ጠቅላላ ፍችና ምንነት በዝርዝር ለማስረዳት ተሞክሯል። ከዚህ በኋላ በማ ንም አእምሮ ውስጥ ፍቅር ረቂቅ ከመሆኑ የተነሣ እንዴት በተግባር ይተረጉማል? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ስለሆነም በዚህ ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍት ፍቅርን በሥራ ላይ ስለማዋል የሚያስተምሩትን በመመርመር ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይሞክራል።

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት «ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ÷ እነሆ÷መልካም ነው። እነሆም ያማረ ነው÷» በማ ለት ከተናገረው ቃል እንነሣለን። መዝ.132÷2። ነቢዩ በዚህ

ቃል ከፍቅር የሚመነጭ መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ መተዛዘን፣ በጠቅላላው የልብ አንድነት ሊኖር እንደሚገባ አመል ከቷል፤ የወንድሞች ኅብረትና አንድነት መልካም ያማረም ነውና። ይህ የሚገኘው ታዲያ ቀድሞ መዋደድ ያለ እንደ ሆነ ነው። ፍቅርም ከእግዚአብሔር የሚገኝ ጸጋ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም «ወዳጆች ሆይ ፍቅር÷ ከእግዚአብሔር ስለሆነ÷ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ÷ እርስ በርሳችን እንዋደድ።» በማለት በመካከላችን ሊኖር የሚገባው ምድራዊውና ኃላፊውን ጊዜያዊ ፍቅር ሳይሆን የማይጠፋ ዋጋ የሚገኝበት ሰማያዊው መንፈሳዊ ፍቅር መሆኑን አመል ከቷል። 1ዮሐ.4÷7። በመቀጠልም ይህን ከእግዚአብሔር የሚገኝ /የሚሰጥ/ መንፈሳዊ «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።» ሲል መንፈሳዊው ፍቅር ፍጹም የሆነ የኅብረት የአንድነት መሣሪያ መሆኑን አስረድቷል። 1ዮሐ.4÷8። ይኸው ሐዋርያ በሌላ ምንባብ ደግሞ እግዚአብሔርም በዚሁ ፍቅር እንደወደደንና አንድ ልጁን ለቤዛ ዓለም በመስቀል ተሰቅሎ ሕይወት ይሆነን ዘንድ እንደሰጠን ከተጠቀሰው ቃሉ «ወዳጆች ሆይ÷ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።» በማለት በመፋቀር መኖር የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ግዴታቸው መሆኑን ገልጧል። 1ዮሐ.4÷11። ይህን ሃሳቡን የበለጠ ሊያጠናክረውና ስለ ፍቅር የሰዎችን ግዴታ አክብዶ ሲገልጽ «ማንም÷ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።» ብሏል። 1ዮሐ.4÷20-21። በዚህ ትምህርቱም እርስ በርስ መዋደድ እግዚአብሔርን ከመውደድ የሚገኝና ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን አስረድቷል።

በቅዱስ ወንጌልም «እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ...እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ።» በ

ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው በሰዎች መካከል ያለው ፍቅር እርስ በርስ በመዋደዳቸው መገለጥ እንደሚኖርበት ለማስገንዘብ ነው። ዮሐ.15÷12-14። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ «የወንድማማች መዋደድ ይኑር።» ማለቱ የጌታችንን ትምህርት ተመርኩዞ ነው። ዕብ.13÷1። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ» በማለት በሰዎች ሁሉ መካከል ያሉ የወንድማማች መዋደድ በተግባር በሚታይ መንፈሳዊ ፍቅር መገለጥ የሚገባው መሆኑን አስተምሯል። 1ጴጥ.1÷22።

ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ሁሉ ሰማያዊ በሆነው መንፈሳዊ ፍቅር እርስ በርስ መዋደድ ከእግዚአብሔር የሚገኝ የተቀደሰ ስጦታ ነው። በጽኑ የክርስትና መሠረተ እምነት ላይ የታነፁ ሁሉ በዚህ ፍጹም ፍቅር ሊዋደዱ እንደሚገባቸው ያውቃሉ። መሠረታዊ የሆነ የክርስትና ትምህርትና ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ብስለት ከሌለ ስለዚህ ሰማያዊ ፍቅር ማወቅና መናገር አይቻልም፤ በዚህ ፍቅር መኖርም ከባድ ነው፤ የማያውቁትን በምግባር መግለጥ አይቻልምና።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጽኑ ትምህርተ ሃይማኖት ላይ መመሥረታቸውን ለተሰሎንቄ ምእመናን ሲገልጽ «እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለወንድማማች መዋደድ ግንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም» ብሏቸዋል። 1ተሰ.4÷9። ይህ የሚያመለክተውም ፍጹም መንፈሳዊ ፍቅር ከጽኑ የመንፈሳዊ ሕይወት አዝመራ የሚለቀም ጣፋጭ ፍሬ መሆኑን ነው።

ይኸው ሰማያዊ መንፈሳዊ ፍቅር የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመፈጸም የፈጣሪ ታማኝ አገልጋይና ወዳጅ የመሆን ማረጋገጫም ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ÷ እንደወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ ...እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ÷ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።» በ

ግለት በወንጌል ያስተማረው ለዚህ ምስክር ነው። ዮሐ.13÷34-35። በዚህ ትምህርት መሠረት የእግዚአብሔር ወዳጅ ፍቅርና እርስ በርስ መዋደድ በተግባር መገለጥ አለበት። የእግዚአብሔር ወገን ነኝ ግለት በአንደበት ብቻ ሳይሆን በሚታይ ፍቅር እርስ በርስ በመዋደድ በሥራ መተርጉም ይኖርበታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ለእውነት እየታዘዛችሁ ንብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ ተዋደዱ።» በግለት ይህ ሰማያዊና መንፈሳዊ ፍቅር ፍጹምና ሽንገላ የሌለበት ሊሆን እንደሚገባ አስተምሯል። 1ጴጥ.1÷22-23። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለሮማውያን ክርስቲያኖች በጻፈው ሮልእክቱ «ፍቅራችሁ ያለ ንብዝነት ይሁን። ...በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» በግለት ስለ ፍቅር ተግባራዊ አፈጻጸም አስተምሯል። ሮሜ.12÷9-10። ለቆሮንቶስ ምእመናን ሲጽፍ ደግሞ «አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ኩቶ እንሰጥም። ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች /ንብዝነት በሌለው ፍቅር/ ራሳችንን እናሳተናለን» በግለት እውነተኛው ፍጹም ፍቅር ከንብዝነት የነጻ መሆኑን አስረድቷል። 2ቆሮ.3÷7።

ስለዚህ በወንድሞች መካከል የሚኖረው የእርስ በርስ ፍቅር በተወሰነ ጊዜ ታይቶ የሚጠፋ፣ በአንድ ወቅት ፈክቶ በሌላ ጊዜ የሚጠወልግ ወረት መሆን የለበትም። ከዚህ ይልቅ በጽኑ እምነት ላይ በቅሎ በጊዜው ሁሉ እያበበ መንፈሳዊ በረከትንና ረድኤተ እግዚአብሔርን እያፈራ የሚኖር ዘላቂ መሆን ይገባዋል። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ላሉ ክርስቲያኖች «እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም።» በማለት የጸለየላቸው። 1ተሰ.3÷13።

ሐዋርያው እንዳደረገው ሁሉ ፍቅር እንዲጸና፣ እንዲ ያድግና ፍሬም እንዲያፈራ በጸሎት የታጠረና በጥንቃቄ የሚጠበቅ መሆን አለበት። ከዚህ በመነሣት ነው ቅዱስ ጴጥሮስም በመልእክቱ «ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ ...እግዚአብሔርንም በመሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።» በግለት ፍጹም ሰማያዊ ፍቅር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሊጓዝ የሚገባው የክርስትና ሕይወት ግጣፈጫ እንጂ እንደገለባ እሳት ብልጭ ድርግም የሚል መሆን እንደሌለበት የሚመክረው። 2ጴጥ.1÷7። ስለሆነም ፍቅራችን ከንብዝነትና ከወረት ነፃ ሆኖ ሕግጋትን በመፈጸም በግከበር በተግባር የሚገለጥ እንዲሆን መጸለይ ይገባናል። የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትንም የማይረሳ ልዑል እግዚአብሔር ለቀደሙት አበው እንደተለመነ እንዲለመነን የፍቅር ሰዎችም እንዲያደርገን፣ በፍቅሩ በመጽናትም መንግሥቱን ለመውረስ እንዲያበቃን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

አነግሥቶ ያስጀመረኝ፣ አስጀምሮም ያስፈጸመኝ ልዑል አምላካችን እግዚአብሔር ከብር ምስጋና ይግባው እሜን።

ወይትባረክ እግዚአብሔር

ተፈጸመ

‹‹እግዚአብሔር ፍጥረታትን የሚመራው የሚመግበውና በፍቅርም የሚገዛው በሕግና በሥርዓት ነው። በመሆኑም ሕጉንና ሥርዓቱን መጠበቅ ይገባል። ይህም እግዚአብሔርን የመውደዳችን ለእግዚአብሔርም የመገዛታችን ማረጋገጫ ነው። ይኸንንም የነገረን ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዮሐ.14÷15። ከዚህ አንጻር ይህ በቀሲስ እሸቱ ታደሰ ተተርጉሞ የቀረበልን ሕግጋተ እግዚአብሔር እንዴት በፍቅር መኖር እንዳለብን በሰፊው ያስተምረናል። በሐዋርያው በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርትም፡- ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅት በነም ናት ይለናል። ሮሜ.7÷12 ፈቃደ ሥጋችንን ለፈቃደ ነፍሳችን እንድናስገዛ መንገድ ይመራናል። መንገድነቱም የብርሃን መንገድ ነው። ምክንያቱም ሕጉ በመንፈሳዊ ሕይወት ለምንራመደው ጎዳና መብራት ነውና። መዝ.108.105። ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን ይኸንን መጽሐፍ የግል ገንዘቡ አድርጎ ቢጠቀምበት ዕውቀት ያነሰው ተምሮ፣ የተስተካከለ ተመክሮ በድፍረት ኃጢአት የወደቀም ተገሥጾ የተስተካከለ ሕይወት ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ።››

መምህር ደጀኔ ሺፈራው።

ዋጋ ብር 40፡00

BAPP 0930012813